አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝም ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጹሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ "ከመድሀኒት አዋቂዎች አንጻር"

በ

ብርቱካን ደባይ

ግንቦት/2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝም ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ “ከመድሀኒት አዋቂዎች አንጻር”

በ

ብርቱካን ደባይ

አማካሪ

የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)

ግንቦት/2012ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ “ከመድሀኒት አዋቂዎች አንጻር”

በ

ብርቱካን ደባይ

## የፈተና ቦርድ አባላት ስም፣ቀንና ፊርማ

| የፈተና ቦርድ አባላት | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|
| የአማካሪ ስም<br>ዶ/ር የኔዓለም አረዶ | ____________________ | ____________________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም<br>____________________ | ____________________ | ____________________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም<br>____________________ | ____________________ | ____________________ |

# ምስጋና

በቸርነትህ ብዛት እስከዚች ሰዓት ድረስ ጠብቀህ ያደረስከኝ፤ልዑል እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሀለሁ! በመቀጠል ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጹሑፌን በማረም፣ ስህተቶቼን በማቃናት እና አቅጣጫ በማሳየት ጥናቴ እዚህ እንዲደርስ የረዱኝን መምህሬ እና አማካሪዬ ዶ/ር የኔዓለም አረዶን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ የትምህርት እድሉን በመስጠት እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ላደረጉልኝ ትብብር አመሰግናለሁ፡፡

በዚህ ጥናታዊ ጹሑፍ መረጃ በመስጠት ለተባበራችሁኝ፤ለአቶ አውራሪስ ፈቃዴ፣ ለአቶ ሱሊህማን አብዲ፣ ለወ/ሮ አረጋሽ ሽታዬ፣ ለአቶ ወሰኔለህ ጫኔ፣ ለአቶ ሙሳ ሀሰን፣ ለአቶ ደረጀ ወሰኔ፣ ለአቶ አገኘሁ ትርፌ፣ ለአቶ አህመድ ጀማል፣ ለአቶ ኑሩሁሴን አህመድ፣ ለአቶ ሽዋረገድ አጥናፉ፣ ለአቶ ጀማል መሀመድ እና ለአቶ መንገሻ ሀይሌ እንዲሁም ለንዑስ መረጃ አቀባዬዎቼ በሙሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ስኬታማ እንድሆን ሁሌም ለምትረዱኝ፤ከጎኔ ሆናችሁ ለምታግዙኝ፤ቤተሰቦቼ በተለይም እናቴ ፋንታዬ ደርቤ እና ውድ ወንድሜ ጥላሁን ደርቤ ላደረጋችሁልኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይክፈላችሁ፤እድሜና ጤና አብዝቶ ይስጥልኝ፡፡

# ማውጫ


ምስጋና ............................................................ i

ማውጫ ............................................................ ii

ሙዳዩ ቃላት ............................................................ vii

አጠቃሎ ............................................................ viii

ምዕራፍ አንድ ............................................................ 1

መግቢያ ............................................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ............................................................ 3

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............................................................ 7

1.3. የጥናቱ ዓላማ ............................................................ 8

1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ............................................................ 8

1.3.2. ዝርዝር አላማዎች ............................................................ 8

1.4. የምርምር ጥያቄዎች ............................................................ 8

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ............................................................ 9

1.6. የጥናቱ ወሰን ............................................................ 9

1.7. የጥናቱ ስነ ዘዴ ............................................................ 10

1.7.1. የናሙና አመራረጥ ስልት ............................................................ 10

1.7.2. የመረጃ አሰባሰብ ............................................................ 11

1.7.2.1. ምልከታ ............................................................ 12

1.7.2.2. ቃለ መጠይቅ ............................................................ 13

1.7.3. የመረጃ መተንተኛ ስልት ............................................................ 13

1.8. የመስክ ተሞክሮ ............................................................ 14

1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ............................................................ 15

1.10. የጥናቱ አደረጃጀት ............................................................ 16

1.11. የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ............................................................ 17

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................................ 18

ክለሳ ድርሳናት ....................................................................................................... 18

2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ ............................................................................................ 18

2.1.1. የባህል ህክምና ምንነት ................................................................................... 18

2.1.2. የባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎች ማንነት ................................................................. 20

2.1.3. በባህል ሕክምና በሽታን የመለያ እና የምርመራ ዘዴዎች ............................................ 22

2.1.4. ባህል፣ ጤና እና ሥነ ምህዳር ........................................................................... 22

2.1.4.1. ባህል ........................................................................................................ 22

2.1.4.2. ጤና ......................................................................................................... 23

2.1.4.3. ሥነ ምህዳር ............................................................................................... 23

2.1.5. ሀይማኖት፣ እምነት እና ሀገረሰባዊ መድሀኒት ........................................................ 25

2.1.6. የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማ እና አሰጣጥ .................................................... 28

2.1.7. የሀገረሰባዊ መድሀኒት ህክምና እውቀት ተስተላልፎ .................................................. 29

2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ....................................................................................... 31

2.2.1 የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Functionalism Theory) ............................................. 31

2.2.2. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ (Performance centerd Approche) .................................. 35

2.2.3. የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ (Medical Ecology Theory) .................................... 38

2.2.4. የንድፈ ሃሳቦች ትስስር ..................................................................................... 39

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ................................................................................... 41

2.3.1. በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች . 41

2.3.2. በስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል በሀገር ውስጥ እና በውጪ የተካሄዱ ጥናታዊ ጽሑፎች ............ 50

2.3.3. በሥነ ህብረተሰብ (Sociology) ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት .................................. 53

2.3.4. በሀገር ውስጥ እና በውጪ ምሁራን፤ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም እንዲሁም በተለያዩ የጥናት መድረኮች ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጹሑፎች .......... 54

ምዕራፍ ሶስት ........ 60
የሸዋሮቢት ከተማ አካባቢያዊ ዳራ ........ 60
3.1. መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ........ 60
3.2. የአካባቢ ስያሜ እና የህዝብ አሰፋፈር ........ 61
3.3. የህዝቡ ቋንቋና ሀይማኖት ሁኔታ ........ 61
3.4. የትምህርት ሁኔታ ........ 62
3.5. የህዝቡ መተዳደሪያ ........ 62
3.6. የቱሪስት መስህብ ........ 63
3.7. የባህል ገፅታ ........ 68
ምዕራፍ አራት ........ 70
ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ ........ 70
4.1. በሀገረሰብ ህክምና የሚድኑ፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚያጠቁ በሽታዎች ........ 70
4.2. በሀገረሰብ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴ ........ 72
4.3. ለሀገረሰብ መድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆች መገኛ ቦታዎች ........ 75
4.4. ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ የዕፅዋት ክፍሎች ........ 77
4.5. ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ተያያዥ እምነቶች፣ ልማዶችና የተመረጡ ቀናት ........ 78
4.6. ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ሂደት ........ 84
4.6.1. ለቆላ ቁስል (አንትራክሲ) የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ........ 86
4.6.2. ለአልማዝ ባለጭራ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ........ 87
4.6.3. ለችፌ በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ........ 88
4.6.4. እባብ ለነደፈው ሰው የሚዘጋጅ መድሀኒት ........ 90
4.6.5. ለአይሬ በሽታ የሚዘጋጅ መድሀኒት ........ 91
4.6.6. ለእከክ ፣ ሰውነትን ለሚያቆስል እና ለማዲያት የሚዘጋጅ መድሀኒት ........ 92
4.6.7. ለወፍ በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ........ 93
4.6.8. ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ለሆድ መንፋት የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ........ 93
4.6.9. ለላሽ የሚዘጋጅ መድሀኒት ........ 94

4.6.10. ለምች በሽታ የሚዘጋጅ መድሀኒት ....96
4.6.11. ለኪንታሮት በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ....96
4.7. በሸዋሮቢት አካባቢ ጎልተው የሚታዩ የበሽታ አይነቶችና የመድኃኒቶች አሰጣጥ በሰንጠረዥ ....96
4.8. የሀገረሰብ ህክምና እውቀት እና ተስተላልፎ ....101
4.9. የሀገረሰባዊ መድሀኒት ምስጢራዊነት ....103
4.10. ዘመናዊ ሀኪሞች ለሀገረሰባዊ ህክምና ያላቸው አመለካከት ....106
4.11. ባህላዊ ሀኪሞች ለዘመናዊ ህክምና እና ለባለሙያዎቹ ያላቸው አመለካከት ....108
4.12. የባህል ሀኪሞች በታካሚዎች ዘንድ የሚመረጡባቸው ቅድመ ሁኔታዎች (ምክንያቶች)....110
ምዕራፍ አምስት ....114
5.1. ማጠቃለያ ....114
5.2. ይሁንታ ....117
የማጣቀሻ ጹሑፎች ....118

## የሰንጠረዥ እና የፎቶ ግራፍ እንዲሁም ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ማውጫ


አባሪዎች ........ 124

አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ ........ 124

አባሪ ሁለት፡- በባህላዊ ሀኪሞች መኖሪያ ቤት የተገኙ የባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች መረጃ ........ 125

አባሪ ሶስት፡- ለአካባቢው ማህበረሰብ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ዘመናዊ ሀኪሞች መረጃ ........ 126

አባሪ አራት፡- ስለ ጥናቱ አካባቢ አጠቃላይ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ የሀይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች እና እናቶች መረጃ ........ 127

አባሪ አምስት፡- የመስክ ምልከታ መከታተያ ቅጽ ........ 128

አባሪ ስድስት፡- ለባህል ህክምና ባለሙያዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ 129

አባሪ ሰባት፡- ለባህል ህክምና ተጠቃሚዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ 132

አባሪ ስምንት፡- ለዘመናዊ ሀኪሞች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ 134

አባሪ ዘጠኝ፡- በአካባቢው ለሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች፣የሀይማኖት አባቶች እና ተወላጆች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ 136

አባሪ አስር፡- ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት መገኛ ስፍራዎች እና የመረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ በከፊል ........ 137

## ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| **መብረስ** | የመድሀኒቱ የማዳን ሀይል መቀነስ፣ መጥፋት |
| **መንጻት** | መጽዳት (ውጫዊ እና ውስጣዊ) ፣ መታጠብ፣ ከሰዎች ጋር ክፉ አለመነጋገር፣ መጥፎ አለማሰብ፣ ከፈጣሪ ጋር በፀሎት፣በስግደት መታረቅ |
| **ሙቀጫ** | ከተለያየ የእንጨት አይነት የሚሰራ (ለመውቀጫ የሚያገለግል) |
| **ቀረጢት** | ከቅዳጅ ጨርቅ በእጅ የተሰፋ መቋጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል |
| **አይሰምርም** | መድሀኒቱ አያድንም፣ መድሀኒት አይሆንም |
| **የተተፋልኝ/ተተፋልኝ** | ከቤተሰብ አልያም ከወዳጅ ዘመድ ወይም ከጓደኛ ሰዎችን ከህመማቸው እንዲያድን ወይም እንዲፈውስ የተሰጠው፣ የተመረቀለት፣ የተነገረው፤የመድሀኒት አይነት (እውቀት) |
| **አንተራክሲ** | የበሽታ አይነት ሲሆን የበሽታው ሌላኛው ስያሜ የቆላ ቁስል በሚል ይታወቃል |
| **ህዶድ** | ለአይሬ በሽታ መድሀኒት የሚሆን የዕፅ አይነት |
| **አንጉስተር** | ለተለያዩ በሽታዎች መድሀኒት የሚሆን የዕፅ አይነት ሲሆን ሌላው ስያሜው እሬት በሚል ይታወቃል |

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት “ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት እውቀት፣አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ” በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ ሀገር በቀል የህክምና እውቀትና ልማድ መመርመር ነው፡፡ የምርምሩ ዋና አላማ የማህበረሰቡን ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በመመርመር ባህላዊ ልማዱን ገልጾ ማሳየት ሲሆን በአካባቢው በባህላዊ ህክምና የሚፈወሱ በሽታዎችን መለየት፣ ለሀገረሰባዊ መድሀኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶች ከምን ከምን እንደሚገኙ መግለጽ፣ የመድሀኒቶቹን አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ማሳየት እና በአካባቢው የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች የህክምና እውቀት ተስተላልፎ ሂደት መግለጽ የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የመስክ መረጃ፤በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበው በመቅረጸ ድምፅ፣ በማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ እና በፎቶ ተሰንደዋል፡፡ የመስክ መረጃ ሰጪዎች ከክርስትና እምነት ተከታዮች እና ከእስልምና እምነት ተከታዮች የተውጣጡ ሲሆኑ ከሀገረሰብ ሀኪሞች፣ ከባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች፣ ከዘመናዊ ሀኪሞች እና ከሀገር ሽማግሌዎች፤በአላማ ተኮር፣ አመቺ እና ጠቋሚ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ ከቁልፍ እና ከአጋዥ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ መረጃዎች አይነታዊ የምርምር ስልት በመጠቀም በይዘትና በምድብ ተደራጅተዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ ክዋኔ ተኮር እና የጤና ሥነ ምህዳር (Medical Ecology) ንድፈ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ በገላጭ እና ተንታኝ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በትንታኔው መሰረት ለጥናት የተመረጠው አካባቢ ቆላማ መሆን የአካባቢውን ማህበረሰብ ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጋለጥ ምክንያት መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በአብዛኛው የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚያጠቁ በሽታዎችም፤የቆላ ቁስል፣ አልማዝ ባለጭራ፣ ችፌ፣ ላሽ፣ በእባብ መነደፍ፣ ሆድ ቁርጠት (ተቅማጥ)፣ ኪንታሮት፣ ምች፣ አይሬ፣ እከክ (ቁስል) እና የወፍ በሽታ መሆናቸው ተደርሶበታል፡፡ በአካባቢው ያሉ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች በሀይማኖት፣ በብሔር እና በአመለካከት የተለያዩ መሆናቸውንም ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች በእይታ፣ በመነካካት እና በጠየቅ በሽታን እንደሚለዩ በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡ በዚህ መልኩ ከተለዩ በኋላ በሽታዎቹን ለማከም በአብዛኛው በአካባቢው ያሉ ዕፅዋት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ የመድሀኒቱ አሰባሰብ ፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ስርዓቱም እንደ ባህል ሀኪሙ እውቀት፣ እምነት፣ ልምድ እና አመለካከት፤ ሰዓትና ቀናት ተመርጠው እንዲሁም የተለያዩ ክንዋኔዎች ከተከናወኑ በኋላ፤የተሰበሰቡት ዕፆች በመፍጨት፣ በመውቀጥ፣ በመቀቀልና በማድረቅ፤በሚጠጣ፣ በሚታሰርና በሚቀባ መልክ ተዘጋጅተው የሚሰጥ መሆኑ ተገልጧል፡፡ በጥናቱ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችም በሀይማኖት፣ በብሔር እና በአመለካከት የተለያዩ መሆናቸውንና ወደ ባህል ሀኪሞች ለመሄድ ልዩነቱን መሰረት እንደማያደርጉ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ ከተለያየ ብሔረሰብ፣ ሀይማኖት እና አመለካከት ያለው የማህበረሰብ ክፍል ጋር በመገናኘት ማህበራዊ ተግባቦትን መፍጠር መቻላቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በተጠኚው ማህበረሰብ፤በዘመናዊ ሀኪሞች መድሀኒት ያልተገኘላቸው በሽታዎች በባህላዊ ህክምና የሚዳኑ መሆናቸው፣ ህክምናውን በፍጥነት ማግኘት የሚችሉ መሆኑ እና እርስ በርስ ያላቸው ቅርርብ የጠበቀ መሆኑ፤ከዘመናዊ ህክምና ይልቅ ባህላዊ ህክምናው ተመራጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ህክምና የአካባቢውን ማህበረሰብ ጤንነት በማስጠበቅ፣ ማህበራዊ መስተጋብር በመፍጠር፣ እርስ በርስ ወዳጅነትን እና አንድነትን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከተው የወረዳው የጤና ጽ/ቤት፣ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም ግለሰቦች የሀገረሰባዊ ህክምና እውቀቱን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሀገር በቀል የሆነው እውቀት ተጠብቆ እንዲቆይ እና ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ሀገረሰባዊ ህክምና ከዘመናዊው ህክምና በፊት የነበረና እና በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ባህላዊ ዕውቀት ነው። ሀገረሰባዊ ህክምና የማህበረሰቡ እምቅ ባህሎች፣ እምነቶች እና ልማዶች ድምር እውቀት ሲሆን በሽታን መከላከል፣ መመርመር እና ማከም ማለት ነው (K,Andrae,2017)። ባህላዊ መድኃኒት ከበሽታ መፈወስ ብቻ ሳይሆን የሰውን አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ፣ አዕምሯዊና ቁሳዊ ደህንነት በመጠበቅ ረገድም ይጠቅማል። እንደ Bruce and Willcox (2012) ገለጻ በአፍሪካ፣ በእስያ እና በላቲን አሜሪካ ያሉ ሀገራት የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ፍላጎታቸውን ለማሟላት ባህላዊ መድሀኒቶችን ይጠቀማሉ። አያይዘውም በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥም ምዕራባዊውያኑ በዘመናዊ ህክምናው ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ቢሆንም፤ኢትዮጵያውያን በሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ይበልጥ አመኔታ እንዳላቸው አስረድተዋል (Bruce and Willcox,2012,P,24) ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዘመናዊ የጤና አገልግሎቶች በከተሞች ውስጥ በትኩረት እየተሰራባቸው ያሉ፤ በተለይም ቁጥሩ እየጨመረ ካለው የህዝብ ብዛት ጋር እኩል በመጓዝ የጤና እንክብካቤ ተደራሽነት እንዲኖር፤በገጠሩ ኢትዮጵያ ለሚኖሩት አብዛኞዎቹ ኢትዮጵያውያን ተደራሽ እንዲሆኑ በጤናው ዘርፍ እየተሰራ ነው። ይሁን እንጂ ባህላዊ መድሀኒት ይበልጥ ተደራሽ እና አቅምን ያገናዘበ በመሆኑ እስከ 80% የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ባህላዊ ህክምናውን እንደ ዋና የጤና እንክብካቤ ምንጭ እንደሚጠቀምበት (Bruce and Willcox,P,28,2012) ገልጸዋል።

ባህላዊ መድኃኒት በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል። 85% የሚሆነው የማህበረሰብ ክፍል የሚኖረው በገጠር ነው። በመሆኑም የጤና እንክብካቤው ሽፋን አናሳ በመሆኑ አመራጭ የጤና መጠበቂያ ዘዴ ይፈልጋል። ከዚህ አንጻር 80% የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል ባህላዊ መድሀኒት እንደ ዋና የጤና መጠበቂያ ተቋም ይመለከተዋል (Franklin,W,2011,P,32) በማለት ይገልጻሉ። አያይዘውም አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሰው ልጅ ጤና፤የፈጣሪ ስጦታ ነው የሚል እምነት ያለው ሲሆን ከዚህ እምነት የተነሳ ባህላዊ ሀኪሞች የሰውን ልጅ ጤና ለመመለስ የተላኩ የፈጣሪ ስጦታዎች ናቸው የሚል አመለካከት

ስላላቸው፤ባህላዊ ህክምናው ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ ተቀባይነት ማግኘቱን (Franklin,W,2011,P,33) ያስረዳሉ።

ይሁን እንጂ የባህላዊ ሕክምና ሙያተኞች እውቀት በብሔራዊ የጤና ስርዓት ዘርፍ ችላ መባሉን እና አንዳንድ ባህላዊ ሀኪሞች በባህላዊ መድሃኒቶች እና ልምዶቻቸው ላይ በመመርኮዝ በቂ ሳይንሳዊ እና የሰነድ ዕውቀት አለመኖሩ፣ የኢትዮጵያ መንግስት የባህላዊ ህክምና አሰራሮችን የሙያ ብቃት ለማጎልበት ያለው ቁርጠኝነት ዝቅተኛ መሆን፣ የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ መንግስት ምንም ዓይነት ድጋፍ አለማግኘታቸው፣ የባህላዊ መድኃኒት ምዝገባ ሂደት በኢትዮጵያ ውስጥ ግልፅ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀርጾ አለመቀመጡ የኢትዮጵያ ባህላዊ መድሃኒት እውቅና እንዳይኖረው አድርጓል (Franklin,W, 2011)።

በተጨማሪም ባህላዊ ህክምናዎች በልምድ ብቻ የሚሠራባቸው መሆኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ብቻ እንዲወሰን አድርጓል። ይህም ሀገረሰባዊ ዕውቀት ብዙ ርቀት እንዳይሄድ አድርጎታል። እንደዚህም ሆኖ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጲያውያን ባህላዊ መድኃኒት ተጠቃሚ ናቸው፤መድኃኒቱ ለማንም ከተነገረ ይረክሳል በሚል እምነት ምስጢራዊ ሆኖ በቃል እንዲተላለፍ መደረጉ የሚገባውን ያህል እንዳይበለፅግ እንቅፋት ሆኖበታል ይላሉ (ሻሂዳ፣2017፣ገፅ፣33)።

በሸዋሮቢት ከተማ ውስጥ ዘመናዊ የህክምና መስጫ ተቋማት ቢኖሩም ሀገረሰባዊ ህክምናው በስፋት ለማህበረሰቡ የጤና ሽፋን በመስጠት ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል። ሞቃታማ አከባቢዎች ተናዳፊ ነፍሳት በቀላሉ ለመንቀሳቀስ እና የሚፈልጉት ቦታ ለመዘዋወር ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው በስፋት እንዲራቡ ምክንያት ይሆናል በማለት (Kelley,2008) ያስረዳሉ። እነዚህ ተናዳፊ ነፍሳት የአካባቢውን ማህበረሰብ በማጥቃት ለበሽታ እንዲጋለጥ ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው።

ሸዋሮቢት ከተማ የተለያየ ሀይማኖት፣ እምነት እና አመለካከት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአንድነት የሚኖሩባት ከተማ እንደመሆኗ መጠን በባህላዊ ህክምናው ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎችም እንደዚሁ በሀይማኖት፣ በእምነት እና በአመለካከት የተለያዩ ናቸው። በተለያዩ ወቅቶች ማህበረሰቡ በበሽታ ሲጠቃ፤እራስን ከበሽታው ለመከላከል፤ግላዊ፤ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስጠበቅ፤ወደ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በመሄድ ህክምናውን ማግኘት የግድ ይሆናል። እነዚህ ሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎች እንደ እምነት ስርዓታቸው እና እንዳላቸው የህክምና

እውቀት ለታማሚዎች አገልግሎት ይሰጣሉ። አካባቢው ያፈራቸውን ዕፆች በግብዓትነት በመጠቀም እና በማዘጋጀት ታማሚዎችን ይፈውሳሉ። በመሆኑም በአካባቢው ያሉ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት ቀማሚዎች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እና በጥናት የተደገፈ መረጃ ለማቅረብ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ተገቢ ነው። በዚህ መሰረት ይህ ጥናት በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ የሚገኙ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት ህክምና እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ምን እንደሚመስል መርምሯል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሀገረሰባዊ መድሃኒት በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የማህበረሰብ ልማድ ነው። እያንዳንዱ ማህበረሰብ ራሱን ከበሽታ የሚከላከልበት፣ የሚፈውስበት እና የሚጠብቅበት የራሱ የሆነ ሀገር በቀል እውቀት አለው። ይህ ሀገር በቀል እውቀት ከዕፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት በተገኙ ግብዓቶች መንፈሳዊ አምልኮዎችን፣ እምነት እና ልምዶችን በአንድ ላይ በማጣመር ለማከም፣ ለመመርመር እና በሽታን ለመከላከል ወይም ደህንነትና ጤንነትን ለመመለስ የሚያገለግል የጤና ልምምድ፣ አቀራረብ፣ ዕውቀት እና እምነት ነው። የባህል ሕክምና እውቀት፣ ልማድና አተገባበር ሥርዓት መቼ ተጀመረ? እንዴት? እና እነማን ጀመሩት? ለሚሉ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ፣ መረጃና ማስረጃ ማግኘት እንደሚያስቸግር፤በመስኩ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች (አሰፋ፣2008፤ Pankhurst,1996; Alemayehu,1984) ጠቁመዋል። ይሁን እንጂ የተለያዩ የጥናት ስራዎችን ዋቢ በማድረግ እና የታሪክ መጻህፍትን በማገላበጥ ካገኟቸው ሀሳቦች በመነሳት የተወሰኑ መረጃዎችን አቅርበዋል።

Alemayehu (1984) የባህል ህክምና አጀማመር አስመልክተው ሲገልጹ “የሰው ልጅ በሽታን መከላከል፣ መድኃኒት መጠቀምና መፈወስ የጀመረው ከጥንተ-ክርስቶስ ልደት 25,000 ዓ.ዓ በፊት ነው” ይላሉ። በሌላ በኩል (Desta ,2004) እና (Pankhurst ,2005) በኢትዮጵያ የባህል ሕክምና ታሪክ አጀማመር በቂ የታሪክ ማስረጃ እንደሌለ ገልጸው፤ስለኢትዮጵያውያን የባህል መድኃኒት አጠቃቀም እውቀት የመጀመሪያ ደረጃና መረጃ የሚሉት የ”Alessandro Zorzi እና የFrancisco Alvares”ን ዘገባ ነው። በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን በባህላዊ ሕክምና ስልት ዕፅዋትን፣ እንስሳትና ማዕድናትን በማዘጋጀትና በመቀመም፤ሰውነትን

በመብጣት፣ በመተኮስ፣ በማከምና በመጠገን፤ሕመምን የመፈወስ ልምድ እና እውቀት እንደነበራቸው የጠቆሙ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሻሂዳ ሲያስረዱ፤በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥንታውያን መዛግብት ጥናት ተመራማሪ መርሻ አለኸኝን ጠቅሰው"አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ባጠፉበት ወቅት እንግሊዛውያኑ ከቤተ መጻሕፍታቸው ብዙ መጻሕፍት ወስደዋል፡፡ ከወሰዱት መካከል ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ለማንቀሳቀስ የሦስት ሰዎችን ትብብር የሚጠይቁ ሁለት ትልልቅ "ዕፀ ደብዳቤ" የተባሉ ስለ ባህላዊ መጽኃኒቶች የሚዘረዝሩ ይገኙባቸዋል" (2017፣ገፅ፣3)፡፡ እንደዚህ ያሉ በርካታ መጻሕፍት፤በተለያዩ ጊዜያት ከአገር ተሰርቀው መውጣታቸውና በሌሎች ሀገሮች ምርምር እየተደረገባቸው እንደሚገኝም አስረድተዋል፡፡

Pankhurst (1996) ደግሞ ኢትዮጵያውያን የባህል መድኃኒትን ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ይጠቀሙ እንደነበር፤ከመድኃኒት መቀመሚያ መጻሕፍት መካከል በግዕዝ "Matsahafe Fews" በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ፤"Mastahafe Medhanit" ደግሞ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ታዋቂ መጻሕፍት እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡ እነዚህ የባህል መድኃኒት መቀመሚያ መጻሕፍት ከሥነ ምህዳር የሚገኙ የተለያዩ ግብዓቶችን በማካተት፤የዕፅዋት፣ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ እና የማዕድናት ውጤቶችን ዝርዝር፤አስማታዊ እና መለኮታዊ አምልኮዎችን አጠቃለው የያዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ይህንን አስመልክቶ ሻሂዳ (2017፣3) ሲያስረዱ ባህላዊ ፈውስ፣ ባህላዊ መድኃኒትና ቅመማ ላይ በግዕዝ የተጻፉ መጻሕፍት ያሉ ሲሆን የመድኃኒት ቅመማን በተመለከተ ምን ተቀላቅሎ፣ ለምን ዓይነት በሽታ ፈውስ እንደሚሆን የሚያስረዱ የተለያዩ የብራና መጻህፍት አሉ፡፡ ይሁን እንጂ የግዕዝ ቋንቋ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ እየተዳከመ መምጣቱ፤በቤተ ክህነት ብቻ መወሰኑ እነዚህ ጽሑፎች እንዳይነበቡ፤የያዙት ዕውቀት ጥቅም እንዳይሰጥ አድርጓል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሻሂዳ አያይዘውም በአገሪቱ ዘመናዊ ሕክምና ከተጀመረ አጭር ጊዜ (100 ዓመት) መሆኑንና ከዛ በፊት ሰዎች ሲታመሙ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙት በባህላዊ ህክምና እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሀገር በቀል የህክምና እውቀቱ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ እና ጥናት ባለመደረጉ የሚገባውን ያህል ማደግ እንዳልቻለ አብራርተዋል፡፡ ሻሂዳ ቀጥለውም "መጽሐፈ መድኃኒት ላይ ይህንን ቅጠል ከዚህ ነገር ጋር ቀምመህ ለዚህ በሽታ ተጠቀም ይላል፡ ፡ ይህንን በደንብ ጥናት አድርገንበት መድኃኒቶችን ዘመናዊ በሆነ መንገድ በፋብሪካ ደረጃ

ማምረት የሚቻልበት አቅም መፈጠር ነበረበት። አሁን እኮ በተገኘው ነገር ደቁሰው ነው የሚያቀርቡት” (ሻሂዳ፣2017፣3) በማለት ቸል መባሉን ገልጸዋል።

Bruce and Willcox (2012) እንደሚያሥረዱት በብዙ የበለጸጉ አገራት ውስጥ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች በየዓመቱ ለባህላዊ መድኃኒት ወጪ ይደረጋሉ። ለአብነት ያህል እ.ኤ.አ. በ 2012፤32 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጓል። ይህም በ2021 ወደ 60 ቢሊዮን ዶላር እንደሚጨምር ገልጸዋል ።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ Bruce and Willcox (2012) የዓለም ጤና ድርጅት (WHO,2002) ያወጣውን መረጃ በመጥቀስ እንደሚያስረዱት በዓለም ዙሪያ ለባህላዊ መድኃኒት በዓመት እስከ 83 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያህል ወጪ ይደረጋል። ባህላዊ መድኃኒቶችም ለዘመናዊው መድኃኒት ሕክምናዎች እድገት አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ይገልጻሉ። አንድ ሶስተኛ እና አንድ ሁለተኛ የሚሆኑ ዘመናዊ መድኃኒቶች የተገኙት ከዕፅዋት ሲሆን ዲጂታልሲስ፣ ሞርፊን፣ ኩዊይን እና ቪንካ አልካሎይድ የተባሉ ታዋቂ መድሀኒቶች ከዕፅዋት የተገኙ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ሀገረሰባዊ ህክምና፤ከአራቱ የፎክሎር ዘርፎች ውስጥ በሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Customs) ዘርፍ ስር እንደሚካተት (Dorson,1972) ያሥረዳሉ። የኢትዮጲያ የባህል ህክምና ዘርፍ በሁለተኛ ዲግሪና በሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲሁም ለተለያዩ ኮንፈረንሶች እና መድረኮች በሀገር ውስጥ እና በውጪ የቀረቡ በሂውማኒቲስ፣ ማህበራዊ ሳይንስ እና በሥነ ህይወት ሳይንስ ፋካልቲ ትምህርት ክፍሎች ጥናቶች ተካሂደዋል። ከእነዚህም ውስጥ ዓለማየሁ (2000)፣ ምህረት (2000)፣ መስፍን (2002)፣ ተመስገን (2003)፣ ደነቀ (2003)፣ትዕግስት (2008)፣ፍቅርተ (2009)፣ Young (1970)፣ Alemayehu (1984)፣ Mirgissa (1993)፤ Abraraw (1998)፤ Elsabeth (1976)፣ Fekadu (2001)፣ Getachew (2002)፣ Yared (2004)፣ Wondwosen (2006)፣ Mekonen. (2010) ጥቂቶቹ ናቸው።[1]

የጥናታዊ ጹሁፎቹ ይዘት ይዘውት እንደተነሱት ዓላማ የተለያየ ቢሆንም በአብዛኛው ትኩረታቸውን ያደረጉት የባህላዊ መድሀኒቶቹ አዘገጃጀት፣ አቀማመም እና አሰጣጥ ስርዓት መመርመር ላይ ነው። አንዳንድ ጥናቶች፤በአንድ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ

---

[1] በዳራው ክፍል የተዘረዘሩት ጥናታዊ ጹሑፎች ከተለያዩ ትምህርት ክፍሎች ተውጣጥተው ዳሰሳ የተደረገባቸው (በምዕራፍ ሁለት) ሲሆን፤ እነዚህ ጥናታዊ ጹሑፎች በዓመተ ምህረት ደረጃ (እ.ኢ.አ) የቀረቡ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

የባህል ሀኪሞች መድሀኒቶቹን ሲያዘጋጁና እና አገልግሎቱን ሲሰጡ የሚከውኗቸውን ክዋኔዎች፣ ልማዶች እና እምነቶች፣ መመርመር ላይ ትኩረታቸውን አድርገዋል። የተወሰኑት ጥናቶች ደግሞ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች በሽታዎች ሲከሰቱ በተፈጥሯዊ እና በመለኮታዊ መንገድ ህመምተኞችን የሚፈውሱበትን ስርዓት ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ የአንድ ማህበረሰብ ባህላዊ መድሀኒቶች አዘገጃጀት፣ አቀማመም እና አጠቃቀም ስርዓት፤ ከሀይማኖት፣ ከእምነት እና ከልማድ የሚለይ አይደለም። ይሁን እንጂ እነዚህን ተያያዥ ጉዳዮች አስተሳስሮ  የማጥናት ሁኔታ እምብዛም አይስተዋልም።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጹሑፍ እና ፎክሎር ት/ክፍል ውጪ የተካሄዱ ጥናቶች እንደየሙያ መስካቸው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ እና ጭብጣቸው በተወሰነ መልኩ ይለያያል። ከእነዚህም ውስጥ በታሪክ ት/ክፍል የተጠኑ ጥናቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱ የበሽታ አይነቶችን እና የባህል ህክምና ታሪክ ይዳስሳሉ። በሥነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች ደግሞ አካባቢያዊ ባህልን መሰረት በማድረግ የባህላዊ ህክምናውን ተግባር እና ስርዓት ተመልክተዋል። የተወሰኑ ጥናቶች ባህላዊ ህክምናውን ከአንድ ሀይማኖት እና ልማድ ጋር በማያያዝ ለማጥናት የተሞከሩባቸው ጥናቶችም አሉ።

በመሆኑም በጥናቱ ሂደት ሊነጣጠሉ የማይገባቸው የሀገረሰባዊ መድሀኒት ተያያዥ እምነቶችና ልማዶች በተለያየ ፈርጅ ቀርበው ይገኛሉ። ይህም ሀገረሰባዊ መድሀኒት ከልማድ፣ ከእምነት እና ከሀይማኖት ጋር ያለውን መስተጋብር ማሳየት ስለማይችል በፎክሎር የጥናት መስክ ክፍተት ይፈጥራል። ስለሆነም ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች የአንድን ማህበረሰብ እምነት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እና የአኗኗር ዘዴ የሚያሳዩ በመሆናቸው ከሀይማኖት፣ ከእምነት እና ከልማድ አኳያ ያላቸውን ቁርኝት በሚገባ መመርመር ተገቢ ይሆናል።

በአጠቃላይ የባህል ሕክምና እውቀት የማህበረሰብን አካባቢያዊ እውቀት፣ እምነት፣ ደንብ፣ ሥርዓት፣ ተግባርና ሙያን ታሳቢ ያደረገ፤ጥበባዊ ድርጊትን ያካተተ፤የተለያዩ የበሽታ መንስኤዎችን፣ አውዳዊ ሥርዓቶችን፣ የጤና መጠበቂያና በሽታ መከላከያ ዘዴዎችን መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ ጥናት በሸዋሮቢት ከተማና ዙሪያዋ የሚተገበረውን የባህል ህክምና እውቀት ከአካባቢው አየር ጸባይ ጋር ያለው ግንኙነት እና የበሽታ መንስኤ፣ የባህል መድሀኒት ባለሙያዎች፤ከሀይማኖት፣ ከእምነት እና ከልማድ አንጻር ያላቸውን አመለካከት መግለጽ፣ የምርመራ ሂደት፣ የመድሀኒት አቀማመም እና አሰጣጥ ስርዓት ምን ይመስላል የሚሉት ትኩረት ተደርጎባቸዋል ።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ርዕስ ለመምረጥ ያነሳሳኝ ምክንያት ተወልጄ ባደኩበት በሸዋሮቢት ከተማ ማህበረሰቡ በተለያዩ ወቅቶች በአደገኛ በሽታዎች ሲጠቃ፤አንዳንዶቹ ወደሀገረሰባዊ ሀኪሞች በመሄድ ሲፈወሱ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች በመሄድ ህይወታቸው ያለፉ ብሎም ለከባድ የአካል ጉዳት የተዳረጉ ሰዎችን ተመልክቻለሁ፡፡ በሌላ በኩል በአካባቢው ካሉ ዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች እንደሰማሁት በተለያዩ ወቅቶች በበሽታ ሲጠቁ ወደ ባህላዊ ሀኪሞች በመሄድ የህክምና አገልግሎት በማግኘት እንደሚፈወሱ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በተለያዩ አጋጣሚዎች አንዳንድ ወደ ዘመናዊ ሀኪሞች የሚሄዱ ታካሚዎችን፤ዘመናዊ ሀኪሞቹ አንችልም በሚል ወደ ባህላዊ ሀኪሞች የሚልኳቸውን ታማሚዎች በቅርበት ለማየት ችያለሁ፡፡ ከዚህ አንጻር በአካባቢው የሚገኙ የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች እውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ ስርዓት ምን ይመስላል? ዘመናዊ ሀኪሞችስ በባህላዊ ህክምናው ላይ እምነት ያሳደሩበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች የመመለስ ጉጉት ስላደረብኝ፤

ሁለተኛ፡- በሸዋሮቢት ከተማና ዙሪያዋ የተለያየ ብሔረሰብ፣ ሀይማኖት እና አመለካከት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአንድነት የሚኖሩበት አካባቢ ነው፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ያሉ የሀገረሰብ ሀኪሞችም አንድ አይነት እምነት፣ ቋንቋ እና አመለካከት ያላቸው ሰዎች አለመሆናቸውን ተረድቻለሁ፡፡ በመሆኑም ከእምነት አስተምሯቸውና ካላቸው የአመለካከት ልዩነት አንጻር ለሀገረሰብ ህክምና ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚለውን መመርመር ተገቢ መሆኑን ስላመንኩ እና ታካሚዎችም የሀይማኖት፣ የአመለካከት እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ ልዩነቶችን የሚያስተናግዱ በመሆናቸው ለባህል ህክምናው ያላቸው እሳቤ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን አምናለሁ፡፡ ስለሆነም እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ወደ ማህበረሰቡ ቀርቦ ጥናትና ምርምር ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ መረዳት በመቻሌ ለጥናት እንድነሳሳ ምክንያት ሆኖኛል፡፡ የቀደመው ልምዴ እንዳለ ሆኖ በክፍለ ትምህርታችን የፎክሎር ኮርሶችን በምንወስድበት ጊዜ ሀገረሰባዊ መድሀኒት አንድ የጥናት መስክ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን ዳሰሳ ሳደርግ በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ በሀገረሰባዊ መድሀኒት ዙሪያ የተደረገ ጥናት አለመኖሩን በማወቁ በዚሁ ርዕስ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማድረግ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚሰጡ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥን በመመርመር ባህላዊ ልማዱን ገልፆ ማሳየት ነው። ይህ ጥናት ቀጥሎ የቀረቡ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

### 1.3.2. ዝርዝር አላማዎች

- ✓ በአካባቢው በባህላዊ ህክምና የሚፈወሱ በሽታዎችን መለየት
- ✓ በማህበረሰቡ ለሀገረሰባዊ መድሀኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶች ከምን ከምን እንደሚገኙ መግለጽ
- ✓ የመድሀኒቶቹን አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ማሳየት
- ✓ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶቹ የሚሰበሰቡበት ቀናት እና ሰዓታት፤ከእምነት እና ከልማድ አኳያ ያላቸውን ትዕምርታዊ ፋይዳ ማሳየት የሚሉት ናቸው።
- ✓ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች የህክምና እውቀት ተስተላልፎ ሂደት መግለጽ

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ከላይ የተመለከቱትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

- ✓ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚከሰቱ፤በባህላዊ ህክምና የሚዳኑ በሽታዎች እና መንስኤያቸው ምንድን ነው?
- ✓ በማህበረሰቡ ለባህል ህክምና መድሀኒት መቀመሚያ የሚሆኑ ግብዓቶች ከምን ይገኛሉ?
- ✓ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች አዘገጃጀት፣ አጠቃቀም እና አወሳሰድ መንገዶች ምን ይመስላሉ?
- ✓ ለመድሀኒቶቹ መሰብሰቢያነት እና መቀመሚያነት የሚመረጡ ጊዜያት እና ሰዓታት ባህላዊ ሀኪሞቹ ከሚከተሉት ሀይማኖት፣ እምነት እና ልማድ አንጻር ያላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳ ምንድን ነው?
- ✓ በአካባቢው የሚገኙ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት ሀኪሞች የእውቀት ምንጮች እነማን ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

- ✓ የተጠኝውን ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ ስርዓት ልማዱን ገልጾ ያሳያል፡፡
- ✓ ይህን የጥናት ወረቀት ማግኘት ለቻሉ አንባቢዎች በአካባቢው ላይ ስለሚከሰቱ በሽታዎች እና ስለሚሰጡ መድሀኒቶች ግንዛቤ በመፍጠር፤የበሽታዎቹ ምንነት ሳይታወቅ ለሞት እና ለአካል ጉዳት የሚዳረጉ አካላትን በተወሰነ መልኩ ይታደጋል፡፡
- ✓ በሀገረሰባዊ ልማድ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ የዘርፉ ምሁራን ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡
- ✓ በዚህ ርዕስ ዙሪያ በሳይንሳዊ መንገድም ይሁን ባህላዊ ጥበቡ ላይ በመመስረት ሰፊ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ አካላት በመነሻነት ያገለግላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ፣ ጊዜ፣ ገንዘብ እና አቅም ታሳቢ በማድረግ ትኩረት እና ገደቡ ተወስኗል፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ በሀገረሰባዊ ልማድ ዘርፍ ስር ከሚካተተው ሀገረሰባዊ ህክምና ላይ አተኩሯል፡፡ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች የተለያዩ በመሆናቸው ጥናቱ፤ለሰው የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚሰጡ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በመመርመር ባህላዊ የህክምና ልማዱን ገልጾ ማሳየት ላይ አተኩሯል፡፡ ይሁን እንጂ የባህል መድሀኒቶችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማጥናት የፎክሎር የጥናት መስክ ትኩረት ባለመሆኑ ጥናቱ ባህላዊ ገፅታ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች ላይ ያለውን ሀገር በቀል እውቀት መርምሯል፡፡ የዕፅዋት ሀገረሰባዊ መድሀኒት ላይ ትኩረት ያደረገበት ምክንያት በቅድመ መስክም ሆነ በመስክ የመረጃ አሰባሰብ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በአካባቢው የሚገኙ የሀገረሰብ የህክምና ባለሙያዎች መድሀኒቶቹን የሚያዘጋጁት ከዕፅዋት መሆኑ ጥናቱ የዕፅዋት የሀገረሰብ ህክምና ላይ እንዲያተኩር አድርጎታል፡፡

ከቦታ አንጻር፤በሸዋሮቢት ከተማ ውስጥ ዘጠኝ (9) ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ዙጢ ቀበሌ (05)፣ ጫሬ (03)፣ የዋንዛ ቀበሌ (08)፣ ማድያ (04) እና ፓፓዬ ሰፈር (02) ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት በሸዋሮቢት ከተማ ውስጥ ያሉ የባህል ሀኪሞች በብዛት የሚገኙበት በመሆናቸው ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮችን መረጣ

በተመለከተም በቀበሌዎቹ ውስጥ በሚኖሩ ባህላዊ ሀኪሞች፣ የሀገረሰብ ህክምና ተጠቃሚዎች እና ዘመናዊ ሀኪሞች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ እነዚህ ባህላዊ ሀኪሞች የሚሄዱ ታካሚዎች በአምስቱ (5) ቀበሌዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ ሳይሆኑ በዘጠኙም ቀበሌዎች እና በዙሪያው የሚገኙ ቆላማ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት የተጠቀምኳቸው መረጃ አቀባዮች ከዘጠኙም ቀበሌዎች የተውጣጡ ናቸው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ስነ ዘዴ

ይህ ጥናት ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት እውቀት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ፣ ማህበረሰቡ ለባህላዊ ህክምና እና ሀኪሞች ያለውን አመለካከት እንዲሁም ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ስለሚመርጧቸው ቀናት እና ስለሚከውኗቸው ገቢሮች ያላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳ በስፋት የሚመለከት በመሆኑ ገላጭ ጥናት (Descriptive study) እና ተንታኝ የአተናተን ስልት (analysis Methods) ተጠቅሟል፡፡

### 1.7.1. የናሙና አመራረጥ ስልት

በሸዋሮቢት ከተማ ከሚገኙ ዘጠኝ ቀበሌዎች ውስጥ ለጥናቱ የተመረጡት አምስት (5) ሲሆኑ እነዚህም ዙጢ ቀበሌ (05)፣ ጫሬ (03)፣ ማድያ (04)፣ ፓፓዬ ሰፈር (02) እና ዋንዛ (08) ቀበሌዎች ናቸው፡፡ ያለው አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት አስመልክተው ሲያስረዱ "አላማ ተኮር (Purposeful sampling) ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ይዞት የተነሳውን አላማ ከግብ ለማድረስ ያግዙኛል የሚላቸውን አካላት በሚገባ በማጤን ይመርጣል"(2009፣136)፡፡ በመሆኑም የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ሁነኛ መረጃ አቀባዮች አሉባቸው የተባሉ አምስት (5) ቀበሌዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በብዛት የሚገኙት በእነዚህ ቀበሌዎች ውስጥ በመሆኑ፤ቀበሌዎቹ ውስጥ ያሉ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በጥናቱ ተሳታፊዎች ቢሆኑ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን አላማ ማሳካት እንዲችል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ከሚል እምነት የተነሳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጥናቱ አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን ተገልግሏል፡፡ ይህ የናሙና ዘዴ ያለው እንደሚያስረዱት "ተመራማሪው ጥናቱን በቅርበት ባገኛቸውና ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ምርምሩን ሲያካሂድ አመቺ ንሞና ተጠቀመ ማለት ይቻላል"(2009፣135) በማለት

ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር በጥናቱ ሂደት መረጃዎቹ በሚሰበሰቡበት ወቅት በሀገረሰባዊ ሀኪሞች የህክምናውን አገልግሎት ለማግኘት የተገኙ ታካሚዎችን በመረጃ ሰጪነት በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል። በተጨማሪም ጠቋሚ የንሞና አመራረጥ ስልት በዚሁ ጥናት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህም በሸዋሮቢት ከተማ ውስጥ የሚገኙ የባህል ሀኪሞችን በተሟላ መንገድ ለማግኘትና መረጃዎችን ምሉዕ ለማድረግ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከራሳቸው ከባህል ሀኪሞች በሚሰጡ ጥቆማዎች ያሉትን ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በማግኘት ሙሉ መረጃ ለማቅረብ አመቺ በመሆኑ በጥናቱ ተግባራዊ ሆኗል። በአጠቃላይ ለጥናቱ ምሉዕነት ሲባል አላማ ተኮር፣ አመቺ እና ጠቋሚ የናሞና አመራረጥ ስልት እንደ አስፈላጊነታቸው በመጠቀም ከአስራ ሁለት (12) የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች፣ ከአምስት (5) የባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች እና ከሶስት (3) ዘመናዊ ሀኪሞች ስለ ሀገረሰባዊ ህክምና ዝርዝር መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናቱ ተካሂዷል።

### 1.7.2. የመረጃ አሰባሰብ

ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል። የመስክ ምርምር በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በጹሑፍ መጠይቅ መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል (ፈቃደ፣1992፣90) ይጠቁማሉ። በመሆኑም በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ቁልፍ እና አጋዥ ከሆኑ መረጃ አቀባዮች በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። በዚህ መሰረት ስለ መድሀኒቶቹ አዘገጃጀት፣ አቀማመም እና አሰጣጥን በተመለከተ በከፊል ምልከታ በማድረግ እና በቃለ መጠይቅ መረጃዎቹ ተሟልተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት፤ቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመጠቀም ቢሞከርም፤የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች እርስ በርስ አለመግባባት፣ መቀናናት እና መናናቅ፤ባለሙያዎቹን ሰብስቦ በማወያየት መረጃ ለመሰብሰብ አልተቻለም። ይኸውም ሁሉም የባህል መድሀኒት ባለሙያዎቹ ባላቸው እውቀት ኩሩ በመሆናቸው አንዳቸው የአንዳቸውን እውቀት የመቀበል እና የመደማመጥ ሁኔታቸው አናሳ ነው።

በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተሰሩ የሁለተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጹሑፎች፣ በቤተ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ጽንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ መረጃዎች፤እንዲሁም ለጥናት የተመረጠው፤የሸዋሮቢት ከተማ አካባቢያዊ መግለጫዎች ለጥናቱ በግብዓትነት አገልግለዋል። በአጠቃላይ ከቀዳማይ እና ከካልአይ የመረጃ ምንጮች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በምስል፣ በድምጽ፣ በፎቶግራፍ እና በማስታወሻዎች በመታገዝ ተሰብስበዋል።

### 1.7.2.1. ምልከታ

ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ቀዳሚው እና አስፈላጊ የሚባለው የመረጃ መሰብሰቢያ አይነት ነው፡፡ ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ያለውን አስተዋፅዖ Goldstein ሲገልፁ፡- "The term 'observation' as used in this context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing , feeling , smeling and testing ,whe never these may be appropriate.''(1964:77)፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፤ሁነቶች ምልከታ ላይ ብቻ የተገደበ አለመሆኑን እና በሁሉም የስሜት ህዋስ፤በመስማት፣ በመዳሰስ፣ በማሽተት እና በመቅመስ መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት በተሳትፏዊ እና ፅሞናዊ ምልከታ መረጃ መሰብሰብ እንደሚቻል (Blaxter,Hughes and Tight, 2006) ይጠቁማሉ፡፡ ይኸውም ተሳትፏዊ ምልከታ ተመራማሪው ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር እየተሳተፈ፣ አብሮ እየከወነ፤እየበላ፣ እየጠጣ፣ እየጨፈረ መረጃ የሚሰበስብበት ስልት ሲሆን ፅሞናዊ ምልከታ ደግሞ ዳር ቆሞ ምን ተከናወነ፣ ተካሄደ የሚለውን በፅሞና በመከታተል መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በዚህ ጥናት ከምልከታ አይነቶች ውስጥ ጽሞናዊ ምልከታ ተገልግያለሁ፡፡ ከባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ጋር ዕፆቹ ወዳሉበት ቦታ ሄጄ የዕፆቹን አይነትና ባህሪ በመመልከት መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ፈቃደኛ ባይሆኑልኝም በከፊል የመድሀኒቶቹን አዘገጃጀትና አቀማመም፤ለቆላ ቁስል፣ ለአይሬ በሽታ፣ ለቁስል (ለእከክ) እና ለላሽ የሚዘጋጁ መድሀኒቶችን አዘገጃጀትና አቀማመም ተመልክቻለሁ፡፡ በተጨማሪም የታካሚዎችን የህመም አይነት እና ደረጃ ለመለየት የሚያደርጉት ምርመራ፣ ታካሚዎቹ የሚያደርጉትን፣ የሚናገሩትን፣ አጠቃላይ ተግባር እና ሂደት እንዲሁም የሀገረሰባዊ መድሀኒት ባለሙያዎችን ሁኔታ ዳር ሆኜ በመመልከት መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

### 1.7.2.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ በመስክ የመረጃ ስብሰባ ወቅት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር በአካል በመገናኘት እንደ ምርምር ጥያቄው አይነት ነጻ እና ዝግ መጠይቆችን በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው፡፡ ፈቃደ አዘዘ ስለ ቃለ መጠይቅ የመረጃ አሰባሰብ ሲያስረዱ፡- በመስክ ጥናት ወቅት ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ለመጠቀም ከተወሰነ በዝግ እና በክፍት መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠቀም እንደሚቻል (1990፣101) ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ክፍት እና ዝግ የመረጃ መሰብሰቢያ አይነቶችን እንደ አስፈላጊነቱ በማፈራረቅ ተገልግያለሁ፡፡ በዚህ መሰረት ከአስራ ሁለት (12) የሀገረሰባዊ መድሀኒት ቀማሚዎች፣ ከአምስት (5) የሀገረሰባዊ መድሀኒት ተጠቃሚዎች እና ከሶስት (3) ዘመናዊ የጤና ባለሙያዎች መረጃ ሰብስቢያለሁ፡፡ ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች ውስጥ አስራ ሁለቱ (12) የባህል ህክምና ባለሙያዎች በቁልፍ መረጃ አቀባይነት የተመረጡት ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው እወቅና፣ ተቀባይነት፣ ከሚሰጡት አገልግሎት እና ለጥናቱ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ በመሆናቸው እንዲሁም መረጃ ለመስጠት ያላቸውን ፍቃደኝነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሀገረሰባዊ ህክምና እውቀት፣ ስለመድሀኒት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም፣ በመድሀኒት ስብሰባ፣ ቅመማ እና አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚከውኗቸው ክንዋኔዎች፣ ከልማድ እና ከእምነት አንጻር፣ መድሀኒቶቹን የሚቀምሙባቸው ቀናትና ሰዓታት፣ ባህላዊ ሀኪሞች ለዘመናዊ ሀኪሞች ያላቸውን አመለካከት፣ ዘመናዊ ሀኪሞች ለባህል ህክምና አና ለባለሙያዎቹ ያላቸውን አተያይ፣ ሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎች በታካሚዎች ዘንድ ያላቸውን ተመራጭነት እንዲሁም አጠቃላይ ስለባህል ህክምና እና የህክምና ባለሙያዎች መረጃ ለመሰብሰብ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

### 1.7.3. የመረጃ መተንተኛ ስልት

ጥናቱ አይነታዊ እንደመሆኑ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ከቁልፍ እና አጋዥ መረጃ አቀባዮች የተገኙ መረጃዎች በአይነት እና በይዘት ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ ያለው ሲያስረዱ"አይነታዊ የምርምር ሂደት ተፈጥሯዊ መልክ ያለው ነው፡፡ ይኸውም ምልከታ ማካሄድ ያዩትን መዘገብ የዘገቡትን በተገቢው መግለጽን ያካትታል"(2009፣20)፡፡ በመሆኑም ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን፤በገለጻ መልክ መቅረብ የሚገባቸውን

በገላጭ፤ትንታኔ የሚያሻቸውን፤ትዕምርቶችን፣ ሀሳቦች፣ ሁነቶች፤ተንታኝ ስልትን ተጠቅሞ ሰፋ ያለ ትንታኔ በመስጠት ጥናቱ ተካሂዷል። ለጥናቱ ማስኬጃ የሆኑ የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ፣ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ እና የጤና ሥነምህዳር (Medical Ecology) ንድፈ ሀሳብም ማስተንተኛ ሆነው አገልግለዋል ።

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

ጥናቱ ከተጀመረ ጀምሮ መረጃ ለመሰብሰብ መስክ እስከወጣሁበት ድረስ ባለው ጊዜ ከእኔ ጥናት ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ግንኙነት ያላቸው መጽሀፎች፣ መጽሔቶችና ጆርናሎች እንዲሁም የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና የሶስተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጹሑፎችን በማንበብ በቂ መረጃ ሰበሰብኩ። ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ለመስክ አስፈላጊ የሆኑ መቅረጸ ድምጽ፣ ካሴት፣ ፎቶ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተር አዘጋጀሁ። ቅድመ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ መረጃ ለመሰብሰብ የካቲት3/2012 ወደ መስክ ወጣሁ። ከሰባት ሰዓት (7:00) የመኪና ጉዞ በኋላ ለጥናት የተመረጠው አካባቢ ደረስኩ፤እረፍት አድርጌ፤አካባቢውን ቃኝቼ፤ወደ ማደሪያዬ ሄድኩ። በማግስቱ የካቲት4/2012 ወደ ከተማ አስተዳደሩ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አመራሁ። በከተማ አስተዳደሩ ጊቢ ውስጥ ላገኘኋቸው ሰዎች ወደ ቢሯቸው የመጣሁበትን ምክንያት ሳስረዳቸው የወረዳው የህዝብ ግንኙነት ሚዲያ ልማት ባለሙያውን አቶ ሽጋው ንጋቱን እንዳነጋግር ጠቆሙኝ። አቶ ሽጋው ንጋቱ ቢሮ ስገባ፤በፀሀፊያቸው በኩል ስብሰባ ላይ እንደሆኑ እና ከሁለት ቀን በኋላ መመለስ እንዳለብኝ ተነግሮኝ ተመለስኩ።

በሁሉቱ ቀናት በአካባቢው ካሉ የባህል መድሀኒተኞች ጋር ትውውቅ ለማድረግ በአካባቢው ያሉ ታዋቂ ሰዎችን ይዤ ወደ መስክ ወጣሁ። ለጥናት የተመረጠው አካባቢ የትውልድ ስፍራዬ በመሆኑ መረጃ አቀባዮችን እና በሁሉም ቀበሌዎች ያሉ የሀገር ሽማግሌዎች እና ታዋቂ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎችን ለማግኘት አልተቸገርኩም። ከሁለት ቀን በኋላ የካቲት6/2012 ወደ ከተማ አስተዳደሩ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ አቶ ሽጋው ንጋቱ ቢሮ አመራሁ። አቶ ሽጋውም አስፈላጊው ትብብር ሁሉ በማድረግ በእሳቸው በኩል ያለውን መረጃ ከሰጡኝ በኋላ ሌሎች ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እና ከሌሎች የስራ ባልደረቦቻቸው የሚያገኟቸውን መረጃዎች አሰባስበው እንደሚሰጡኝ ቃል ገቡልኝ፤በእለቱ የስራ ባልደረቦቻቸው የሌሉ በመሆናቸው በማግስቱ የካቲት7/2012 እንድመለስ ነገሩኝ። የካቲት7/2012 በድጋሜ በመሄድ ስለ ጥናት አካባቢው ዝርዝር መረጃ ሰጥተውኝ ተመለስኩ።

ዋናውን የጥናቴን ስራ የመጀመሪያውን ዙር ከየካቲት 10- 20/2012 ድረስ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ከአምስቱ ቀበሌዎች (ከጫሬ ቀበሌ፣ ከዙጢ ቀበሌ፣ ከማድያ፣ ከፓፓዬ ሰፈር እና ከዋንዛ ቀበሌ) ማህበረሰቡ፤ባህላዊ ህክምና ከሚያገኝባቸው ከስድስት (6) የሀገረሰብ መድሀኒት ቀማሚዎች ጋር በመገናኘት አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። ከመጀመሪያ ዙር መረጃ ስብሰባዬ በፊት በታዋቂ ሰዎች እና በቤተሰቦቼ በኩል ስለ ጥናቴ አላማ እና ግብ፤ሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎቹ እንዲያውቁ አድርጌ ስለነበር መረጃውን ለማግኘት የገጠመኝ ችግር አልነበረም። ይሁን እንጂ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ምስጢራዊ ከመሆናቸው የተነሳ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎቹ ስለሚያዘጋጇቸው መድሀኒቶች ሙሉ በሙሉ የማይናገሯቸው መረጃዎች ነበሩ። ሆኖም ይህን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት በትዕግስት እና ደጋግሜ በመጠየቅ እንዲሁም ከባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች ተጨማሪ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናቴን ምሉዕ ለማድረግ ጥረት አድርጌያለሁ።

በሁለተኛ ዙር የመረጃ ስብሰባዬ ቀሪዎቹን የባህል ሀኪሞች፤የሚያውቋቸውን ዘመዶቼን እና ባለሙያዎቹን የሚቀርቧቸውን ሰዎች በመያዝ ከየካቲት 22-30 ድረስ ባሉት ስምንት ቀናት ውስጥ ተጨማሪ ስድስት ሀገረሰባዊ መድሀኒት ቀማሚዎች ጋር በመሄድ በመጀመሪያ ዙር መረጃ ስብሰባ ወቅት የጎደሉኝን መረጃዎች እና ተጨማሪ ለጥናቴ ማጠናከሪያ የሚሆኑ አንዳንድ የበሽታ አይነቶች እና የመድሀኒት ቅመማ ሂደት፣ የባህል መድሀኒት ምስጢራዊነትን በተመለተ እና ዘመናዊ ሀኪሞች እና ባህላዊ ሂሞቹ ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ።

በሶስተኛ ዙር መረጃ ስብሰባዬ፤በጥናቱ አካባቢ በመቆየቴ የመኪና ጉዞ አልነበረብኝም። በመሆኑም ከመጋቢት 1-10 ድረስ ለአስር ቀናት ያህል በጥናቴ የታዩ የመረጃ ክፍተቶችን ለመሙላት፤መረጃዎችን በመሰብሰብ፤አጠናቅሬያለሁ። በዚሁ በመጋቢት ወር በሀገራችን በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት በሚፈለገው መልኩ ለመንቀሳቀስ እና መረጃ አቀባዬዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንብኝም ቀድሜ ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎቹን መሰብሰብ በመቻሌ የመረጃ ክፍተት እንዳይኖርብኝ አድርጓል።

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ጥናቱ ከመረጃ ሰጪዎች እምነት እና ልማድ አንጻር ውስንነት አጋጥመውታል። በተለይም ሀገረሰባዊ የህክምና እውቀት ምስጢራዊ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉ ሊጠና የሚችል አለመሆኑ

አንዳንድ መረጃ አቀባዮች መረጃውን ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆናቸው እና የተወሰኑ መረጃዎችን በመስጠት የተወሰኑትን ደግሞ የመደበቅ ችግር፣ ለጥናቱ በተፈለገው ልክ መረጃዎች እንዳይሟሉ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም መረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ ለመነሳት ፈቃደኛ አለመሆናቸው፤እንዳንድ ለፎቶ ግራፍ ፍቃደኛ የሆኑ የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች ቢኖሩም ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆችን የሚሰበስቡባቸው ቦታዎች ተራራማ እና ወደ ስፍራው ገብቶ ፎቶ ለማንሳት አስቸጋሪ መሆኑ፤በሀገራችን የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ፤የተለያዩ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘትና ጥናቱን ይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችሉ ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሁም ፎቶ ግራፎችን በበቂ ሁኔታ ለማሰባሰብ እንዳይቻል ማድረጉ፤ በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው፡፡

እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ከማህበረሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ መረጃ አቀባዮችን በትግስትና በሂደት በማግባባት፤አመኔታን ለመፍጠር በአካባቢው ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን በመያዝ እንዲሁም የጥናቱን አላማና ግብ በማስረዳት ችግሮቹን ለመቅረፍ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እያፈራረቁ በመጠቀም ማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ጎልማሶች እና እናቶች የጥናቱን አካባቢ ዳራ የተመለከቱ መረጃዎች በመሰብሰብ ችግሩን ለማቃለል ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም በፎቶ ግራፍ በኩል ደግሞ የመረጃ አቀባዮችን ፈቃደኝነት ታሳቢ በማድረግ፤ፎቶ ግራፍ ለመነሳት ፈቃደኛ የሆኑ የባህል መድሀኒት ቀማሚዎችን፤ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸውን ዕፅዋቶች፣ ባለሙያዎቹ ታካሚዎቹን ሲያክሙ እንዲሁም የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ለአጥኝዋ መረጃ ሲሰጡ የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## 1.10. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ በምዕራፍ አንድ፤መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፤ዋና አላማ እና ዝርዝር አላማዎች፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የናሙና አመራረጥ ስልት፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ቸግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች እንዲሁም የጥናቱ አደረጃጀት የሚሉት ተካተዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ሲሆን በዚህ ስር፤የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ እና ንደፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ ሶስት፤የሸዋሮቢት ከተማ አካባቢያዊ ዳራ በዚህ ስር፤መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ አካባቢያዊ ስያሜ፣ የህዝቡ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ መተዳደሪያ እና የባህል ገፅታ የሚሉት ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡

በምዕራፍ አራት የጥናቱ ትንተና የቀረበበት ክፍል ሲሆን በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በይዘት ከተደራጁ በኋላ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በመጨረሻው ምዕራፍም ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ ቀርበው፤ዋቢ ድርሳናት እና አባሪዎችም በጥናቱ መጨረሻ ተካተዋል፡፡

## 1.11. የጥናቱ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች

በጥናቱ ሂደት ከቀዳማይ እና ከካላዓይ የመረጃ ምንጮች መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ፣ መረጃዎቹ በሚተረጎሙበት እና በሚተነተኑበት ጊዜ ሥነምግባራዊ ደንቦችን በመከተል ነው፡፡

በመስክ መረጃ ስብሰባ ወቅት፤የጥናቱ ኣካባቢ ተወልጄ ያደኩበት በመሆኑ፤የባህል ሀኪሞቹን ለመተዋወቅ፣ ተንቀሳቅሼ መረጃ ለመሰብሰብ እና ጥናቴን በታቀደለት ጊዜና ሰዓት ለማጠናቀቅ ትልቅ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ለማግኘት፤ቀዳሚው ተግባር የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃደኝነት ማግኘት በመሆኑ፤መረጃ አቀባዮቹ ስለ ጥናቱ አላማ እና ግብ በሚገባ እዲገነዘቡ በማድረግና ለሚሰጡኝ መረጃዎች ታማኝ እንደሆንኩ በማስረዳት ከመረጃ ሰጪዎቹ ይሁንታን በማግኘት መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ መረጃ አቀባዮቹ የሰጡኝ መረጃዎች ምስጢራዊ በመሆናቸው መረጃዎቹን ለትምህርት አላማ ብቻ በማዋል የመረጃ አቀባዮች ምስጢር ተጠብቋል፡፡

በተጨማሪም በመረጃ ጥንቅር እና ትንተና ወቅት መረጃዎቹን በትክክል መገልበጥ እና ከተገኙት መረጃዎች በመነሳት ትንታኔ ለመስጠት አስፈላጊ በመሆኑ በተቻለ መጠን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ትንታኔ በመስጠት ረገድ ጥንቃቄ ተደርጓል ፡፡

በመጨረሻም ከጥናቱ ጅማሬ እስከ ፍጻሜ በመረጃ አቀባይነት የተሳተፉ አካላትን በሙሉ ማመስገን ተገቢ በመሆኑ መረጃ አቀባዮች እና በጥናቱ ሂደት በአንድም በሌላም መንገድ ድጋፍ ያደረጉ አካላት ተመስግነዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ከእኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳባዊ መረጃዎች፣ ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝቶች እና በተለያዩ ትምህርት ክፍሎች የተሰሩ ጥናታዊ ጹሑፎች ቀርበዋል፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የባህል ሕክምና ምንነት፣ የባህል ሕክምና ባለሙያዎች ማንነት እና ምድብ፣ በባህል ህክምና በሽታን የመለያና የምርመራ ዘዴ፤ባህል፣ ጤና እና ሥነ ምህዳር፤ ሀይማኖት፣ እምነት እና ሀገረ ሰባዊ መድሀኒት፤የሀገረሰባዊ መድሀኒት አሰባሰብ፣ አቀማመም እና አሰጣጥ እንዲሁም የሀገረሰባዊ መድሀኒት ህክምና እውቀት ተስተላልፎ የሚሉት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. የባህል ህክምና ምንነት

የባህል መድኃኒት ከዘመናዊው የህክምና ዘመን በፊት በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ሀገር በቀል እውቀት ሲሆን ጤናን በመጠበቅ ረገድ እምቅ ባህሎችን፣ እምነቶች እና ልማዶችን በመጠቀም በሽታን መከላከል፣ በሽታን መፈተን፣ የአካል ወይም የአእምሮ ህመምን መንከባከብ፣ ጤንነትን ወደነበረበረበት መመለስ የሚያስችል ሀገር በቀል እውቀት ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች ለሚከሰቱ በሽታዎች ከፎክ ቡድኑ ውስጥ የባህል ህክምና አዋቂ፤የተሻለ የመፈወስ ችሎታ ያለው አካል የማህበረሰቡን ጤንነት ወደነበረበት ለመመለስ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን አዘጋጅቶ ፈውስ እንደሚሰጥ (Helman,1984) ከዚህ በታች በቀረበው ጥቅሳቸው ያስረዳሉ፡፡

> Folk medicine thus tends to be conceptualized within a hierarchical model of knowledge and sophistication of thought, in which it is typically located in a sort of lower midsection between official,scientific medicine at the hierarchical pinnacle and “primitive ”medicine on the bottom stratum (Helman,1984,P.101).

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ባህላዊ መድሀኒት፤ጤናን የመመርመር፣ የመፈተሽ፣ መንከባከብ ሂደት ሲሆን የሰውን፣ የእንስሳትንና የዕፅዋትን ጤና ለመጠበቅ የሚያስችል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ እውቀት መሆኑን ቀጥሎ የቀረበው ጥቅስ ያስረዳል፡፡

> Thai traditional medicine is defined as "the medical processes dealing with the examination, diagnosis, therapy, treatment, or prevention of diseases, or promotion and rehabilitation of the health of humans or animals, midwifery Thai massage, as well as the preparation, production of Thai traditional medicines and the making of devices and instruments for medical purposes. All of these are based on the knowledge or textbooks that were passed on and developed from generation to generation (Chuthaputt, and Chokevivat,2005,P.1).

ባህላዊ መድኃኒት ትልቅ ስፍራ የነበረው አሁንም እየተሰራበት ያለ ሀገር በቀል እውቀት ሲሆን የዘመናዊ ህክምና አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፤እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አቅምን ያገናዘበ አለመሆኑ ማህበረሰቡ ትኩረቱን ባህላዊ መድኃኒት ላይ እንዲያደርግ ሆኗል፡፡ አሰፋ ባልቻ "የኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ-ዓመት ጉዞ" በሚለው መጽሐፋቸውም በባህል ህክምና ዘርፍ በፅሁፍ የሰፈሩ ጥንቅሮችን፣ ቁጥርና ፊደላት ማስላት፣ መናፍስት፣ ዕፅዋትን፣ ማዕድናትን እንዲሁም በእንስሳት ተዋፅዖ ፈውስን ማግኘት ኢትዮጵያውያን ምን ያህል ልቀውበት እንደነበር ይጠቁማሉ፡፡

እንደ Steiner ገለጻ ባህላዊ ህክምና ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ ማዕድናትን በግብዓትነት በመጠቀም እንዲሁም መንፈሳዊ ህክምናዎችን፣ አቅምን የሚፈትኑ ቴክኒኮችን እና ልምዶችን፣ አቀራረቦችን፣ ዕውቀቶችን እና እምነቶችን በቡድን አልያም በግል በመከወን ህመምን መመርመር፣ ማከም አና ጤናን መጠበቅ ወይም ደህንነትን ማስቀጠል መሆኑን (1986,P.68) ያሥረዳሉ፡፡

በመሆኑም የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና የተለየ ጥበብን የሚፈልግ፤በተፈጥሮና በሳይንስ መካከል ያለውን ሚዛናዊነት የማስጠበቅ ባህሪ ያለው ሲሆን ለታማሚው ፈውስ ለመስጠት፤ የታማሚውን አካላዊ፣ አዕምሯዊና መንፈሳዊ ሁኔታ በጥልቀት ማጤን ይጠበቃል፡፡ ይህም የተለየ ጥበብንና ተሰጥኦን የሚጠይቅና ለተመረጡ ሰዎች ብቻ የሚሰጥ ፀጋ ተደርጎ እንዲታሰብ አድርጎታል (ሻሂዳ፣2017፣ገፅ1) በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል የዓለም ጤና ድርጅት (WHO,2002, P.9-11) በዕውቀትና በእምነት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ዕፅዋት፣ እንስሳት፣ ማዕድናትና የመሳሰሉትን በተወሰነ የቅመማ ሂደት አዘጋጅቶ በሽታን ለማከም፣ ለመከላከልና ጤናን ለመጠበቅ የሚደረግ ክንውን በማለት ይገልጸዋል፡፡ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ (በፀበል፣በጸሎት፣በዱዓ እና በእምነት) የሚካሄድ የሕክምና አገልግሎትን፤ከባህላዊ የህክምና ዘዴ ይመድበዋል፡፡

በአጠቃላይ የሀገረሰባዊ መድኃኒት ሙያ፤የዕውቀትና ተግባር ድምር ውጤት የሆነ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማኅበራዊ ጠንቆችንና ተውሳኮችን ለመከላከልና ለማስወገድ እንዲሁም ለመመርመር የሚተገበር ጥበብ ሲሆን እውቀቱ ባላቸው ባለሙያዎች ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት በሚገኙ ግብዓቶች በሽታን ማከም፣ ጤናን መንከባከብ እና ደህንነትን ማስቀጠል የሚያስችል፤ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ ለዘመናት ሲተገበር የቆየ፣ ከሰው ልጅ ንቃተ ህሊና፣ አስተሳሰብና ፍልስፍና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የዘመናት ጥበብ፣ ልምድ፣ ተሞክሮና ዕውቀት ውጤት ነው፡፡

### 2.1.2. የባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎች ማንነት

በኢትዮጵያ ውስጥ የባህል ሀኪሞች በተለያዩ እምነቶች ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ በክርስትናው (በኦርቶዶክስ)፤መጸሐፍ ገላጭ፣ ባለዛሮች፣ ጠንቋዮች፣ ወጌሻዎች ያሉ ሲሆን በእስልምና እምነት ውስጥ ደግሞ (ከቢር፣ሼኮች፣ቃልቻ፣አረጋሳዎች) በዋናነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን (Franklin,2011) ይገልጻሉ፡፡

ከእነዚህ የእምነት ስርዓቶች ውስጥ የወጡ የባህል ህክምና ባለሙያዎች፤በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ አውቅና ያላቸው ሲሆኑ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት በሚገኙ ግብዓቶች በተለያየ ሙያ ውስጥ ያለን (ነርስ፣ የፊዚክስ ባለሙያ፣ የጥርስ ህክምና ባለሙያ፣ መድሀኒት ሸያጭ፣ አዋላጅ ነርስ፣ የአጥንት ህክምና ባለሙያ፣ የወሊድ ቁጥጥር አገልግሎት፣ የጥርስ ሀኪም፣ የዕፅ አዋቂ እና መንፈሳዊ አገልጋዮች) እንዲሁም ሌሎች የማህበረሰቡ ክፍሎችን ጨምሮ የሚያገለግሉ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ በአብዛኛው ማህበረሰብ ውስጥ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው፤ለማህበረሰቡ ደህንነት ዋስትናዎች እና የመጀመሪያ ምርጫዎችም ናቸው (Mekonen,2019,P.82) በማለት ይገልጿቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ የሀገረሰብ መድሀኒት የህክምና አይነቶች አራት መሆናቸውን (Desta, 2004, PP.67-68) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም፡- የዕፅ መድሀኒት ህክምና (Herbal Medication)

ከዕፅዋት በሚገኙ፤ከዕፅዋት ቀንበጥ፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ ግንድ፣ ስር፣ አበባ እና ፈሳሽ በመጠቀም የህክምና አገልግሎት መስጠት የመጀመሪያው ሲሆን ባለሙያዎቹም የዕፅ መድሀኒት ቀማሚዎች እንደሚባሉ አስረድተዋል፡፡

ሁለተኛው፡- ከማዕድናት (Mineral Medication) በሚገኙ ግብዓቶች መድሀኒቶችን በማዘጋጀት ለሰውም ሆነ ለእንስሳት እንዲሁም ለዕፅዋት መድሀኒት የሚሰጡ ናቸው፡፡

ሶስተኛው፡- መንፈሳዊ እና ስነልቦናዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት (Medication of Psychosocial condtion) የሚከወኑ ሲሆን መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ህመምተኞችን በጸበል፣ በጸሎት እና በምልጃ፤ዛር፣ አጋንትን፣ እርኩስ መንፈስ እና ሌሎች የሰውን ጤና የሚያውኩ የጤና ጠንቆችን፤እምነትን መሰረት በማድረግ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ቄሶች፣ ሼኮች፣ ቃልቻዎች እና መጸሐፍ ገላጮችን የሚያካትት ነው፡፡

አራተኛው፡- ቴክኒካዊ እውቀትን እና ብልሀትን በመጠቀም የሚሰጠው የህክምና አይነት (Medical Practice) ሲሆን በአብዛኛው የተሰበሩ፣ የወለቁ እና ሌሎች የአካል ጉዳት ችግሮች ያጋጠሟቸውን ሰዎች የሚያክሙ ናቸው፡፡ በዚህ ህክምና ውስጥ ወጌሾች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከዚህ በፊት ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የሀገረሰባዊ መድሀኒት ባለሙያዎች በሽታን ለመለየት፣ ለመመርመር እንዲሁም ለማከም አካባቢያዊ ግንዛቤን፣ ልማድን፣ ሀይማኖትን፣ እምነትን እና ሀገር በቀል አውቀትን እንዲሁም ሥነ ምህዳራዊ ገፅታን መሰረት በማድረግ ህሙማንን እንደሚፈውሱ ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ አካባቢ ለሚከሰት በሽታ በሥነ ምህዳሩ የሚገኙ ግብዓቶች የዕፅዋት፣ የእንስሳት እና የማዕድናት ውጤቶች ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያላቸው ሲሆን ከእነዚህ ግብዓቶች የተገኙ መድሀኒቶች ይበልጥ ፈዋሽነታቸውን አስተማማኝ ለማድረግ እምነት እና ሀይማኖት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚወስዱ የቀረቡት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት፤ደስታ ካቀረቧቸው የሀገረሰባዊ መድሀኒት የህክምና አይነቶች ውስጥ የዕፅ መድሀኒት ህክምና (Herbal Medication) ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በአብዛኛው ከዕፅዋት ቀንበጥ፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ ግንድ፣ ስር፣ አበባ እና ፈሳሽ የሚገኙ የዕፅ ውጤቶችን እና ግላዊ እውቀት፣ ልምድና ችሎታ በማስተባበር፤መድሀኒት ቀምመው የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች በመሆናቸው

ከላይ ከቀረቡት የህክምና አይነቶች የዕፅ መድሀኒት ህክምና አይነት፤ይህንኑ ሀሳብ የሚያንጸባርቅ በመሆኑ፤በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ እነዚህ ሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎችም፤የዕፅ መድሀኒት ቀማሚዎች ተብለው ይጠራሉ፡፡

### 2.1.3. በባህል ሕክምና በሽታን የመለያ እና የምርመራ ዘዴዎች

በባህል ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴ እንደ ባለሙያዎቹ እውቀት፣ እንደ ማህበረሰቡ ባህል፣ ልማድ እና ስርዓት መሰረት በአይነታቸው፣ በይዘታቸው እና በተግባራቸው የተለያዩ መሆናቸውን (Sofowora,1982) ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያው እይታዊ የምርመራ ዘዴ (visual examination) ሲሆን የታካሚውን የሰውነት ክፍሎች በማየት በሽታን መለየት፤ሁለተኛው፤ ክሊኒካዊ የመለያ ዘዴ (clinical examination)፤የታካሚውን አጠቃላይ ተክለ ሰውነት በመፈተሽ (ስብራትን፣ ትኩሳትን፣ የእጅ ወይም የእግር አጥንት መመርመር፣ የሰውነት ክብደት ለውጥን) ማረጋገጥን ይመለከታል፡፡ ሶስተኛው፤ባዮሎጂካዊ የመለያ ዘዴ (Biological examinations)፤ታካሚዎችን በማስቀመስ፣ በማስሸተትና በመነካካት በሽታን የሚለዩበት መንገድ ሲሆን፤አራተኛው የህሙማንን ማህበራዊ ህይወት (የታካሚውን ዳራ)፤አኗኗር እና አጠቃላይ የታካሚውን ሁኔታ በማጤን በሽታ እንደሚለዩና እንደሚመረምሩ (Sofowora,1982,P.29-30) አስረድተዋል፡፡

### 2.1.4. ባህል፣ ጤና እና ሥነ ምህዳር

#### 2.1.4.1. ባህል

ባህል የሰው ልጅ ማንነት ውስጥ የአንድ ህብረተሰብ አኗኗር ስርዓት ሲሆን ቋንቋን፣ ሥነ ጥበብን፣ ሥነ ጹሑፍን፣ ሙዚቃን፣ ጭፈራን፣ ሀይማኖትን፣ ቴክኖሎጂን፣ አስተሳሰብን፣ አለባበስን፣ ስነ ህንጻን፣ ሕግን፣ አስተያየትን፣ ፍልስፍናን፣ አፈታሪክን እና እውቀትን ያጠቃልላል፡፡ ባህል የሚታየውን እና የማይታየውን (ውጫዊ እና ውሳጣዊ) የሰው ልጅ በንቁው እና ኢ-ንቁ የአዕምሮ ክፍሉ የሚያስበውን፣ የሚቀበለውን እና የሚያምንበትን፣ ማንነትን፣ ግላዊ እና የማህበራዊ ቡድን ህይወትን የሚመራ፣ ስለአለም እና ስለሌሎች አካላት እንዲሁም ስለመለኮታዊ ሀይል፣ ስለ ተፈጥሮና አካባቢን የሚመለከት የማህበረሰብ ህግ እና ደንብ ሲሆን ይህም በቃል፣ በምልክት፣ ጥበብ እና በከበራ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚሸጋገር (Helman,1984) አስረድተዋል፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ጥቅስም ይህንኑ ያጠነክራል፡፡

> culture is a set of guidelines (both explicit and implicit) which an individual inherits as a member of a particular society, and which tells him how to view the world, and how tobehave in it in relation to other people, to supernatural forces or gods, and to the natural environment. It also provides him with a way of transmitting these guidelines to the next generation by the use of symbols, language, art and rituall (Helman,P.32).

በመሆኑም ባህል፤የአንድ ቡድን የህይወት መልክና መመሪያ ሲሆን የማህበረሰቡን ውስጣዊ እና ውጫዊ ሀሳብ፣ ንግግር፣ አቋም፣ ስሜት፣ አተያይ፣ (ከሰው፣ ከፈጣሪና ከተፈጥሮ) ጋር ያለን ግንኙነት ያጠቃልላል። ይህ የማህበረሰብ ማንነት፤በምልክት፣ በቋንቋ፣ በድርጊት (በክንውን)፣ በጥበብ እና በከበራ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚሸጋገር Helman ከዚህ በፊት በቀረበው ጥቅሳቸው ጠቁመዋል።

### 2.1.4.2. ጤና

ጤና ከጥሩ ወይም ከመጥፎ ስሜት፤ከውጫዊ ገጽታ ያለፈ፤አካላዊ፣ መንፈሳዊ እና ሥነ ልቦናዊ የህይወት ደህንነት ነው። ይሁኔ (2010፣ገፅ፣5-29) ጤና ማለት "የበሽታ አለመኖር ሳይሆን የተሟላ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ ደህንነት ነው" በሚል የዓለም ጤና ድርጅት ያቀረበውን ብያኔ በመተቸት፤ጤና፤ውስብስብ፣ ሰፊና ፈርጀ ብዙ መገለጫዎች እንዳሉት ያስረዳሉ። ይኸውም ሰው፤የአዕምሮ፣ የአካል፣ የስሜት፣ የአካባቢና የማኅበራዊ ውስብስብ መስተጋብሮች ያለው፤ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች፤በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግለሰቡ ጤንነት እና ደህንነት ጋር እንደሚያያዙ (Winkelman, 2009) ይገልጻሉ።

### 2.1.4.3. ሥነ ምህዳር

ሥነምህዳር ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው ፍጡራን ሁሉ ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር የሚያጠና ሲሆን አብዛኞቹ የሥነ ምህዳር ጥናት ባለሙያ፤ህይወት ያላቸውን እና የሌላቸውን፤እንስሳትን፣ እጽዋትን፣ ውሀማ ቦታዎችን፣ ደኖችን፣ ሀይቅ (አሳ አጥማጆችን) እና አጠቃላይ የተፈጥሮ ስርዓትን ያጠናሉ። በአጠቃላይ የሥነ ምህዳር ጥናት ተፈጥሮ እንዴት ተሰራች? የሚለውን መመርመር ነው። ቀጥሎ የቀረበው ጥቅስ ይህንኑ የሚያስረዳ ነው።

> Ecology is defined as the study of the interactions between organisms and their environment,including both the living (biological) and non-living (physical) components. Most ecologists study wildlife, wetlands, forests, fisheries, or parts of these and other natural systems. The concepts and principles that make up the ecological sciences deal with how nature works (Bruce and Holly,2012,P.1).

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሥነ ምህዳር፤አካባቢን፣ ሰዎችን፣ የአየር ንብረትን፣ መሬትን፣ መልከ ዓምድርን፣ ውሃን እና የአካባቢን ማህበራዊ ውህደት በመመርመር ያላቸውን ትስስር የሚፈትሽ ነው፡፡ ጤናማ ሥነ ምህዳር እንዳይኖር፤የሰው ልጅ የጤና ችግሮች፤በተፈጥሮ ሥነ ምህዳራዊ ገፅታዎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሥነ ምህዳር መፈራረስ በሰዎች ላይ በሽታ አምጪ ተህዋስያን እንዲጨምሩ፣ መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ የምርታማነት መቀነስ፣ የምግብ አቅርቦት መቀነስ እና የንጹህ ውሃ እጥረት እንዲሁም የአየር ብክለት እንዲኖር፤ አጠቃላይ የተፈጥሮ ስርዓት እንዲዛባ በማድረግ፤የሰው ልጅ ጤና ተጋላጭነት እንዲጨምር ያደርጋል ፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ David (2010) አካባቢያዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ለጤና ቀውስ ምክንያት መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሰውን የጤና ችግሮች ለመፍታት ከስነ ምህዳራዊ እውነታው እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሆኑ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ለውጦች አንጻር መመርመር፤ስነ ምህዳራዊ ስርዓትን እና ማህበራዊ አውድን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ መሆኑን (David,2010,P.205-213) ይመክራሉ፡፡

በተጨማሪም በሥነ ምህዳራዊ ስርዓቶች ወይም በነባራዊው የአለም ሥርዓቶች ውስጥ ያሉ የሰው ልጆች ተግባራት ደህንነትን ያስቀጥላሉ፤አልያም የጤና መታወክ መንስኤ ይሆናሉ፡ ፡“ለጤና መሠረታዊ ሁኔታዎች፤ሰላም፣ መጠለያ፣ ትምህርት፣ ምግብ፣ ገቢ፣ የተረጋጋ ሥነ ምህዳራዊ፣ ዘላቂ ሀብቶች፣ ማህበራዊ ፍትህና ፍትሃዊነት” መሆናቸውን (WHO፣2007) (Hssell *et al*፣1992; Rapport,1995) ን ጠቅሰው ያስረዳሉ፡፡

ይህንኑ በተመለከተ Bruce and Holly (2012) ሥነ ምህዳር፤የተፈጥሮ ስርዓትን፤ዕፅዋትና እንስሳት አጠቃላይ ተግባርና ስርዓት የሚያጠና ሳይንስ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከCharles Darwin's”The Origin of Species” በ1859 ከወጣው እትም በኋላ በሥነ ምህዳር

ጥናት አዲስ የአጠናን አቅጣጫ የተፈጠረ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ይኸውም የሥነ ምህዳር ጥናት፤ተለዋዋጭ የተፈጥሮ ስርዓትን የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን፣ የተፈጠሩና ያሉ የተፈጥሮ ገጽታዎች ስርዓት እና ተግባር ላይ ብቻ ሳይገደብ በጊዜ ሂደት ተፈጥሮ በሚለውጣቸው ህይወት ያላቸው እና ህይወት የሌላቸው፤በማህበረሰብ ወስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑና እና ማህበራዊ ገፅታን የሚቀይሩ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን መመርመር ላይ ትኩረት ያደረገ አተያይ ብቅ ማለቱን ጠቁመዋል፡፡

ጤና አስፈላጊ እና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ተፈጥሮ በሰዎች ላይ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ ይልቅ፤ ሰዎች፤በአካባቢያቸው ላይ የሚደርሱት ጥፋት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የስነ ምህዳር ጤናማ መሆን በሰዎች ላይ ለሚከሰቱ በሽታዎች ፈውስ መሆን የሚችሉ ግብዓቶችን በማስጠበቅ ረገድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰው እና ሥነ ምህዳር የተቆራኙ ጉዳዮች በመሆናቸው አንዱ ለአንዱ የችግር መንስኤም፤መፍትሔም ሆነው ይገኛል፡፡ የሥነ ምህዳር ጤናማነት፤ለሰው ልጅ ጤና መሆን ዋስትና ነው፤በሌላ በኩል የሰው ልጅ ጤና፤ለሥነ ምህዳር እንክብካቤ ወሳኝ ነው፡፡

በአጠቃላይ የሥነ ምህዳር ጥናት በምድር ላይ ያሉ ህይወት ያላቸውና የሌላቸው ፍጥረታትን፤ ሰው፣ እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ማዕድናትን፣ ወንዞችን፣ ተራራዎችን፣ አየርን፣ አፈርን እና አጠቃላይ የተፈጥሮ ስርዓት፤ያላቸውን ተግባር፣ ተፅዕኗቸውን፣ የእርስ በርስ ትስስራቸውን፤ የሚያጠና፤የሚመረምር፤የሚፈትሽ ሳይንስ ነው፡፡

### 2.1.5. ሀይማኖት፣ እምነት እና ሀገረሰባዊ መድሀኒት

ሃይማኖት በተለየ ሁናቴ የአምልኮ ወይም የእምነት መርሆ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ የሥነ ምግባርና የመንፈሳዊ ፍልስፍና ደንቦችን በውስጡ የሚያጠቃልል፤ሕዝብ የሚመራበት የግብረ ገብ፣ የመመሪያዎች፣ የእምነት፣ የደንቦችና የመንፈሳዊ ሥርዓቶች ስብስብ ነው፡፡ ሀይማኖት እና እምነት ማህበረሰባዊ መዋቅርን፣ ህግን እንዲሁም መድሀኒትን ጨምሮ ቅርፅ የሚያሲዝ፤ የሚመራ መሆኑን Franklin”Religion and beliefs consistently shape social structures, laws, and even medicine” (2011,P.2) በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ ታሪኩ (2017) ገለጻ በዓለም ውስጥ በርካታ ሃይማኖቶች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በብዛት ተስፋፍተው የሚገኙት፤ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱሂዚም እና ቡድሂዝም የተባሉት ሀይማኖቶች ናቸው፡፡ በሀይማኖት ውስጥ ላሉ አማኞች፤እምነት ጠንካራ መሳሪያቸው ነው፡፡ እምነት በአንድ በሆነ ነገር ላይ ያለን ሙሉ አመኔታ እና መተማመን ሲሆን በሃይማኖት

ውስጥ እምነት፤የሃይማኖትን አስተምህሮ ከመረጃ ይልቅ፤በመንፈሳዊ የአዕምሮ ጽናት መቀበል የሚያስችል ጠንካራ አመኔታ ነው። እምነት ያላልታየን እና ያልተዳሰሰን እውነት እና ሐሳብ በልብ አመኔታ የምንቀበልበት ኃይል ነው (ታሪኩ፣2017፣ገፅ፣17) በማለት ይገልጻሉ።

> A belief is an observation and a personal claim of how one thinks the world works, based on memories, experience and hearsay. Such observations may allow a person to make predictions that events will repeat, or deductions of other phenomena. Religion is the set of beliefs that include the idea that one can control future events by adopting a specific set of beliefs (usually unjustified and unfalsifiable), and acting on them even though there is no evidence your actions are having the desired effect, OR even that the desired effect could ever be achieved (Rob,2019,P.2) .

ከቀረበው ምንጭ መረዳት እንደሚቻለው እምነት ግላዊ አተያይ ወይም አመለካከት ሲሆን ስለአንድ ጉዳይ፣ ሁነት ወይም ክንውን ከግላዊ ልምድ፣ እውቀት እና ስሞታ (ከሌሎች ሰዎች ከተሰማ) ሀሳብ በመነሳት፤አለም ምን ትላለች? እንዴት ትቀበለዋለች? ታምንበታለች፤ የሚለውን ከግላዊ እምነት ጋር በማስተሳሰር የሚገለጽበት መንገድ ነው። ይኸውም በተደጋጋሚ ከታየ፣ ከተከሰተና ካጋጠመ ሁነት ጋር በማስተሳሰር፤ስለ ጉዳዩ የሚኖረን አመኔታ ነው። በሌላ በኩል ሀይማኖት፤የእምነት ስብስብ ሲሆን የማይመረመር፣ ሊረጋገጥ የማይችል (ማስረጃ የሌለው) የዚህን አለም የሰው ልጅ አኗኗር ስርዓት ለማስተካከል፣ ለማረም እና ለማቃናት፤ ተግባርን ከተስፋ ጋር በማጣመር፤መንፈሳዊ ስርዓትን፣ መመሪያን እና ትዕዛዝን የምንቀበልበት ተቋም ነው።

ስለሆነም ሀይማኖት፤የሰውን ማንነት የሚቀርጽ፣ የእለት ተዕለት ተግባራትን፣ እንቅስቃሴን፣ ድርጊትን፣ ክንውን፣ ስርዓትን፣ ደንብን፣ አመለካከትን እና አጠቃላይ የአኗኗር ስርዓትን የሚቆጣጠር በመሆኑ በማንኛውም ሀይማኖት ውስጥ ያለ አማኝ ተግባሩን ከሀይማኖቱ ጋር በማያያዝ ይተገብራል። በዚህ የአኗኗር ስርዓት ውስጥ መሰረታዊ ከሚባሉት ጉዳዮች አንዱ ጤና ነው። የሰው ልጅ ጤና በተለያዩ ምክንያቶች ይታወካል፤ጤናን ወደነበረበት ለመመለስ ደግሞ መድሀኒት ማግኘት አስፈላጊ ነው። መድሀኒት ፈውስ መሆን እንዲችል እምነት ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛል። ታማሚው፤መድሀኒቱን ከእምነቱ በማያያዝ በመድሀኒቱ ላይ የፈጣሪ ሀይል ተጨምሮበት እድናለሁ፤በሚል እምነት መድሀኒቱን ይወስዳል።

በመሆኑም ሀይማኖት እና መድሀኒት አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተቆራኙ፤ይልቁንም የሚጋሩት የጋራ ተግባር ያላቸው ናቸው። መድሀኒት፤ ሀይማኖት በመድሀኒት ውስጥ ቅርጽ እንዲይዝ ያደርጋል፤ሀይማኖትም፤በመድሀኒቱ ላይ የመፈውስ ሀይሉ እንዲጨምር የራሱን አስተዋጾ ያበረክታል። Franklin ሀይማኖት እና መደሀኒት አምስት የጋራ የሚያደርጓቸው ተግባር እና መገለጫዎች መኖራቸውን (2011,P.11-13) ይገልጻሉ። እነዚህም፡- ሁለቱም ማመንን ወይም መቀበልን የሚጠይቁ ናቸው፤ትዕዛዝ የሚተላለፍባቸው ናቸው፤የተቋቋሙ እና የተደራጁ ናቸው፤ስቃይን መቀነሻ፤ ህመምን ወይም ስሜትን ማለስለሻ ናቸው፣ የሚያስተዳድራቸው አካል ያላቸው እና የሚቀበላቸው፣ የሚያምንባቸው፤ተከታይ ያላቸው ናቸው በማለት ይገልጧቸዋል።

ይህንኑ አስመልክቶ በምድራችን ላይ መድሀኒት የሚሆኑ ዕፆች ስለመኖራቸው በክርስትና እምነትም ሆነ በእስልምና እምነት ውስጥ (በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርዓን) ላይ ሰፍሯል፡

“ከዚያም ከፍሬዎች ሁሉ ብይ የጌታሽንም መንገዶች (ላንቺ) የተገሩ ሲኾኑ ግቢ ከሆዶችዋ መልኮቹ የተለያዩ መጠጥ ይወጣል በርሱ ውስጥ ለሰዎች መድሀኒት አለበት በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች በእርግጥ ታምር አለበት” ቁራዓን (ምዕ16.ቁ፡69)።

በክርስትና እምነት (በመጽሐፍ ቅዱስ) ውስጥም እንዲህ ቀርቧል። ”በወንዙም፡ አጠገብ፡ በዳሩ ፡ ላይ፡ በዚህና፡ በዚያ፡ ፍሬው፡ የሚበላ፡ ዛፍ፡ ኹሉ፡ ይበቅላል፡ ቅጠሉም፡ አይረግፍም፡ ፍሬውም፡ አይጎድልም፡ ውሃውም፡ ከመቅደስ፡ ይወጣልና፡ በየወሩ፡ ኹሉ፡ የፍሬ፡ በኩር፡ ያገኛል፤ ፍሬውም፡ ለመብል፡ ቅጠሉም ለመድኀኒት፡ ይሆናል”(ሕዝቅኤል 47.ቁ፡12)።

የሀይማኖት ተቋማት በሚመሩባቸው (በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርዓን) አስተምህሮ፤ በምድር ላይ ለሰው ልጆች መድሀኒት ሆነው የተፈጠሩ ዕፆች፣ ለድህነት (ለፈውስ) የተፈጠሩና በፈጣሪ ዘንድ የተባረኩ መሆናቸውን በማስተዋል፤የሰው ልጅ፤እነዚህን ዕፆች መድሀኒት መሆናቸውን አምኖ፣ ተቀብሎና አክብሮ ከበሽታው ሊድን፣ ፈውስ ሊያገኝባቸው እንደሚገባ ተመልክቷል።

በአጠቃላይ በሃይማኖትና በሕክምና መካከል ያለው ግንኙነት እምነት ነው። እምነት በአንድ ጉዳይ፣ አጋጣሚ ወይም ክስተት ላይ ያለን አመኔታ ሲሆን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ እንደሚከተለው ሀይማኖት ስርዓት እና እንደሚቀበለው እምነት በመድሀኒት ላይ፤አንድ የማይታይ፤የማይዳሰስ አካል፤ሀይል ተጨምሮ እድናለሁ፤እፈወሳለሁ የሚል አመለካከት አለው፡

፡ይኸውም መድሀኒቱ ከመደረጉ በፊት፤ፀሎት ማድረግ፣ ልመና ማቅረብ፣ በመድሀኒቱ ላይ አንድ ሀይል እንዳለ በሙሉ ልብ ማመን እና መድሀኒቱን መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ስለሆነም መድሀኒት፣ ሀይማኖት እንዲሁም እምነት እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ሳይሆኑ በመካከላቸው ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው እሳቤዎች ናቸው፡፡ በባህል ህክምናው ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሙያዎችም፤የእውቀት ምንጫቸው ግለሰብ ቢሆንም የሚያድነው፤የሚፈውሰው ፈጣሪ እንደሆነ በልበ ሙሉነት በመቀበል፤መድሀኒቱን ከመቁረጣቸው በፊት፣ ሲቆርጡ፣ ሲቀምሙ እና ለታማሚዎች ሲሰጡ እንደ እምነት ስርዓታቸው፤በሚያምኑበት እምነት ፀሎት፣ ዱዓ፣ ልመና አድርገው አገልግሎቱን እንደሚሰጡ (Franklin,2011,P,45) ይገልጻሉ፡፡

### 2.1.6. የባህል መድኃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማ እና አሰጣጥ

በባህላዊ ህክምና ሂደት መድሃኒት መሰብሰብ፣ መቀመም እና መስጠት ዋና ተግባር ነው፡፡ እንደ (Sofowora,1982; Alemayehu,1984) ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ባለሞያዎች ዕፅዋቱን በአካባቢያቸው በማልማት ወይም ዕፅዋቱን ከአካባቢ በመፈለግ ይሰበስባሉ፡፡ በሌላ በኩል (Young,1970; Alemayehu,1984) እንደሚያስረዱት፤አንድ ባህላዊ ሃኪም፤ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ግብዓቶችን ለመቀመምና ለመስጠት፤ዕፅዋቱ የሚበቅሉበትን ቦታ፣ ስያሜ፣ የመሰብሰቢያ ጊዜና ወቅትን ማወቅ፤የመድሃኒት የመሰብሰቢያ ቁሳቁሶችን መለየት፤ዕፅዋት ስለሚሰበሰቡበት ሁኔታና አሰጣጥ የተሻለ ግንዛቤ ሊኖረው እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ አያይዘውም ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አሰጣጥን በተመለከተ ባህላዊ መድሃኒቶች ከተለያየ ቦታ ተሰብስበው ከተቀመሙ በኋላ፤በአፍንጫ እንዲሸተቱ፣ በአፍ እንዲማጉ፣ በሽታው በታየበት የአካል ክፍል ላይ እንዲቀቡ፣ በአንገት ወይም በክንድ አልያም በግንባር ላይ እንዲንጠለጠሉ ሆነው ተዘጋጅተው ለታካሚዎች እንደሚሰጡ ያስረዳሉ፡፡

ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለመለየት፣ ለመሰብሰብ፣ ለማዘጋጀትና ለመቀመም የሥነ ምህዳር እውቀትና ተሰጥኦ አስፈላጊ ከሆኑም ባሻገር የዕፅዋትን ባህርይ፣ መገኛ ቦታ፣ መጠሪያ ስያሜ፣ የሚሰበሰቡበትን ጊዜና ወቅት፣ የዓየር ንብረት ጠንቅቆ ማወቅን እንደሚጠይቅ (Alemayehu,1984) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባህል መድሃኒቶች ለተፈለገው ዓይነት ፈውስ ዝግጅት ሲሰበሰቡ የተለያየ ተምሳሌታዊነት ያላቸው የመድሃኒት ዕፅዋት መቆፈሪያ፣ መቁረጫና ማዘጋጃ የሚያገለግሉ ቁሶች፣ የመድኃኒት ሰብሳቢው ብቃት፣ ዕፅዋት የሚሰብሰቡበት ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንደሚገባ (Young,1970,P.45-46) ይጠቁማሉ ፡፡

በአጠቃላይ የባህል ሀኪሞች ለባህላዊ መድሃኒት ቅመማ የሚውሉ ዕፅዋት፣ የማዕድናት እና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን በተለያዩ መንገዶች ከመኖሪያ አካባቢያቸው፣ ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ ቦታ ይሰበስባሉ። ለመድኃኒት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ሲለዩ፣ ሲሰበስቡና ሲቀምሙ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱን ለማንገስና ይበልጥ ፈዋሽ እንዲሆኑ ለማድረግ የዕፅዋት ማንገሻ ጸሎት፣ እምነታዊ ክዋኔና ሥርዓተ ገቢር፤ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ሥርዓቶች እንደሚፈጸሙ (Young,1970; Alemayehu,1984) ያሥረዳሉ። በዚህ መልኩ ከተዘጋጁ በኋላ እንደ በሽታው ዓይነትና ባህርይ በተለያየ መልኩ (የሚጠጡ፣ የሚሸተቱ፣ የሚታኙ፣ የሚቀቡ፣ በሚታጠንና በክታብ መልክ የሚንጠለጠሉ) ተደርገው ይሰጣሉ።

## 2.1.7. የሀገረሰባዊ መድሀኒት ህክምና እውቀት ተስተላልፎ

ባህላዊ መድሀኒት ረጅም ዘመን ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ የኖረና አሁንም ያለ ሀገር በቀል ጥበብ መሆኑን የመስኩ ምሁራን (Sofowora,1982) ያስረዳሉ። ይህ ሀገር በቀል እውቀት የባህል ሕክምና በአፋዊ (በቃል) አንዳንዴ በጽሑፍ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ባህላዊና መንፈሳዊ ይዘት ያለው ክዋኔ ነው። እንደ ዘመናዊ ሕክምና ማንኛውም ሰው በመማርና በማጥናት ሕክምናውን መስጠት አይችልም። ለበሽታው የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ምስጢራዊና እውቀቱም ለተመረጡ ሰዎች ብቻ የሚተላለፍ ነው። አንድ የባህል ሐኪም መሆን የሚፈልግ ሰው፤እውቀቱ እንዲሰጠው አካላዊ፣ አዕምሯዊ መንፈሳዊ ስሜቶችን የሚመረምሩ ዓይኖች ሊኖሩት ይገባል። ይህም ባህላዊ ሕክምና ጥበብ መሆኑን እንዲሚጠቁም (ሻሂዳ፣2017፣ገጽ፣14) ይገልጻሉ።

በተለያዩ ሀገራት በተለይም በኢትዮጲያ ውስጥ ባህላዊ ህክምና ለረጅም ዘመን ዘልቆ የቆየ ሀገር በቀል ጥበብ ነው። ይህ ጥበብ አብዛኛውን ጊዜ በቃል እየተላለፈ የመጣ ሲሆን የዚህ እውቀት ባለቤት ጥበቡን ለሌላ አካል የሚያስተላልፈው አንድም በውልደት ማለትም ለወለደው በባህሪው ለተመሰገነ፣ ቁጥብ እና ጠንቃቃ ለሆነ፤ለመጀመሪያ ልጅ፤አንድም ታማኝ ለሆነ ምስጢረኛ የቅርብ ወዳጅ፤አለበለዚያም ታዛዥ እና ትሁት ለሆነ፤ስለ ዕፅዋት የተሻለ እውቀት እና ግንዛቤ ላለው ሰው ነው። በሌላ በኩል ከተለያዩ የጥበብ መጸሐፍት በማንበብ እና በመማር የዕፅዋቱን መገኛ ቦታ፣ እያንዳንዱ ዕፅዋት ለምን በሽታ አገልግሎት ላይ እንደሚውል፣ እንዴት እንደሚዘጋጅ፣ እንደሚቀመም እና እንደሚሰጥ ማወቅ ይቻላል። ይሁን እንጂ የባህል መድሀኒት አዋቂው ይህንን እውቀት አሳልፎ የሚሰጠው አቅሙ እየደከመ ሲሄድና ዕፅዋቱን እና ማዕድናቱን ሌሎችንም ግብዓቶች ካሉበት ቦታ ሰብስቦ ማምጣት ሲያዳግተው አለበለዚያም

“የመሞቻ ቀኔ ደርሷል” ብሎ ሲያምን እንደሆነ (Mekonen,,2019,P.83; Alemayhu, 1984, P.119-123) ገልጸዋል።

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር፤የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ፣ የክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ እና የጤና ሥነ ምህዳር (Medical Ecology) ንድፈ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1 የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Functionalism Theory)

የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ መነሻው የዝግመተ ለውጥ (Evolution) ንድፈ ሀሳብ ሲሆን በተወሰነ መልኩ የራሱ ወደ ሆነው ስነ ሰባዊ አመለካከት የመጣው በእውቁ የስነ ህብረተሰብ አባት በ Durkheim ተፅዕኖ ነው፡፡ ንድፈ ሀሳቡ በ1940ዎቹ እና 50ዎቹ በ Benjamin Patkine አማካኝነት የተዋወቀ ሲሆን መሰረቱን ያደረገው Herbert Spencer, Emile Durkheim, Talcotk Parsons እና Robert Merton በሚባሉ አቀንቃኞች ስራ ላይ መሆኑን (Jons,1994; Sims and Stephens, 2005) ያብራራሉ፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋነኛ አቀንቃኞችም Malinowski እና Radcliffe Brown የተባሉ የስነ ህብረተሰብ ተመራማሪዎች መሆናቸውን (Finnegan,1977,P,69) ይገልጻሉ፡፡

ስለ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ምሁራን ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡ (Malinowski) መሰረታዊ የንድፈ ሀሳቡ ማተኮሪያ "ባህል ሁልጊዜም የፍጡራን ፍላጎት ማሚያ ነው" የሚል ሲሆን ይህ እሳቤ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ የሚፈልጋቸው (የሚያስፈልጉት መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶች) አሉት፡፡ እነዚህን ፍላጎቶች ደግሞ የማህበረሰቡ ሎሮች የሚያሚሉ መሆን ይገባቸዋል፤የሚል አመለካከት ያለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን መሰረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ፍላጎቶችን የማያሚላ ከሆነ ፎክሎር አላስፈላጊ ነው፤ወደሚል ሀሳብ ያመራል፡፡

የMalinowski ብያኔ፤አንድ የፎክሎር ዘውግ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ጠቀሜታ ወይም አገልግሎት የሚያመለክት አገላለፅ እንደሆነ (Schoemarker,1990) ያስረዳሉ፡፡ በፎክሎር ውስጥ የሚታዩ አራት ዋና ዋና ዘውጎች አሉ፤የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ ቁሳዊ ባህሎች፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ስነቃሎች እንዲሁም ትውን ጥበባት ሲሆኑ እነዚህ ሎሮች የማህበረሰቡን ማንነት፣ አመለካከት፣ ወግና ስርዓት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ እስከሆኑ ድረስ ሀሳብን፣ ስሜትን፣ ፍላጎትን እና ማንነትን መግለጫዎች በመሆናቸው ለማህበረሰቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይኸውም ስነ ቃሉ ለሚነገርበት ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ እንዳለ ሁሉ ሀገረሰባዊ እምነቱና መድሃኒቱም፤ቁሳዊ ባህሉ፣ ትውን ጥበቡ እና ሀገረሰባዊ ልማዱ ለማህበረሰቡ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

Bascom (1954) የተግባራዊነትን ንድፈ ሀሳብ ብያኔ ሲገልጹ ፎክሎርና ሰዎች የተሳሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ፎክሎር የማስተማር፣ የማምለጫ፣ የማስቀጠያ እና ማህበራዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል በማህበራዊ መዋቅር ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉት Radcliffe Brown (1922) ማህበረሰብ ራሱን ፈጣን በሆነ ምጋቤ ምላሽ ውስጥ እንዲቆይ የሚያደርግ ስርዓት ሲሆን ተቋማት ደግሞ በተግባራቸው ወይም ባላቸው ፋይዳ ማህበረሰቡ እንደ ስርዓት የሚቀጥልበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ ናቸው በማለት ይገልጹታል፡፡ ይህ አገላለጽ ማህበራዊነት ከስነ ተፈጥሯዊ ቅርጾች እና ግዑዛን ነገሮች የተለየና የተለያየ ደረጃ ያለውን እውነታ ያካተተ ሲሆን በዚህ መልክ የተደራጀውን ማህበረሰብ እንዲቀጥል እና ማህበረሰቡ ያለውን ፍላጎት እንዲያሟላ ደግሞ ተቋማት የራሳቸው ሚና ስላላቸው ይደራጃሉ፤ የሚል ነው፡፡

እንደ ሰለሞን አገለለጽ ሶስት አይነት ተፅዕኖ የፈጠሩ የተግባራዊነት አስተሳሰቦች አሉ (2007፣ ገፅ፣ 75-76)፡፡

1. የሰው ልጅ ፍላጎትን መሠረት ያደረገው የMalinowski አገላለጽ ማንኛውም ግለሰብ ሰባት መሰረታዊ ፍላጎቶች አሉት፡፡ እነሱም፡- የተመጣጠነ ምግብ፣ ዘር መተካት፣ የሰውነት ምቾት፣ ደህንነት፣ ግንኙነት፣ እንቅስቃሴና እድገት ናቸው በሚል ያስቀምጣቸዋል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሎር ከላይ የተዘረዘሩትን የሰውን ልጅ ፍላጎት ማሟላት ይገባዋል የሚል እሳቤን የያዘ ነው፡፡
2. በቡድን ውስጥ ያሉ ማህበራዊ መዋቅሮች (Social Structures) ባላቸው ጠቀሜታና ሚና ላይ ትኩረት የሚያደርገው ተመራማሪ Radcliffe Brown ራድክሊፍ ሲሆን መዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት (Structural Functionalism) በመባል ይታወቃል፡፡ ማህበራዊ መዋቅሮች በተለያየ ደረጃ የተዋቀሩ በመሆናቸው ማህበረሰቡ በእነዚህ መዋቅሮች ውስጥ ተካታች በመሆኑ ተቋማትና ባህሎች የእነዚህ ማህበራዊ መዋቅሮች አስቀጣይ በመሆን ያገለግላሉ፡፡
3. የEmile Durkheim እና የ Maresel Mnanous አስተሳሰብ የሆነው የሠው ልጅ አዕምሮ መዋቅር ባለው ንቃተ ህሊናው አያያዥ አማካኝነት ለማህበራዊ አንድነት ወይም ትስስር (Social Solidarity or Cohesion) እና ለባህላዊ ንባብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ እሳቤ በማህበረሰብ ውስጥ አንድነት ያለው ሀይልን የሚያራምዱ የጋራ እምነቶች፣ሀሳቦች እና የሞራል ዝንባሌዎች ስብስብ እንዲሁም ማህበራዊ አንድነትን የሚያስረዳ ሀሳብ ነው፡፡

የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ ማህበረሰብን እንደ አንድ እንደተራጀ ስርዓት በመመልከት የተደራጀና አንድ የሆነ የማህበረሰብ መዋቅር መኖሩን ማመልከት መቻሉ እና ማህበራዊ መዋቅሮች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚያበረታታ የማጠንጠኛ ነጥብ ይዞ መምጣቱ የንድፈ ሃሳቡን ጠንካራ ጎን የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ሁልጊዜም በቡድኑና ዓውዱ ውስጥ የሚፈጠር ክስተትን የሚመለከት በመሆኑ፣ቡድን፣በተመሳሳይ ሁኔታ ይሰራል ከሚል ግምት ባሻገር፣ቡድኖች በዘመናት ውስጥ ተመሳሳይ ሆነው ይቆያሉ የሚል አስተሳሰብን ያራምዳል፡፡ ሆኖም ሁሉም ቡድን በተመሳሳይ መንገድ ይሰራል የሚል ማጠንጠኛ ሀሳብ ይዞ በዚህ እሳቤ መገልገል፣ቡድንን አይለወጤ አድርጎ መመልከት የንድፈ ሀሳቡን ክፍተት የሚያሳይ ነው፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ የተራክቦታዊ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች፣ተግባራዊነት፣የከዋኞችን እና የተራክቦን ሂደት ውስብስብነት በበቂ ሁኔታ የማስረፅ አቅም ያንሰዋል በሚል ይተቹታል፡፡ ከዚህ በጨማሪም የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ሎር፣ለማህበረሰብ ያለው ጠቀሜታ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ የንድፈ ሃሳቡን ክፍተት የሚያሳይ ነው፡፡

ፎክሎር፣የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ ቁሳዊ ባህሎች፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ስነቃሎች እንዲሁም ትውን ጥበባትን የሚጠቀልል ሲሆን እነዚህ ሎሮች የማህበረሰቡን ማንነት፣ አመለካከት፣ ወግና ስርዓት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ እስከሆኑ ድረስ ሀሳብን፣ ስሜትን፣ ፍላጎትን እና ማንነትን መግለጫዎች በመሆናቸው ለማህበረሰቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይሰጣሉ፡፡

በአጠቃላይ የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣በአንድ ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ የሚያተኩር ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች ማንኛውም ሎሮ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጥቅሞች አሉት የሚል ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡

የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ማንኛውም ሎር ለማህበረሰቡ ካለው ፋይዳ አንጻር ማየት እንደሚቻል የሚያቀነቅን ንድፈ ሃሳብ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰለሞን ያቀረቧቸውን ሶስት ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀሳቦች ከዚህ በፊት ባለው ክፍል ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ከማህበረሰቡ ሎሮች ውስጥ አንዱ የሆነው ሀገር በቀል የሀገረሰባዊ መድሀኒት እውቀት

የማህበረሰቡን ጤና በመጠበቅ፤ውጫዊና ውስጣዊ ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ሎር፤የሰውን ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት አስፈላጊ ነው፤ ጠቃሚ ነው፤የሚል  ማጠንጠኛ ያለውን የMalinowskiን ብያኔ መሰረት በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል። ይሁን እንጂ ይህ ጥናት ሎር፤በመዋቅራዊ ጠቀሜታዊነት ላይ ካለው ፋይዳ አንጻር የሚመረምረውን Radcliffe Brown እና ሎር፤የጋራ እምነቶች፣ ሀሳቦች እና የሞራል ዝንባሌዎች ጋር ያለው መስተጋብር ላይ ትኩረት የሚያደርገው የ Emile Durkheim እና የ Maresel Manous አተያይ ይቃረናል ማለት አይደለም።

### 2.2.2. ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ (Performance centerd Approche)

ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ዘመናዊ የንድፈ ሃሳብ አይነት ሲሆን አንድ የፎክሎር ቅንጣት የተሸመነበትን ቁስ የሚመለከት ነው፡፡ ክዋኔ ከቴክስት ጋር የተያያዘ ሲሆን የትኛውም ፎክሎር ክዋኔ ካለው ህይወት አለው፡፡

በፎክሎር ጥናት፤የአውድ ተኮር ክዋኔ ንድፈ ሃሳብ (Contextual-centered Performance theory) መስራች፣ አቀንቃኝ፣ አባት Richard Bauman ሲሆን አውድ-ተኮር ክዋኔ (Context-centered performance) የአውድና እና የክዋኔ አላባውያንን (Elements) በማካተት፣ በማጣመር፣ በማያያዝ ግንኙነት እና ያላቸውን መስተጋብር በመረዳት ትንተና ማድረግን ይመለከታል (Dundes,1980,P,92)፡፡

አውድ-ተኮር ክዋኔ፤የፎክ ቡድን እና የሎር እሳቤን አጣምሮ በመያዝ፤ባህላዊና ማኅበራዊ አውዶችን የሚመለከት መሆኑን (Bauman,1986) ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል ክዋኔ፤ሀሳብና ድርጊትን የያዘ፤አንዱ እርስ በእርስ የመግባቢያ መንገድ መሆኑን “Performance is a mode of communicative behavior and a type of communicative events.” (Bouman, P.41) በማለት ይገልጹታል፡፡ ክዋኔ ተግባቦታዊ ሁነቶች በአንድነት የሚቀርቡበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ሁነት እና ተግባቦታዊ ሥርዓትን ይመለከታል፡፡

የአንድ ፎክሎር ክዋኔ እንደ ማህበረሰቡ እና ባህሉ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ክዋኔ ከትንሽ አጋጣሚ እስከ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያስፈልገው አጋጣሚ ድረስ ማህበረሰቡ የሚገለገልበት እና ራሱን የሚገልጽበት መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ክዋኔ ማለት ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ የክዋኔውን ድባብ፤ከዋኞቹንና በውስጡ ያለውን እምቅ ጥበብ፣ ታዲሚውን እና መቼቱን የያዘ ነው፡፡ ክዋኔ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ ከዋኙ፤የአከዋወን ብቃቱን እና የመድረክ አያያዝ ችሎታውን ያሳያል፡፡ እንደ Bauman (1992,P,74) ገለጻ ክዋኔ የሚለው ቃል ጥበባዊ ድርጊት ሆኖ ድርጊትን እና ክስተትን፣ የክዋኔውን ሁኔታ፣ ዋኞችን፣ ጥበቡን፣ ታዳሚውን እና መቼቱን አጣምሮ የሚያሳይ ተግባቦታዊ ጥበብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ለክዋኔ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ከሚባሉት ነጥቦች መካከል ከዋኝ (Performer)፣ታዳሚ (audience)፣ አውድ (context) እና የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers) ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ሂደት የከዋኙ እና የታዳሚ በአንድ ላይ መገኘት የግድ ይሆናል፡፡ ከዚህ

አንጻር በባህል እና በማህበረሰብ መካከል በመሆን ማህበራዊ ዘላቂነት እንዲኖር፣ ከዋኙ ትልቁን ድርሻ ይወጣል፤ውስጣዊ ስሜትን፣ ጥበብን፣ እውቀትን እና ችሎታን በማሳየት ማህበራዊ መስተጋብሩ ይበልጥ እንዲጠነክር ያደርጋል።

በክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው ብቻውን የከዋኝነት ሚና ሊጫወት ይችላል። በሌላ በኩል ታዳሚዎች ባሉበት ሊከወን ይችላል። Finnegan ይህንን ሀሳብ አስመልክቶ ሲያሥረዱ “They may be acting singly; in pairs; in a small or a large group; interacting or exchanging with other  single or collective performers as leader, follower, or equal; overlapping or interchanging with more audience - like roles.”(1992,PP.89) በማለት ይገልፁታል። እንዲሁም “በአንድ አጋጣሚ በሚነሳ ሀሳብ፣ በሚፈጠር ክስተት እና በተገኘ አጋጣሚ በሚደረግ ተግባቦት፤በከዋኙ የሚመራ የስሜት፣ የእውቀት እና የድርጊት ቅንብር ነው” (Finnegan, 1992,P.90) በማለት ያስረዳሉ።

Bauman የከዋኔ አላባዊያንን በሚያስረዱበት ክፍል መቼትን፤ክዋኔው የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የከዋኙን የአከዋወን ስልት፣ የተሳታፊዎቹን ሁኔታ፣ ተሳታፊዎች እና የነበራቸው ስሜት፣ የክዋኔ ቅደም ተከተል የሚሉትን ይጠቅሳሉ (1992,P.299)።

በፎክሎር ጥናት “አሃድ/ቴክስት” አንድ አካል ሲሆን የፎክሎር ሁነት (Event)፤አውድ (Context) እና ክዋኔ (performance) መሰረታዊ ይዘት ናቸው (Ben-Amos,1975; Bauman,1992,P,69)። በክዋኔ ውስጥ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ፣ የክዋኔ ጠቋሚዎች እጅግ የተቆራኙ ነገሮች ናቸው።

ከእነዚህ ነጥቦች ውስጥ አውድን በሚመለከት፤ትርጉማዊ አውድ፣ ተግባቦታዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የሁነት አውድ፣ ግለሰባዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በሚል በስድስት ከፍለውታል (Bauman,1986)። ይሁን እንጂ በስድስት የተከፋፈሉትን ጠቅለል አድርገው ለሁለት  ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በሚል አስቀምጠዋቸዋል።

በመሆኑም ባህላዊ አውድ፤አንድ የፎክሎር ቅንጣት የያዘው ሃሳብ ምንድን ነው? ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች ጋር እንዴት ይዛመዳል? በባህል ውስጥ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? በሀይማኖት ተቋማት እና በእምነት ቤቶች ያለው ተዋረዳዊ አካሄድ ምን ይመስላል? የአንድ ማህበረሰብ የእርስ በርስ ግንኙነት ምን ይመስላል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚመልስ ሲሆን ማህበራዊ አውድ ደግሞ የባህሉ ባለቤት ማን ነው? የዘር፣ ቋንቋ እና የሀይማኖት

ልዩነታቸው ምን ይመስላል? የስራ ሁኔታቸውና በማህበረሰብ ውስጥ ያለው የጾታ ልዩነት እንዴት ይታያል? ባህሉ በማህበረሰቡ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ አለ? እንዲሁም ማህበረሰቡ ያለበት ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሉ ዝርዝር ነጥቦችን ይመለከታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት ሀገረሰባዊ መድሀኒት በማህበረሰቡ ዘንድ ምን አይነት ስሜት ይፈጥራል? ሀገረሰባዊ መድሀኒት ከሀይማኖት እና ከእምነት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው? የሀገረሰባዊ መድሀኒት ሀኪሞች ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብር ምን አይነት ነው? የዚህ እውቀት ባለቤት ማን ነው? ሀይማኖት፣ አመለካከት፣ ቋንቋ፣ ማንነት፣ የማህበረሰቡን የመተዳደሪያ ገቢ፣ የባህል ህክምና ተጠቃሚዎች ለባህል ህክምናው እና ለባህል ሀኪሞቹ ያላቸው አመለካከት፣ ይህ አመለካከት በባህል ሀኪሞቹ ላይ እና በታካሚዎች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ምን ይመስላል? የሚሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ለመመለስ አውዱን መመልከት እና በክዋኔው ላይ መመስረት ተገቢ በመሆኑ፤በዚህ መሰረት ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ "ፎክ ቡድን" የጥናቱ አካላይ ማኅበረሰብ (ኗሪው)፣የባህል ሕክምና ባለሙያዎች፤የባህል ሕክምና ተጠቃሚዎች፣ የዘመናዊ ሕክምና ባለሙያዎችን እንዲሁም ተጨማሪ መረጃ ሰጪዎችን ይመለከታል፡፡ በተጨማሪም "ሎር"፤የተጠኚውን ማኅበረሰብ የጋራ እውቀት፣ ጥበብ፣ አመለካከት፣ ሀይማኖት፣ እምነት፣ እሴት ማህበራዊ መስተጋብሮችን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ አንጻር የባህል ሀክምና ባለሙያው በከዋኝነት ቀዳሚውን ሚና የሚወጣ ሲሆን የህክምና አገልግሎቱን ለማግኘት የሚሄደው አካል (ታካሚው)፤ 'ታዳሚ' በሚለው የክወኔ አላባ ሲገለጽ፣ በሥነ ምህዳሩ ወይም በተፈጥሮ ምክንያት የበሽታ መከሰትና የማህበረሰቡ ጤና መታወክ፤ የባህል ህክምና ባለሙያውን እና ታካሚውን የሚያገናኝ የክዋኔ አጋጣሚ ነው፡፡ በባህል ህክምና አገልግሎቱ ወቅት የሚታዩ ሀይማኖታዊ፣ እምነታዊ እና ልማዳዊ ድርጊቶች፣ እንደ ባህል ህክምና ባለሙያው የሚፈቀዱ እና የሚከለከሉ ቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ህክምና ሁኔታዎች፤ የህክምና አገልግሎቱ እየተሰጠ ያለ መሆኑን የሚጠቁሙ ሁነቶች ናቸው፡፡

### 2.2.3. የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ (Medical Ecology Theory)

የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ በጤና ሳይንስ ዘርፍ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር አዲስ የሚባል አተያይ ሲሆን በመድሀኒት እና በሥነ ምህዳር መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠና ሳይንስ ነው። በዚህ አሳቤ፤በሰው ጤና ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ፈጣሪነት፤አካባቢያዊ የሆኑ ህመሞች፤ ሰው፣ አካባቢን እና ተፈጥሮ ያላቸውን ግንኙነት እንዲሁም ሥነ ምህዳር በጤና ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ የሚመረምር ነው። ቀጥሎ የቀረበው የ Gennadiy,etal, ጥቅስ ይህንኑ ያጠናክራል።

> Medical ecology (ecological medicine) is a comparatively new direction of the medical science at the intersection of medicine and ecology, “complex scientific discipline studying all the aspects of environment influence on the man’s health” (Reymers, 1990) making focus on the environment illnesses, people interaction and the environment in the sphere of people’s health as well as interaction of the environment risk factors and people’s health (2016,PP.1).

የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ በሰው ልጅ ጤና ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያላቸውን አካባቢያዊ ገጽታዎች የሚያጠና ሳይንስ ነው። ጤናማ አኗኗር እንዲኖር የሥነ ምህዳራዊ ተግባር እና ፋይዳ አጠቃላይ ሂደቶችን ለመረዳት የሚያበረክተው አስተዋፅዖም ከፍ ያለ ነው። የአካባቢ ብክለት በምንተነፍሰው አየር፣ በምንጠጣው ውሃ እና በምንበላው ምግብ ላይ ለውጥ ያመጣል። ይህም ጤናማው ማህበረሰብ ወደ ከፋ የጤና እክሎች እንዲያመራ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥር መሆኑን (Gennadiy ,etal,2016,P.34) ያብራራሉ።[2]

ይህ አቅጣጫ በሰው ልጅ ጤና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሥነ ምህዳራዊ ገጽታዎችን በማጥናት የብዝሀ ሕይወት እና አካባቢ፤ሰው እና ተፈጥሮ ተጣጥሞ የሚኖርበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ትኩረት ያደርጋል። በሰው ጤና፣ በአካባቢ በሽታ እና በሰዎች መስተጋብር ላይ ትኩረት በማድረግ የጤና እና የአካባቢ መስተጋብር ውስጥ አካባቢያዊ መንስኤዎች ያላቸውን ጫና ይመረምራል ።

---

[2] Medical Ecology Theory በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ለንድፈ ሀሳቡ የአማርኛ አቻ ፍቺ ከምንጩ ማግኘት ስላልተቻለ በአጥኝዋ ትርጓዋሜ መሰረት”የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ” በሚል የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል።

በዚህ ጥናት በሸዋሮቢት እና ዙሪያዋ የሚከሰቱ፤በሀገረሰባዊ መድሀኒቶች የሚዳኑ በሽታዎች፣ የበሽታ መከሰቻ መንስኤ፣ በሽታዎቹ የሚፈወሱበት ሂደት፤መድሀኒቶቹ ከየት እና መቼ ይገኛሉ? እንዴት ይዘጋጃሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ለጥናት የተመረጠውን አካባቢ፣ ሥነ ምህዳራዊ ገፅታ መመርመር ተገቢ በመሆኑ ሸዋሮቢት እና ዙሪያዋ ከበሽታና ከመድሀኒት አንጻር ያለው ተፈጥሯዊ ስርዓት ምን ይመስላል? በሽታዎቹ የሚከሰቱበት ሥነ ምህዳራዊ መንስኤ ምንድን ነው? ጤናን ለመመለስስ በግብዓትነት የሚያገለግሉ መድሀኒቶች ከየት እና እንዴት ይገኛሉ? የሚሉትን ሀሳቦች ለማስረዳት የጤና ሥነ ምህዳር (Medical Ecology) ንድፈ ሃሳብ አስፈላጊ በመሆኑ በጥናቱ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 2.2.4. የንድፈ ሃሳቦች ትስስር

ቀደም ሲል በቀረቡት ገፆች የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሃሳብ፣ የክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ እና የጤና ሥነምህዳር (Medical Ecology) ንድፈ ሃሳቦች ይዘት እና ትኩረት በቅደም ተከተል ቀርቧል፡፡

የጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ በአንድ አካባቢ ለበሽታዎች መከሰት ምክንያት ወይም መንስኤው እራሱ ተፈጥሮው ነው፤የአካባቢ ምቹ አለመሆን፤በአጠቃላይ በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ያለው ግንኙነት ለሰዎች ደህንነት ተፅዕኖ አለው፤የሚል አተያይ ያለው ንድፈ ሃሳብ ሲሆን የጥናት አካባቢው ቆላማ በመሆኑ ምክንያት ማህበረሰቡን ምን ምን በሽታዎች ያጠቁታል? መፍትሔያቸውስ ምንድነው? የሚሉትን ሀሳቦች በዋናነት በትንተና ለማሳየት አስፈላጊ በመሆኑም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በመሆኑም እነዚህን በሽታዎች ለመከላከል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እውቀቶች፣ ባህሎች፣ ስርዓቶች እና ልማዶች፤በሀሳብ እና በድርጊት ይገለጻሉ፤ይከወናሉ፡፡ ማህበረሰቡ እራሱን ከበሽታ ለመከላከል፤ለዘመናት ሲጠብቃቸው እና ሲከውናቸው የነበሩ እንዲሁም በማህበረሰብ የአመለካከት ለውጥ የተጨመሩ አልያም የተቀነሱ ስርዓተ ክዋኔዎችን አስተባብሮ ይከውናል፡፡ እነዚህ በድርጊት የሚገለጹ ክዋኔዎች፣ በሀሳብ የሚገለጹ ስርዓቶችና ልማዶች የማህበረሰቡ ጤንነት ማስጠበቂያ፤በሽታን መከላከያና ደህንነትን ማስቀጠያ በመሆን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢው ማህበረሰቡን የሚያጠቁ በሽታዎች መንስኤያቸው ምንድነው፣ ሀገረሰባዊ ህክምና ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው፣ በህክምና ስርዓቱስ ምን ምን ክንዋኔዎች ይከወናሉ የሚሉ መሰረታዊ ነጥቦችን የያዙ ሲሆን ሶስቱም ንደፈ ሃሳቦች እርስ በርስ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የሥነ ምህዳር አሉታዊ ተፅዕኖ፤ለጤና መቃወስ ምክንያት ይሆናል፤ የጤና

ቀውስ ደግሞ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ለማህበረሰቡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሽፋነ እንዲሰጡ ያነሳሳል፡፡ በመሆኑም ሀገረሰባዊ ህክምና ለማህበረሰቡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት በመስጠትና የማህበረሰቡን ደህንነት በማስቀጠል ረገድ የራሱን ሚና ይወጣል፡፡

በቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ ህክምና አገልግሎቱ ወቅት የሚከናወኑ ክንዋኔዎች ደግሞ ህክምናውን ይበልጥ አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ፤ ከተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ ከክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ እና ከጤና ሥነ ምህዳር ንድፈ ሃሳቦች አንጻር ተካሂዷል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን አስመልክቶ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ሰባት (7) ጥናቶች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ በትምህርት ክፍሉ ከተመለከትኳቸው ጥናቶች ውስጥ በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን አስመልክቶ የተካሄደ ጥናት አላገኘሁም። በዚህ ርዕስ ዙሪያ በሌሎች ትምህርት ክፍሎች ማለትም በአንትሮፖሎጂ፤ሶስት(3)፣ በሲሶሎጂ፤አንድ (1) እና በታሪክ ት/ክፍል፤አንድ (1) እንዲሁም በተለያዩ ስብሰባዎች (የጥናትና ምርምር ማቅረቢያ መድረኮች) ላይ አራት (4) ጥናቶች ቀርበዋል፤በአጠቃላይ አስራ ስድስት (16) ጥናቶች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል፡ ፡ እነዚህ ጥናቶች ከይዘት፤ጥናቶቹ ከሌሎች ጥናቶች በተለይ ካላቸው ጠንካራ ጎን በመነሳት እና ለዚህ ጥናት ከሚሰጡት እውቀትና ተሞክሮ አንጻር፤ቅኝት ተደርጎባቸዋል። እነዚህ ጥናቶች ይዘውት ከተነሱት አላማ፣ ከጥናት ዘዴ፣ ከትንታኔ እንዲሁም ከውጤት አንጻር የተቃኙ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት፤ያላቸውን ጠንካራ ጎን፣ በጥናቶቹ የታዩ ክፍተቶች እና ይህ ጥናት የሚሞላቸው ጉድለቶች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ቀርቧል። በመሆኑም ዳሰሳ የተደረገባቸው ጥናታዊ ጹሑፎች በተጠኑበት ትምህርት ክፍል እና ጥናቶቹ በቀረቡበት መንገድ ተደራጅተው ቀርበዋል።

### 2.3.1. በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጹሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በኤም.ኤ ዲግሪ ደረጃ በሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ከተጠኑ ጥናቶች መካከል የአለማየሁ ዘሪሁን ጥናት ቀዳሚው ነው።

አለማየሁ ዘሪሁን (2000) "የኑዌር ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ህክምና እውቀት፣ አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት የመጀመሪያው ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዋና ትኩረት የኑዌር ማህበረሰብ የሀገረሰብ ህክምና አከዋወን ምን እንደሚመስል በመመርመር ሀገረሰባዊ ልማዱን ለሌላው ማህበረሰብ ገልጾ ማሳየት ነው። በጥናቱም በባህል ህክምና የሚዳኑ በሽታዎች ምን ምን ናቸው? ህክምናውን የሚሰጡ የባህል መድሀኒት እውቀት ያላቸው አካላት እነማን ናቸው? ለመድሀኒትነት የሚውሉ ግብዓቶችን ከየት እና እንዴት ያገኛሉ? የመድሀኒቶቹ ቅመማ ስርዓት ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስተዋል። እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ

የመረጃ መሰብሰቢያዎች አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገላጭ ትንተና ስልት በመጠቀም ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። በዚህ መሰረት በጥናቱ የኑዌር ማህበረሰብ የበሽታዎቹ መንስኤ ከፈጣሪ እና ከሀገረሰባዊ እምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በመንፈሳዊ ሀኪሞች የሚከናወን የህክምና ስርዓት እንዳለ እና የማህበረሰቡ የጤና ችግሮች የተለያዩ የህክምና እውቀት ባላቸው Tetwal (ቴትዋል)፤Rieth (ይስ)፣ gam (ጋም) እና gok (ጎክ) በሚባሉ የኑዌር የባህል ሀኪሞች አማካኝነት እንደሚድኑ በጥናቱ ተደርሶበታል። ባለሙያዎቹ መድኃኒቶችን በአብዛኛው ከዕፅዋት፣ የተወሰኑት ደግሞ ከእንስሳት እና ከማዕድናት ውጤቶች እንደሚቀምሙ እና በመንፈሳዊ ሀይል በመታገዝ በሽታዎችን በመፈወስ የማህበረሰቡን የጤና ችግሮች የሚቀርፉ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል።

የኑዌር ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በቃል የሚተላለፍ የህክምና እውቀት ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ አሁን ያለው ባህላዊ እውቀት በሂደት ሊለወጥ አልያም ሊጠፋ የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑን ገልጸዋል።

የአለማየሁ ጥናት የኑዌር ማህበረሰብ የባህል ህክምና አዘገጃጀት፣ አሰጣጥ ሂደት እና ስርዓቱን በማሳየት ረገድ፤የክለሳ ድርሳናት አቀራረብ እና በትንተና ሂደት የሚታየው ስርዓታዊ አደረጃጀት የጥናቱን ጠንካራ ጎን የሚያሳይ ቢሆንም የናሙና አመራረጥ ሂደት፣ የጥናት አካባቢ እና መረጃ አቀባዮች የተመረጡበትን መስፈርት አለመግለጽ እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ብቁነት ላይ ምክንያታዊ ሃሳብ አለመቅረቡ የጥናቱን ክፍተት የሚሳይ ነው።

የአለማየሁ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳሰለው፤የሁለታችንም ትኩረት ሀገረሰባዊ መድሀኒት እውቀት፣ አመለካከት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ የእኔ ጥናት ከዕፅዋት የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ማተኮሩ እና የአለማየሁ ጥናት ደግሞ፤ በመንፈሳዊ ሀኪሞች የሚሰጡ የህክምና ስርዓትን መመልከት መቻሉ ከእኔ ጥናት ይለየዋል። ይሁን እንጂ እምነት እና ባህላዊ ህክምና ያላቸውን ትስስር መመልከት መቻሉ ሌላው የአለማየሁን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋራ የሚያመሳስለው ነጥብ ነው።

ምህረት ዳኘው (2002) "በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሀኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም" በሚል ርዕስ ባደረጉት ጥናት ዘመናዊ ህክምናው በተሻለ ሁኔታ በሚሰጥበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሀገረሰባዊ ህክምና በስፋት የሚሰጥበትን ምክንያት መለየት፣ የህክምና አሰጣጥ ስርዓቱን መከታተል እና ውጤታማነቱን ከታካሚዎች ማረጋገጥ እንዲሁም እምነት

በሀገረሰባዊ ህክምና ላይ ያለውን ጫና ማሳየት የጥናቱ ትኩረት ናቸው። በዚህ ጥናት ከሀገረሰባዊ የህክምና ባለሙያዎች እና ከዘመናዊ ሀኪሞች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በጹሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ባህላዊ ሀኪሞቹ ህክምናውን የሚሰጡት ለመድሀኒቶቹ በግብዓትነት የሚውሉትን ዕጾች ከተለያዩ ክፈለ ሀገራት በማስመጣት እንደሆነ እና መድሀኒቶቹ የሚሰበሰቡበት የተለየ ስርዓት ያላቸው መሆኑን አትተዋል።

ይኸውም መድሀኒቶቹ የሚዘጋጁት በፀሎት፤የመድሀኒቶቹ የመቁረጫ የተለዩ ቀናት መኖራቸው፤ለመድሀኒቶቹ ፈዋሽነት ሀይል የሚጨምሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ባለሙያዎች መድሀኒቱ እንጂ ስርዓቱ አይጠቅምም የሚል አመለካከት ያላቸው መሆኑንም አንስተዋል። ጥናቱ በተካሄደበት በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሀኒቶች ተጠቃሚ መብዛት ምክንያት ህክምናው በፍጥነት ማግኘት መቻሉ፣ ከክፍያ አንጻርም መድሀኒቱን የሚያገኙበት ክፍያ ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም በመድሀኒቱ እፈወሳለሁ የሚል እምነት ስላደረባቸው እንደሆነ በጥናቱ ገልጸዋል። በመሆኑም ጥናቱ በተደረገበት ከተማ ባህላዊ ሀኪሞች አዘውትረው የሚፈውሷቸው የወፍ በሽታ (ጉበት)፣ የኪንታሮት፣ የነቀርሳ፣ የአልማዝ ባለጭራ እና ችፌ ከሰውነት መቁሰል ጋር የተያያዙ በሽታዎች እንደሆኑ ተጠቁሟል።

በጥናቱ ማጠቃለያም የባህል ሀኪሞች ሙሉ በሙሉ ዕውቀት ያላቸው ናቸው ባይባልም ለከተማው ህዝብም ሆነ ለሌላው ማህበረሰብ ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ መሆኑን ጠቁመዋል። በመሆኑም የባህል ህክምናው ከዘመናዊ ህክምናው ጋር ተጋግዞ መስራት ቢቻል የጤና ችግሮችን በማቃለል ረገድ ከፍተኛ አስተዋፆ ያለው መሆኑን ተገንዝበው የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እና የማህበረሰብ አባላት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፤ እንዲሁም እውቀት እና ችሎታ ላላቸው ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ ቢሰጣቸው የተሻለ ይሆናል የሚል የይሁንታ ሀሳብ አቅርበው ጥናታቸውን አጠናቀዋል።

በምህረት ጥናት ውስጥ ጥናቱን የተሳካ ለማድረግ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፤እምነት በባህላዊ ህክምናው ላይ ከፍተኛ አስተዋፆ ያለው መሆኑን ጠቁመዋል። ሆኖም የናሙና አመራረጥ ስልት፣ በቂ ጽንሰ ሃሳባዊ ማስረጃዎች አለማቅረብ እና በትንተና ሂደት የሚታዩ ጉድለቶች የጥናቱን ክፍተት የሚያሳዩ ናቸው ።

የምህረት ጥናት፤የባህላዊ መድሀኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም ትኩረት አድርጎ መነሳቱ፣ ሀይማኖት እና እምነት በባህላዊ ህክምናው ዘርፍ ያለውን ተፅዕኖ መዳሰስ መቻሉ

ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ይሁን እንጂ የምህረት ጥናት ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ላይ ማተኮሩ የእኔ ጥናት ደግሞ የዕፅዋት ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ በተጨማሪም በምህረት ጥናት ውስጥ መንፈሳዊ ህክምና በአንድ ክፍል የተዳሰሰ መሆኑ፤ከእኔ ጥናት እንዲለይ አድርጎታል፡፡

መስፍን ፈቃዴ (2002) "የሀገረሰባዊ መድሀኒት ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ዋና ትኩረት በደብረ ማርቆስ ከተማና ዙሪያዋ የሚከናወነውን የሀገረሰባዊ መድሀኒት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል በመመርመር ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውን ገልጾ ማሳየት ነው፡፡ የሀገረሰብ መድሀኒቶች አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ከማህበረሰቡ እምነት እና ልማድ አንጻር ምን እንደሚመስሉ መመርመር፣ የባህል ሀኪሞቹ የህክምና እውቀት መነሻና ተስተላልፎ ማሳየት እንዲሁም የመድሀኒቶቹ የመቁረጫ ቀናት እና ቁሳቁሶች ትምዕርታዊ ፋይዳ መግለጽ የሚሉት ዝርዝር የትኩረት ነጥቦቹ ናቸው፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያዎች በኩል ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የጹሑፍ መጠይቅን፣ በፎቶ እና በመቅረጸ ድምጽ በመጠቀም ከአውራ እና አጋዥ መረጃ አቀባዮች አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ እና ተንታኝ የአጠናን ስልት ቀርበዋል፡፡ በጥናቱም በደብረ ማርቆስ አከባቢ ያሉ ባህላዊ ሀኪሞች የህክምና እውቀቱን ከሀይማኖት ተቋማት ማለትም ከቆሎ ትምህርት ቤት፣ ከአረብ ኢስላሚክ እና ከቤተሰብ እንደሚያገኙት ጠቁመዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ሀኪሞቹ ለመድሀኒትነት የሚያውሏቸው ግብዓቶች ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት እንደሚያገኙ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ መድሀኒቶች፤ በኦርቶዶክስ ሀይማኖት፤ረቡዕ እና አርብ (በጻጉሜ) ወር ቢቆረጡ ፈዋሽነታቸው አስተማማኝ እንደሚሆን፤በእስልምናው ሀይማኖት ደግሞ በየትኛውም ጊዜና ሰዓት ቢቆረጡና ቢዘጋጁ በመድሀኒቱ ላይ ምንም አይነት ለውጥ እንደማይኖረው አትተዋል፡፡

በጥናቱ እንደተገለጸው የሀገረሰባዊ መድሀኒት ተጠቃሚዎችም በባህላዊ ሀኪሞቹ በሚደረግላቸው የስነልቦና ድጋፍ፣ አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቁት ወጪ ዝቅተኛ በመሆኑና በመድሀኒቶቹ ፈውስ አገኛለሁ ብለው ማመናቸው ሀገረሰባዊ ህክምናውን ተመራጭ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡ ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ ከመድሀኒት ምጣኔ ጋር በተያያዘ በታካሚዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ምክንያት መሆኑን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ ባህላዊ ሀኪሞች ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር ተቀራርበው የሚሰሩበት ሁኔታ ቢመቻች የተሻለ እንደሚሆን በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡ በመስፍን ጥናት፤የጥናቱ ዋና አላማዎች፣ ዝርዝር አላማዎች እና

ትንታኔዎች ተሰናስነው የቀረቡ ቢሆንም በአጠናን ዘዴው የሚታዩ ክፍተቶች አሉ። ለአብነት ያህል ጥናቱ የተከተለውን የምርምር አይነት አይገልጽም፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴው ምን እንደሆነ እና አውራ እና አጋዥ መረጃ አቀባዮች በምን አይነት የናሙና ዘዴ ተመረጡ፤ የሚሉትን ጥያቄዎች አይመልስም።

የመስፍን ጥናት፤ከእኔ ጥናት ጋራ የሚመሳሰልበት የመጀመሪያው፤በትኩረት ነጥቡ ነው። ይኸውም በሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ቅመማና አጠቃቀም ላይ ትኩረት ማድረጉ እና እምነት በሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ያለውን ጫና ማሳየት መቻሉ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰልባቸው ነጥቦች ናቸው። ይሁን እንጂ የመስፍን ጥናት ከዕፀዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ መድሀኒቶችን መዳሰሱ፤የእኔ ጥናት ደግሞ ከዕፀዋት የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ተለይተው ጥናት የተደረገባቸው መሆኑ እንዲሁም የመስፍን ጥናት ከማህበረሰባዊና ከባህላዊ ጥበቡ ይልቅ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ላይ ማተኮሩ ከእኔ ጥናት ይለየዋል።

ተመስገን በየነ (2003) "በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፣ የመድሀኒት አሰጣጥ በግሼ ወረዳ" በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ዋና አላማ በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች የመድሀኒት ቅመማና አሰጣጥ ስልት ምን እንደሚመስሉ ከልምድ፣ ከእምነት እና ከባህል አኳያ መመርመር ሲሆን የሀገረሰብ ህክምና ጥበብ መተላለፊያ መንገዶችን ማሳወቅ፣ በሀገረሰብ ህክምና ለመድሀኒት አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን መለየት እና ለግብዓቶቹ መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ቀናት ትዕምርታዊ ፋይዳ መግለጽ የሚሉ ተጨማሪ ነጥቦችን ተመልክተዋል። በመረጃ ስብሰባ ወቅትም በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በቡድን ተኮር ውይይት ከአውራ እና አጋዥ መረጃ አቀባዮች ከባህላዊ ሀኪሞች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከዘመናዊ ሀኪሞች እና ከባህላዊ ታካሚዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስበዋል። ጥናቱ በተካሄደበት ግሼ ወረዳ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በእይታዊ፣ ክሊኒካዊ፣ ባሎጂካዊ እና በመጠየቅ እንዲሁም ማህበራዊ ሁኔታቸውን በማጤን በሽታዎችን እንደሚለዩ አመላክተዋል። ሀገረሰባዊ ሀኪሞቹ ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በአብዛኛው ዕፅዋት ሲሆኑ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶችም ተጨማሪ እንደሆኑ ገልጸዋል።

በግሼ ወረዳ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ከእምነት ተቋም የወጡ መሆናቸውን እና ለታካሚዎችም በዝቅተኛ ወጪ አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ድጋፍ ማድረጋቸው የህክምና አገልግሎቱን ተመራጭ እንዲሆን አድርጎታል። ይሁን አንጂ የባህል ህክምናው ከመጠን እና ተያያዥ ችግሮች የተነሳ በታካሚዎች ላይ ጉዳት እንደሚደርስ አመላክተዋል። በመጨረሻም

ባህላዊ ህክምናውን አስተማማኝ ለማድረግ ዘመናዊ ሀኪሞች እና ባህላዊ ሀኪሞች ተቀራርበው ቢወያዩ እና በአብሮነት ቢሰሩ የተሻለ እንደሚሆን ጠቁመው አልፈዋል፡፡ የተመስገን ጥናት እስካሁን ከቀረቡት ጥናቶች ለየት የሚያደርገው እና እንደ ጠንካራ ጎን ሊወሰድ የሚገባው የባህል ሀኪሞችን የምርመራ ዘዴ እና አተገባበር ሳይንስ ከደረሰበት የምርመራ ዘዴ ጋር በማያያዝ ለመጠቆም መሞከሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለጥናቱ ማስኬጃነት የተጠቀማቸውን ጽንሰ ሃሳባዊ ብያኔዎች በንድፈ ሀሳብነት ማቅረቡ የጥናቱን ክፍተት የሚያሳይ ነው፡፡

የተመስገን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ትኩረት ማድረጉ ነው፡፡ ነገር ግን በተመስገን ጥናት ውስጥ ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የክርስትናውን ሀይማኖት ይልቁንም በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ላይ ያተከረ መሆኑ፤የእኔ ጥናት ደግሞ ከዕፅዋት የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ማተኮሩ እና በእስልምናውም ሆነ በክርስትናው ያሉ የባህል ሀኪሞችና ታካሚዎች የጥናቱ ታላሚዎች መሆናቸው፤ከተመስገን ጥናት የሚለይበት መሰረታዊ ነጥብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተመስገን ጥናቱን ያካሄደበት አካባቢ የአየር ጸባይ ደጋማ ሲሆን የእኔ ጥናት የሚካሄደው ቆላማ በሆነችው ሸዋሮቢት ከተማ እና ዙሪያዋ ላይ መሆኑ ሌላው ለጥናቱ ልዩነት ማሳያ ነው፡፡

ደነቁ አበረ (2003) "የሀገረሰባዊ መድሀኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ በወላይታ ሶዶና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ትኩረት በወላይታ ከተማና አካባቢዋ የሚከናወነውን የሀገረሰባዊ መድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በመመርመር ሀገረሰባዊ ልማዱን ገልጾ ማሳየት ሲሆን በጥናቱም የመድኃኒቶቹ አዘገጃጀትና የአሰጣጥ ሂደት ምን ይመስላል? በአካባቢው የሚገኙ መድኃኒቶች ከምን ከምን ይቀመማሉ? እንዲሁም በአካባቢው የሚገኙ የባህላዊ መድኃኒት ሀኪሞች እምነት እና አመለካከት ምንድነው? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች በማንሳት ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

አጥኝው ጥናቱ ይዟቸው የተነሳቸውን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ በመሆኑም በወላይታ ሶዶ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች መድሀኒቶቹን የሚቀምሙባቸው ቀናት ረቡዕ፣ አርብ እና እሁድ መሆናቸውን በመግለጽ ያላቸውን ትዕምርታዊ ፋይዳ ከማህበረሰቡ ልምድና እምነት ጋር አያይዘው ገልጸዋል፡፡ ባህላዊ ሀኪሞቹም ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በአብዛኛው ከዕፅዋት የሚገኙ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የሚገኙ ባህላዊ ሀኪሞች የህክምና

እውቀቱን ያገኙት ከቤተሰብ ከአባት፣ ከአያት፣ ከቅርብና ከእሩቅ ዘመዶች እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለህክምና በሄዱባቸው ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በሚሰሟቸው መረጃዎች እንደሆነ አትተዋል፡፡ በመጨረሻም በሀገረሰባዊ ሀኪሞች እና መድሀኒቶች ላይ ከመንግስት አካላት በኩል የሚታይ ክፍተት መኖሩን ጠቁመው ባህልና ቱሪዝም እንዲሁ የቅርስ ጥበቃ ማህበር ትኩረት ሰጥቶ ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር በማቀራረብ ቃላዊ የሆነውን የህክምና ጥበብ በምስልና በድምጽ ተመዝግበው ቢቀመጡ የተሻለ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

በደነቁ ጥናት ግልጽ እና ተገቢ የሆኑ አብይ እና ዝርዝር አላማዎች እንዲሁም የምርምር ጥያቄዎችን በማቅረብ ጥናቱን የተሳካ በማድረግ የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩም በጥናቱ ሂደት የአደረጃጀት፣ የትንታኔ አካሄድ እና ሌሎች ሰዋሰው ችግሮች (የፊደላት፣የቃላት፣አ/ነገር) ግድፈቶች መጉላት የጥናቱን ክፍተት የሚያሳይ ነው፡፡

የደነቁ ጥናት የትኩረት ነጥብ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ላይ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም በእኔ ጥናት ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት ዋና ትኩረት መሆኑ፣ የደነቁ ጥናት ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ ትኩረት ማድረጉ፣ እንዲሁም ሀገረሰባዊ ሀኪሞች እና መድሀኒቶች ከእምነት ጋራ ያላቸው ቁርኝት አለመዳሰሱ፤ከእኔ ጥናት የሚለዩት ነጥቦች ናቸው፡፡ በእኔ ጥናት ውስጥ እንደ እምነት ስርዓቱ ሀገረሰባዊ ሀኪሞቹ ምን ያደርጋሉ፣ መድሀኒቶቹ ከሚሰበሰቡባቸው ሰዓትና ቀናት አንጻር ያላቸው ትዕምርት ምንድነው የሚሉት ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡

ትዕግስት ምህረት (2008) "ሀገረሰባዊ የእንስሳት በሽታ መለያ ዘዴዎች የመድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በይልማ ዴንሳ ወረዳ" በሚል ርዕስ ያቀረበችው ጥናት ዋና አላማ በምዕራብ ጎጃም ዞን በይልማ እና ዴንሳ ወረዳ የሚከናወን ሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡ ሀገረሰባዊ የእንስሳት በሽታ መለያ ዘዴዎችን መግለጽ፣ ለሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት ቅመማ የሚውሉ ዕፅዋቶችን አሰባሰብ ስርዓት መግለጽ፣ የመድሀኒቶቹን ቅመማና አሰጣጥ ሂደቶች መለየት እንዲሁም ሀገረሰባዊ የእንስሳት ህክምና ባለሙያዎች እውቀት ለመዳና ተስተላልፎ መቃኘት የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በምልከታና በቃለመጠይቅ፤ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ በማስታወሻ እና በፎቶግራፍ ተሰብስበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ በምዕራብ ጎጃም ዞን በይልማና ዴንሳ ወረዳ የሚገኙ ሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት

ባለሙያዎች በክሊኒካዊና ስነ ህይወታዊ የመለያ ዘዴዎች እንደሚለዩ፤በአብዛኛው እይታዊ በሽታን የመለያ ዘዴ እንደሚጠቀሙ ተጠቁሟል፡፡ ለሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት መቀመሚያ የሚውሉ ግብዓቶችም ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ መሆናቸው ተገልጧል፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ከጳጉሜ አንድ እስከ ህዳር አስራ ሁለት ወር የሚመረጡ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ የእነዚህ ወራት መመረጥ ምክንያትም ጳጉሜ አምስት እና ስድስት ቀኖች መንግስተ ሰማያት ተከፍታ ስለምትውል እና ዕፅዋት፤በእነዚህ ወራት በብዛት የሚገኙበትና የሚበቅሉበት በመሆኑ የሚፈልጉት የዕፅዋት ክፍል ሳይጓደል ማግኘት ስለሚቻል እንደሆነ ተገልጧል፡፡ በይልማ ዴንሳ ወረዳ የሚገኙ ሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት ባለሙያዎች ጥበቡን የሚቀስሙት ከአብነት ትምህርት ቤት ጋር እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመጨረሻም የወረዳው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት ባለሙያዎች ጋር ውይይት ቢያደርግ እና እውቅና ቢሰጣቸው፣ ዘመናዊ የእንስሳት ህክምና ባለሙያዎች ከሀገረሰባዊ የእንስሳት መድሀኒት ባለሙያዎች ጋር ተቀራርበው የሚሰሩበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም መሆኑን ጠቁመው አልፈዋል፡፡

የትግዕስት ጥናት ጠንካራ ጎን አላማዎቹን እና የምርምር ጥያቄዎቹን ግልፅ አድርጎ ከመነሳት እና ጥናቱን ከግብ በማድረስ ተገቢ እና አስፈላጊ የሆኑ መረጃ መሰበሰቢያ መሳሪያዎችን ተግባራዊ መደረጉ፣ በጽንሰ ሃሳብ እና ንድፈ ሃሳብ አደረጃጀት እና አቀራረብ እንዲሁም አጠቃቀመ ሂደት፤ጠንካራ እና የተደራጀ ትንተና በማቅረብ፤በአጠቃላይ በይልማና ዴንሳ ወረዳ የሚከናወነውን ሀገረሰባዊ የእንስሳት ህክምና እውቀት በማሳየት፤አዲስ የጥናት አቅጣጫ ይዞ በመምጣት ረገድ የሚታይ ጠንካራ ጎን ቢኖርም መረጃ አቀባዮች የተመረጡበት የናሙና አመራረጥ ስልት አለመግለጽ፤እንዴት፣ ለምን አላማ ተመረጡ የሚለውን ጥያቄ አለመመለሱ የጥናቱን ክፍተት የሚያሳይ ነው፡፡

የትዕግስት ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለታችንም ጥናት የምናደርግበት ርዕሰ ጉዳይ ሀገረሰባዊ መድሀኒት መሆኑ ሲሆን፤የትዕግስት ጥናት ትኩረት ሀገረሰባዊ የእንስሳት ህክምና ሲሆን የእኔ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው ለሰው የሚዘጋጁ ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች ላይ መሆኑ ከእኔ ጥናት በእጅጉ ይለየዋል፡፡

ፍቅርተ ማቴዎስ (2009) "ከዕፀዋት የሚገኙ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ዕውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በከምባታ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ዋና አላማ የከምባታ ብሔረሰብ የሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ዕውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በመመርመር ባህላዊ ልማዱን ገልጾ

ማሳየት ነው። በከንባታ ማህበረሰብ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች የህክምና ዕውቀት መፈተሽ፣ የሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን ምስጢራዊነት መለየት፣ አዘገጃጀት እና አቀማመም ስርዓቱን መመርመር እንዲሁም ትዕምርቶችን መተርጎም የሚሉትም የጥናቱ ትኩረቶች ናቸው። አጥኝዋ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ እና በጽሞናዊ ምልከታ ከተለያዩ አካላት ሰብስበዋል።

በከንባታ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በሽታን በእይታ፣ በመነካካት እና የታካሚውን የህመም ሁኔታ በመጠየቅ የበሽታውን አይነት መለየት እንደሚችሉ በጥናቱ ተጠቁሟል። ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እንደሚበቅሉበት ቦታና እንደባለሙያዎቹ ዕውቀት ለዕፆቹ መገኛ ያላቸው አመለካከት የተለያየ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም በከንባታ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸውን ዕፆች ከወንዝ ዳር፣ ከተራራ እና አካባቢውን በመዘዋወር እንደሚያዘጋጁ ተገልጧል። ዕፆቹ ከተገኙ በኋላም እንደበሽታው አይነትና እንደ ባለሙያዎቹ ዕውቀት ከዕፅዋት ቀንበጥ፣ ከአበባው፣ ከግንዱ፣ ከቅርፊት እንዲሁም ከስሩ ሊቀምሙ እንደሚችሉ ተጠቁሟል።

በሌላ በኩል የአካባቢው ማህበረሰብ ቀናቶችን እርጥብ እና ደረቅ ቀናት በሚል እንደሚከፍላቸው አስረድተዋል። ረቡዕ፣ አርብና እሁድ እርጥብ ቀናት ሲባሉ ሀሙስ፣ ማክሰኞ እና ቅዳሜ ደግሞ ደረቅ ቀናት በሚል እንደሚታወቁ ተገልጧል። በመሆኑም በደረቅ ቀናት የሚሰበሰቡ መድሀኒቶች አይሰምሩም ተብሎ ስለሚታመንባቸው በእርጥብ ቀናት ተሰብስበው እንደሚዘጋጁ ተጠቁሟል። ባጠቃላይ በከምባታ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ባህላዊ ሀኪሞች በብዛት ዕፅዋትን ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ ተጠቁሟል።

በመጨረሻም በሀገረሰባዊ ሀኪሞች እና በዘመናዊ ሀኪሞች መካከል ያለው አመለካከት ልዩነት ለመቀየር እና በጋራ ተቀራርበው መነጋገር እንዲችሉ የተሻለ ስራ በመስራት ማህበረሰቡን ማገልገል ቢችሉ፣ የሚመለከተው አካል በከምባታ ብሄረሰብ የሚገኙ የሀገረሰባዊ ሀኪሞችን ስልጠና በመስጠት የህክምና አገልግሎቱን የተሻለ ከማድረጉም በላይ በመድሀኒት ምጣኔ እና አጠቃቀም ችግር ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ ቢቻል፣ ቃላዊ የሆነውን የህክምና እውቀት በምስል፣ በድምጽ እና በፎቶግራፍ የተደገፈ ማስረጃ በማጠናቀር እንዲቀመጡ ቢደረግ የተሻለ እንደሚሆን በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል።

ይህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ፣ በናሙና አመራረጥ ስልት፣ በትንታኔ እና በአደረጃጀት የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩም ንድፈ ሃሳብን በትንታኔ ውስጥ በማሳየት ረገድ ክፍተት ይታያል፡፡ ለአብነት ያህል በምዕራፍ ሁለት ላይ የቀረበው Medical Ecology Theory በጥናቱ ጥቅም ላይ እንደሚውል የተገለጸ ቢሆንም በትንታኔው ውስጥ ንድፈ ሃሳቡ ያበረከተው አስተዋፅዖ ጎልቶ አይታይም፡፡

የፍቅርተ ጥናት በከንባታ ማህበረሰብ ላይ ያተኮረ ሲሆን የእኔ ጥናት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ ላይ ያተኮረ መሆኑ፤የጥናት አካባቢ ምርጫ የእኔን ጥናት ከፍቅርተ ጥናት ይለየዋል፡፡ ሆኖም የሁለታችንም የጥናት ትኩረት ሀገር በቀል ህክምና ላይ መሆኑ በተለይ የሁለታችንም ጥናት ከዕፅዋት የሚዘጋጁ መድሀኒቶች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ የእኔ ጥናት ከፍቅርተ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነው፡፡

ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ የተካሄዱ የሀገረሰባዊ ህክምና ጥናቶች ትኩረትና ይዘት እንደየሙያ መስካቸው፤የጥናታቸው ርዕስ ጉዳይና ጭብጥ የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡[3]

### 2.3.2. በስነ-ሰብዕ ትምህርት ክፍል በሀገር ውስጥ እና በውጪ የተካሄዱ ጥናታዊ ጽሑፎች

Young Allan (1970) “Medical Beliefs and practices of Begamder Amhara” በሚል ርዕስ ሎሳንጀለስ ፔንሰልቪያ ዩኒቨርሲቲ በአንትሮፓዎሎጂ ትምህርት ክፍል ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ሲሆን የጥናቱ ትኩረት የአማራውን ብሔረሰብ፤በይበልጥም የጎንደርን ባህላዊ መድሀኒት በመመርመር ማህበረሰቡ በባህላዊ መንገድ እና በአምልኮታዊ ስርዓት አማካኝነት ተፈጥሯዊና መለኮታዊ በሽታዎችን እንዴት እንደሚከላከሉ፣ የበሽታዎቹን መንስኤዎች፣ የባህል ሀኪሞች እና የህክምናቸውን አከዋወን ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የጎንደር ማህበረሰብን  የባህል ሀኪሞች አለማዊ እና መንፈሳዊ ሀኪሞች በሚል ምድብ ከፍለዋል፡፡ አለማዊ ሀኪሞች፤የዕፅ መድሀኒት አዋቂዎች ወጌሻዎች፣ አዋላጆች፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ወይም አምልኮታዊ የሚባሉት አስማተኞች፣ ደብተራዎች፣ ጠንቋዮች እና ሼኮች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም በመንፈሳዊ የህክምና ባለሙያዎች ስር የተዘረዘሩት የአውቀት ምንጫቸው አልያም ሀይማኖታዊ ሽፋናቸውን ብቻ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት

---

3 በዚህ ጥናት ዳሰሳ የተደረገባቸው የሁለተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሑፎች፤አሁን የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ት/ክፍል የሚል መጠሪያ የያዘው፤በቀድሞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ት/ክፍል የተሰሩ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

የተመደቡ እንጂ ያላቸው እውቀት፤መንፈሳዊ፣ አለማዊ ወይንስ ቅልቅል? የሚለው ጥያቄ በሚገባ የተፈተሸ አለመሆኑ የጥናቱን ክፍትት የሚያሳይ ነው። ይሁን እንጂ የቤጌምድር (የጎንደር) ማህበረሰብ አለማዊ እና መንፈሳዊ ስርዓት እና ልማድ ያላቸው የባህል ህክምና ጥበብን በማስተዋወቅ እና የባህል ህክምና ምድብ ማሳየት መቻላቸው ለመስኩ ቀላል የማይባል አስተዋጽዖ አበርክተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ ስለባህላዊ መድሀኒቶች ያለው አመለካከትና እምነት ምን እንደሆነ ዳሰሳ አድርገዋል።[4]

Mirgissa Kaba (1993) "Indigenous Medicical Beliefs and Practices among the Illubabor oromo" በሚል ርዕስ ለአንትሮፓሎጂ ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታዊ ፁሁፍ ዋና አላማ በኢሉባቡር የሚከናወነውን ሀገረሰባዊ ህክምና ከማህበረሰቡ እምነት አንጻር መፈተሽ ነው። ይህ ጥናት በአይነታዊ እና በመጠናዊ የአጠናን ዘዴ፤ከባህል ህክምና ባለሙያዎች፣ ከባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች እንዲሁም በአካባቢው ካሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች በመደበኛ እና ኢ መደበኛ ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በጽሑፍ መጠይቅ አስፈላጊ መረጃዎችን የሰበሰቡ ሲሆን የመድሀኒት አቀማመም እና አሰጣጥ ስርዓቱን በተመለከተ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም በሰነድ ፍተሻ መረጃዎችን አሟልተዋል። በመሆኑም በጥናቱ መሰረት በአካባቢው ያሉ የሀገረሰባዊ ህክምና ባለሙያዎች ስለሚፈውሷቸው በሽታዎች መንስኤ እና ስለ መድሀኒቶች አቀማመም እና አሰጣጥ ያላቸው እውቀት ተመሳሳይ መሆኑን ተገልጧል። በዚህ መሰረት ለሀገረሰባዊ መድሀኒት ግብዓት ሆነው የሚያገለግሉት ከዕፅዋት፣ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶች እንደሆኑ ያስረዳል። ከዚህ ጋር ተያይዞም የሀገረሰባዊ ህክምና ባለሙያዎች መንፈሳዊ እና አለማዊ በመባል በሁለት ይከፈላሉ። በመለኮታዊ ሀይል በመታገዝ ህመምተኞችን ለመፈወስ ጫት በመቃም፣ ዱዓ (Duai) በማድረግ እና በጸሎት በሽተኞችን እንደሚፈውሱ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል አለማዊ የሀገረሰባዊ መድሀኒት ባለሙያዎች ከአካባቢያቸው በሚያገኟቸው ዕፅዋት፣ እንስሳት እና ማዕድናትን በመጠቀም ለታማሚዎች ፈውስ እንደሚሰጡ ያስረዳሉ። በአጠቃላይ አለማዊም ሆኑ መንፈሳዊ መድሀኒተኞች ይህንን እውቀት የሚያገኙት ራቢ (Rabby) ከሚባል ሀገረሰባዊ የእምነት ስርዓት መሆኑን ያሰረዳሉ። የMirgissa ጥናት ከሌሎች በመስኩ ከተደረጉ ጥናቶች የሚለየው በእስልምናው እምነት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ፣ እምነታዊ እና ልማዳዊ ክንውኖች ላይ ትኩረት አድርጎ የተጠና መሆኑ ነው። የሚርጊሳን ጥናት ከእኔ ጥናት የሚያመሳስለው፤አለማዊ ህክምና ተብሎ

[4] በአንትሮፓሎጂ ት/ክፍል ከተጠኑ ጥናታዊ ጽሑፎች መካከል በ Young Allan የቀረበው ጥናት፤ የአጠናን ስነ ዘዴው ያልተገለጸ በመሆኑ በዚህ ጥናት ቅኝት፤ የጥናቱ የአጠናን ዘዴ አልቀረበም።

በተከፈለው የህክምና አይነት ውስጥ ዕፅዋትን በግብዓትነት ተጠቅመው መድሀኒት የሚያዘጋጁ መሆኑ በተወሰነ ደረጃ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም በተለየ መንፈሳዊ ሀይል አጋዥነት መድሀኒቶችን የሚያዘጋጁ መሆናቸው ከእኔ ጥናት ይለየዋል፡፡

Abraraw Tesefay (1998) “Traditional medicine in an Urban Center Belief and practices (the case of Dessie town northen Ethiopia” በሚል ርዕስ ለአንትፓሎጂ ት/ክፍል ለኤም.ኤ ዲግሪ ያቀረቡት ጥናት ትከረት የደሴ አካባቢ ማህበረሰብ የጤና ችግሮች ሲያጋጥሙት የሚወስዳቸው መፍትሔዎች እና ለሀገረሰባዊ ሀኪሞች ያላቸውን አመለካከት ለይቶ ማሳየት ነው፡፡ የባህል ሀኪሞች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና፣ ህመምተኞችን የሚፈወሱበትን ዘዴ መለየት ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ለዘመናዊው ህክምና ያለውን ፋይዳ መግለጽ ተጨማሪ ትኩረቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በአይነታዊ እና በመጠናዊ የአጠናን ስልት፤ከባህል ህክምና ባለሙያዎች፣ ከባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች፣ ከዘመናዊ ሀኪሞች እና ከአካባቢው ነዋሪዎች በመደበኛ እና ኢ መደበኛ ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በጹሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባህል ህክምና ባለሙያዎቹን የመድሀኒት አቀማመም እና አሰጣጥ ሂደቱን ምልከታ በማድረግ የመስክ መረጃ ስብሰባ ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም በሰነድ ፍተሻ ተጨማሪ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ዘመናዊ ህክምና በሚሰጥባቸው የከተማ አካባቢዎችም በስፋት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ ያለውን የማህበረሰብ ክፍል የአገልግሎት ሽፋን አንደሚሰጡ ተመልክቷል፡፡ ባህላዊ ህክምናው ከዘመናዊ ህክምናው ይልቅ ተመራጭ እንዲሆን ያደረጉት የታካሚዎችን የኢኮኖሚ አቅም ያገናዘበ መሆኑ፣ መንፈሳዊ፣ መለኮታዊ እና አለማዊ ህክምናውን በአንድነት የያዘ መሆኑ፤በባህል ሀኪሞች እና በመለኮታዊ ሀይል ተዓምር እድናለሁ የሚል እምነት ማሳደር መቻሉ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባህላዊ ህክምናው ከመለኮታዊ ሀይል ጋር የተያያዘ መሆኑ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም በዘመናዊው ህክምና መፍትሄ ያልተገኘላቸው በሽታዎች (ስኳር፣ሳንባ ምች፣ጨብጥ፣ችፌ) እና ሌሎችም በባህላዊ ህክምናው የሚፈወሱ መሆናቸውን አመላክቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ ባህላዊ የህክምና አገልግሎቱ ከፍተኛ ሽፋን ያለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአብራራው ጥናት ሀገረሰባዊ የዕፅ መድሀኒት ህክምና ላይ የተደረገ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው መሰረታዊ ነጥብ ነው፡፡ ይህ ጥናት የደሴ አካባቢ ማህበረሰብን የህክምና

አውቀት ማሳየቱ፣ የማህበረሰቡን የባህል ህክምና ልማድ እና አመለካከት መፈተሽ መቻሉ፤ከእኔ ጥናትም ሆነ ከሌሎች ጥናቶች የሚለይበት ነው፡፡

### 2.3.3. በሥነ ህብረተሰብ (Sociology) ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት

Yared Paulos (2004) “Beliefs and Practices of Traditional Medicine among Women in Reproductive Health care; A study in Damot Woreda,Wolayta Zone” በሚል ርዕስ ለሶሲዎሎጂ ት/ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት በሴቶች በስነ ተዋልዶ ጤና ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜ እና ከወሊድ በኂላ ያለውን የሀገረሰባዊ መድሀኒት አጠቃቀም በሚመለከት ሰፋ ያለ ጥናት አድርገዋል፡፡ ይህ ጥናት አይነታዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ሲሆን በዞኑ ካሉ ሀያ ሁለት (22) ቀበሌዎች ውስጥ ስድስት (6) ቀበሌዎችን በመምረጥ፤ሰላሳ አራት (34) ያገቡ፣ ሰላሳ (30) ያላገቡ ሴቶችን እንዲሁም አስራ ስድስት (16) የባህል መድሀኒት ቀማሚዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ጥናቱን አካሂደዋል፡፡ በዚህ መሰረት ሴቶች፤በሶስቱም ደረጃዎች ማለትም በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜ እና በድህረ ወሊድ ጊዜ የሚገጥማቸውን የጤና ችግር ለመከላከል ሀገረሰባዊ መድሀኒት በስፋት አገልግሎት ላይ እንደሚያውሉት ይገልጻሉ፡፡ በጥናቱም በወላይታ ማህበረሰብ በቅድመ ወሊድ እንክብካቤ እና በወሊድ ጊዜ የአባላዘር በሽታን ለመከላከል ሀገረሰባዊ ህክምናው በስፋት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች የድህረ ወሊዲ እና የወሊድ ቁጥጥር አገልግሎት ለማግኘት መዋላቸው ጠቃሚ አለመሆኑንም በጥናታቸው አስረድተዋል፡፡ ባጠቃላይ ጥናቱ በተደረገበት ወላይታ ዞን የሀገረሰባዊ መድሀኒት እውቀት በቃል የሚገኝ እንጂ ከመለኮታዊ ሀይል የሚሰጥ አለመሆኑን ጭምር ገልጸዋል፡፡

ይህ ጥናት በሲሶሎጂ ትምህርት ክፍል የተጠና ጥናት በመሆኑ ከሀገር በቀል እውቀቱ ይልቅ ማህበረሰባዊ ግንባታው ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጥናቱ አካሄድ በመስኩ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ሀገር በቀል አውቀቱን፣ ጥበቡን እና ተስተላልፎን በትኩረት እንዳይመለከት፣ ከማህበረሰቡ ጥበብ፣ አውቀት እና ግንዛቤ ይልቅ፣ የማህበረሰብ መዋቅር (Social Structure) ላይ እንዲያዘነብል በማድረግ ሀገረሰባዊ የመድሀኒት እውቀት ጥናት ላይ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የያሬድ ጥናት መስኩ በሚፈልገው አካሄድ መሰረት የተቃኘ፤በማህበረሰብ ጥናት ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ሀገረሰባዊ የመድሀኒት አዘገጃጀት እና አጠቃቀም በስፋት አለመዳሰሱ፤ከፎክሎር የጥናት መስክ አንጻር ክፍተት ይታይበታል፡፡

ይሁን እንጂ በተወሰነ መልኩም ቢሆንም ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች በሴቶች ስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ላይ ያላቸውን ድርሻ መመርመር ላይ ማተኮሩ እስካሁን ዳሰሳ ከተደረገባቸው ጥናቶች እና ከእኔ ጥናት ትኩረት የተለየ ያደርገዋል፡፡

### 2.3.4. በሀገር ውስጥ እና በውጪ ምሁራን፤በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም እንዲሁም በተለያዩ የጥናት መድረኮች ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጹሑፎች

Elsabeth Dorothea (1976) “Traditional Medicine and Magic among the Amhara of Ethiopia” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ትኩረት በአማራው ማህበረሰብ ላይ ሲሆን ጥናቱም በተጠኘው አካባቢ የሚገኙ የህመም መንስኤዎችን፤በወቅቶች መፈራረቅ የሚመጡ አስከፊ በሽታዎች እና በመናፍስት ማለትም በእርኩስ መንፈስ (በሰይጣን) አማካኝነት የሚመጡ በሽታዎች በሚል በሁለት ወገን በመክፈል ተመልክተውታል፡፡ በጥናቱ ሂደትም ከተጠኘው ማህበረሰብ፤ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች፤በቃለ መጠይቅ፣ በጹሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰቱ በሽታዎች፤የሰውን ልጅ ለመቅጣት በአምላክ ቁጣ የሚመጡ መሆናቸውን በጥናቱ አመላክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ከእርኩሳን መናፍስት የሚመጡ ዛር፣ ጥላወጊ፣ አይነጥላ እንዲሁም በሰዎች ላይ እርኩሳን መናፍስት በመስፈር ጤንነትን የሚያናጉ በሽታዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ በሰይጣን ልክፍት የሚመጡ የጤና ችግሮች በመለኮታዊ ሀይል ማለትም በፀበል፣ በፀሎት እና በእምነት የሚፈወሱ መሆናቸውን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የተነሳው መለኮታዊ የሆነው የህመም መንስኤ እና መለኮታዊ ፈውስን (መንፈሳዊ ህክምና) ላይ መሆኑ፤በቄሶች እና በሀይማኖት አባቶች መሪነት በሚደረግ ፀሎት፣ ምልጃና ልመና የሚዳኑ በሽታዎች ላይ ያተኮረ መሆኑ ከእኔ ጥናት ይለየዋል፡፡

ሌላው Alemayehu Moges (1984) “Traditional Ethiopian Medicine” በሚል ርዕስ ለ8ኛው አለም አቀፍ የኢትዮጲያ ጥናት ኮንፍረንስ ያቀረቡት ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት የኢትዮጵያን ባህላዊ መድሀኒቶችን ማጥናት ሲሆን የባህላዊ መድሀኒቶችን እውቀት ፈላጊ ማነው? አስተማሪውስ ማን ነው? ምን ያስተምራሉ? እንዴትና መቼ ይማራሉ? በሽታዎቹስ ምን ምን ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሞከረ ጥናት ነው፡፡ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች (በቃለ መጠይቅ፣በጹሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ) እንዲሁም የተለያዩ መንፈሳዊ መጽሀፍትን በማገላበጥ መረጃዎቹን አደራጅተዋል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናታቸው መደምደሚያ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ካህናት፣

መምህራን እና ዲያቆናት እንዲሁም መሪጌቶች የባህላዊ መድሀኒት እውቀትን ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እንደሚማሩ ያስረዳሉ። በመሆኑም ይህንን እውቀት ለማግኘት እንስሳትን፣ ዕፅዋትን እና ማዕድናትን ከቤተ ክርስቲያን አስተምሮዎች ጋር አስተሳስሮ በትኩረት ማጤን እንደሚገባ ገልጸዋል። ይህ ጥናት ከርዕሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ብሔራዊ ጥናት ቢሆንም በጥናቱ ሙሉ ሀገሪቱን ለማዳረስ አስቸጋሪ በመሆኑ የአንድ ወገን ጥናት እንዲሆን አድርጎታል። ከዚህ አንጻር ጥናቱ፤ትኩረት እና ገደቡን ወስኖ መነሳት አለመቻሉ የጥናቱን ደካማ ጎን የሚያሳይ ነው። የአለማየሁ ጥናት በአብዛኛው የሀገረሰባዊ መድሀኒት ታሪካዊ ገፅታውን መመርመር ላይ ያተኮረ ቢሆንም ከዕፅዋት የሚዘጋጁ መድሀኒቶችን መፈተሽ መቻሉ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል።

Fekadu Fulas (2001) “The Role of Indigineous Medical Plants in Ethipian Health care” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት አብይ ትኩረት የሀገረሰባዊ መድሀኒት አጠቃቀም ያለውን ስርዓት እና ህግ፣ ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። ጥናቱ በመጠናዊ እና በአይነታዊ (ቅልቅል) የአጠናን ዘዴን በመከተል ተካሂዷል። በመሆኑም በሀገራችን ኢትዮጵያ ባህላዊ መድሀኒቶች በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ጥቅም ላይ እንደሚውል እና እነዚህም በአብዛኛው ከዕፅዋት በሚገኙ ግብዓቶች የሚዘጋጁ መሆናቸውን በጥናታቸው ማረጋገጥ መቻላቸው፤በጥናቱ የታየ ጠንካራ ጎን ነው።

Getachew Addis (2002) “perceptions and practices of Modern and Traditional Health practitioners about traditional medicne in Shirka district,Arsi zone Ethiopia” በሚል ርዕስ ያቀረቡት የጥናት ወረቀት ዋና አላማ የዘመናዊ እና የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ስለ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በጥናቱም፤ክፍት እና ዝግ የጹሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅተው ፈቃደኛ ለሆኑ መረጃ አቀባዮች የቀረቡ ሲሆን ከአርባ (40) ዘመናዊ ሀኪሞች እና ከሰማንያ (80) ባህላዊ ሀኪሞች ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። በዚህ መሰረት ጥናቱ፤ቢያንስ በአንድ አጋጣሚ ዘመናዊ ሀኪሞችም ይሁኑ ባህላዊ ሀኪሞች ሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ገልጸዋል። ይህ ሀገረሰባዊ እውቀት ቃላዊ በመሆኑ በሙያው እውቀት የሌላቸው ሀሰተኛ ባለሙያዎች እንዲፈጠሩ መንገድ በመክፈት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲስፋፉ እድል ይፈጥራል። በመሆኑም ይህ ቃላዊ የህክምና ጥበብ ትኩረት ተሰጥቶት በጹሑፍ ተሰንዶ ቢቀመጥ የተሻለ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

የጌታቸው ጥናት የዘመናዊ እና የሀገረሰባዊ ህክምና ባለሙያዎች ጥናት ላይ መገደቡ ከእኔ ጥናት የሚለይበት መሰረታዊ ነጥብ ነው፡፡ የእኔ ጥናት የሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት እውቀት፣ አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ሂደት፣ የበሽታ መለያ ዘዴዎች፣ የሀገረሰብ ህክምና እውቀት ተስተላልፎ፣ ዘመናዊ ሀኪሞች ለባህላዊ ሀኪሞች ያላቸው አመለካከት የሚሉት እና ሌሎች ንዑሳን ርዕሶች የተመለከተ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

Abraham,Andargie,and Berhanu (2013) “Community knowledge, attitude and practice about malaria in a low endemic setting of Shewa Robit Town, northeastern Ethiopia” በሚል ርዕስ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አጋዥነት የቀረበው ጥናት ዋና አላማ የሸዋሮቢት ከተማ ማህበረሰብ ስለ ወባ በሽታ ያላቸውን እውቀት፣ አመለካከት እና ልምድ መገምገም ሲሆን በሸዋሮቢት ከተማ ከሚገኙ ዘጠኝ ቀበሌዎች ውስጥ አራቱ(4) ተመርጠዋል፡፡ ከአራቱ ቀበሌዎች ውስጥ ዘጠና አምስት አባዎራዎች (95) እና በአካባቢው የሚገኙ ሁለት ነርሶች (2) ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ እድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ስልት በመጠቀም አራት መቶ ሀያ አምስት (425) የሚሆኑ ግለሰቦች የደም ምርመራ ሲደረግላቸው ሁለት መቶ ሰማንያ አራት (284) ግለሰቦች ደግሞ ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል፡፡

በዚህ መሰረት ለወባ በሽታ መንስኤ በዋናነት የቢንብ ትንኝ ስትሆን፤ረሀብ፣ የአየር ጸባይ ለውጥ እና የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ተጨማሪ ለበሽታው መያዝ መንስኤ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል ከተወሰኑት የመረጃ ምንጮች እንደተገኘው መረጃ፤ወባ ከሰው ወደ ሰው እንደሚተላለፍ ተረጋግጧል፡፡ የወባ በሽታ ምልክቶችም ብርድ ብርድ ማለት፣ ትኩሳት እና የምግብ ፍላጎት መቀነስ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ በሽታውንም ለመከላከል፤ ምግብ በተገቢው መንገድ መመገብ፣ የግል እና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ፣ መኖሪያ ቤትን እና አካባቢን በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስረጨት በሽታን ለመከላከል እንደሚያግዝ ተደርሶበታል፡፡ በመጨረሻም የአካባቢው ማህበረሰብ ስለ ወባ በሽታ መንስኤ፣ ስርጭት እና የመከላከያ ዘዴዎች ያለው እውቀት ከፍ ያለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ስለ ወባ በሽታና ስርጭት ይበልጥ ግንዛቤን ለማሳደግ ለከተማው ነዋሪዎች ተጨማሪ የጤና ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ለጥናት የተመረጠው አካባቢ (ሸዋሮቢት) ከተማ የአየር ንብረት ሁኔታ ቆላማ በመሆኑ ማህበረሰቡ በተለያዩ በሽታዎች ይጠቃል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት የማህበረሰቡን ጤና ከሚያናጉ በሽታዎች መካከል የወባ በሽታ የተመረጠበት ምክንያት አልተገለፀም፣ ለምን በአንድ

በሽታ ላይ ብቻ ጥናት ተካሄደ? ሌሎች በሽታዎች የሉምን? ወይስ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ አለመሆኑ የጥናቱን ክፍተት የሚያሳይ ነው።

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የመጀመሪያው ነጥብ፤የሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው፤ለጥናት የተመረጠው ቦታ፤የሽዋሮቢት ከተማ ማህበረሰብ መሆኑ ነው። የእነ አብርሀም ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው፤ጥናቱ መጠናዊ መሆኑ፣ የጥናቱ ትኩረት የወባ በሽታ ላይ ሳይንሳዊ በሆኑ ጥናቶች በመደገፍ የወባ በሽታ መንስኤው፣ ምልክቶቹ እና መከላከያ ዘዴዎቹ ምንድን ናቸው? የሚሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ነው። ሆኖም የእኔ ጥናት ትኩረት አካባቢው ቆላማ ከመሆኑ የተነሳ በአካባቢው የሚከሰቱ በሽታዎች፣ ህብረተሰቡ ሀገር በቀል በሆነ እውቀት፤ከዕፅዋት በሚዘጋጁ መድሀኒቶች በሽታዎቹን እንዴት ይከላከላቸዋል የሚሉትን ጉዳዮች መመርመር ነው። በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት ስለበሽታዎቹ እና ስለመድሀኒቶቹ በሳይንስ የተረጋገጠ ወይም በቤተ ሙከራ ተሞክረው የተረጋገጡ የሳይንስ ውጤቶች ላይ ሳይሆን ማህበረሰቡ ከባህሉ፣ ከእምነቱ እና ከልማዱ አንጻር በሽታዎቹን ለመከላከል የሚጠቀሟቸውን ሀገር በቀል ዕውቀቶች መፈተሽ ነው።

Mekonen Mersa (2010) “Indigenous Medicine, Beliefs and practices Among the kunama in sheraro,Tigray” M.A Thesis; Department of Ethiopian Study በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት በሀገር በቀል ህክምና የሚተገበሩ አምልኮችን እና የተለያዩ ተግባራትን መመርመር ዋና ትኩረታቸው ነው። በተጨማሪም ባህላዊ ሀኪሞቹ የህክምና እውቀቱን ከየት እንዳገኙት መግለጽ፣ ማህበረሰቡ ለባህላዊ ሀኪሞች ያለውን አመለካከት ማስረዳት እንዲሁም ማህበረሰቡ ለባህላዊ እና ለዘመናዊ ህክምና ያለውን የአመለካከት ልዩነት ማሳየት የሚሉትን ነጥቦች ተመልክተዋል። በዚህ ጥናት ከባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች፣ ከባህል መድሀኒተኞች እና በአካባቢው ያሉ የእድሜ ባለጸጋዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፤ የባህል ህክምና ስርዓቱን በሚመለከት በኢተሳትፏዊ ምልከታ መረጃዎችን አጠናቅረዋል። በመሆኑም በጥናቱ፤የኩናማ ማህበረሰብ በሽታን ለመከላከል ሀገረሰባዊ መድሀኒቶችን አዘውትሮ እንደሚጠቀም ተገልጧል። ሀገረሰባዊ ሀኪሞች የአካባቢው ማህበረሰብ የሚከውናቸውን አምልኮች እና ልማዶች በመከወን አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው ተመራጭ እንዳደረጋቸው ገልጸዋል። በኩናማ ማህበረሰብ እምነት የበሽታዎች መከሰት ምክንያት ሁለት መሆናቸውን ይገልጻሉ። ይኸውም ተፈጥሯዊ እና መለኮታዊ ሲሆኑ ተፈጥራዊ የሚባሉት በድንገት የሚደርስ አደጋ እና ከሰውነት መቁሰል ጋር የተያያዙ ናቸው፤መለኮታዊ የሚባሉት ደግሞ

በሚላኩ መናፍስት እንደ ቡዳ፣ዛር፣በእርኩሳን መናፍስት ቁጣ የሚመጡ በሽታዎች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ የመኮንን ጥናት አዲስ እይታ ይዞ የመጣ ባይሆንም የኩናማ ማህበረሰብ ተፈጥሯዊ እና መለኮታዊ ህክምና ጥበብ ማሳየት መቻሉ ከሌሎች ጥናቶች ይለየዋል፡፡

የMekonen ጥናት በባህላዊ ህክምናው ውስጥ የሚከወኑ አምልኮዎች እና ተግባራት መመርመር ዋና አላማቸው መሆኑ፣የእኔ ጥናት ደግሞ በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ከዕፅዋት የሚያዘጋጇቸውን መድሀኒቶች የተመለከተ መሆኑ የመኮንን ጥናት ከእኔ ጥናት በእጅጉ ይለየዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ወቅቶች የሚከሰቱ በሽታዎችን መንስኤ ተፈጥሯዊ እና መለኮታዊ በሚል በሁለት መንገድ በማቅረብ በተፈጥሯዊም ይሁን በመለኮታዊ መንገድ ፈውስ የሚያገኙበትን ሂደት ያትታል፡፡ የእኔ ጥናት ተፈጥሯዊ የሆነውን በሽታ መንስኤ እና ተፈጥሯዊ የሆነውን የፈውስ መንገድ የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነጥብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መለኮታዊ የበሽታን መንስኤና የህክምና ሂደት የማይዳስስ መሆኑ ደግሞ ከመኮንን ጥናት የሚለይበት ነው፡፡ በአጠቃላይ  ይህ ጥናት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ማህበረሰቡ በሀገር በቀል እውቀት እራሱን ከበሽታ ለመከላከል የፈጠረውን ጥበብ መፈተሽ መቻሉ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

እስካሁን ዳሰሳ ከተደረገባቸው ጥናቶች በተጨማሪ በታሪክ ትምህርት ክፍል የAssefa Balcha (1992) “Traditional Medicine in Wallo: Its Nature and History” በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥናቱ ዐቢይ አላማ የወሎን የባህል ሕክምና ገጽታ እና ታሪክ ማጥናት ነው፡፡ በጥናታቸውም ማህበረሰቡ ከባህል ህክምናው ጋር ተያይዞ የሚፈጽማቸውን ልማዳዊ ድርጊቶች እና አምልኳዊ ስርዓቶች መርምረዋል፡፡ ጥናቱ በአይነታዊ የአጠናን ዘዴ፣ባህላዊ እና ዘመናዊ ሀኪሞችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን አጠናቅረዋል፡፡ በመሆኑም ሀገር በቀል እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች ስለበሽታ እና መድሀኒት ያላቸውን አተያይ አስረድተዋል፣እንዲሁም በዘመናዊው አና በባህላዊው ህክምና መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ዳሰዋል፡፡

የኢትዮጲያ የባህል ህክምና አጀማመር፣ በዘመን እና በነገስታት ለውጥ ያሳየውን እድገት እና የታዩ ክፍተቶችን እንዲሁም ተስተላልፎውን በግልጽ ለመረዳት አስቸጋሪ መሆኑን ቢገልጹም ኢትዮጲያ በቀደምት ዘመናት በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፓለቲካዊ ጉዳዮች ከተለያዩ ሀገራት

ጋር የነበራት ግንኙነት በባህል ህክምናው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ እንደሚኖር አስረድተዋል፡፡ የአሰፋ ጥናት የወሎ ማህበረሰብ ባህላዊ የህክምና ጥበብ ማሳየት መቻል፣ የኢትዮጲያን የባህል ህክምና ታሪካዊ ሂደት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለማሳየት መሞከሩ፣ የበሽታዎችን ዳራ እና ቅድመ እይታ ማቅረብ መቻሉ ከእኔ ጥናትና ከሌሎች ጥናቶች የሚለዩበት ነው፡፡ ሆኖም የሁለታችንም ጥናት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ላይ መሆኑ የእኔን ጥናት ከአሰፋ ጥናት የሚያመሳስለው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በፊት የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ዋና ጭብጣቸው ሀገረሰባዊ መድሀኒት ላይ ሲሆን እንደ ጥናት መስካቸው፣ ይዘውት እንደተነሱት አላማ እና እንደ ጥናታቸው ትኩረትና ገደብ፤የአጠናን ዘዴ፣ መረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴያቸው የተለያዩ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ አንዳንዶቹ ጥናቶች በሀገር ደረጃ፣ ሌሎቹ ደግሞ በአንድ ማህበረሰብ ላይ በማተኮር ማህበረሰቡ እራሱን በሀገር በቀል እውቀት እንዴት ከበሽታ ይከላከላል፤የሚለውን ጉዳይ በስፋት ዳሰዋል፡፡ በጥናታቸው ሂደት ከዕፅዋት፣ ከእንሰሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶችን፤ ከመንፈሳዊ (አምልኮታዊ) ህክምና ጋር በማስተባበር መድሀኒቶችን አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ተገልጧል፡፡ የእኔ ጥናት “ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ” በሚል ርዕስ፤በሸዋሮቢት አካባቢ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከናወነውን ሀገረሰባዊ የዕፅዋት ህክምና ስርዓት ለማጥናት አልሞ የተነሳ ጥናት በመሆኑ ከሌሎች ጥናቶች ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የሸዋሮቢት ከተማ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ለጥናት የተመረጠው አካባቢ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ አካባቢያዊ ስያሜ እና የህዝቦች አሰፋፈር፣ የማህበረሰቡ ቋንቋ፣ ሀይማኖት እና መተዳደሪያ የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡

## 3.1. መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ

የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ ካሉት አምስት (5) የከተማ አስተዳደሮች አንዷ ስትሆን ከክልሉ ርዕሰ ከተማ፤ከባህርዳር፤በስተ ምስራቅ እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ከደብረ ብርሀን፤በስተ ሰሜን ምስራቅ ትገኛለች፡፡ ከተማዋ በሰሜን፤የኦሮሚያ ዞን ጅሌ ጥሙጋ ወረዳ፣ በምዕራብ፤ቀወት ወረዳ፣ በደቡብ፤ቀወት እና ከፊል ጣርማበር ወረዳ፣ በምስራቅ፤አፋር ክልል ሰሙሮቢ ገልገሎ ወረዳ ያዋስኗታል፡፡ ከተማዋ ከአዲስ አበባ በስተ-ሰሜን በሁለት መቶ ሀያ አምስት (225) ኪ.ሜ፣ ከዞኑ ዋና ከተማ ከደ/ብርሀን፤በዘጠና አምስት (95) ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህርዳር፤በአዲስ አበባ በኩል ሰባት መቶ ሰማኒያ ስምንት (788) ኪ.ሜ እና በደሴ (ወሎ) በኩል ደግሞ ስድስት መቶ ሀምሳ ስድስት (656) ኪ.ሜ ርቀት ላይ ሸዋሮቢት ከተማን ማግኘት ይቻላል፡፡ የከተማ አስተዳደሯ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት አስራ አራት ሺ ሶስት መቶ ሀያ ሰባት (14.327) ስኩዬር ኪሎ ሜትር ሲሆን የአየር ንብረት ሁኔታዋ 100% ቆላማ፤የሙቀት መጠን ከፍተኛ ሰላሳ ሰባት (37)፤ዝቅተኛው 28 ሲሆን፤ከባህር ጠለል በላይ ያለ ከፍታ፤11266 ሜትርና ከባህር ጠለል በታች ያለው ዝቅታ፤1237 ሜ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም አመታዊ  የዝናብ መጠኗ 570 ሚ.ሊ ሊትር እንደሆነ የህዝብ ግንኙነት ሚዲያ ልማት ቢሮ የተገኘ የሰነድ መረጃ (የካቲት14/2012) ይጠቁማል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለእርሻ የሚውል መሬት 5068 ሄ/ር፣ በመስኖ የሚለማ 2563፣ ደረቅ መሬት 2505 እና በተፈጥሮ ሰው ሰራሽ ደን የተሸፈነ 956ሄ/ር መሬት መኖሩን የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር የህዝብ ግንኙነት ሚዲያ ልማት ቢሮ (ሸ/ከ/አ/ህ/ግ/ሚ/ል/ቢ፣ የካቲት13/2012) የተገኘ የሰነድ መረጃ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር

አምስት (5) የገጠር እና አራት (4) የከተማ በድምሩ ዘጠኝ (9) ቀበሌዎች አሉ፡፡[5] በከተማው ሁለት (2) የመንግስት የጤና ማዕከላት እና አስራ ሁለት የግል ኪሊኒኮች እንዲሁም አስራ ዘጠኝ (19) ፋርማሲዎች መኖራቸውን ከሰነድ መረጃው ላይ ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ ሴት፡- ሰላሳ ሺ ሰላሳ አምስት (30.035) ፤ወንድ፡-ሀያ ስምንት ሺ አንድ መቶ ዘጠና ስምንት (28.198) በአጠቃላይ ሀምሳ ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት (58.233) ህዝብ እንደሚገኝ የማዕላዊ ስታቲስቲስ ባለስልጣን በ2007 ዓ.ም ያወጣው መረጃ ይጠቁማል፡፡

## 3.2. የአካባቢ ስያሜ እና የህዝብ አሰፋፈር

ሸዋሮቢት ከተማ (ሮቢ፣ሻህ ሮቢት፣ሸዋሮቢት ወይም ሮቢት) በሚል ስያሜ ትታወቃለች፡፡ ከተማዋ በ1947 ዓ/ም ወታደራዊ ስልጠና ይሰጡ በነበሩ ኢትዮጵያዊ የጦር አዛዥ ራስ አበበ አረጋይ በሚባሉ ባላባት መቆርቆሯን የ85 አመት እድሜ ባለፀጋው አቶ አፈራ ንጉሴ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት28/2012) ገልጸውልኛል፡፡

## 3.3. የህዝቡ ቋንቋና ሀይማኖት ሁኔታ

ሸዋሮቢት ከተማ የአማራ፣ የአፋር፣ የአርጎባ፣ የኦሮሞ፣ የትግሬ እና የጉራጌ ብሔረሰቦች፤ በሰላም እና በመቻቻል በጋራ የሚኖሩባት ከተማ ነች፡፡ በከተማ አስተዳደሩ አብላጫውን ቁጥር የያዘው የአማራ ብሔረሰብ ቢሆንም የአፋርኛ፣ አርጎብኛ፣ ኦሮምኛ እና ትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ይገኙበታል፡፡ ከሀይማኖት አንጻር ደግሞ የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ (ኦርቶዶክስ፣ ሙስሊም፣ ፕሮቴስታንት) እንዲሁም የተሀድሶ እምነት ተከታዮዎች ያሉ ሲሆን አስራ አንድ (11) የኦርቶዶክስ ማምለኪያ ስፍራዎች፣ ስምንት (8) የፕሮቴስታንት፣ አራት (4) የእስልምና እምነት ተከታዮች ማምለኪያ ስፍራዎች እና ሁለት (2) የተሃድሶ አማኞች ማምለኪያዎች መኖራቸውን (ሸ/ከ/አ/ህ/ግ/ሚ/ል/ቢ፣የካቲት16/2012) የተገኘ መረጃ ይጠቁማል፡፡

[5] በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ካሉ ዘጠኝ ቀበሌዎች ውስጥ (03) ቀበሌ (ጫሬ፣ብርቱካን ሰፈር፣ብቅ እንቅ እና ሀይማ) የተባሉ አራት ንዑስ ቀበሌዎችን የያዘ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

## 3.4. የትምህርት ሁኔታ

በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ውስጥ ያሉ የትምህርት ማዕከላት ከ1-4ኛ ክፍል ሶስት (3) የመንግስት እና አራት (4) የግል ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ፤ከ1-8ኛ ክፍል ደግሞ አስራ ስምንት (18) የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች፤እንዲሁም በ1952ዓ.ም የተመሰረተውና ስድሳ (60) ዓመት እድሜ ያስቆጠረው የሸዋሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ይገኛል፡፡ ሌላው በ2012 ዓ.ም የተከፈተውና በዚሁ አመት ትምህርት የጀመረው፤የዙጢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡ በተጨማሪም አንድ (1) ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ እንዲሁም ስድስት (6) የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ሸ/ከ/ህ/ግ/ሚ/ል/ቢ፣የካቲት16/2012) ይገኛሉ፡፡

## 3.5. የህዝቡ መተዳደሪያ

በሸዋሮቢት ከተማ ውስጥ የሚኖሩ 54.58% የሚሆነው የማህበረሰብ ክፍል መተዳደሪያ ንግድ ሲሆን 44% ያህሉ የህብረተሰብ ክፍል ደግሞ በግብርና ይተዳደራል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ 5068 ሄክታር የሚታረስ መሬት ሲኖር፤ማሽላ፣ ማሾ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ሽንኩርት በዋናነት የሚመረቱ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ የሚገኙ አርሶ አደሮች የሮቢትን ወንዝ በመጠቀም የመስኖ ልማት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በተለይም ሽንኩርት (ቀዩ ወርቅ) በአመት እስከ ሶስት ጊዜ በማምረት ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን ሌሎች በርካታ ቋሚ አትክልትና ፍራፍሬ በማምረት ወደ ገበያ ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር 1.42% የሚሆነው በመንግስት ስራ የሚተዳደር መሆኑን አቶ ሽጋው ንጋቱ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት1/2012) አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ፤ከሰሌ፣ ድግጣ፣ መዛዝኝ፣ ዶሪ፣ ጠድቻ፣ ቁርቁራ፣ ጥዬ፣ ቀለም፣ ቅንቦ፣ የግመል በጠጥ እና ወይባ በአካባቢው ታዋቂ ዕፅዋት ናቸው፡፡ ግመል ደግሞ ለአካባቢው ማህበረሰብ፤ለጭነት ማጓጓዣ አገልግሎት የምትሰጥ የቤት እንሰሳት ስትሆን፤ዘንዶ፣ አማርሌ፣ ሰስ፣ ድኩላ፣ ነብር፣ ነብራርትና ጦጣ በአካባቢው ያሉ ታዋቂ የዱር እንስሳት መሆናቸውን የአካባቢው ነዋሪ የ82 አመት የእድሜ ባለፀጋው አቶ ጌታነህ ፈቂ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት22/2012) ገልፀውልኛል፡፡ [6]

---

[6]ስለ ሸዋሮቢት ከተማና ዙሪያዋ አጠቃላይ መልከዓ ምድራዊ ገፅታ፣የህዝብ አሰፋፈር፣ ብዛት፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣መተዳደሪያና የትምህርት ሁኔታ በሚመለከት ሙሉ የሰነድ መረጃ ለማግኘት የከተማ አሰተዳደሩን የህዝብ ግንኙነት ቢሮ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት በማነጋገር መረጃዎችን ለማጠናቀር ቢሞከርም የተደራጀ የጹሑፍ መረጃ ማግኘት ስላልተቻለ፤መረጃው ይኖራቸዋል ተብለው ከታሰቡና ከታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ የጎደሉ መረጃዎችን ለማሟላት ተሞክሯል፡፡

## 3.6. የቱሪስት መስህብ

ሸዋሮቢት ከተማ የጎብኚዎችን ቀልብ ለመሣብ የሚያስችሉ በርካታ ልዩ ልዩ ገጽታዎች ከታደሉ የአማራ ክልል ወረዳዎች ውስጥ አንዷ ነች፡፡ በአባቢው የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች የሀይማኖት ሽፋን ያላቸው በመሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ ከመስህብነት ባሻገር ወደ ፀበል ስፍራው በመሄድና በመጠመቅ ከተለያዩ በሽታዎች ይፈወሳሉ፡፡

በሌላ በኩል በእስልምና እምነት የፀሎት ቦታ ወደ ሆነው መስጅድ በመግባት ዱዓ በማድረግ ደህንነታቸውን የሚያስቀጥሉባቸው ስፍራዎች በመሆናቸው በዚህ ጥናት ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የማህበረሰቡን የእደ ጥበብ እውቀት የሚያሣይ ጥንታዊና ታሪካዊው የጎዜ መስጅድ ይገኝባታል፡፡ መስጅዱ ከከተማዋ በ 15ኪ.ሜ ርቀት ኮረብታ ላይ ይገኛል፡፡ በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች፣ከአባቶቻቸው የወረሱትን ታሪክ በማውሣትና፣በንጣፍ ድንጋይ ላይ በአረብኛ የተፃፈውን ቁጥር እንደ አብነት በመጥቀስ በ722 ወይም በ111 ሂጅራ የተገነባ ሲሆን ከ1275 አመት እድሜ በላይ ያስቆጠረ ጥንታዊ መስጅድ መሆኑን በአካባቢው ያገኘኋቸው የ91 አመት እድሜ ባለጸጋው አቶ አወል ጀማል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት21/2012) ይናገራሉ፡፡

ጎዜ መስጅድ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ከ30’ ደቂቃ የመኪና ጉዞ እና ከአንድ ሰዓት ተኩል (1፡30) ያህል የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ታሪካዊ መስጅድ ከአረብ አገር የተሰደዱ ሙስሊሞች /ሱሀቦች/ እንደሰሩት ይነገራል፡፡ ከመካ የተሰደዱት አረቦች /ሱሀቦች ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ጊዜ አርባ (40) የሚሆኑ መስጅዶችን በአንድ ወቅት ወይም በተመሣሣይ ጊዜ ግንባታውን የጀመሩ ሲሆን የመጨረሻው ወይም 40ኛ የሆነው መስጅድ ጥንታዊ የጎዜ መስጅድ መሆኑ በአፈታሪክ ይነገራል፡፡ ’ጎዜ’ የሚለው ስያሜም በወቅቱ ግንባታውን የሚገነቡት አረቦች፣ እዚህ ጓዜን ላሣርፍ ሲሉ፣ከዚህ ጋር ተያይዞ ’ጎዜ’ የሚለው ስያሜ እንደተሰጠው፣አቶ አወል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት21/2012) ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የጎዜ የመጀመሪያ ወይም ጥንታዊ ስሙ ’ቃጥ’ ይባል እንደነበር አስረድተዋል፡፡ አረቦቹ፣በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በአማራ እና በሌሎች ክልሎች መስጅዶችን እንደሰሩ ይነገራል፡፡

**የአቡነ አረጋዊ ፀበል**

ሌላው ሸዋሮቢት ከተማ ከታደላቸው የተፈጥሮ መንፈሳዊ መስህቦች ውስጥ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የአቡነ አረጋዊ ፀበል ነው፡፡ ይህ ቦታ ከከተማዋ 7ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

በስፍራው ያሉ የሀይማኖት አባት ስለ ፀበል ስፍራው ሲያስረዱ፤የአቡነ አረጋይ ፀበል የፈለቀበት ጊዜ በውል ባይታወቅም ጸበልተኞች ከደብረ ሲና የአረጋይ ጸበል በቅል ይዘው ሲመጡ፤አሁን የአቡነ አረጋይ ጸበል የሚገኝበት ቦታ ላይ ቅሏ አምልጣቸው እንደተሰበረችና በዚያን ጊዜ ጸበሉ እንደፈለቀ ይነገራል፤ይላሉ ቄስ ሙላቱ ታየለት (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት28/2012)። አያይዘውም የጸበል ስፍራው ስለሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ያስረዳሉ።

በአሁኑ ጊዜ የአቡነ አረጋይ ጸበል ፈዋሽነቱ ከአካባቢው ነዋሪዎች አልፎ፤ የተለያዩ ክፍለ ሀገራት ያሉ ክርስቲያኖችን (ኦርቶዶክስ) የሳበ የተፈጥሮ ፈውስ ስፍራ ነው። በዚህ ጸበል ውስጥ የማንኛውም የእምነት ተከታይ መጸበል ይችላል። ፀበሉ፤ሞቃታማ፤አልፎ አልፎም እጅግ የሚፈላ በመሆኑ ለመጠመቅ ከባድ የሆነ መንፈሳዊ ቦታ ነው። ይህ መንፈሳዊ ቦታ በቅዱሳን አባቶች የተባረከ እና ቃል ኪዳን ያለው ቦታ መሆኑን፤በስፍራው ያገኘኋቸው ቄስ ሙላቱ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት28/2012) ነግረውኛል።

ይህ መንፈሳዊ የፈውስ ቦታ ድንቅ ድንቅ ተዓምራት የሚታይበት፤አይነ ስውራን ብርሀናቸውን ያገኙበት፣መራመድ የማይችሉ፤የተራመዱበት፣ በድዌ የተመቱ የሚፈወሱበት ሲሆን በተለይ ለእከክ፣ ለቁስል እና ሰውነት ላይ ለሚወጣ ለየትኛውም በሽታ ፍቱን መሆኑን በፀበል ስፍራው ያገኘኋቸው ወ/ሮ አስካለ ደምሴ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት4/2012) ገልጸዋል።

በዚህ የፀበል ስፍራ በርካታ ተረኮች ይነገራሉ። መሪጌታ እንግዳሰው ሀይሌ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 2/2012) "አንድ ሰው ወደ እዚህ የፀበል ቦታ ከመምጣቱ በፊት ንፁህ መሆን አለበት፤ ካልሆነ ግን ፀበሉ እጅግ በጣም ይፈላል፤ፀበሉን የሚጠብቁ ዘንዶ፣ ነብር እና ሌሎች አስፈሪ እንስሳቶችም ይመጣሉ። እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ብዙ ጊዜ ተፈጥረዋል፤በዚህ ጊዜ ካህናት አባቶች ተጠርተው፤ፀሎት አድርገው ነው፤የሚጠመቁ ሰዎች ወደ ፀበሉ የሚገቡት፤ ፀበሉን የሚጠብቁ (ዘንዶና ነብር) በአባቶች ፀሎትና ልመና ይሰወራሉ" በማለት አስረድተዋል።

ፎቶ ግራፍ 1፦ አቡነ አረጋዊ ጸበልን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ



ምንጭ፦ የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤2011ዓ.ም።

**የአቦ ጸበል**

ከአቡነ አረጋይ ጸበል በመቀጠል ብዙ ሰዎችን እያስተናገደ የሚገኘው ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ የመስህብ ቦታ የአቦ ጸበል ነው። ይህ ጸበል የፈለቀበት ጊዜ በውል ባይታወቅም ከአቡነ አረጋዊ ጸበል ቀጥሎ እንደፈለቀ መሪጌታ እንግዳሰው (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት3/2012) ገልጸዋል።

ይሁን እንጂ የጸበል ስፍራው በአካባቢው ማህበረሰብ ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱን መሪጌታ እንግዳሰው እንዲህ ያስረዳሉ።

የአካባቢው ማህበረሰብ አሁን እንደሚታየው ብዙ አልነበረም፤ትንሽ ቁጥር ያለው ህዝብ ነበር፤በወቅቱም የአቡነ አረጋዊ ፀበል የፈለቀበት ጊዜ ስለነበርና ድንቅ ድንቅ ተዓምራቶች የሚያሳይ በመሆኑ በአካባቢው ያለው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ትኩረቱን ያደረገው በአቡነ አረጋዊ ጸበል ላይ ነበር፡፡ አሁን ላይ የህዝብ ቁጥሩ እየጨመረ ሲመጣ፤የአቦ ፀበልም ታዓምር እየተሰማ ሲሄድ፤ወደ ፀበል ስፍራዎቹ የሚመጡ ምዕመናን ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፤ከአቡነ አረጋዊ ፀበል ባልተናነሰ፤ወደ አቦ ፀበል ብዙዎች ይመጣሉ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት3/2012)፡፡

ይህ መንፈሳዊ የጸበል ስፍራ ለአካባቢው ማህበረሰብ በመንፈሳዊ ፀበልነት እያገለገለ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የፀበል ቦታውን ለማጠናከር፣ ለምዕመናን ምቹ ለማድረግ፤ከጸበልተኞች በሚገኝ ገቢ እና ከማህበረ ወይንዪ (ቤተ ክርስቲያንን እና የፀበል ስፍራዎችን ለማገልገል የተሰባሰቡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ማህበር) ጋር በመሆን የተለያዩ ድጋፎች እየተደረገለት እንደሚገኝ ቄስ አዱኛ አንዳርጌ (ቃለ መጠይቅ፣14/07/2012) ገልጸዋል፡፡[7]

አቦ ጸበል ሲጠመቁ ያገኘኒቸው ወ/ሮ ዚነት "አቦ ፀበልም ሆነ አቡነ አረጋዊ ፀበል፤ የአላህ ስጦታዎች እንደሆኑ አምነን መጥተን እንጠመቃለን፤እንድናለንም፡፡ ይህ ቦታ የሙስሊምም የክርስቲያንም ነው" (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት30/2012) በማለት ገልፀውልኛል፡፡

**ፎቶ ግራፍ 2፡-የአቦ ጸበልን የሚያሳይ**



ምንጭ፡- የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ባህልናቱሪዝም ቢሮ፤2011ዓ.ም፡፡

---

[7] ማህበረ ወይንዪ ፤ ቤተክርስቲያንን እና የፀበል ስፍራዎችን በገንዘብ፣በእውቀትና በሀሳብ ለማገልገል የተሰባሰቡ የኦርቶዶክስ ምዕመናን ቡድን ወይም ማህበር የሚገልጽ መጠሪያ ነው፡፡

## የአብዱ ፍል ውሀ

ይህ ቦታ ከከተማዋ ሸዋሮቢት 2 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ የተፈጥሮ መስህብ ስፍራ ነው፡፡ ይህ ቦታ ከሌሎች የመስህብ ቦታዎች ውሀው በበለጠ መልኩ የፈላ ሲሆን ለመሰረተ ልማት አመቺ የሆነ ቦታ በመሆኑ፤ለልጆች መዋኛ ገንዳዎች ቢሰሩ፣ ልዩ የመዝናኛ ስፍራ ለማድረግ እንቅስቃሴ ቢጀመር ባለሃብቱ ተጠቃሚ፤የአካባቢው ማህበረሰብም መንፈሳዊ እርካታ የሚያገኝበት ተፈጥሯዊ ቦታ ማድረግ እንደሚቻል ገልጸው፤የቱሪስት ስፍራው እስካሁን ድረስ በማህበረሰቡ ጥበቃ እየተደረገለት እንደሚገኝ አቶ ደምሴ ጫኔ (ቃለ መጠይቅ፣04/06/2012) ገልጸውልኛል፡፡

**ፎቶ ግራፍ 3፡- የአብዱ ፍል ውሀን የሚያሳይ**



ምንጭ፡- ከሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤2011ዓ.ም፡፡

### 3.7. የባህል ገፅታ

ሸዋሮቢት ከተማ እና ዙሪያዋን የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያዩ መረዳጃ ባህሎች አሏቸው። እቁብ፣ እድር፣ ህመምተኞችን የመጠየቅ፣ እስረኞችን የመጎብኘት፣ የሰርግ፣ የለቅሶ እንዲሁም የሀዘንም ሆነ የደስታ ጊዜያትን በአንድነት የማሳለፍ፣ ሁሉም ብሔረሰብ፤ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት፤የባህል አልባሳት፣ ጌጣጌጥን መጠቀም እንዲሁም ክብረ በዓሎችን፤ በክርስትናው (የልደት፣የጥምቀት እና የትንሳኤ) ፤በእስልምናው (ኢድ፣አረፋን እና መውሊድን) በጋራ ተፈቃቅረው የማክበር ባህል አላቸው። እነዚህ ክብረ በዓላት የአካባቢውን ማህበረሰብ እርስ በርስ ግንኙነት የሚያጠነክሩ ከመሆናቸውም ባሻገር ሁሉም ሙያተኞች በተገናኙባቸው አጋጣሚዎች የራሳቸውን እውቀት እንዲገልጡ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የባህላዊ ህክምና እውቀት ተገልጦ የሚታይ በመሆኑ በክርስትና እና በእስልምና እምነት የሚከበሩ ክብረ በዓሎች በጥናቱ ተካታች ሆነዋል።

> በእኛ አካባቢ በደስታችንም ሆነ በሀዘናችን ጊዜ በአንድነት ነው የምናሳልፈው፤አንድ ቤት ሰርግ ለመደገስ ሲታሰብ፤ሙስሊሞችም ክርስቲያኖችም ሆነን በጋራ ተጋግዘን፤መስራት የምንችለውን አግዘን፤ ይደገሳል። ሰርጉ የተደገሰበት ቤት፤በአንድ ወገን ለሙስሊም የሚሆን ምግብ፤በሙስሊሞች ታርዶ፣በሙስሊም ሴቶች ተዘጋጅቶ፣በሙስሊም አሰተናጋጆች እንስተናገዳለን፤ለክርስቲያኖችም እንደዚሁ፤ክርስቲያኖች አርደው፤ክርስቲያኖች አብስለው ያቀርባሉ። እናም በአንድነት ነው የምናሳልፈው፤በሀዘን ወቅትም ቢሆን ሙስሊም ቤት ሀዘን ካለ፤ ክርስቲያኖች መጥተው፤አጽናንተው ሀዘናችንን ተጋርተው ይሄዳሉ፤እኛም እንደዚሁ ክርስቲያን ቤት ሀዘን ሲገባ ሀዘናቸውን እንጋራለን።
>
> ክብረ በዓላት ሲኖሩ (ልደት፣ ጥምቀት እና ትንሳኤ) ወቅት፤ተጠራርተን በዓሉን በጋራ እናከብራለን። ክርስቲያኖች፤ሙስሊሞች የሚበሉትን እና የሚጠጡትን አዘጋጅተው ይጠራሉ፤እኛም ሀይማኖታችንን አክብረን፤ በልተን ጠጥተን በጋራ በዓሉን እናሳልፋለን። ክርስቲያኖችም (በኢድ፣ በአረፋ እና በመውሊድ) እንዲሁም በፆማችን ወቅት ወደ ቤታችን ይመጣሉ፤እንደ ሀይማኖታቸው ለክርስቲያኖች የሚሆነውን እናቀርባለን፤ እናም በዚህ መልኩ በጋራ ተከባብረን፣ ተቻችለን እንኖራል ይላሉ አቶ ሰይድ አወል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት24/2012)።

በእነዚህ ክብረ በዓላት ጊዜ የተለያየ ሀገር በቀል እውቀት፣ ችሎታና ጥበብ ያላቸው (መድሀኒተኞች፣ በጥንቆላ የሚተዳደሩ፣ አስማት አድራጊዎች፣ ክታብ ሰሪዎች፣ አንጥረኞች፣

ሽማኔዎች፣ የእደ ጥበብ ሙያተኞችና ሌሎችም) በዚሁ አጋጣሚ እንደሚታደሙ ገልፀዋል፡፡ በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ ድንገተኛ ለሚታመሙ፣ ለሚጥል በሽታ፣ በድንገት ደም ለሚፈሳቸው፣ ለነፍሰ ጡሮች፣ ለወላዶች፣ ለህጻናት እና በተለያየ በሽታ ለተያዙ ሰዎች በእነዚህ አጋጣሚዎች ያላቸውን እውቀት በመጠቀም ታማሚዎችን እንደሚፈውሱና ያላቸውን ሙያ እንደሚያስተዋውቁ አቶ ሰይድ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት24/2012) ገልጸውልኛል፡፡

በከተማው የተለያዩ የእደ ጥበብ ሙያተኞች ያሉ ሲሆን ለአብነትም የሽመና፣ የቆዳ እና የብረታ ብረት ስራዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ የዘንባባ ስራ ሙያተኞች ዘንባባን በግብዓትነት በመጠቀም፤ ሰኔል፣ ምንጣፍ፣ ኮፍያ እያዘጋጁ ለማህበረሰቡ በሽያጭ መልክ ያቀርባሉ፡፡ በሽመናው፣ በቆዳና ብረታብረት ሙያተኞችም እንደዚሁ የራሳቸውን እውቀት፣ ጥበብና ልምድ እየተጠቀሙ የተለያዩ የእደ ጥበብ ውጤቶችን በማምረትና ወደ ገበያ በማቅረብ የአካባቢውን ማህበረሰብ ያገለግላሉ፡፡ በአካባቢው ከተወሰኑ አመታት በፊት ይኖሩ ከነበሩ የሽመና ባለሙያዎች የመኖሪያ ቦታ ጋር ተያይዞ “ሽማኔ ማህበር” በሚል ስያሜ የሚጠራው ሰፈር ይህንኑ የሚያረጋግጥ መሆኑን አቶ አጥቃው በላይ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት27/2012) ገልፀውልኛል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ

በዚህ ምዕራፍ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰቡን የሚያጠቁ በሽታዎች እና መለያ ዘዴዎች፣ ለሀገረሰባዊ መድሀኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋት መገኛ ቦታዎች፣ ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸው የዕፅዋት ክፍሎች፣ የመድሀኒቶቹ አዘገጃጀትና አጠቃቀም፣ የሀገረሰብ መድሀኒቶች የሚዘጋጁባቸው እና የሚሰጡባቸው ቀናት እና ሰዓታት ትዕምርታዊ ፋይዳ፣ የሀገረሰብ ህክምና እውቀት ለመዳ መንገዶች፣ የባህል ህክምና እውቀት ምስጢራዊነት፣ ዘመናዊ ሀኪሞች ለባህላዊ ህክምና ያላቸው አመለካከት፣ ባህላዊ ሀኪሞች ለዘመናዊ ህክምና እና ለባለሙያዎቹ ያላቸው አመለካከት እንዲሁም ባህላዊ ሀኪሞች በታካሚዎች ዘንድ የሚመረጡባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚሉት ነጥቦች ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 4.1. በሀገረሰብ ህክምና የሚድኑ፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚያጠቁ በሽታዎች

በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያዩ በሽታዎች ይጠቃሉ፡፡ የበሽታዎቹ መከሰቻ አጋጣሚዎች የተለያዩ ቢሆኑም የወቅቶች መፈራረቅ እና የአየር ንብረት ለውጥ ለጤና መቃወስ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ለበሽታ የመጋለጥ ምክንያት የአየር ንብረት ሁኔታው ሞቃታማ መሆን ነው፤የሚል አመለካከት አላቸው፡፡

የዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የባህል ህክምና ባለሙያ አቶ አውራሪስ ፍቃዴ በአካባቢው ስለሚከሰቱ በሽታዎች እንዲህ ያስረዳሉ፡-

> የተለያዩ በሽታዎችን አክማለሁ፡፡ የቆላ ቁስል፣ ችፌ፣ አልማዝ ባለጭራ፣ የወፍ በሽታ፣ እባብ ለነደፈው ሰው፣ ላሽ፣ አይሬ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ለሌሎችም በሽታዎች መድሀኒት እሰጣለሁ፡፡ ቀዬያችን ቆላማ በመሆኑ የተለያዩ ነፍሳት እንዲራቡ ያመቻቸዋል፤እነዚህ ነፍሳትም የሰውን የአካል ክፍል በመንከስ፣ በመንደፍ፣ ሽንታቸውን በመሽናት እና በላያቸው ላይ በመዞር እንዲለከፉ ያደርጋሉ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት15/2012)፡፡

ሌላው የማደያ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የሀገረሰብ ሀኪም አቶ ሱሊህማን አብዲ በአብዛኛው ማህበረሰቡ ስለሚጠቃባቸው በሽታዎች ሲያስረዱ፡-

> እኔ ነፍስ ካወኩበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ አካባቢ የሚከሰቱ በሽታዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የወፍ በሽታ፣ ምች፣ እከክ (የሰውነት መቁሰል) ፣ የቆላ ቁስል፣ አልማዝ ባለጭራ የተባሉት በተደጋጋሚ የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚያጠቁ በሽታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ በሽታዎች አብዛኛውን ጊዜ ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የሚታዩ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 9/2012)፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ አረጋሽ ሽታዬ በአካባቢው ላይ ስለሚከሰቱ በሽታዎች ሲገልፁ፡-

> አካባቢያችን በእጅጉ ቆላማ ነው፤ሞቃታማ ነው፤እኔ ለአንዳንድ በሽታዎች መድሀኒት እሰጣለሁ፡፡ በአብዛኛው በአካባቢያችን ብዙ ሰዎች በወፍ በሽታ፣ ምች፣ ተቅማጥ (የሆድ ህመም) ፣ የቆላ ቁስል፣ አልማዝ ባለጭራ፣ ኪንታሮት እና በሌሎች በሽታዎች ተይዘው ወደ እኔም፤ወደ ሌሎችም መድሀኒተኞች ይሄዳሉ፡፡ ወደ ደጋ ዘመዶች አሉኝ፤ ነገር ግን እንደዚህ አይነት ህመም ታመምን ሲሉ አልሰማሁም፤በእነዚህ በሽታዎች የሚያዙት እዚሁ ሀገራችን ነው (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት19/2012)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በሸዋሮቢት እና ዙሪያዋ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን በአብዛኛው የሚያጠቁ በሽታዎች፡- የቆላ ቁስል፣ የወፍ በሽታ፣ አልማዝ ባለጭራ፣ ችፌ፣ አይሬ፣ በእባብ መነደፍ፣ እከክ (ለሚቆስል) ፣ ኪንታሮት፣ ላሽ፣ ምቺ እና ሆድ ቁርጠት መሆናቸውን እና የእነዚህ በሽታዎች መንስኤ፤በዋናነት የአየር ንብረቱ ሞቃታማ (ቆላማ) መሆን ነው፡፡ የአየር ንብረቱ ሞቃታማ መሆን ተናዳፊ ነፍሳት እንዲራቡ እና በንቃት ለመንቀሳቀስ ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥርላቸው፤የአካባቢውን ማህበረሰብ በማጥቃት (በመንከስ፣ በመቆንጠጥ፣ ሽንታቸውን በመሽናት፣ በላያቸው ላይ በመዞር እና መርዛቸውን በመርጨት) በበሽታ እንዲጠቁ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ በሽታዎች ማህበረሰቡን በተደጋጋሚ የሚያጠቁ በመሆናቸው በአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ በባህል ህክምና ባለሙያዎች ዘንድ እውቅና ያላቸው በመሆኑ በዚህ ጥናት ዋና ዋና በሽታዎች ተብለው ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከተገኘው መረጃ በመነሳት ለጥናት በተመረጠው በሸዋሮቢት ከተማ እና ዙሪያዋ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን በተመሳሳይ ወቅት እና ጊዜ በተደጋጋሚ የሚያጠቁ በሽታዎች

መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በጥናቱም እነዚህ በሽታዎች በማህበረሰቡ ሀገር በቀል እውቀት የሚፈወሱበት ሂደት እና ስርዓት በቅደም ተከተል በትንታኔ ቀርበዋል፡፡ [8]

## 4.2. በሀገረሰብ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴ

በሸዋሮቢት ከተማ እና ዙሪያዋ የሚገኙ የሀገረሰባዊ ህክምና ባለሙያዎች በሽታን የሚለዩበት እና የሚመረምሩበት መንገድ የተለያየ ነው፡፡ በእይታ፣ በመነካካት፣ በመጠየቅ የበሽታውን አይነት፣ ደረጃና ባህሪ ይለያሉ፡፡ ለመለያ መንገዳቸው መለያየት እንደምክንያት የሚያነሱት የበሽታዎቹ መለያየት፣ ያላቸው እምነት እና እውቀት እንዲሁም የበሽታዎቹ ባህሪ (በግልጽ የሚታዩና የማይታዩ፣ የሚደበቁ፣ የሚያመረቅዙ፣ እራሳቸውን የሚሸፍኑና የህመም ስሜት ብቻ ያላቸው እንዲሁም ምንም አይነት ምልክት የማያሳዩ በሽታዎች) መኖራቸው፤ የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ የምርመራ ዘዴ መለያየት የሚጠቀሱ ምክንያቶች መሆናቸውን ከመስክ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የባህል ሀኪም አቶ ሙሳ ሀሰን ስለ በሽታ መለያቸው ሲገልጹ፡- “እኔ በብዛት የማክመው በሽታ የቆላ ቁስል ነው፡፡ በሽታውን የምለየውም በእይታ፣ በመነካካት እና በመጠየቅ ነው፡፡ በቆላ ቁስል የተያዘ ሰው፤ትንኟ የነደፈችበት ቦታ ላይ ትጎደጉዳለች፤ ዙሪያዋን ታብጣለች፤በፍጥነት በታካሚው ተክለ ሰውነት በመሰራጨት ልብ እንዲደክም እና ሰውነት እንዲዝል በማድረግ ወደ ሞት የሚወስድ ነው” (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት23/2012)፡፡

ይህንን አስመልክቶ የጫሬ ቀበሌ ነዋሪው ሀኪም አቶ ደረጀ ወሰኔ በሽታን ስለሚለዩበት መንገድ ያስረዳሉ፡-

> የቆላ ቁስል የታመመ ሰው ሲመጣ ገና ሰውነቱን ሳይ እለየዋለሁ፤ሰውነቱ በጣም ይዝላል፣ ይደክማል፣ አይኑ የሞተ ሰው አይን ነው የሚመስለው፤ ጠጋ ብዬ ቁስሏ ያለችበትን ቦታ ሳይ ደግሞ በእጅጉ እለየዋለሁ፡፡ ቁስሏ ያለችበት ቦታ ትጎደጉዳለች፣ የቁስሉ ዙሪያ ያብጣል፡፡ እነዚህን ምልክቶች ሳይ በሽታው የቆላ ቁስል መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ እኔም መቼ ጀመረሽ/ህ ብዬ እጠይቃለሁ፤ምክንያቱም በሽታው አጣዳፊ እና በቶሎ የሚገድል በመሆኑ ከደከመ በኋላ ለመጣ ሰው መድሀኒት አልሰጥም፤ መድሀኒቱ ሀይለኛ ስለሆነ በሽታው ካዳከማቸው በኋላ መድሀኒቱን ብሰጥ፤ የመድሀኒቱ ሀይል ታማሚዎቹን ሊገድላቸው ይችላል፡፡ ለዚህ ነው የታመመውን ሰው አልያም ከታማሚው ጋር አብሮ የመጣውን ቤተሰብ፣

[8] የበሽታው አይነት፤የመድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ሂደት ትንታኔ በ4.6 ላይ የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ዘመድ፣ ጓደኛ በደንብ የምጠይቀው። በሽታው ትኩስ እና ታማሚውን ያላዳከመው ከሆነ፤የተዘጋጀ መድሀኒት ካለኝ እሰጠዋለሁ፣ ከሌለኝም መድሀኒቱ ከሚገኝበት ቦታ እስቀማመጣ ድረስ ይጠብቃሉ።

በሽታው በተለያየ የሰውነት ክፍል፤አይን ላይ፣ ጉንጭ ላይ፣ ግንባር ላይ፣ አፍንጫ ስርና አገጭ ላይ ሊወጣ ይችላል። ይሁን እንጂ ህክምናችንን አስቸጋሪ የሚያደርግብን፤ቁስሏ ከንፈር ላይ ስትወጣ ነው። ምክንያቱም ከንፍሩ ላይ በዚች በሽታ የተነደፈ ሰው አፉን እና ጉሮሮውን በመዝጋት መመገብም ሆነ መናገር እንዳይችል ታደርገዋለች፤በዚህ ጊዜ የታማሚው ቤተሰብ አጠቃላይ ስለህመሙ ለመናገር፤ለእኛ ለመድሀኒተኞች ለማስረዳት ይቸግረዋል። አስታማሚዎችም ይቸገራሉ፤ መድሀኒቱን ለማድረግ አመቺ ቦታ ባለመሆኑ ለእኛ ለባለሙያዎቹም አስቸጋሪ ይሆናል። ታማሚው እንደ ሌሎቹ መመገብ ስለማይችል፤ አስታማሚዎች በማንኪያ ለስለስ ያለ (ፍትፍት) በጉሮሮው እንዲወርድ መንከባከብ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ቁስሉ በተቀሩት የአካል ክፍል ላይ ቢወጣ መድሀኒቱን እንደ ልብ ለማሰር እና ታማሚውንም ለማስታመም አይከብድም። ይህ በሽታ በአብዛኛው በጋ ላይ ነው የሚመጣው፤በክረምት ብዙ አይደለም፤አየሩ እየሞቀ ሲሄድ በሽታው በስፋት ሰዎችን ያጠቃል፤ አየሩ እየቀዘቀዘ ሲሄድ፤ይጠፋል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት19/2012)።

ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ ደረጀ ወሰኔ ከሰጡት መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ለህክምና የሚመጡ ታማሚዎችን በሽታ ለመለየት፤በእይታ፣ በመንካት (በመዳሰስ) እንዲሁም የህመሙን ሁኔታ በመጠየቅ ይረዳሉ። ይህም በታካሚዎች ላይ ህመሙ ያለበት ደረጃ ታውቆ ተገቢውን ህክምና አንዲያገኝ ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ነው።

ሌላው ፓፓዬ ሰፈር ነዋሪ የሆኑት አቶ አገኘሁ ትርፌ የአልማዝ ባለጭራ በሽታ የሚለዩበትን መንገድ ሲያስረዱ፡-

የታመመ ሰው ወደ ቤቴ ሲመጣ ምንድነው ያመመህ(ሽ)? የቱጋ ነው ያመመህ(ሽ)? ምን ይሰማሀል/ይሰማሻል? ከጀመረህ ስንት ቀን ሆነህ(ሽ) ብዬ እጠይቃለሁ፤ከዚያም የታመመውን የሰውነት ክፍል እንዲያሳየኝ እነግረዋለሁ፤ሰውየው የታመመው አልማዝ ባለጭራ መሆኑን የማውቀው፤በሽታው ያረፈበት የታማሚው ገላ ላይ መስመር ይሰራል፤ በመስመሮቹ ዙሪያ ደግሞ እትር እትር የሚሉ ትንንሽ እብጠቶች ይታያሉ፤ በገላው ላይ የሚታየውን መስመር (ታካሚውን እንዳያመው) ቀስ ብዬ እነካዋለሁ፤ እብጠት ከተሰማኝ፤መስመሩ ያረፈበት ገላ ከሌላው በተለየ ከጠበቀብኝ (ከጠነከረብኝ)፤የእጅ እና የእግር ስሮቹን፤ስጋው

ከሽፈነብኝና ስሮቹን ማግኘት ካልቻልኩ፤የታመመው/የታመመችው ግለሰብ አልማዝ ባለጭራ መሆኑን አውቃለሁ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 4/2012)፡ ፡

በተጨማሪም በማድያ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ አህመድ ጀማል ስለበሽታ መለያቸው ሲያስረዱ፡ -

አልማዝ ባለጭራ በሽታ ሰዎችን በብዛት የሚያጠቃው በበጋ ነው፡፡ እኔ አልማዝ ባለጭራ የታመመ ሰው የምለየው በመጀመሪያ በማየት ነው፤ ከዚያም በመጠየቅ፤በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው ገላው ሽፍ ይላል፤ በተደጋጋሚ ያስለዋል፤ውጋትም አለው፡፡ በበሽታው ከሶስት ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ የታመመ ሰው ከመጣብኝ የኤች.ኣይ.ቪ. በሽተኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፤የኤች.አይ.ቪ. በሽተኞች ላይ የሚወጣ ቁስል እና የአልማዝ ባለጭራ ቁስል ይመሳሰላል፤እኔም ቁስሉ እንዳይነካኝ በጥንቃቄ መድሀኒቱን እሰጣለሁ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት25/2012)፡፡

መረጃው በተሰበሰበበት አካባቢ ያሉ የባህል ሐኪሞች ውጫዊ ሕመምን፤ቆስለው የሚታዩ፣ የአካል ክፍል (ቀለምን፣ አቋምንና የሰውነትን ቅርፅ) የሚለውጡ፤(የወፍ በሽታ፣ የቆላቁስል፣ በእባብ መነደፍ፣ ሆድ ቁርጠት/ተቅማጥ)፤ከውስጣዊ ስሜት ምልክት በመውሰድ፤የበሽታ ዓይነት፣ ተፅዕኖ እና ባሕርይን እንደሚለዩ እና ከሰውነት ክፍል፤ዓይን፣ ምላስ፣ አገጭ፣ ቅንድብ፣ አፍንጫ፣ የእጅና የእግር ሥሮች፤በሽታን ለመለየት ተመራጭ ቦታዎች መሆናቸውን፤በመስክ የተገኙ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የታካሚውን ተክለ ሰውነት እና አጠቃላይ አቋም በመፈተሽ፤የልብ ምት፣ የሰውነት ሙቀት መጨመር/መቀነስ፣ የጅማት መሸማቀቅ፣ የሰውነት መድከም (መዛል)፣ የሰውነት ክብደት መጨመር/መቀነስ፣ መዝለፍለፍ፣ መንቀጥቀጥ፣ የድካም ስሜት፣ እራስን መሳት፣ ማላብ፣ የራስ እና የሆድ ሕመም ተጨማሪ በታካሚዎች ላይ የሚታዩ ምልክቶች መሆናቸውን አቶ ሱሊህማን (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት4/2012) አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በዳበሳ፣ በንክኪ፣ በማሸት፣ በማጠፍና በመዘርጋት፣ በመጨበጥና በማላላት፣ በመጫንና በመልቀቅ፤የአተነፋፈስ ሥርዓት፣ የልብ ትርታ፣ የደም ዝውውር፣ የጡንቻ መሸማቀቅ፣ የትኩሳት መጠንን በመለካት፣ የተለያዩ የበሽታ ምልክቶችን ለማረጋገጥ እና መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል፤የታካሚውን ሰውነት መዳበስና መነካካት አስፈላጊ መሆኑን መስክ ላይ ያገኘኋቸው አቶ ወሰኔለህ ጫኔ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት9/2012) ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች ውስጣዊ ሕመምን ለመለየት፤በሰውነት አካል ላይ ምልክት ማግኘት ለሚከብዱ

የሕመም ዓይነቶች፤የስሜት ሕዋስን በመጠቀም ምርመራ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ከመስክ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው በአብዛኛው የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚያጠቁ በሽታዎች የቆላ ቁስል፣ የወፍ በሽታ፣ አልማዝ ባለጭራ፣ አይሬ፣ ኪንታሮት፣ ምች፣ እከክ (ቁስል)፣ ተቅማጥ (ሆድ ቁርጠት) ፣ ችፌ፣ በእባብ መነደፍና ሳሽ ሲሆኑ፤ በአካባቢው ያሉ የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች፤በሽታዎቹን፤በእይታ፣ በመዳበስ፣ በመነካካት፣ በመጠየቅ፣ የልብ ትርታን በማዳመጥ፣ የሙቀት መጠን በመለካት እና ልዩ ምልክቶችን በማጤን የበሽታውን አይነት፣ ደረጃና አጠቃለይ የታካሚውን ሁኔታ መረዳት እንደሚችሉ ነው፡
፡

## 4.3. ለህገረሰብ መድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆች መገኛ ቦታዎች

በሸዋሮቢት ከተማ እና ዙሪያዋ የሚገኙ አካባቢዎች ለመድሀኒትነት የሚውሉ ዕፆች ከተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ናቸው፡፡ ከመኖሪያ አካባቢያቸው፣ በቅርብ እና በርቀት ካሉ ከተራራ ላይ፣ ከወንዝ ዳር፣ ከጊቢያቸው ውስጥ እና ከእርሻ ቦታዎች፣ ከእምነት ስፍራዎች (ከፀበል ቦታ፣ ከመስጅድ አካባቢ፣ ከመንገድ ዳርና ከፍራሽ ቤቶች (ከፈረሱ ቤቶች) አካባቢ እንደሚያገኙ የዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ወሰኔለህ ጫኔ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> እኔ መድሀኒት ከምሰጣቸው በሽታዎች ውስጥ አይሬ የሚሏትን በሽታ አለች፡፡ ለዚች በሽታ የምጠቀመውን ዕፅ ከሮቢ ወንዝ ዳር አገኛለሁ፣ ትንሽ እራቅ ብዬም ከፍል ውሀ ፀበል ዙሪያ እና ከምታይው ተራራ ላይ አመጣለሁ፡፡ ለበሽታው መድሀኒት የምትሆነው ስሯ ነች፤ቅጠሏም ከአመት እስከ አመት አይደርቅም፤አይጠፋም፤እናም የታመሙ ሰዎች ሲመጡብኝ አልቸገርም፡፡ ስሯን ነቅዬ አመጣና ግንባራቸው ላይ አስርላቸዋለሁ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት27/2012)፡፡[9]

ሌላው የባህል ህክምና ባለሙያ ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆችን ስለሚያገኙባቸው ቦታዎች ሲገልፁ፡-

> ብዙ ጊዜ የማክማቸው በሽታዎች ሆድ ቁርጠት፣ እከክ እና ቁስል ለወጣበት ሰው፤ቅጠል ከጓሮዬ በጠስ አድርጌ፣ አሸት አሸት አድርጌ እሰጣቸዋለሁ፤የአላህ ፍቃድ ሆኖ ያሽራቸዋል፤አናም እሩቅ አልሄድም፤

[9] የዙጢ ኮረብታ፤ ከዙጢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤ በስተምስራቅ፤ከአካባቢው ነዋሪዎች፤በስተ ደቡብ ፤ የሚገኝ በዕፅዋት የተሸፈነ ኮረብታ ሲሆን፤የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች፤ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸውን እፆች በብዛት የሚገኙበት ቦታ በመሆኑ ከስፍራው አስፈላጊ ዕፆችን እንደሚሰበስቡ ጠቁመዋል፡፡

አዚሁ ቅያችን አለ፤በጋ ሲሆን ነው እንጂ ፀሀዩ የሚያደርቀው፤ በቀዝቃዛው ወቅት አዚሁ አገኝዋለሁ፡፡ በበጋ ታሞ የሚመጣ ሰው ካለም እዚህ ቅርብ ካለው ወንዝ ዳር ሄድ ብዬ አመጣለሁ፡፡[10] ካጣሁ ካጣሁ ደግሞ ሌላ ሀኪም ጋር እንዲሄዱ እነግራቸዋለሁ ይላሉ አቶ ኑሩሁሴን (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 7/2012) ፡፡

በተጨማሪም ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ ሙሳ ሀሰን ዕፆቹን ስለሚያገኙበት ቦታ ያስረዳሉ፡-

ለመድሀኒት የምጠቀማቸውን ቅጠሎች በቀላሉ አላገኛቸውም፤እራቅ ያለ ቦታ መሄድ ይኖርብኛል፡፡ እንዲያውም ቦታው አስፈሪ ነው፤ብዙ የዱር አራዊት አሉበት፤በተለይ እባብ እና ዘንዶ መኖሪያቸው ነው፡፡ እኔም እንኳን ያስፈራኛል፤የአላህን ትዕዛዝ ሳልጠብቅ መድሀኒት ለመቁረጥ ብሄድ ለኔም አይቀርልኝም፤ንፁህ ሆኜ ነው፤መድሀኒት ለማምጣት የምሄደው (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 5/2012)፡፡

ከአቶ ሙሳ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች በቅርበት የሚገኙ አለመሆናቸውና ዕፆቹን ለማግኘት፤ለህይወት አስጊ ወደሆኑ ቦታዎች መሄድ ግድ መሆኑን፤በዚህ ሂደት እራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጥ ሁኔታ ሊገጥማቸው እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ዕፆቹን ለመሰብሰብ ከመሄዳቸው በፊት መጽዳት፤(ሰውነትን መታጠብ፣ መጥፎ ንግግር ከመናገር መቆጠብ፣ መስገድ፣ መፀለይ እና ከፈጣሪ (ከአላህ) ጋር መታረቅ እንዲሁም ጥንቃቄ ማድረግ፤ይደርሳል ተብሎ ከሚታሰብ ቁጣ እራስን መከላከል የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ በመነሳት ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፅዋቶች እንደ በሽታው አይነት እና እንደመድሀኒቱ (ዕፆቹ) አይነትና ባህሪ የሚገኙበት ቦታ የተለያየ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንዳንድ መድሀኒቶች በቅርብ የሚገኙ፣ በጓሮ (ከአትክልት ስፍራ፣ ከሰፈር፤ከመንገድ ዳርና ፍራሽ ቤቶች (ፈርሰው ካልተነሱ ቤቶች) ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ እራቅ ካሉ ቦታዎች ከተራራዎች፣ ከደኖች፣ ከወንዝ ዳር እና ከእርሻ ቦታዎች (ከማሳ ውስጥ/ከመስኖ) የሚገኙ መሆናቸውን የቀረቡት መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

[10] ሌላው የባህል መድሀኒተኞች ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸውን ዕፆች የሚያገኙት ከሮቢት ወንዝ ዳር እና በወንዙ አቅራቢያ ከሚገኙ የፀበል ስፍራዎች አካባቢ ሲሆን አካባቢው እድሜ ጠገብ ዛፎች እና ፈውስ መሆን የሚችሉ ዕፆች የሚገኙበት ቦታ ነው፡፡ በተጨማሪም የሮቢት ወንዝ የአካባቢውን ማህበረሰብ የመስኖ ልማት ተጠቃሚ እያደረገ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

## 4.4. ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ የዕፅዋት ክፍሎች

የፍርፍር ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሸዋረገድ አጥናፉ ለመድሀኒትነት ስለሚጠቀሟቸው የዕፅዋት ክፍሎች ሲገልጹ፡-

> በቆላ ቁስል ለተያዘ ሰው፣ በአልማዝ ባለጭራ፣ እባብ ለነደፈው እንዲሁም ለተቅማጥ (ለሆድ ህመም) የሚሆን መድሀኒት እሰጣለሁ፡፡ የምጠቀመውም ዕፅዋት ነው፤ከዕፅዋቱም በአብዛኛው ቅጠላቸውን እና ከዕፅዋቱ የሚወጣውን ውሀና ደም ነው የምጠቀመው፡፡ አንዳንድ አብሮ አደጎቼ ደግሞ ስሩንም፣ ቅርፊቱንም ያደርጉታል፤እኔ ግን ቅጠሉን ነው የማዘጋጀው እና እንደ እውቀታችን፣ እንደልምዳችን ነው የምንሰጠው (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 10/2012)፡፡

የፓፓዬ ሰፈር ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ አረጋሽ ስለሚጠቀሙት የዕፅዋት ክፍል ሲገልጹ፡- “እኔ አይን ላይ የምትወጣዋን አይሬ የተባለችውን፤በሽታ ነው የማድነው፤ለሆድ ህመምና ለህጻናት በሽታም ቅጠል ቀጠፍ አድርጌ መድሀኒት እሰጣለሁ፡፡ አይሬ ለተባለችው በሽታ የምጠቀመው መድሀኒት፤ስር ነው፤ስር ነቀል አድርጌ፤በግንባራቸው ላይ እንዲያስሩ አደርጋለሁ” (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት6/2012)፡፡

ሌላው ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ ሙሳ ሀሰን ስለሚጠቀሟቸው የዕፅዋት ክፍሎች ሲያስረዱ፡- “መድሀኒት ለምሰጣቸው በሽታዎች፤ለአንዱ በሽታ እንኳን ከሶስት ወይም ከአራት አይነት ዕፅዋት፤ከአንዱ ቅጠሉን፤ከሌላው ቀንበጡን፤ከሌላው ደግሞ ስሩን እጠቀማለሁ፤በሽታው እንደሚገኝበት ደረጃ ማለቴ ነው” (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት2/2012) ፡፡

የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ከሰጡት መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ የዕፅዋት ክፍሎች አንድም፤የሀገረሰብ ሀኪሞቹ እንዳላቸው እውቀት፣ ልምድ እና አመለካከት፤አንድም እንደ በሽታው አይነት እና ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸውን ነው፡፡ የህክምና አገልግሎት የሚሰጧቸው በሽታዎች ተመሳሳይ ቢሆኑ እንኳን የተለያየ ዕፅ እና የዕፅዋት ክፍሎችን ለመድሀኒትነት ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም ተመሳሳይ በሽታ የሚያክሙ የሀገረሰብ ሀኪሞች አንዳንዶቹ የዕፅዋቱን ቅጠል ሲጠቀሙ ሌሎቹ ደግሞ የዕፅዋቱን ግንድ፣ ቅርፊት፣ አበባ፣ ቀንበጥ፣ ስርና ውሀ በመጠቀም ታማሚዎችን እንደሚፈውሱ ከመስክ የተገኘው መረጃ ጠቁሟል፡፡

ይህም የባህል ሀኪሞች ከመጡበት የዘመናት ህክምና ልምድ እና አመኔታ እንዲሁም ከታካሚዎች እምነት፣ ፍላጎት እና ተቀባይነት ጋር የተያያዘ ሲሆን፤እንደ ወቅቱ ሁኔታ ከሶስቱ አንዱ ለመድሀኒትነት የሚያገለግለው ዕፅ ቢጠፋ (ባይገኝ) የተገኙትን የዕፅ ውጤቶች እና ሶስተኛውን (የጠፋውን) ዕፅ ሊተካ የሚችለውን ሌላ ዕፅ በመጨመር፤አልያም የሁለቱን ዕፆች መድሀኒት በተለያየ ሁኔታ ማለትም በመጠን፤ደጋግሞ በመስጠት እና መጠኑን ከመደበኛው ከፍ በማደረግ ህመምተኞችን እንደሚፈውሱ አስረድተዋል። በዚህ መልኩ ያላቸውን ሀገር በቀል እውቀት በመጠቀም፤በተለያዩ በሽታዎች የተያዙ ሰዎችን በማከም ግላዊ፣ ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ ጤንነትን፣ ደህንነትን እንደሚያስጠብቁ ለመረዳት ተችሏል።

## 4.5. ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ተያያዥ እምነቶች፣ ልማዶችና የተመረጡ ቀናት

አቶ አገኘሁ የመድሀኒት ዝግጅት ላይ ስላላቸው እምነት እና ልማድ ሲያስረዱ፡-

> መድሀኒቶችን ሳዘጋጅ ለመድሀኒቱም ሆነ ለራሴ ስል የማደርጋቸው ነገሮች አሉ፤መድሀኒቱን ድንገት ተነስቼ መቁረጥ አልችልም፤ መድሀኒቶቹን ነገ የምቆርጥ ከሆነ ዛሬ ማታ ወይም ሌሊት ተነስቼ ሰውነቴን እታጠባለሁ፤መድሀኒት ለመቁረጥ እንደምሄድ፤ለልጆቼም፤ ለባለቤቴም አልናገረም፤ማንንም ሰው ባላገኝ እወዳለሁ፤ከሰዎች ጋር ከተገናኘሁና ስለመድሀኒቱ ከተናገርኩ፤መድሀኒቱ ይረክሳል፤መድሀኒት ለማዘጋጀት ጥንቃቄ ማድረግ አለብኝ፤ይህ ካልሆነ፤መድሀኒቱ ፈውስ አይሰጥም (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት29/2012) ይላሉ።

ይህንኑ አስመልክቶ አቶ ወሰኔለህ ጫኔ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

> መድሀኒት የመቁረጫ ቀናት መመረጥ አለባቸው፤በተገኘው ቀን ሁሉ መድሀኒት አይቆረጥም፤አይደለም መድሀኒት ለመቁረጥ ይቅርና ሰው እንኳን መንገድ ለመሄድ ሲያስብ፤አዲስ ቤት ለመግባት ሲወስን፤ ቅዬውን ለመልቀቅ ሲፈልግ የሚመርጣቸው ቀናት አሉ፤ትዳር ለመመስረት፤ ከሀገር ለመውጣትም የሚመረጡ ወራት አሉ። እናም እኔ መድሀኒት ለመቁረጥ ካሰብኩ ረቡዕ እና አርብን እመርጣለሁ። ይህን ማድረጌ ለእኔም ለታማሚውም ይበጃል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት26/2012)።

ሌላው የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያ አቶ ሸዋረገድ አጥናፉ በባህል ህክምና ሂደት ያላቸውን እምነትና ልማድ ሲገልጹ፡- “እኔ ለመድሀኒት ያለኝ ክብር ትልቅ ነው፤መድሀኒቶቼን አክብሬ ስለማዘጋጅ፤የሰጠሁት መድሀኒት ፍቱን ነው፤መድሀኒት አድርጌለት ያልዳነ የለም” ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት4/2012)።

ከመረጃ አቀባዮቹ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች የሚቆረጡበት፣ የሚዘጋጁበት እና ለታካሚዎች የሚሰጡበት ስርዓት እንደ ግለሰቡ፤ማህበረሰቡ፤እምነት፣ ባህል፣ ልማድ የአኗኗር ስርዓት እና አመለካከት የተለያየ መሆኑን ነው። በአካባቢው ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች መድሀኒቶችን ከማዘጋጀታቸው በፊት፣ በዝግጅት ወቅት እና ለታማሚዎች የሚሰጡበት ስርዓት፤ከቀናትና ከሰዓታት አንጻር አገልግሎት የሚሰጡበት ምክንያት እንዳላቸው ቁልፍ መረጃ አቀባዮች አስረድተዋል።

የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ ሙሳ ሀሰን መድሀኒት ስለሚቆርጡባቸው ቀናት፣ ሰዓታትና ቁሶች እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

> እኔ የእስልምና እምነት ተከታይ ነኝ። ከአባቴ ለተተፋልኝ በሽታዎች መድሀኒት እሰጣለሁ፤ከአላህ ጋር አድናለሁ፤የሚያድነው አላህ ነው፤እኛ ምክንያቶቹ ነን። ከማክማቸው በሽታዎች ውስጥ የወፍ በሽታ፣ የሆድ ቁርጠት (መንፋት)፣ እባብ ለነደፈው ሰው፣ ለህጻናት (ለአይነ ወግ) ፣ የተቅማጥ (ድንገተኛ) ፣ የቆላ ቁስል እና አይሬ የተባሉ በሽታዎች ናቸው። ይሁንና መድሀኒት ለመቁረጥ፤ቀን አልመርጥም። ሁሉም ቀናት ከአላህ የተሰጡን ናቸው፤ስለዚህ ይህ ጥሩ ቀን፤ይህ ደግሞ መጥፎ ቀን ነው፤አልልም። ታማሚዎች ታመው ወደ እኔ ከመጡ በየትኛውም ቀን መድሀኒት እቆርጣለሁ፤ እሰጣለሁ።
>
> ይሁን እንጂ ለሁሉም በሽታዎች የምቆርጣቸው መድሀኒቶች አንድ አይነት ዝግጅት የላቸውም። ለወፍ በሽታ፣ እባብ ለነደፈው ሰው እና ለልጆች፤ለአይነ ወግ (የሰው አይን) የማዘጋጃቸውን መድሀኒቶች የማመጣቸው እሩቅ ካለ ቦታ ነው። እነዚህን መድሀኒቶች ለማመጣት ከመሄዴ በፊት ገላዬን እታጠባለሁ፤እሰግዳለሁ፤ከጠዋቱ 11:00 በኋላ ነው መድሀኒቶቹ ወደሚገኙበት ቦታ የምሄደው። ከሁሉም በላይ ግን ለህጻናት (ለልጆች) የምሰጠውን መድሀኒት ለመቁረጥ ስሄድም ሆነ ስመለስ ሰዎች እንዳያገኙኝ እጠነቀቃለሁ። መድሀኒቶቹን ለማምጣት ስሄድ ሰዎች ካገኙኝ መድሀኒቶቹን ሊያዩብኝ፣ ሊጠይቁኝ፤ብዙ ሊያናግሩኝ ይችላሉ፤ይህ ከሆነ ደግሞ መደሀኒቱ ምስጢራዊ መሆኑ ይቀራል፤አይሰምርም፤ ይረክስብኛል፤ሌሎቹ ለሆድ ቁርጠት፣ ለተቅማጥ (ሆዱ ለሚነፋው ሰው) እና በድንገት ደም ለሚፈሰው ሰው (ደምን ለማስቆም) ለመድሀኒትነት የምጠቀማቸውን ዕፆች ደግሞ ከጊቢ ውስጥ አገኛለሁ።[11] እነዚህን

---

[11] የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ ሙሳ ሀሰን ጊቢ ውስጥ ለመድሀኒት የሚያገለግሉ በርካታ ዕፆች አሉ። መረጃ አቀባዬ ፍቃደኛ ሆነው ባደረኩት ምልከታ መሰረት እፆቹ በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይጠፉና በቤት ውስጥ እንስሳት እንዳይበሉ በሚል፤ በክሰሌ እሾህ ተከልለው ይገኛሉ።

በየትኛውም ጊዜ እና ሰዓት ቆርጬ አዘጋጃለሁ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት 27/2012)፡፡

አቶ ሙሳ አያይዘውም፤ለሆድ ቁርጠት (ለመንፋት)፣ለተቅማጥ እና ደም ለማስቆም የሚጠቀሟቸው ዕፆች ከጊቢያቸው ውስጥ የሚያገኙ በመሆናቸው ምንም አይነት ቁስ ሳይጠቀሙ በእጃቸው ቀጥፈው፣ በእጃቸው አሽተው፤ለታካሚዎች እንደሚሰጡ፤ታካሚዎቹም ከባህል ሀኪሞቹ የተሰጣቸውን የዕፅ ውጤት በመጭመቅ የሚሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ለአይሬ መድሀኒት የሚጠቀሟትንም ስር እንደዚሁ ዕፅዋቱን በእጃቸው በመንቀል፤ስሩን ቆርጠው ለመድሀኒትነት የሚያስቀሩ መሆናቸውንም ገልፀውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት27/2012)፡፡ እኔም በመስክ ወቅት መድሀኒቶቹን ሲቆርጡና ሲያዘጋጁ እንድመለከት ፈቃደኛ ሆነው፤ባደረኩት ምልከታ መሰረት፤የመድሀኒት መቁረጫ፣ ማዘጋጃ እና መስጫ ተብለው የተለዩ ቁሶች እንደሌላቸው አረጋግጫለሁ፡፡

በተጨማሪም አቶ ሙሳ ለሌሎቹ በሽታዎች መድሀኒት የሚሆኑ ዕፆችን ለመሰብሰብ፤ቤት ውስጥ ባገኙት (ቢላዋ፣ማጭድ፣መጥረቢያ) እንዲሁም ለዕፆቹ ማጠራቀሚያ የሚሆን ቅዳጅ ጨርቅ በመያዝ ዕፆቹን እንደሚሰበስቡ ገልጸዋል፡፡

የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ አገኘሁ ትርፌ “እኔ የማክመው በሽታ የቆላ ቁስል እና አልማዝ ባለ ጭራ ነው፡፡ ለእነዚህ በሽታዎች ግብዓት የሚሆኑ መድሀኒቶችን የምሰበስበው ከዕፅዋት ነው፡፡ መድሀኒቶችን ለመቁረጥ ከመሄዴ በፊት ሰውነቴን እታጠባለሁ፤ሰዎች ባያገኙኝ እመርጣለሁ” ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት29/2012)፡፡

እንደ አቶ አገኘሁ ገለጻ ለሚያክሟቸው የበሽታ አይነቶች ዕፆቹን ለመሰብሰብ ወደ ወንዝ ዳር ሲሄዱ፤የግል የመድሀኒት መቁረጫ ቢላዋ እና የተቆረጡትን ዕፅ መሰብሰቢያ የሚሆን ቀረጢት (ከቅዳጅ ጨርቅ በእጅ የተሰፋ መቋጠሪያ) ይይዛሉ፡፡ መደሀኒት ለመቁረጥ የሚጠቀሙት ቢላዋና መድሀኒት የሚሰበስቡበት ቀረጢት (መቋጠሪያ) ከመድሀኒታቸው ውጪ ለሌላ አገልግሎት እንደማይጠቀሙበት ገልፀውልኛል፡፡ ለመድሀኒት መውቀጫም የሚጠቀሙት ሙቀጫ፤ከመድሀኒት ውጪ ሌላ ግብዓት እንደማይወቀጥበት ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት29/2012)፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን ቁሶች፤እንደ ቅዱስ እቃ ስለሚመለከቷቸው፤ለምግብነት የሚያገለግሉ የዕፅዋትና የእንስሳት ውጤቶች በእነዚህ ቁሶች እንደማይዘጋጁ አስረድተዋል፡፡ ይህም መድሀኒት የተለየ ክብር ያለው መሆኑን ታሳቢ በማድረግ፤ሰዎችን ከበሽታ ለማዳን

የሚዘጋጅ ዕፅ፤ከሌሎች  የእለት ከእለት መጠቀሚያ ቁሶች ጋር ማነካካት ተገቢ አለመሆኑን በማመን ነው፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ አቶ ሸዋረገድ አጥናፉ ስለዝግጅታቸው ሲገልፁ፡-

> እኔ ለምቆርጣቸው ዕፆች ትልቅ ክብር አለኝ፤በጥንቃቄ ነው የማዘጋጃቸው፣ሰው ከህመሙ ለሚድንባቸውን ዕፆች ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፤ካላከበርናቸው ፈጣሪ የዘራባቸውን ፈውስ ይደብቁብናል፤ መድሀኒቶቹን ነገ ለመቁረጥ ካሰብኩ ዛሬ ማታ ገላዬን እታጠባለሁ፤ ከቤተሰቦቼ፣ ከልጆቼና ከባለቤቴ ጋር የሚያጋጭ ነገር ቢኖር እንኳን እታገሳለሁ፤ከማንም ሰው ጋር እላፊ ንግግር ላለመነጋገር እጠነቀቃለሁ፤ በማለዳ ተነስቼ ጸሎቴን አደርሳለሁ፡፡[12] ከዚያም ሰዎች ሳይነሱ መድሀኒቶቹን ከሚገኙበት ቦታ ስብስቤ፤ሰዎች ሳይነሱ ተመልሼ እደርሳለሁ፡፡ የሰበሰብኳቸውን መድሀኒቶችም ሳዘጋጅ ነጠል ብዬ ነው፤ወደ ጓሮ ዘውር ብዬ አዘጋጃለሁ፡፡ ምክንያቱም ሰዎች እያዩት የተዘጋጀ መድሀኒት ጥሩ አይሆንም፤ፈዋሽ እና ለሰዎች መፍትሔ የሚሆነው ከላይ የተናገርኳቸው ጥንቃቄዎች ሲተገበሩ እና ምስጢራዊ ሲሆኑ ነው፤ መድሀኒት መሆን የሚችሉት ብዬ አምናለሁ፡፡
>
> አቶ ሸዋረገድ አያይዘውም እነዚህን ዕፆች ለመሰብሰብ ወደሚገኙበት ስፍራ ስሄድ፤ዕፆቹን መቁረጫ ሊሆነኝ የሚችል፤ቤት ውስጥ ያገኘሁትን ብረት ነገር እይዛለሁ፤ዕፆቹን ቆርጬ በነጠላዬ ጫፍ ቋጠር አድርጌ እመጣለሁ፡፡ የሰበሰብኳቸው ዕፆች የሚወቀጡ፣ የሚደርቁ እና የሚፈጩ ከሆነ ቤት ውስጥ በምንጠቀምባቸው ቁሶች (ብረት ምጣድ፣ ሙቀጫ፣ ሳፋ) እንዲሁም ሌሎች ቁሶችን እጠቀማለሁ፡፡ ለመድሀኒት ማዘጋጃ ብዬ የለየሁት እቃ የለም፤ቤት ውስጥ ባገኘሁት በማንኛውም እቃ እቀምማለሁ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 4/2012) ይላሉ፡፡

የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ከሰጡት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው፤ለባህል ህክምና መድሀኒት ሆነው የሚያገለግሉ የዕፅ ውጤቶች ዝግጅት እንደ በሽታዎቹ አይነት እና እንደሚጠቀሟቸው ዕፆች የተለያዩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ በባህል ህክምና የሚዳኑ በሽታዎች  ከላይ የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ከሰጡት መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፤መድሀኒቶቹን ከመቁረጣቸው በፊት ሰውነታቸውን የሚታጠቡበት ምክንያት፤ሰውነትን መታጠብ ከመንጻት ጋር  ስለሚያያዝ፤ይህም የባህል ህክምና ባለሙያው ከባለቤቱ (ከሚስቱ) ጋር ግብረ ስጋ

[12] ቁልፍ መረጃ አቀባዬ፤ አቶ ሸዋረገድ አጥናፉን መድሀኒት ለመቁረጥ ከመሄዳቸው በፊት ስለሚፀልዩት ፀሎት ለመጠየቅ ሞክሬያለሁ፡፡ ነገር ግን የሰጡኝ ምላሽ “ፀሎት ለፈጣሪ እንጂ፤ለሰው አይነገርም” የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም መረጃ አቀባዬ ፈቃደኛ ሆነው መረጃውን ማግኘት ባለመቻሌ በትንተናው ውስጥ ማካተት አልቻልኩም፡፡

ግንኙነት ሊያደርግ፤ሌሎች መድሀኒቱን ሊያረክሱ፤ፈጣሪንም ሊያስቀይሙ የሚችሉ ተግባራት ሊፈጽም ይችላል የሚል እምነት ያላቸው በመሆኑና ይህ ተግባር በባህል ሀኪሞቹ አመለካከት የሚያቆሽሽ፣ መድሀኒቱ እንዳይሰራ (እንዲበርስ)፤እንዲረክስ የሚያደርግ፣ በክርስትናው (ከእግዚአብሔር)፤በእስልምናውም (ከአላህ) ጋር የሚለይ (የሚያጣላ) ነው፤ተብሎ ስለሚታመን ዕፆቹን ለመቁረጥ ከመሄዳቸው በፊት እራስን ማንጻት (ማፅዳት) ተገቢ መሆኑን ይጠቁማሉ። የባህል ህክምና ባለሙያዎች መድሀኒቶችን ለመሰብሰብና ለማዘጋጀት ዕፆቹ ወደሚገኙበት ቦታ ከመሄዳቸው በፊት ፀሎት የማድረጋቸው ምክንያት፤ፀሎት ሰውን ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ መሆኑን በማመን፤ለመድሀኒቶቹ ፈዋሽነት፤ለባለሙያውም ይቅርታን፣ ጥበብና እውቀትን እንዲሰጣቸው፤የሚቀመመው መድሀኒት እንዲሰምር፤ከሁሉ አስቀድሞ በፀሎት አላህን (ፈጣሪን) መማፀን ቀዳሚ ተግባር ነው ከሚል እምነት በመነሳት መሆኑን የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል።

በተጨማሪም መድሀኒቱን ለመቁረጥ ሰዎች ከመኘታቸው ሳይነሱ መድሀኒቱን የሚቆርጡበት ምክንያት፤ሰዎች የምድር ፍጥረታትን ከመንካታቸው በፊት መድሀኒቱን ብንቆርጥ አዳኝ ይሆናል ከሚል እምነት በመነሳት እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮቹ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል። እንደ ሀገረሰብ መድሀኒት ባለሙያዎቹ እምነት፤የሰው ልጅ በአንድም ሆነ በሌላም መንገድ በየቀኑ፤በየሰዓቱ (አላህን/እግዚአብሔርን) (ፈጣሪን) ያስቀይማል፤ይበድላል፤በተለይም በጨለማ የሚሰራው ሀጢያት እጅግ የከፋ በመሆኑ፤ከሀጢያት መልስ ፈጣሪ የፈጠራቸውን ፍጥረታት በመንካት እንዲረክሱ ያደርጋል። ይህ የሀጢያት ውጤት አዳኝ፣ፈዋሽ እና በእግዚአብሔር ወይም በአላህ ዘንድ የተመረቁ ዕፆች፤እንዲረክሱ፤የማዳን ሀይላቸው እንዲደክም (እንዲሰወር) ያደርጋል። ከዚህ አንጻር ዕፆቹ ሰው ሳይነካቸው ካልተቆረጡ (ካልተሰበሰቡ) ጥቅም አልባ ናቸው፤በሚል እምነት መድሀኒቶቹ ሰው ሳይነሳ ቢቆረጡ ለሀገረሰብ ሀኪሙ በረከት፣ ለታካሚዎቹም ፈውስ እንደሚሆኑ በማመን መድሀኒቶቹን እንደሚያዘጋጁ ለመረዳት ተችሏል።

እንዲሁም ለህጻናት (ለአይነ ወግ) የሚዘጋጁ መድሀኒቶች የተለየ ትኩረት የሚሰጡበት ምክንያት ህጻናት በፈጣሪ (በአላህ) ዘንድ ንጹህ፤በክርስትናውም፤የመንግስተ ሰማያት ምሳሌዎች፤ከየትኛውም ሀጢያት የጸዱ በመሆናቸው፤የተለዩ ናቸው ከሚል እምነት በመነሳት ለህጻናት የሚዘጋጅ መድሀኒት ሰው ሳይነሳ፣ የትኛውም እንቅስቃሴ እና የዕለት ተዕለት ተግባራት ሳይጀመሩ፤ንፅህናቸውን ከሚያጎድፍ (ከሚያቆሽሽ)፤ከየትኛውም ሰው የተለየ ጥንቃቄ

የሚደረግበት መሆን አለበት በሚል እምነት፤ የተለየ ትኩረት እንደሚያደርጉ የቀረቡት መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆች ካሉበት ስፍራ ለማምጣት እና ለማዘጋጀት እራስን ማጽዳት (ንፁህ መሆን)፤የተቆረጠው (የተሰበሰበው) መድሀኒት ፍቱን እንዲሆን ከማድረጉም በላይ፤ፈውስ መሆን የሚችሉ ዕፆች ከሀገረሰብ ህክምና ባለሙያው እንዳይሰወሩ ማድረግ የሚችሉ መሆናቸውም ተገልጧል፡፡ በሌላ በኩል ከሰዎች መራቅ፤ሰው በተኛበት ሰዓት እና ጊዜ መድሀኒቶችን ካሉበት ቦታ መሰብሰብ እና መቀመም፤መድሀኒቱ በሰዎች አይታ ውስጥ እንዳይገባ እና እንዳይረክስ በማድረግ የመድሀኒቱን ፍቱንነት ከፍ እንደሚያደርገው ተጠቁሟል፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ በማድያ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ወሰኔለህ ጫኔ እንዲህ ይላሉ፡- "እኔ የማክመው በሽታ የቆላ ቁስል፣የወፍ እና የእከክ በሽታ ነው፡፡ ለእነዚህ በሽታዎች መድሀኒቶችን የምቆርጠው እሮብ እና አርብ ነው፡፡ በእነዚህ ቀናት የሚቆረጡ መድሀኒቶች ፈዋሽ ናቸው፡፡ በጣም ካልቻልኩ እና የደከመ ሰው ከመጣብኝ ግን በየትኛውም ቀን ቢሆን እቆርጣለሁ" (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት26/2012)፡፡ መረጃ አቀባዩ እነዚህ ቀናት መንግስተ ሰማያት የሚከፈትባቸው ቀናት ናቸው፤በሚል እምነት ዕፆቹን ለመቁረጥ የሚመርጧቸው ቀናት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ሌላው ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ ደረጀ ወሰኔ መድሀኒቶቹን ስለሚሰበስቡበት እና ስለሚቀምሙበት ጊዜ እና ሁኔታ ሲያስረዱ፡-

> ለብዙ በሽታ መድሀኒት እሰጣለሁ፤ለሆድ ቁርጠት፣ ለአይሬ፣ ለወፍ፣ ለእከክ፣ ለቆላ ቁስል እና ለሌሎችም በሽታዎች መድሀኒቶችን እሰጣለሁ፡፡ ለእነዚህ በሽታዎች የማዘጋጃቸውን መድሀኒቶች የምቆርጣቸው በተመቸኝ ቀን ነው፤ቀኖችን አልመርጥም፤ ብቻ አምላኬ ሆይ የምቆርጣቸውን ቅጠሎች ለመድሀኒት በልልኝ እላለሁ፡፡ ከዚህ የቀረ የማደርገው የለኝም (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት28/2012)፡፡

ከላይ የሀገረሰብ ሀኪሞቹ ከሰጡት መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም የባህል ሀኪሞች መድሀኒቶቹን የሚሰበስቡበት፣ የሚያዘጋጁበት እና የሚቀምሙበት እንዲሁም ለታካሚዎቹ የሚሰጡበት ሰዓት እና ቀናት እንዲሁም ቁሶች ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ እንደ ባህል ሀኪሞቹ እውቀት፣ ልምድ፤እንደ በሽታው አይነት፤ስለ መድሀኒቶቹ እና ስለ በሽታው እንዳላቸው እምነት እና አመለካካት፤እንደሚከተሉት ሀይማኖት ስርዓት፣ ለዘመናት እንዳለፉበት የአኗኗር ዘይቤ እና ነገሮችን እንደሚያጤኑበት የአረዳድ ሁኔታ  የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሰውንም ሆነ

ፈጣሪን ማስቀየም፣ ቅድመ ዝግጅቶችን መዘንጋት፣ የመድሀኒት ስብሰባ፣ ቅመማ እና አሰጣጥ ሂደት ማዛባት፤ስርዓተ ገቢር ማጓደል የሚያስከትለው መጥፎ እድል አለ፤ብለው በሚያምኑና በሚተገብሩ የባህል ሀኪሞች ላይ ቅጣት ሊያመጣ፤በመኖር እና ባለመኖር ስጋት ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት ተችሏል።

ለመድሀኒት መቁረጫ፣ መውቀጫ ማድረቂያ እና መዘፍዘፊያ የሚጠቀሟቸው ቁሶች እንደ ባለሙያዎቹ ልማድና አመለካከት፤አንዳንዶቹ ለመድሀኒት መቀመሚያ የሚጠቀሟቸውን ቁሶች በጥንቃቄ እና በክብር ከሌሎች የእለት ተዕለት አገልግሎት ሰጪ ቁሶች በመለየት መድሀኒቶችን የሚያዘጋጁ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በቅርብ ባገኙት ቁስ፤መድሀኒቶችን የሚያዘጋጁ መሆኑን፤ ይህም በመድሀኒቶቹ ዝግጅት ላይ ካላቸው እምነትና ልማድ አንፃር የሚለያዩ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

በመሆኑም በአካባቢው የሚገኙ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች፤እራስን አፅድቶ መድሀኒት ካልተቆረጠ መድሀኒቱ አያድንም፣ መድሀኒቱም ሰው ካየውም ሆነ ለሰው ከተነገረ ይረክሳል፤ይበርሳል፣ ለመድሀኒቱ ክብር ካልተሰጠ ፈውስ አይሆንም፣ ለመድሀኒቶቹ መቁረጫና ማዘጋጃ የሚሆኑ የተለዩ ቁሶች መጠቀም አስፈላጊ ነው፣ ፀብ፤ክርክርና ክፋትን ማራቅ ለመድሀኒቱ ፍቱንነት ወሳኝ መሆኑን በማመን እነዚህን የመድሀኒት ዝግጅት ልማዶቻቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ። በአንዳንድ የባህል ሀኪሞችም ረቡዕ እና አርብ ለመድሀኒት መቁረጫ የሚመርጧቸው ቀናት መሆናቸውም ተገልጧል። ይህም በአካባቢው ማህበረሰብ በተለይም በባህል ሀኪሞች ዘንድ ክፉ ነገር ማድረግ፣ ፀብና ክርክርን ማንገስ፣ መቆሸሽ፣ ሰላምን ማጣትና ማሳጣት፣ ክፋትና ተንኮል በልብ ውስጥ መያዝ፣ ንቀት እና ትዕቢት ከፈጣሪ ዘንድ (ከእግዚአብሔር/ከአላህ) የሚያጣላ፤ የሚያርቅ፤የሚለይ ነው የሚል የጋራ እምነት አላቸው። ይህም ፈዋሽ የሆኑ ዕፆችን በመሰወር እና የሚቆረጡ መድሀኒቶች ፈውሰ አልባ እንዲሆኑ ምክንያት ይሆናል በሚል እምነት ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ለማወቅ ተችሏል።

## 4.6. ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ ሂደት

በሸዋሮቢት ከተማና እና አካባቢዋ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያዩ በሽታዎቸ ይጠቃሉ። እነዚህን በሽታዎች ለመከላከል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የባህል ሀኪሞች ከተለያዩ ዕፆች በሚገኙ ግብዓቶች እራሳቸውን ከበሽታ ይከላከላሉ። ከዕፅዋት ከሚገኙ አበቦች፣ ስራስር፣ ግንድ፣ ቅጠልና እና ፍሬ አብሮ በመውቀጥ፣ በመፍጨት፣ በመቀላቀል መድሀኒቶችን ያዘጋጃሉ። እነዚህ መድሀኒቶች የሚዘጋጁት እንደ በሽታው አይነት፣ እንደ ሀገረሰብ ሀኪሞቹ የህክምና

ልምድ እና እንዳላቸው እውቀት የሚወሰን ሲሆን በተለያየ መልክ ተዘጋጅተው ለታካሚዎች ይሰጣሉ፡፡

እንደ አቶ ወሰኔለህ ጫኔ ገለጻ፡- “ለተለያዩ በሽታዎች መድሀኒት አዘጋጃለሁ፡፡ መድሀኒቶቹንም የማገኘው ከዕፅዋት ነው፤የማገኛቸውን የዕፅዋት ውጤቶች በመውቀጥ፣ በመፍጨት፣ በመቀጥቀጥ እንዲሁም ከዕፅዋቶቹ ላይ የምፈልገውን የዕፅዋት ክፍል በቀጥታ እጠቀመዋለሁ” (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት19/2012) ይላሉ፡፡

በተጨማሪም አቶ ሙሳ ሀሰን “መድሀኒቶቹ ከተለያየ ቦታ ተቆርጠው ወይም ስራቸው ተቆፍሮ አልያም ግንዳቸው ተልጦ ከተሰበሰበ በኋላ እንደ በሽታው አይነት በመውቀጥ፣በመፍጨት፣ በማድረቅና በመቀቀል ይዘጋጃሉ” በማለት ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት27/2012)፡፡

የባህል መድሀኒት ባለሙያዎቹ ከሰጡት መረጃ በመነሳት በባህል ህክምና ለመድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ ዕፅዋትን፤ይዘት፣ ዓይነት፣ ጣዕም እና ባሕርይ በመለየት፤ከዕፅዋት ግብዓት፤ ከሰብሎች፣ ከዛፍ፣ ከሥራሥር እና ፍራፍሬዎች፣ የሀረግ እና የሣር ዓይነቶችን ይለያሉ፡፡ እነዚህ ዕፆች ከተሰበሰቡና ከተለዩ በኋላ እንደ ሀገረሰብ መድሀኒተኞች እውቀት፣ ልምድ እና ስርዓት፤እንደበሽታዎቹ አይነት፤ከዕፅዋቱ፤ቅጠል፣ ቀንበጥ፣ አበባ፣ ፍሬ፣ ሥር፣ ግንድ፣ ቅርፊት እና መሰል ይዘቶችን፤ነቅለው፣ ለቅመው፣ ቆርጠው፤ሰብስበው እንደ በሽታዎቹ አይነትና እንደ ባለሙያዎቹ እውቀት እና ልምድ፤ደርቀው፣ ተፈጭተው፣ ተወቅጠው፣ ተነፍተው፣ ተዘፍዝፈው እና ተቀቅለው በተለያየ አይነት፣ መጠንና ክንውን የቅመማ ሂደቱ እንደሚከናወን የቀረቡት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የሀገረሰብ ሀኪሞች ለመድሀኒትነት የሚጠቀሟቸው የዕፅዋት አይነቶች የተለያየ ይዘት፣ ጣዕም፣ ሽታና ስያሜ ያላቸው ሲሆኑ፣ እንደ በሽታው አይነት እና ባህሪ ከቅጠላቸው፣ ከግንዳቸው፣ ከፍሬያቸው፣ ከቅርፊታቸው፣ ከዕፆቹ ውሀ፣ ከስሮቻቸው ላይ አስፈላጊ ግብዓቶችን በመውሰድ በአይነት፣ በይዘት እና በመጠን ለይተው፤አዘጋጅተው ለታካሚዎች ይሰጣሉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የበሽታዎቹ አይነት፣ መድሀኒት መሆን የሚችሉ የዕፅዋት አይነቶች፤አዘገጃጀት እና የአሰጣጥ ሂደታቸው፤በቅድም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 4.6.1. ለቆላ ቁስል (አንትራክሲ) የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በዚህ በሽታ ሲያዙ ከተለያዩ የዕፅዋት አይነቶች መድሀኒቶች ያዘጋጃሉ፡፡ የዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሙሳ ሀሰን ስለመድሀኒቱ ሲገልጹ፡- ለዚህ በሽታ በግብዓትነት የሚጠቀሟቸው ዕፆች፤ዕፀ ልቡና፣ አሜራ እና የጀሞ ቅጠል የተባሉ የዕፅዋት አይነቶች ናቸው፡፡ አንድ ሰው በሰውነቱ ላይ  የድካም፣ የመቁሰል እና በቁስሏ ላይ መጎድጎድ ምልክቶችን ሲያይ ወደ ባህል ህክምና ባለሙያዎች ይሄዳል፡፡ ይህ በሽታ ሁለት አይነት ሲሆን ወንዴ እና ሴት ይባላል፡፡ ወንዴ የቆላ ቁስል በታማሚው ላይ ቁስሉ አይሰፋም፣ በእጅጉም አይጠዘጥዝም እንዲሁም በታማሚው ላይ ያለው የህመም ስሜት በአንጻራዊነት የቀነሰ ሲሆን ሴቴ የቆላ ቁስል፤በታማሚው ሰውነት ላይ የሚወጣው ቁስል ከወንዴው በተወሰነ መልኩ የሰፋ እና ታማሚውን በማድከም በአፋጣኝ ለሞት የሚያዳርግ ነው፡፡

በአብዛኛው በሴቴ የቆላ ቁስል የተያዘ  ሰው የመዳን እድሉ ጠባብ መሆኑን የባህል ህክምና ባለሙያው ይገልጻሉ፡፡ በህክምና ጊዜ የበሽታው ልዩነት የሚታየው የመድሀኒቱ መጠን እና መድሀኒቱ የሚያደርግበት ቀን ብዛት እንጂ፤የመድሀኒት ልዩነት የለውም፡፡ ሀገረሰባዊ ሀኪሞቹም፤ዕፀ ልቡና፣ አሜራ እና የጀሞ ቅጠል ከተባሉት ዕፅዋት፤ቅጠሎቻቸውን በመውሰድ አድርቆ መውቀጥ፤ከዚያም በደንብ የደቀቀውን ለመለየት መንፋት፣ ተነፍቶ የተለየውን እና የደቀቀውን መድሀኒት (ዱቄት)፤ በቅባት (ጭቃ ቅባት) እና በጥቂት ውሀ በመለወስ በጥንቃቄ ቁስሏ ላይ ብቻ (ሌላውን ገላ እንዳይነካው) በማድረግ መቀባትና በሀበሻ ጨርቅ ማሰር ነው፡፡ መድሀኒቱ ሲቀባ፤በሽታውን እንዳገኘው የሚታወቀው፤ታካሚው፤ቁስሉ በጣም ይጠዘጥዘዋል፤ እስከ ልቡ ድረስ ይሰማዋል፤መድሀኒቱን ካሰረ በኋላ ወንዴ የቆላ ቁስል ከሆነ በሶስት ቀን ውስጥ ይድናል፤ሴቴ የቆላ ቁስል ከሆነች ደግሞ ሰባት ቀን ትቆያለች፤ከሰባት ቀን በኋላ ትጠፋለች፡፡ ታካሚው ከመድሀኒቱ ባሻገር መዳን የሚችለው ወተት፣ ስጋ እና ዳቦ መብላት ማቆም ሲችል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምግቦች ገንቢ እና ሀይል ሰጪ በመሆናቸው ቁስሉ ላይ ያሉ በአይን የማይታዩ ነፍሳቶች እንዳይሞቱ ይበልጥ እንዲጠነክሩና የመድሀኒቱ የማዳን ሀይል እንዲቀንስ በማድረግ፤ቁስሉን በማባባስ እስከ ሞት ሊያደርስ ይችላል፡፡ በሽታው ከታማሚው ውስጥ እስቀመጨረሻው እንዲነቀል (እንዲጠፋ) ማድረግ አይቻልም፤ከሁለት እስከ ሶስት አመት ድረስ በታማሚው ውስጥ ተደብቆ ሊቆይ እና በእነዚህ አመታት ውስጥ በሽታው በታማሚው ላይ ሊመለስ (ሊያገረሽ) ይችላል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት13/2012)፡፡

ፎቶ ግራፍ 4. ዕፀ ልቦና (ለቆላ ቁስል) የሚዘጋጅ መድሀኒት



ፎቶ ግራፍ 5. የጀሞ ቅጠል (ለቆላ ቁስል)



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን18/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.2. ለአልማዝ ባለጭራ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

መረጃ አቀባዬ እንደሚሉት አልማዝ ባለጭራ በሽታ በአካባቢው በብዛት ማህበረሰቡን ከሚያጠቁ በሽታዎች አንዱ ሲሆን በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው በሰውነቱ ላይ ሽፍታ ይታይበታል፤ውጋትና ሳል አለው፤ቁስሏ ባረፈችበት ገላ ላይ የተቅመዘመዘ (ዚግዛግ) የሚመስል መስመር ያበጃል፤ በመስመሩ ዙሪያ እትር እትር ይላል፤ዙሪያውን ይቆስላል፡፡ የዚህ አይነት ምልክት የታየበት ሰው በአካባቢው የሚገኙ የባህል ሀኪሞች ጋር በመሄድ ከተለያዩ ዕፅዋቶች የተቀመመ መድሀኒት ይሰጠዋል፡፡

የሀገረሰብ ሀኪሞቹ ለመድሀኒቱ በግብዓትነት የሚጠቀሟቸው ዕፅዋቶች፡- አሜራ፣ የእንኮይ ቅጠል፣ ጎጂ ቅጠል፣ አደሪ (ከሰሌ)፣ ዕፀ እስራኤል (ቀጠጥላ) እና ጎርጠብ የተባሉ ዕፆችን ሲሆኑ ከእነዚህ እፆች ላይ ቅጠላቸውን መውሰድ፤አንድ ላይ በማድረግ ማድረቅ ከዚያ መውቀጥ፣ ኪዚያም በፋልዚን (በቅባት) ለውሶ ቁስሏ ያለችበት ቦታ ላይ በጣት እየቆነጠሩ መቀባት ፍቱን መድሀኒት ሲሆን፤በሌላ በኩል ደግሞ ቅጠሎቹን እርጥቡን መውቀጥ፣ ከዚያም ለአንድ ሰው ሁለት ማንኪያ፤አንዱን ማንኪያ ለሶስት ቀን፤አንዱን ማንኪያ ደግሞ ለሶስት ቀን መቀባት፤በስድስት ቀናት ውስጥ ታካሚውን ሙሉ ለሙሉ ያድነዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በሽታ ለመዳን መድሀኒቱን መውሰድ ብቻ ሳይሆን፤ወተት፣ ስጋ፣ ዳቦ እና ጠላ መድሀኒቱን በማብረስ (የማዳን ሀይሉን በማጥፋት) ፤በሽታውን የሚያነግሱ በመሆናቸው ታካሚው ከእነዚህ ምግቦች መከልከል አለበት፡፡ በዚህ በሽታ (7-15 አመት) እድሜ ያላቸው ታዳጊዎች ቢያዙ መድሀኒቱም ሆነ መጠኑ አይለይም፡፡ ምክንያቱም መድሀኒቱ ወደ ሆድ ስለማይገባ (ስለማይጠጣ)፤አይጎዳም፤መጠኑም አይለይም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በሽታው ልጆችን (ህጻናት)

አያጠቃም፤በስፋት ወጣቶች እና ጎልማሶች ላይ ይታያል  አቶ አገኘሁ ትርፌ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት15/2012)።

ፎቶ ግራፍ 6. ዕፀ እስራኤል (ቀጠጥላ) ፤(ለአልማዝ ባለጭራ) የሚዘጋጅ መድሀኒት



(ምንጭ፦ በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 23/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.3. ለችፌ በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

ሌላው በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያጠቃው ችፌ የተባለው በሽታ ነው። አቶ ኑሩሁሴን ለዚህ በሽታ መድሀኒት ግብዓትነት የሚጠቀሟቸው ዕፅዋቶች እንድኳኩላ እና ዕፀ ዋጊኖስ ሲሆኑ ዲኒ በተጨማሪነት የሚያገለግል ግብዓት ነው።

ከእነዚህ ዕፅዋቶች የእንድኳኩላ ስሩ፣ የዕፀ ዋጊኖስ ቅጠልና ፍሬው እንዲሁም ዲኒ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ናቸው። የእንድኳኩላውን ስር መውቀጥ፤ማድረቅ እንደገና መውቀጥ፤ከዚያ ዕእፀ ዋጊኖሱን ቅጠል እና ፍሬ መውቀጥ ከዚያ ማድረቅ፤ከዚያም እንደገና መውቀጥ፤መንፋት፤ ዲኒውንም መውቀጥ (ሶስቱም ለየብቻ ይዘጋጅና ይቀመጣል)። ከሶስቱም ዕፆች ተነፍቶ የተቀመጠውን (የላመ/የደቀቀውን) ለየብቻ ማስቀመጥ፤ታካሚ በመጣ ጊዜ ከሶስቱም ውጤቶች፤ አንድ አንድ ማንኪያ (ሶስት ማንኪያ) አንድ ዕቃ ላይ በማጠራቀም፤አንድ ማንኪያ ቅቤ

ቀላቅሎ፤ በጣት እየቆነጠሩ በሽታው ከታካሚው ላይ እስከሚጠፋ ድረስ መቀባት ፍቱን መድሀኒት መሆኑን (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት13/2012) ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል ለችፌ በሽታ መድሀኒት የሚያዘጋጁበትን መንገድ አቶ ኑሩሁሴን ሲያስረዱ፡-

የደጋ አበሎ ፍሬ እና የምድር እንቧይ በመፍጨት በማር ለውሶ፤ሁለት ማንኪያ፤ለሰባት ቀናት ያህል መቀባት ፍቱን መድሀኒት መሆኑን ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት13/2012)፡፡

ፎቶ ግራፍ 7. ዕፀ ዋጊኖስ (ለችፌ በሽታ) የሚዘጋጅ መድኃኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 21/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.4. እባብ ለነደፈው ሰው የሚዘጋጅ መድሀኒት

ለጥናት የተመረጠው አካባቢ ሞቃታማ በመሆኑ የተለያዩ አጥቢ ነፍሳቶች እንዲራቡ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም መርዛማ የሆኑ፣እንደ እባብ አይነት ተሳቢ እንስሳት ማህበረሰቡን ያጠቃሉ፡፡ በእባብ የተነደፈ ሰው፣የተነደፈበት ቦታ አይታይም፣ነገር ግን የእባቡ መርዝ በፍጥነት በሰውነቱ ስለሚሰራጭ፣ልብ በፍጥነት ይደክማል፣ይህን ለመከላከል በአካባቢው ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በአካባቢው በሚገኙ፣የእሬት ውሀ (ከዕፁ ላይ የሚወጣውን ውሀ መጠጣት) እና የአሞራ ምሳ ስሩን ማኘክ ፍቱን መድሀኒት ነው ይላሉ አቶ አህመድ ጀማል (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት12/2012)፡፡

አቶ አህመድ አያይዘውም እባብ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብበት አካባቢ የአህያ ጆሮ የተባለውን ዕፅ ስሩን መያዝ፣ጎማ ማጨስ፣ተናዳፊው እባብ እንዲርቅ፣እንዳይቀርብ ያደርጋል፡፡ ከነከሰ (ከነደፈ) ደግሞ የአህያ ጆሮ የተባለውን ዕፅ ስሩን ቀጥቅጦ መጠጣት መርዙ እንዲበርስ ያደርጋል፣በማለት አስረድተዋል፡፡

ፎቶ ግራፍ 8. እሬት (እባብ ለነደፈው ሰው) የሚዘጋጅ መድሀኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፣በቀን19/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.5. ለአይሬ በሽታ የሚዘጋጅ መድሀኒት

አይሬ፤አይን ላይ የሚወጣ በሽታ ሲሆን በዚህ ሀመም የተያዘ ሰው አይኑ ይቀላል፤ያቃጥላል እንዲሁም አይንን በእንባ እየሞላ ለማየት እንዲቸገር ያደርጋል፡፡ የዚህ አይነት ህመም የተሰማው ሰው ወደ ሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች ይሄዳል፡፡ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎቹም የህዶድ ዕፅ ስሯን፤ከድር (ለሽመና አገልግሎት የሚያገለግል) ላይ ክር በመበጠስ፤ስሩን በክሩ ላይ መጠምጠም፤ከዚያም በግንባር ላይ እንዲያስሩ ማድረግ፤ከሶስት ቀን በኋላ ታማሚው በግንባሩ ላይ ያሰረውን ስር መንታ መንገድ ላይ እንዲጥለው ይታዘዛል፤በዚህ መሰረት ታካሚው በግንባሩ ላይ ያሰረው መድሀኒት ሶስት ቀን ከሞላው በኋላ አይኑ፤ወደ ቀድሞ ጤንነቱ ይመለሳል፡፡ ሆኖም አይሬ የተባለው በሽታ ከታማሚው ላይ የሚነሳው በስሯ ላይ ሆኖ በመሆኑ፤ታካሚው በታዘዘው መሰረት ያሰረውን ስር መንታ መንገድ ፈልጎ መጣል ይኖርበታል፡፡ መንታ መንገድ የመሆኑ ምክንያት፤አይሬ በሽታ ላይ ያለው መንፈስ አንዳንድ መንገዶችን ስለማይወዳቸውና የሚሸሽ በመሆኑ ስሩ መንታ መንገድ ላይ መጣል አለበት፡፡ ስለሆነም ስሯ መንታ መንገድ ላይ ከተጣለች በሽታው ከታማሚው ላይ ተነስቶ፤ከሁለቱ መንገዶች አንዱን መርጦ ይሄዳል፤ነገር ግን ስሯ የተጣለችው መንታ መንገድ ላይ ካልሆነ፤ በሽታው ከታማሚው ላይ ተነስቶ ለመሄድ ያለው አማራጭ አንድ መንገድ ብቻ በመሆኑ፤ያንን መንገድ ካልወደደው፤ወደ ታማሚው ሊመለስ ይችላል በሚል እምነት፤ታማሚው የግድ መንታ መንገድ ፈልጎ እንደሚጥል ይደረጋል፡፡ ሆኖም ከታማሚው ውጪ ቤተሰብ፣ ዘመድ ወይም ጓደኛ፤ታማሚው ያሰራትን ስር መንታ መንገድ ላይ እንዲጥል ቢደረግ፤በሽታው ታማሚውን እንደማይለቅና ይበልጥ እንደሚባባስ ወ/ሮ አረጋሽ ሽታዬ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት26/2012) ይገልጻሉ፡፡



ፎቶ ግራፍ 9. ህዶድ (ለአይሬ በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት

(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 27/06/2012 የተነሳ

#### 4.6.6. ለእከክ ፣ ሰውነትን ለሚያቆስል እና ለማዲያት የሚዘጋጅ መድሀኒት

በተለያየ የሰውነት ክፍል ላይ ለሚያሳክክ እና ለሚቆስል እንዲሁም ፊት ላይ ለሚወጣ ማዲያት እሬት (አንጉስተር) የተባለው ዕፅ ለመድሀኒትነት የሚያገለግል ሲሆን ሴቴ እና ወንዴ እሬት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ሁለቱም ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ሲሆን ወንዴ እሬት በጣም ይመራል፤ሴቴ እሬት መራራ ጣዕም የለውም፡፡ ዝግጅቱም፡- እሬቱን መቅጠፍ፤ከዚያ መውቀጥ፤ ከዚያ ማስጣትና ከደረቀ በኋላ መውቀጥ፤የደቀቀውን ለመለየት ይነፋል፤በደንብ የደቀቀውን እና በወንፊት የተለየውን በቅቤ መለወስ፤ፊት ላይ ከሆነ ሰባት ቀን በጣት እየቆነጠሩ መቀባት፤ በሌላ የሰውነት ክፍል ላይ ከሆነ ሶስት ቀን ይቀባል፤በፍጥነት ፍቱን መፍትሄ እንደሚያስገኝ አቶ ኑሩሁሴን (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት18/2012) አስረድተዋል፡፡

ፎቶ ግራፍ 10. እሬት (ለእከክ፣ሰውነት ለሚያቆስል እና ለማዲያት) የሚዘጋጅ መድሀኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 25/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.7. ለወፍ በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

በሸዋሮቢት አካባቢ ሌላው ማበረሰቡን ከሚያጠቁ በሽታዎች ውስጥ የወፍ በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ በዘመናዊው ሀክምና 'ጉበት' በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን በባህል ህክምና፤የሌሊት ወፍ በሰው ጭንቅላት ላይ ስትዞርና ሽንቷን ስትሸና ታማሚው በበሽታው እንደሚያዝ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ በሽታ የተያዘ ሰው በከፍተኛ ደረጃ የምግብ መቀነስ፣ ድካም፣ ሽታ (የምግብ መሽተት)፣ የሰውነት መዛል፣ የአይን ቀለምና የሽንት ቀለም ወደ ቢጫነት መቀየር እንዲሁም ሌሎች ምልክቶች ይታዩበታል፡፡ ለዚህ በሽታ 'አጎብዲ' የተባለውን ዕፅ ስር  መፈቅፈቅ፤ከዚያ ፀሀይ ባለበት ቀን (ምንም አይነት ደመና በሌለበት) ጊዜ  በሳፋ (በዝርግ ዕቃ) ውሀ በማድረግ የተፈቀፈቀውን የአጎብዲ ስር መነስነስ፤ከዚያም ለአንድ ሰዓት ያህል እንዲቆይ ማድረግ እና ታካሚው ከተዘፈዘፈው መድሀኒት ሶስት ጊዜ ፉት እንዲል (እንዲቀምስ) ማድረግ በቀሪው ገላውን/ዋን እንዲታጠብ/እንድትታጠብ ማድረግ ከበሽታው የሚፈውስ መሆኑን አቶ አውራሪስ ፍቃዴ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት19/2012) ያሥረዳሉ፡፡

አቶ አውራሪስ አክለውም፤ለወፍ በሽታ መደሀኒት ሆኖ የሚያገለግለው የወይባ ቅርፊት ከወንዴ ፓፓዬ ቅጠል ጋር አንድ ላይ አድርጎ መውቀጥ፤ከዚያም መቀቀል እና የተቀቀለውን ለሶስት ቀናት ያህል በባዶ ሆድ መጠጣት በሽታውን ከታማሚው ሰው ላይ ነቅሎ እንደሚያወጣው (እንደሚያጠፋው) (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት19/2012) ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በሽታው ከታካሚው ውስጥ ጨርሶ እስከሚጠፋ ድረስ የስንዴም ሆነ ከአጃ ዱቄት የተዘጋጀ፤ዳቦ መብላት፣ ስጋ፣ ወተት በአጠቃላይ ጣፋጭ ምግቦችን መመገብ ለበሽታው መንስኤ የሆነችውን ወፍ በማጠንከር፤በሽታውን በማባባስ፤መድሀኒቱ፤በሽታውን መፈወስ እንዳይችል፤ በሽታው እንዲበረታና መድሀኒቱ የማዳን ሀይል እንዲያጥረው በማድረግ ታማሚውን ለሞት ሊዳርገው ይችላል፡፡



ፎቶ ግራፍ 11. አጎብዲ (ለወፍ በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት

(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 29/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.8. ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ለሆድ መንፋት የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

በተጠኘው ማህበረሰብ፤ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ሆዱን ለነፋው ሰው ከዕፅዋት የሚዘጋጁ መድሀኒቶች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለሶስቱም የሆድ በሽታዎች ተመሳሳይ መድሀኒት እንደሚሰጡ አቶ ጀማል መሀመድ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት17/2012) ነግረውኛል፡፡ አዘገጃጀቱም፡- የአለብላቢት (የእንቧይ ስር) ከመሬት ተቆፍሮ ይወጣና፤ሀኪም ከሚባለው ዕፅ፤ ቅጠሉን መውሰድ እንዲሁም አውጥ ከተባለው ዕፅ፤ቅጠሉን አንድ ላይ አድርጎ መውቀጥ ከዚያም መጭመቅ፤ተጨምቆ የወጣው ፈሳሽ መድሀኒት ነው፡፡ መድሀኒቱ፤ለልጆች (17 አመት በታች ላሉ) የሚሰጥ ከሆነ በቆርኪ (አንድ ቆርኪ) መስጠት፤ለትልቅ ሰው ከሆነ ደግሞ በሲኒ (አንድ ሲኒ) እንዲጠጣ ማድረግ ለሆድ ቁርጠት፤ሆዱን ለሚነፋው ሰው እና ለተቅማጥ ፍቱን መድሀኒት መሆኑን አቶ ጀማል መሀመድ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት17/2012) ገልፀውልኛል፡፡

ፎቶ ግራፍ 12. እንቧይ (ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ለሆድ መንፋት) የሚዘጋጅ መድሀኒት



ፎቶ ግራፍ 13. አውጥ (ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ለሆድ መንፋት) የሚዘጋጅ መድኃኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 02/07/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.9. ለላሽ የሚዘጋጅ መድሀኒት

አካባቢው ሞቃታማ የአየር ንብረት ያለው በመሆኑ 'ሴጉር' የተባሉ ተህዋሲያን እንዲራቡ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ለራስ ፀጉር መበላት ምክንያት ይሆናሉ አቶ አውራሪስ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት15/2012)። በመሆኑም በተለየ ሁኔታ በወንዶች የራስ ፀጉር ላይ የመመለጥ (የመበላት) ምልክቶች ይታያሉ። ይሁን እንጂ ሴቶች በአብዛኛው የፀጉር ቆዳቸው ስለማይደርቅ እና ወዛማ ስለሚሆን፤ተህዋሲያኑን የቆዳው ወዝ እንደልብ ለመንቀሳቀስ ስለማያመቻቸው ከሴቶች የራስ ፀጉር ላይ ይረግፋሉ። በዚህ ምክንያት በሽታው ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን በብዛት ያጠቃል። ይህን የጤና ችግር ለመፍታት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች፤ግዛዋ ከተባለው ዕፅ ላይ የሚወጣውን ደም፣ ዕፀ ፋርስ (አስተናግድ) የተባለውን ዕፅ ቅጠል አንድ ላይ አድርገው በመውቀጥ እና የተወቀጠውን መድሀኒት ከጥቂት ማር ጋር በመቀላቀል ለሰባት ቀን ያህል በተደጋጋሚ መቀባት የተበላው (የተመለጠው) ፀጉር እንደገና እንዲያቆጠቁጥ እና ሴጉር የተባሉት ተህዋሲያን እንዲሞቱ በማድረግ ፀጉርን ወደ ቀድሞው ሁኔታው መመለስ የሚያስችል መድሀኒት መሆኑን አቶ አውራሪስ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት15/2012) ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል።

ፎቶ ግራፍ 14. ግዛዋ (ለላሽ በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 08/07/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.10. ለምች በሽታ የሚዘጋጅ መድሀኒት

በተጠኘው ማህበረሰብ ለምቺ በሽታ ለመድሀኒትነት የሚውሉ ዕፆች በርካታ ናቸው። ለዚህ በሽታ፤ዳማ ከሴ፣ ጢብጢቦና ጋሜ ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፅዋቶች ሲሆኑ እነዚህ ዕፆች ከተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ናቸው። አዘገጃጀቱም፡- የዳማከሴ ቅጠል፣ ጢብጢቦ እና ጋሜ ከተባሉ ዕፆች ላይ፤ቅጠሎቻቸውን በመውሰድ አንድ ላይ ታሽቶ እና ተጨምቆ ሰውነትን መቀባት እንዲሁም ከመጀመሪያ (ከአቦል) አንድ ሲኒ ቡና ጋር ቀላቅሎ መጠጣት ከበሽታው እንደሚፈውስ አቶ ደረጀ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት20/2012) ይገልጻሉ።

ይህንን አስመልክቶ በአብዛኛው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የባህል ሀኪሞች፤ለዚህ በሽታ ተመሳሳይ መድሀኒት እንደሚያዘጋጁ ነግረውኛውል።

ፎቶ ግራፍ 15. ዳማከሴ (ለምች በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት



ፎቶ ግራፍ 16. ጋሜ (ለምች በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት



(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 04/07/2012 የተነሳ ፎቶ)

### 4.6.11. ለኪንታሮት በሽታ የሚዘጋጁ መድሀኒቶች

በኪንታሮት በሽታ የተያዘ ሰው፤ኪንታሮቱ ያረፈበት ቦታ ላይ በተለየ ሁኔታ ይደድራል፤ ከሌላው ገላ በተለየ ይጠብቃል፤ሌላው የሰውነት ክፍል የላላ ነው የሚሆነው፡፡ ለዚህ በሽታ የተለያዩ የዕፅዋት ክፍሎች ለመድሀኒትነት ይውላሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የአዞ ሀረግ፣ አቹች እና ቁልት የተባሉት ዕፃች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

አዘገጃጀቱም፡- የአዞ ሀረግ፤ሀረጓን መቀጥቀጥ፤ከዚያም በሽታው ያረፈበትን የታካሚውን ገላ በምላጭ መቅፈፍ (ማንሳት)፤ከዚያም ከሀረጓ የሚወጣውን ውሀ ቁስሉ ላይ ጠብ፣ ጠብ ማድረግ፤በሽታውን ያጠፋዋል፡፡

በተጨማሪም አቹች እና ቁልት ለኪንታሮት በሽታ መደሀኒት የሚሆኑ ናቸው፡፡ አዘገጃጀቱም፡- ስራቸው ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ በብረት ድስት መቀቀል፤ለሁለት ቀናት ያህል ከተቀቀለ በኋላ፤ ታማሚው ጠዋት በባዶ ሆዱ (ምንም ሳይቀምስ)  ሁለት ሲኒ ይጠጣል፤ ለሶስት ቀን ያህል በተደጋጋሚ ስድስት ሲኒ እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ በአብዛኛው ይህ የዕፅዋት መድኃኒት ኪንታሮቱ ለረጅም ጊዜ በታማሚው ላይ የቆየ ከሆነና በቀላሉ መዳን እንደማይችል ካመኑበት፤ ለታካሚዎች የሚሰጥ የመድኃኒት አይነት ነው አቶ መንገሻ ሀይሌ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 19/2012) ይላሉ፡፡ [13]



ፎቶ ግራፍ 17. አቹች (ለኪንታሮት በሽታ) የሚዘጋጅ መድሀኒት

(ምንጭ፡- በጥናቱ አቅራቢ፤በቀን 30/06/2012 የተነሳ ፎቶ)

[13] የዚህ ጥናት ትኩረት ሀገረሰባዊ የእፅዋት መድሀኒቶች ላይ መሆኑ የተጠቆመ ቢሆንም የአካባቢው የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለአንዳንድ በሽታዎች የሚሰጧቸው መድሀኒቶች ላይ ከእንስሳት እና ከማዕድናት የሚገኙ ግብዓቶችን ያካትታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በመድሀኒት ቅመማ ጊዜ እነዚህ ግብዓቶች ባይጨመሩ የመድሀኒቱን የማዳን ሀይል አንደማይቀንስው እና ግብዓቶቹ ሊቀሩ የሚችሉ መሆናቸውን ገልፀውልኛል፡፡ ከዚህ አንጻር በአካባቢው ያሉ የባህል ህክምና ባለሙያዎች የሚያዘጋጇቸው መድሀኒቶች በአብዛኛው ከእፅዋት የሚዘጋጁ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

በአጠቃላይ የባህል መድኃኒት ቅመማ ሂደት የዕፅዋትን ዓይነት፣ ይዘትና ባሕርይ በመለየት የሚከወን ሲሆን፤ጊዜ እና ሰዓት ጠብቀው እንደሚሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የመድኃኒት ግብዓት አሰባሰብ እና ቅመማ ሂደቱም፤ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆችን ካሉበት ቦታ በመሰብሰብ፣ በማድረቅ፣ በመውቀጥ፣ በማጣራት፣በመንፋት፣ ለመድሀኒት የሚያገለግለው የዕፅ ውጤት ከተለየ በኂላ ልዩ ሙያ፣ ተግባር፣ ዕውቀት፣ ጥንቃቄ እና ትኩረት በመስጠት የመድኃኒት ቅመማ ይካሄዳል፡፡ ከላይ (ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ተያያዥ እምነቶች፣ ልማዶችና የተመረጡ ቀናት) በሚለው ክፍል ውስጥ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው አንዳንድ መድሀኒት ቀማሚዎች ከሰው ተለይተው፤ተደብቀወና ልዩ ጥንቃቄ አድርገው መድሀኒቱን የሚያዘጋጁ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ከጊቢያቸው ውስጥ ያገኟቸውን ዕፆች፤ያለቅድመ ሁኔታ፤ቆርጠው፤ አዘጋጅተው እንደሚሰጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም እንደ ባህል ህክምና ባለሙያዎቹ እምነት፣ እንደሚያክሙት የበሽታ አይነት እና ባህሪ የሚለያይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህ ጥናት የሀገረሰባዊ መድሀኒት ቀማሚዎች፤በመድሀኒት ዝግጅት ወቅት፤የባለሙያዎቹን ፍቃደኝነት ታሳቢ በማድረግ፤በከፊል ባደረኩት ምልከታ በመድኃኒት ቅመማ ወቅት፤ የመቀመሚያ ግብዓት፣ የመድኃኒት ግብዓት አያያዝ እና የቅመማ ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ገንዘብን፣ ዕውቀትን እና ተሰጥኦን አስተባብረውና አቀናጅተው እንደሚከወኑ ተመልክቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ በመድሀኒት ቅመማ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮች፤የአቀማመም ሂደቱን በማዛባት፣ ግብዓቱን ማጓደል፣ እንዲሁም እንደ እምነት እና ስርዓቱ የሚደረሰውን ፀሎት፣ ልመናና ሌሎች ክንዋኔዎች ማስቀረት፤መድሀኒቱን ፈውስ ከማሳጣት ባሻገር ሕመምን በማባባስ፤ ለሞት የሚዳርግ መሆኑን አቶ አገኘሁ ትርፌ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት4/2012) ገልጸውልኛል፡፡[14]

[14] በትንታኔው ክፍል ለመድሀኒትነት ግብዓት የሚሆኑ ዕፆች ፎቶ ግራፍ በከፊል የቀረቡ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

### 4.7. በሸዋሮቢት አካባቢ ጎልተው የሚታዩ የበሽታ አይነቶችና የመድኃኒቶች አሰጣጥ በሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የበሽታው አይነት | የዕፅ አይነት | የመድሀኒት ዝግጅትና አሰጣጥ | የመድሀኒቶቹ አሰጣጥ፤በእድሜ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቆላ ቁስል | ዕፀ ልቦና፣ አሜራ እና የጀሞ ቅጠል | ከሶስቱም ዕፆች ቅጠላቸውን መውሰድ፤ አድርቆ መውቀጥ፤ የደቀቀውን በፋልዚን እና በጥቂት ውሀ ቀላቅሎ መቀባትና በሀበሻ ጨርቅ ማሰር | ለየህጻናት እና የአዋቂዎች የመድሀኒት መጠን ጋር እኩል ይሰጣል፡፡ |
| 2 | የአልማዝ ባለጭራ በሽታ | አሜራ፣ እንኮይ፣ አደሪ (ከሰሌ)፣ ዕፀ እስራኤል (ቀጠጥላ) እና ጎርጠብ | ከዕፆቹ ላይ ቅጠሎቻቸውን፣ መውሰድ፤ ማድረቅ፤ መውቀጥ፤መንፋት ከዚያም ተነፍቶ የተለየውን መድሀኒት ከፋልዚን ጋር ቀላቅሎ፤ ቁስሏ ያለችበት ቦታ ላይ በጣት እየቆነጠሩ መቀባት፤ አልያም ቅጠሎቹ ሳይደርቁ መውቀጥ እና መቀባት፡፡ | በአልማዝ ባለጭራ በሽታ ለተያዘ፤ በየትኛውም የእድሜ ክልል ያለ ሰው በእኩል መጠን መድሀኒቱ ይሰጣል፤ ከእርጥቡ ቅጠል የተዘጋጀውን መድሀኒት ደግሞ ለአንድ ሰው ሁለት ማንኪያ ማድረግ፤አንድ ማንኪያ ለሶስት ቀን፤ አንዱን ማንኪያ ደግሞ ለሶስት ቀን፤ባጠቃላይ ለስድስት ቀን መቀባት፡፡ |
| 3 | የችፌ በሽታ | እንድኳኩላ፣ ዕፀ ዋጊኖስ፣ የደጋ አበሎ እና የምድር እንቧይ | ከእንድኳኩላ ስሩን መቀጥቀጥ፣ እና ዕፀ ዋጊኖስ ከተባለው ፤ ቅጠልና ፍሬውን መውሰድ እና መውቀጥ፤ ዱቄ ለብቻው መውቀጥ፤ ሶስቱንም ለየብቻ ማስቀመጥ፤ ታካሚዎች ሲመጡ ከሶስቱም አንድ፣ አንድ (ሶስት) ማንኪያ በመውሰድ መቀላቀል እና ከአንድ ማንኪያ ቅቤ ጋር መለወስ እና ከዚያም በሽታው እስከሚጠፋ ድረስ መቀባት፡፡ በተጨማሪም የደጋ አበሎ ፍሬውን እና የምድር እንቧይ በመፍጨት በማር ለውሶ ሁለት ማንኪያ ለሰባት ቀን መቀባት፡፡ | ለሁሉም የእድሜ ክልል፤የመድሀኒቱ መጠን ተመሳሳይ ነው፤ ሶስት ማንኪያ፤በሽታው እስከሚጠፋ ድረስ ይቀባል፡፡<br><br>እንዲሁም ሁለቱን ማንኪያ ደግሞ ለሰባት ቀን በጣት እየቆነጠሩ መቀባት፡፡ |
| 4 | እባብ ለነደፈው ሰው | እሬት እና የአሞራ ምሳ | ከእሬቱ ላይ ውሀውን መጠጣት እና የአሞራ ምሳ የተባለውን ዕፅ ስሩን ማኘክ | በማንኛውም እድሜ ውስጥ ያለ ሰው በእባብ ሊነደፍ፤ መድሀኒቱም ሆነ መጠኑ እኩል ነው፡፡ |
| 5 | ለአይሬ በሽታ | ሀዶድ | የሀዶድ ዕፅ፤ በክር በመቋጠር፤ በግንባር ላይ ማሰር | ለልጆችም ሆነ ለአዋቂዎችም ተመሳሳይ ነው፡፡ |
| 6 | ለእከክ፣ ሰውነትን ለሚያቆስል እና ለማዲያት | አሬት | እሬት መቅጠፍ ፣መውቀጥ፤ማስጣት፣ በድጋሜ መውቀጥ እና የደቀቀውን መድሀኒት በቅቤ መለወስ ከዚያም በሽታው ፊት ላይ ከሆነ ለሳባት ቀን ያህል መቀባት፤ በሌላ የሰውነት ክፍል ላይ ከሆነ ሶስት ቀን መቀባት፡፡ | በሁሉም የአድሜ ክልል ሊከሰቱ የሚችሉ ሲሆን የሚሰጠው መድሀኒት በመጠንም ሆነ በይዘት ተመሳሳይ ነው፡፡ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | ለወፍ በሽታ | አጎብዲ፣ ወይባ እና የወንዴ ፓፓዬ ቅጠል | የአጎብዲውን ስር መፈቅፈቅ፤ፀሀይ ባለበት ቀን ማስጣት፤ከዚያም ሳፋ ላይ ውሀ ማቅረብና የተፈቀፈቀውን የአጎብዲ ስር መነስነስ፤ ከዚያም ለአንድ ሰዓት ያህል እንዲቆይ ማድረግ እና ታካሚው ከተዘፈዘፈው መድሀኒት ላይ ሶስት ጊዜ እንዲቀምስ ይደረጋል፤ በቀሪው ገላውን እንዲታጠብ ማድረግ፤ እንዲሁም የወይባ ቅርፊት እና የወንዴ ፓፓዬ ቅጠል አንድ ላይ አድርጎ መውቀጥ፤ መቀቀል እና ለሶስት ቀን ያህል በባዶ ሆድ መጠጣት፡፡ | ለአዋቂዎች ሶስት ጊዜ እንዲቀምሱ ይደረጋል፤ ለታዳጊዎች እና ለህጻናት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲቀምሱ ይደረጋል፤ በቀሪው መድሀኒትም ገላቸውን እንዲታጠቡ ይደረጋል፡፡<br><br>የሁለተኛው መድሀኒት መጠን ለህጻናት፣ለታዳጊዎች እና ለአዋቂዎች እኩል ይሰጣል፡፡ |
| 8 | ለተቅማጥ፣ ለሆድ ቁርጠት እና ሆዱን ለሚነፋው ሰው የሚሰጥ | እንቧይ፣ ሀኪም እና አውጥ | ቅጠላቸውን መውሰድ ፤ መቀላቀል ፤ መውቀጥ፤ተጨምቆ የወጣውን ፈሳሽ መጠጣት ፡፡ | ለአዋቂዎች አንድ ሲኒ ይሰጣል፤ ከ17 አመት በታች ላሉ ደግሞ አንድ ቆርኪ ይሰጣል፡፡ |
| 9 | ለሳሽ በሽታ | ግዛዋ እና ዕፀ ፋርስ (አስተናግድ) | ከዕፆቹ ላይ ቅጠላቸውን መውሰድ፤ቀላቅሎ መውቀጥ፤የተወቀጠውን መድሀኒት ከጥቂት ማር ጋር ቀላቅሎ ለሰባት ቀናት በተደጋጋሚ መቀባት፡፡ | ለአዋቂዎችም ሆነ ለህጻናት እኩል ለሰባት ቀን ያህል እንዲቀቡ ይታዘዛል፡ ፡ |
| 10 | ለምች በሽታ | ዳማከሴ፣ ጢብጢቦ እና ጋሜ | ቅጠሎቻቸውን መውሰድ ፤ አንድ ላይ አድርጎ በእጅ መዳፍ ማሸት እና የሚወጣውን ፈሳሽ ከመጀመሪያ (አንድ ሲኒ) ቡና ጋር ቀላቅሎ መጠጣትና ሰውነትን ማሻሸት፡፡ | ለአዋቂዎች በአንድ ሲኒ ቡና ሲሰጥ፤ ለህጻናት ደግሞ የሲኒ ግማሽ ያህል እንዲጠጡ ይደረጋል፡፡ |
| 11 | ለኪንታሮት በሽታ | የአዞ ሀረግ፣ አቹች እና ቱልት | ከአዞ ሀረግ፤ሀረጓን መቀጥቀጥ እና ቁስሉ ያረፈበት የታካሚውን ገላ በምላጭ መቅፈፍ ፤ ከተቀጠቀጠው ሀረግ የሚወጣውን ፈሳሽ በቁስሉ ላይ ማፍሰስ፤ እንዲሁም አቹች እና ቱልት ከተባሉት ዕፆች ስራቸውን ቆፍሮ ማውጣት እና ለሁለት ቀን ያህል በብረት ድስት መቀቀል፣ ከሁለት ቀን በኂላ ታካሚው ጠዋት ተነስቶ በባዶ ሆድ መጠጣት፡፡ | በኪንታሮት በሽታ የሚያዙት አዋቂዎች ሲሆኑ ታካሚው በባዶ ሆዱ የተቀቀለውን የአጎብዲ ስር በየቀኑ፤ ሁለት ሲኒ፤ በሶስት ቀን ውስጥ ስድስት ሲኒ ያህል እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡<br>እንዲሁም ሀረጉን ቀጥቅጦ፤ከሀረጉ የሚወጣውን ፈሳሽ ቁስሉ ላይ ማፍሰስ፡፡ |

**ምንጭ፡- በመስክ ወቅት ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎች (ከየካቲት 10-መጋቢት10/2012 ዓ.ም)**

## 4.8. የሀገረሰብ ህክምና እውቀት እና ተስተላልፎ

በጥናቱ አካባቢ የሚገኙ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች የህክምና ጥበቡን ከቤተሰብ፣ ከወዳጅ ዘመድ፣ እንዲሁም ቅርበት ካላቸው ሰዎች እንዳገኙ በመስክ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

በዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ አህመድ ጀማል ስለ ሀገረሰብ ህክምና እውቀት ምንጫቸው እንዲህ ያስረዳሉ፡-

> እኔ ይህን እውቀት ያገኘሁት ከእናቴም ከአባቴም አይደለም፡፡ ያደኩት ከባዳ ጋ ነው፤አባትዬው በጣም ይወዱኝ ነበር፤እኔም ታዛዣቸው ነበርኩ፡፡ የሚያክሙትን በሽታ እና መድሀኒቶቹንም ነገሩኝ፤ “ልጄ አደራ ድሆችን እንዳታሰቃይ፤ይልቅስ ገንዘብ እንኳን ይዘው ባይመጡ እንዳትመልስ፤ ባይኖራቸው እንኳን አድናቸው” አደራ ብለውኛል፤ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አባታችን መድሀኒት ለመቁረጥ ሲደክማቸው እና እየሸመገሉ ሲሄዱ እኔ ተተካሁ፡፡ በዚህ መልኩ ነው እውቀቱን ያገኘሁት ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት1/2012)፡፡

አቶ አህመድ አያይዘውም ያላቸውን ሀገር በቀል እውቀት የሚያስተላልፉበትንና ይህን እውቀት የሚቀበለው አካል (ልጅ) ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታ ሲያስረዱ፡-

> እኔም ወደፊት አቅሜ ሲደክም ለአንዱ ልጄ መድሀኒቶቹ ምን ምን እንደሆኑ እነግረዋለሁ፡፡ አሁንም ለወንዱ ልጄ ነግሬዋለሁ፤ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አያውቅም፡፡ ሙሉ ለሙሉ እንዳያውቅ ስለምፈልግ ነው ያልነገርኩት፡፡ ምክንያቱም ልጁ ገንዘብ የሚያታልለው ነው፡፡ አሁን እንኳን መድሀኒት ቆርጬ ቤት አስቀምጥና እገሌ የተባለው ሰው ሲመጣ ስጠው ብዬ አዘዋለሁ፤እኔ በሀያ እና በሰላሳ ብር የምሰጠውን መድሀኒት፤ ልጄ ከሆነ ከሶስት እስከ አራት መቶ ብር ይቀበላቸዋል፡፡ አቅሜ እየደከመ ሲሄድ፤ለወንዱ ልጄ ሙሉ በሙሉ ብነግረው፤ድሆችን ያስለቅስብኛል፤ የጠየቃቸውን ገንዘብ መክፈል የማይችሉ ሰዎች ይሞታሉ፤እኔ ደግሞ እንደዚህ እንዳደርግ አይደለም የተተፋልኝ፡፡ ሴቷ ልጄ ገራገር ነች፤ለሰው አዛኝ እና ልቧ ገር ነው፡፡ ያለኝን እውቀት ለሷ መርቄላት ብሞት ቅርማይለኝ ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት1/2012)፡፡

አቶ አህመድ የባህል ህክምና እውቀቱን፤ከአሳዳጊያቸው ጋር በነበራቸው ቅርበት እና ለአሳዳጊ አባታቸው በነበራቸው ታዛዥነት እንዳገኙት ገልፀዋል፡፡ አቅማቸው እየደከመ ሲሄድ ያላቸውን እውቀት ለሴት ልጃቸው በማስተላለፍ የተሰጣቸውን አደራ እንደሚወጡም አስረድተዋል፡፡

ሌላው የጫሬ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሽዋረገድ ከወላጅ አባታቸው ስላገኙት ስለባህል ህክምና አውቀት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

> እኔ ይህንን እውቀት ያገኘሁት ከአባቴ ነው፡፡ ልጅ ሆኜ አባቴ ወደ ጓሮ ዘወር ብሎ መድሀኒት ሲያዘጋጅ አየው ነበር፡፡ ከቤተሰባችን ውስጥ አባታችን በህይወት በነበረበት ዘመን ወደ ሀኪም ቤት ሄደን አናውቅም፡፡ አባታችን እኛ ከታመምንበት ወደ ጫካ ሄድ ብሎ፤መድሀኒት ቆርጦ ያመጣና ይሰጠናል፤ወዲያው እንድናለን፤አባቴም ቢሆን ዘመናዊ ሀኪም ነክቶት አያውቅም፤ለራሱም መድሀኒቱን ያዘጋጃል፤የሞተውም በ92 አመቱ ነው፡፡ የመጀመሪያ ልጁ ስለነበርኩና በጣም ስለሚወደኝ፤ህይወቱ ሲያልፍ ሁሉንም አስረድቶኝ ነው የሞተው፡፡ አባቴ ካረፈ በኋላ የነገረኝን መድሀኒት እየቆረጥኩ ለማንም ሰጥቼም፤አድኜም አላውቅም ነበር፡፡ በአንድ አጋጣሚ ወደ ባህርዳር ሄድኩ፤ባህርዳር ዙሪያ ወደ ገጠሩ አካባቢ ነበር የሄድኩት፤በዚያ እንዳለሁ ክፉኛ ታመምኩ አብረውኝ የነበሩ ጓደኞቼ ወደ ዘመናዊ ሀኪም ቤት ይዘውኝ ሄዱ፤ነገር ግን ምንም ለውጥ አልነበረኝም፤ከሀኪም ቤት ከወጣሁ በኋላ ጓደኞቼን አካባቢው ላይ ጫካ ወዳለበት ቦታ እንዲወስዱኝ ነገርኳቸው፤ከዚያም ያድኑኛል ያልኳቸውን ዕፆችን ቆርጬ፤ጨምቄ ጠጣሁ፤ ወዲያው ተሻለኝ፡፡
>
> ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው መድሀኒት እየቆረጥኩ ለታማሚዎች መስጠት የጀመርኩት፡፡ ባህር ዳር ሆኜ በዚያ አይነት ህመም የታመምኩት፤የአባቴን ቃል ባለማክበሬ፤በህመም ለሚሰቃዩ መፍትሄ ባለመስጠቴ፤የታዘዘብኝ ቅጣት ነው ብዬ ነው የተቀበልኩት፡፡ አሁን ለብዙ አይነት በሽታዎች መድሀኒት እየሰጠሁ እገኛለሁ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት29/2012)፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ አገኘሁ ትርፌ እውቀቱን ስላገኙበት መንገድ ያስረዳሉ፡-

> ጎረቤታችን የተከበሩ ትልቅ ሰው ነበሩ፡፡ ለአካባቢው ማህበረሰብ መድሀኒት እያዘጋጁ ይሰጣሉ፤አንቱ የተባሉ መድሀኒተኛ ነበሩ፡፡ ሰውዬው ልጅም ሚስትም አልነበራቸውም፤ታዲያ እኔን ከልጅነቴ ጀምሮ በጣም ይወዱኝ ነበር፤እኔም ከሳቸው ቤት አልጠፋም፡፡ ከረሜላውን፣ብስኩቱን እየገዙ ይሰጡኛል፡፡በጣም ነው የምወዳቸው፤ያዘዙኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ልብሳቸውን አጥባለሁ፤ቤታቸውን እጠርጋለሁ ብቻ ያዘዙኝ ሁሉ በደስታ ነው የምፈጽመው፡፡ እድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ “ልጄ እኔ እድሜዬ እየገፋ ነው፤አንተ ደግሞ ገና ልጅ ነህ፤ብዙ በሽተኞችን ለማዳን ጊዜ አለህ፤ትንሽ ትንሽም ፍራንክ ታገኝበታለህ፤ነገር ግን ገንዘብ ከሌላችሁ አላድንም፤መድሀኒት አልቆርጥም እንዳትል አደራ፤የማውቃቸውን

> መድሀኒት መሆን የሚችሉ ቅጠሎች ልንገርህ" ብለው የሚያውቁትን ሁሉ ነግረውኝ ከእሳቸው ጋር እየተከተልኩ ስለመድሀኒት አቀማመሙ እየተማርኩ ቆየሁ፡፡ አሁን እሳቸው በህይወት የሉም፡፡ ባገኘሁት እውቀት፤ይሄው ታማሚዎች ታመው ሲመጡ መድሀኒት እየሰጠሁ ብዙ አመት ሆነኝ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት4/2012)፡፡

በአጠቃላይ ከህገረሰብ ህክምና ባለሙያዎቹ ከተገኘው መረጃ በመነሳት የባህል ህክምና እውቀት ለመዳ እንደ አኗኗር ሁኔታ፣ እንደ አላቸው ቤተሰባዊ ቅርበት እና ማህበራዊ ወዳጅነት የሚወሰን ሲሆን አንዳንዶቹ የባህል ሀኪሞች ከወላጅ ቤተሰባቸው፣ ሌሎቹ፤ካሳዳጊዎቻቸው እንዲሁም ከሚቀርቧቸው የቅርብ ሰዎች እና ከወዳጆቻቸው ያገኛሉ፡፡ የሀገረሰብ ሀኪሞቹ፤ የተሰጣቸውን አደራ ካልተወጡና ያላአግባብ ስዎችን ካንገላቱ፣ አቅመ ደካሞችን እና ገንዘብ የሌላቸውን ካላዳኑ እና የተሰጣቸውን (የተተፋላቸውን) እውቀት፤ገንዘብ ለመሰብሰብ ከተጠቀሙበት ወይም የህክምና ስርዓቱን ካዛቡ ለህመም ወይም ለሞት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ከቀረቡ ምንጮች ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመሆኑም መድሀኒት ማለት፤ለማንኛውም ሰው የማይነገር፤ምስጢራዊ፤ነገር ግን ታሞ ለመጣ ለማንኛውም ሰው በአነስተኛ ክፍያ የሚሰጥ፤ለሀብታምና ለደሀ ተብሎ የማይለይ፤ገንዘብ ላላቸውና ለሌላቸውም የማይከለከልለ ድህነት፤ለፈወስ የተዘጋጀ፤የፈጣሪ (የእግዚአብሔር/የአላህ) ስጦታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.9. የሀገረሰባዊ መድሀኒት ምስጢራዊነት

ስለ ሀገረሰባዊ መድሀኒት ምስጢራዊነት በመስክ ያገኘኋቸው ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ ኑሩሁሴን እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

> መድሀኒት ለማንም አይነገረም፤መድሀኒቱም የሚሰራው ለተመረቀለት (ለተተፋለት) ሰው ብቻ ነው፤አላህ ለመረጠው እንጂ ለማንም ከተነገረ መድሀኒቱ አያድንም፤መድሀኒቱ መብረሱ ብቻ ሳይሆን አደራውን በልቶ፤ ሚስጥሩን ያወጣ ሰው፤ለሞት ወይም ለአካል ጉዳት ይዳርጋል፡፡ ለምሳሌ እኔ መድሀኒቱ የተተፋልኝ ከአባቴ ነው፤አባቴም ሲሞት፤ ለወደድኩት ልጄ እንጂ ለማንም እንዳልናገር ቃል አስገብቶኛል፡፡ በዚህ ምክንያት ለማንም ሰው አልናገርም፤ይህን ቃል አፍርሼ ብናገር፤መድሀኒቱን የምቆርጠው ከጫካ ውስጥ ነው፤በዚያን ጊዜ እባብ አና ዘንዶ ሊነድፈኝ፣ ልሞት እችላለሁ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት28/2012)፡፡

እንደ አቶ ኑሩሁሴን ገለጻ እነዚህን መድሀኒቶች ለባዕድ እና ለሌሎች ሰዎች ምስጢራቸውን አሳልፎ መስጠት እንዲሁም መድሀኒቶቹን አራክሶ ሰዎች እንዲያውቋቸው ማድረግ መድሀኒቶቹ እንዳይፈውሱ ከማድረጉም በላይ በባህል ህክምና ባለሙያው ላይ ቅጣት ሊደርስበት

(ሊታመም ወይም ሊሞት) እንደሚችል፤ከመድሀኒቱ ጋር አብሮ ያለ ሀይል መኖሩን በማመን ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

ሌላው መረጃ አቀባዬ አቶ አውራሪስ ስለ ባህል መድሀኒቶች ምስጢራዊነት እንዲህ ይገልጻሉ፡-

> መድሀኒት፤መድሀኒት መሆን የሚችለው በምስጢር ሲያዝ ነው፡፡ ደግሞ የተደበቀ ነገር ነው፤ውድ የሚሆነው እንጂ አደባባይ የወጣ ምንም ነገር ይረክሳል፡፡ መድሀኒት ለማንም አይነገርም፤ለማንም መንገር፤ፈጣሪ በዕፆቹ ላይ የዘራውን ፈውስ እንዲነሳቸው (እንዲሰወሩ) ያደርጋል፡፡ እኔም ለሌሎች ከተናገርኩ መድሀኒቱ ድጋሜ አይሰራልኝም፤ ከልጆች እንኳን ለአንድ ልጅ ብቻ ነው የሚነገረው፤ለሁሉም አይነገርም፤ከተነገረ መድሀኒቱም ይረክሳል፤የዚህ ዘመን ልጆች ደግሞ ገንዘብ ስለሚያታልላቸው፤ከመድሀኒት ሽያጩ በሚገኘው ገንዘብ እርስ በርሳቸው ሊጣሉ ይችላሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ለማንም ሰው መድሀኒት አልነግርም፡፡ እኔ እንዲያውም መድሀኒቶቼን ለታካሚዎቼ አዘጋጅቼ ስሰጥ፤ለመድሀኒትነት የተጠቀምኳቸው ዕፆች ተለይተው እንዳይታወቁብኝ፤በደንብ አድቅቄ (አልሜ) ነው የምሰጣቸው (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት1/2012)፡፡

በተጨማሪም አቶ ደረጀ መድኃኒቶቹ ለምን ምስጢራዊ እንደሚሆኑ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> ለብዙ በሽታ መድሀኒት አዘጋጃለሁ፡፡ የማዘጋጃቸው መድሀኒቶች ከየትኛው ዕፅ የተቀመሙ እንደሆኑ ለማንም አልናገረም፡፡ መናገርም አልፈልግም፤መድሀኒት የሚሆኑ ዕፆች ፈዋሽ (አዳኝ) እንደሆኑ ሁሉ ገዳይም ናቸው፡፡ ዕፅዋት፤በቅርፊታቸው፣ በግንዳቸው፣ በአበባቸው እና በቅጠላቸው ላይ መርዝ ይይዛሉ፡፡ በሌላ በኩልም በዕፅዋቱ ቅርፊት ላይ መርዝ ያላቸው፤ቅጠላቸው መድሀኒት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ዕፆች በስም አውቆ መድሀኒት አዘጋጃለሁ ቢል ሰዎችን ሊጎዳ ይችላል፡፡ ምክንያቱም መድሀኒት መሆን የሚችሉ የዕፅዋት ክፍል በቅጡ ባለመረዳት ማለቴ ነው፡፡ ይህ የምቀምማቸውን መድሀኒቶች ምስጢራዊ ለማድረጌ ቀዳሚው ምክንያቴ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የማዘጋጃቸውን መድሀኒቶች ለሰዎች ብናገር ከመድሀኒት ሽያጩ የማገኘውን ገቢ ላጣ እችላለሁ፡፡ ስለዚህ የምሰራቸውን መድሀኒቶች ለማንም አልናገርም (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት3/2012)፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የባህል መድሀኒት ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ሳኒ አሊ ባህላዊ መድሀኒት ምስጢራዊ መሆናቸው ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

> በአንድ ወቅት አብሮ አደጎቼ አንዲት ዕፅ “ይቺ ምላስ ጎልጉል ትባላች” ብለው አሳዩኝ፤ እኔም ያቺን ዕፅ በአጋጣሚ መንገድ ላይ አገኘኋት፤እንደ

> ቀልድ እሰኪ ልሞክራት ብዬ ቅጠሏን በጠስ አድርጌ አፌ ውስጥ አስገባኋት፤አላህ ሲቆጣኝ ምላሴ ተጎለጎለ፣ መናገር አልቻልኩም ከዚያም በአካባቢው የነበሩ ሰዎች አይተውኝ፤ለባለቤቴ ነገሯት፤ መድሀኒተኛ ፈልገው ወሰዱኝ፤ያ መድሀኒተኛ፤ያችኑ ዕፅ በጥሶ አመጣና ምላሴ ላይ አደረጋት፤ወዲያው ተሰበሰበልኝ፤ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቅጠል መንካት እፈራለሁ፤ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ዕፆች፤በሽተኛም ያደርጋሉ፣ እናም ከደረሰብኝ ችግር አንጻር መድሀኒት የሚሆኑ ዕፆችን ማንኛውም ሰው ሊያወቃቸው አይገባም፤ ምስጢራዊ መሆን አለባቸው ባይ ነኝ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት1/2012)፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ከሰጡት መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ምስጢራዊነታቸው፤አንዳንዶቹ ስለመድሀኒቶቹ ከተመረቀለት (ከተተፋለት) ባለቤት ውጪ ለሌላ ሰው ከተነገሩ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ (በሀገረሰብ ሀኪሙ ላይ) በመሆናቸው፤አንዳንዶቹ ደግሞ ለብዙ ሰዎች ከተነገሩ እና ከባለሙያዎቹ ውጪ ሌሎች ሰዎች ካወቋቸው ይረክሳሉ፤ የማዳን ሀይላቸው ይቀንሳል ተብሎ ስለሚታመን፤ሌሎቹ ደግሞ የባለሙያዎቹን እውቀት ላለማባከን፤ከመድሀኒት ሽያጩ የሚገኘውን ገቢ ላለማጣት እንዲሁም የባለቤትነት መብቱን ለማስጠበቅ በሚል እምነት መድሀኒቶቹን ምስጢራዊ እንደሚያደርጓቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የሀገረሰብ ህክምና እውቀት ምስጢራዊነትን በተመለከተ፤ለመድሀኒት በግብዓትነት የሚያገለግሉ ዕፆች ሁለት አይነት ገፅታ ያላቸው መሆኑ፤ይኸውም ዕፅዋቱ፤አዳኝ እና ገዳይ (መድሀኒትና መርዝን) የያዙ፤ (በሽታም፤መድሀኒትም) መሆናቸው፤ ከሀገረሰብ ሀኪሞቹ ውጪ ስለዕፆቹ በቂ ግንዛቤ ያለው ባለመኖሩ፤የባህል ህክምና እውቀቱን ካገኙበት፤ቤተሰብ፣ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ፤መድሀኒቱን ምስጢራዊ አድርገው ሊይዙ የገቡትን ቃል ለማክበር ሲሉ፤ መድሀኒቶቹ የተለየ መንፈሳዊ ሀይል ያደረባቸው ናቸው ከሚል እምነት፤በተፈጠረ ስጋትና ፍርሀት ምክንያት፤የባህል ህክምና እውቀቱን ውስብስብ፤ምስጢራዊ (ድብቅ) እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞም የባህል መድሀኒት ባለሙያዎቹ፤መድሀኒት መሆን የሚችሉና የማይችሉ የዕፅዋት ክፍሎች በቀላሉ ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ፤በግዴለሽነት፤ትኩረት ባለመስጠት፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሰዎች ሊጎዱ እንደሚችሉ በማሰብ ምስጢራዊ ሆነው እንዲቆዩ አድርገዋቸዋል፡፡

## 4.10. ዘመናዊ ሀኪሞች ለሀገረሰባዊ ህክምና ያላቸው አመለካከት

የዙጢ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት የህክምና ባለሙያ አቶ ደምሴ ዘውዴ ስለ ባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ሲያስረዱ፡-

ከአካባቢያችንም ሆነ ከሌሎች አካባቢዎች በርካታ ታካሚዎች በተለያየ በሽታ ተይዘው ወደ እኔ ህክምና ተቋም ይመጣሉ፡፡ በቁስል፣በሆድ ህመም፣ በድንገተኛ አደጋ እና በሌሎች በሽታዎች ተይዘው ይመጣሉ፡፡ ታዲያ አስፈላጊው ህክምና ከመደረጉ በፊትም ይሁን ህክምናውን ካገኙ በኋላ ህይወታቸው የሚያልፍ ታካሚዎች በርካቶች ናቸው፡፡ በተለይ ቁስል በተለያየ የአካል ክፍሎቻቸው ላይ ወጥቶባቸው ህክምና ለማግኘት የሚመጡ ታካሚዎች፣ብዙዎቹ ይሞታሉ፡፡ እኔም በአንድ ወቅት ታምሜ ነበር፣በዚሁ በእኔ ጤና ጣቢያ ውስጥ ባልደረቦቼ ህክምናውን ቢያደርጉልኝም ጤናዬ ሊመለስ አልቻለም፡፡ ሊጠይቁኝ የመጡ የሰፈር ሰዎች በሽታው በባህል ህክምና የሚድን መሆኑን ሲነግሩኝ አቅራቢያዬ ወደሚገኙ አቶ ሀሰን የተባሉ እውቅ የባህል ሀኪም ጋር ሄድኩ፣ እርሳቸው ዘመናዊ ሀኪም መሆኔን ያውቃሉ፣እኔም እርሳቸውን በደንብ አውቃለሁ፡፡ “ለምን መጣህ አንተ እኮ የተማርክ ሰው ነህ፣ሰዎችን የምታድን ሰው እንዴት ወደኔ ትመጣለህ” አሉኝ፣የታመምኩት እጄ ላይ ቁስል ወጥቶ ነበርና ማየት ጀመሩ፣ይህ ነው የማልለው ህመም ይሰማኛል፣በጣም ከባድ ጊዜ ነበር፡፡ ትንሽ ቆይተው መድሀኒት ይዘው መጡ፣በሀበሻ ጨርቅ ጥብቅ አድርገው አሰሩልኝ፡፡ በየሶስት ቀኑ እየፈታሁ እንዳስረው ነገሩኝ፣ያዘዙኝን ሁሉ አደረኩ፣በሰባተኛው ቀን ሙሉ ለሙሉ ተሻለኝ፡፡

ከዳንኩ በኋላ አቶ ሀሰን ቤታቸው አስጠሩኝ እና ሄድኩ ”አንተ የተያዝከው በቆላ ቁስል በሽታ ነው፣አንተ የተማርክ ሀኪም ነህ፣ነገር ግን ይህን በሽታ ማዳን አትችልም” አሉኝ፡፡ ቀጥለውም “ልጄ ባለማወቅ በዚህ በሽታ ተይዘው ወደ አንተ ይመጣሉ፣አንተም መርፌ ትወጋቸዋለህ፣እናም አይድኑም፣ይሞታሉ፣ሳታውቅም ቢሆን ነፍስ ታጠፋለህ፣ይች ቁስል መርፌ አትወድም፣መርፌ እየወጋህ የገደልካቸው ብዙ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ እንደዚህ አይነት ህመም ታሞ የሚመጣን ሰው መርፌ እንደማትወጋ ቃል ግባልኝ” አሉኝ፡፡ እኔም ባየሁት እና በእሳቸው እውቀት ተገርሜ ቃል ገባሁላቸው፣ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በዚያ አይነት በሽታ የተያዘ ሰው ወደ እኔ ከመጣ አላክምም፣ወደ አቶ ሀሰን ጋ ነው የምልካቸው፡፡ እርሳቸው አሁን በህይወት የሉም፡፡

> አቶ ሀሰን በህይወት ባይኖሩም ለልጃቸው ሙሳ እውቀታቸውን አስጨብጠው አልፈዋል፡፡ አሁንም እንዲህ አይነት ህመም የሚታይባቸውን ታካሚዎች ወደ ሙሳ ጋር እልካቸዋለሁ፡፡ ከዚህ የተነሳ ለባህል ህክምና ባለሙያዎች ያለኝ ክብር ትልቅ ነው፡፡
>
> አቶ ደምሴ አክለውም በአካባቢው ያሉትን የባህል ሀኪሞች ሰብስቤ ከእኔ ጋር እንዲሰሩ ለማድረግ ብዙ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ነገር ግን የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ካለባቸው የቤተሰብ ሀላፊነት አንጻር ከእኔ ጋር የሙሉ ጊዜ ስራ ለመስራት ፍቃደኛ ሊሆኑልኝ አልቻሉም (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት2/2012)፡፡

ዘመናዊ የህክምና ባለሙያው አቶ ደምሴ ለባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ያላቸው ክብር፤ በህይወት አጋጣሚ ባጋጠሚቸው የጤና ችግሮች ምክንያት፤በዘመናዊ ህክምናው መፍትሄ ያልተገኘለትን በሽታ፤ባህላዊ ሀኪሞቹ መድሀኒት በመስጠት የማዳን ብቃታቸውን በቅርበት መመልከት በመቻላቸው እና በዘመናዊ ህክምና መድሀኒት ያልተገኘላቸው እና ገዳይ የሆኑ በሽታዎች፤ለአመታት የብዙዎችን ህይወት ሲቀጥፉ መኖራቸው፤እንደነዚህ አይነት ሀገር በቀል መድሀኒቶች እውቅና ባለማግኘታቸው እና ድጋፍ ሳይደረግላቸው ችላ በመባላቸው የብዙዎችን ህይወት ሲነጥቅ በቅርበት መመልከት መቻላቸው፤ለህገረሰብ ሀኪሞች የሚሰጡት ክብር እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

ሌላኛዋ የህክምና ባለሙያ ነርስ ስራነሽ ሀይሉ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ከዘመናዊ ሀኪሞች ውጪ መስራታቸው በመድሀኒት ቅመማ ወቅት፣ ከሚጠቀሚቸው የተለያዩ መሳሪያዎች አንጻር እና ከመጠን ጋር ተያይዞ በታካሚዎች ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ እንዲሆን ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር፤ይሁን እንጅ ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ለዘመናት ያካበቱትን ሀገር በቀል እውቀትና ጥበብ ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር በመቀናጀት ቢሰሩ ማህበረሰቡን በተሻለ ሁኔታ ማገልገል እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡

> እኔ በባህል ህክምና ላይ ተቃውሞ የለኝም፤ነገር ግን ሙሉ በሙሉም አልቀበለውም፡፡ ለመድሀኒትነት በግብዓት የሚጠቀሚቸው ዕፆች ፈዋሽ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የአቀማመም ሂደቱ፤የሚጠቀሙት መሳሪያ፣ የመድሀኒቱ መጠን እንዲሁም መድሀኒቶቹን ለታካሚው የሚሰጡበት ሂደት ስህተት አለው፤ባይ ነኝ፡፡ ይሁን እንጂ የሀገረሰብ ሀኪሞቹ ያላቸውን እውቀት ይዘው ወደ ዘመናዊ ሀኪሞች ቢቀርቡ፤ማህበረሰቡን ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ማገልገል ይቻላል ብዬ አምናለሁ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት5/2012)፡፡

በይፋት ሆስፒታል ያገኘኋቸው የህክምና ባለሙያ ዶ/ር ደሳለኝ ተስፉ ስለ ሀገረሰብ የህክምና ባለሙያዎች ያላቸውን ሀሳብ ይገልጻሉ፡፡

> በዚህ የህክምና ተቋም ውስጥ ስሰራ ሶስት አመት ሆነኝ፡፡ በርካታ ታማሚዎችን አክሜያለሁ፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ህክምናችንን ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ ሲያማርሩ እሰማለሁ፡፡ ወደ ባህል ህክምና ባለሙያዎች መሄድ ሳይሻላቸው እንደማይቀር ሲናገሩ እሰማለሁ፡፡ በእኛ ሀገር ደረጃ ዘመናዊ ህክምናችን በቂ ካለመሆኑም አልፎ ብዙ የሚቀረው ነው፡፡ ታዲያ የባህል ህክምና ባለሙያዎች ለማህበረሰቡ አስፈላጊ መሆናቸውን አምናለሁ፡፡ ችግሩ የሚፈጠረው የሚሰጡት መድሀኒት መጠን ላይ ነው (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት7/2012)፡፡

ከመረጃ ሰጪዎቹ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ ሀኪሞች በማህበረሰቡ ያላቸው ተቀባይነት ከፍተኛ ቢሆንም ያላቸውን ሀገር በቀል ዕውቀት ይዘው ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር ለመስራት ፍቃደኛ አለመሆናቸው፤በመድሀኒት ዝግጅት እና አሰጣጥ ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮች እንዲባባሱ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ለዘመናት በአብሮነት የዘለቀውን ሀገር በቀል የህክምና ዘዴ ከዘመናዊ ህክምና ጋር በማጣመር እና ዘመን ወለድ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማህበረሰቡን በላቀ ሁኔታ ማገልገል ቢቻል የተሻለ አማራጭ እንደሚሆን ተጠቁሟል፡፡

## 4.11. ባህላዊ ሀኪሞች ለዘመናዊ ህክምና እና ለባለሙያዎቹ ያላቸው አመለካከት

በሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች እና በዘመናዊ ሀኪሞች መካከል ስላለው መቀራረብ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ ሙሳ ሀሰን ሲያስረዱ፡- "ዘመናዊ ሀኪሞች አብሬያቸው እንድሰራ በተደጋጋሚ ጠይቀውኛል፤እኔም ከእነሱ ጋር መስራት እንደማልፈልግ ነግሬያቸዋለሁ፡፡ ከዶክተሮቹ ጋር አብሬ ብሰራ ልጆቼን ምን አበላቸዋለሁ፤እኔ የምተዳደረው በእርሻ ነው፤እነሱ ቢከፍሉኝ ሁለት ወይም ሶስት ሺ ብር ነው፤በዚህ ገንዘብ አምስት ልጆቼን ማሳደግ አልችልም" ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት17/2012)፡፡

የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ ሙሳ ሀሰን ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር ተቀራርበው መስራት የማይፈልጉበት ምክንያት ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የኢኮኖሚ ችግር አንጻር ሲሆን፤ ያላቸውን የቤተሰብ ብዛት እና ሊያገኙ የሚችሉትን ገቢ በማነጻጸር፤ቤተሰባቸውን ማስተዳደር የማያስችላቸው መሆኑን ስላመኑ ያላቸውን እውቀት፣ ጥበብና ችሎታ በዘመናዊ መንገድ፤ ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር በመቀራረብ እንዳይሰሩበት እንቅፋት እንደሆነባቸው ጠቁመዋል፡፡

ሌላው የባህል ሀኪም አቶ ሽዋረገድ አጥናፉ ስለ ዘመናዊ ሀኪሞችና ህክምና ሲያስረዱ፡-

> ዘመናዊ ሀኪሞች ብዙ ጊዜ በጋራ እንድንሰራ ጠየቁኝ፤እኔም ከሀኪሞቹ ጋር ተስማምቼ መስራት አልቻልኩም፤ምክንያቱም የተማርን ነን ብለው ስለሚያስቡ ለእኛ ለባላገሮቹ ምንም ክብር የላቸውም፤ብዙ ጊዜ ፓሊስ አስፈራርቶኛል፡፡ በአንድ አጋጣሚ አንዲት ልጅ ታማ ሰዎች ወደ እኔ አመጧት፤መድሀኒቱ የሚጠጣ ነው፤ልጅቷ መድሀኒቱን ቀምሳ ደከመች፤ ወደ እኔ ከመምጣቷ በፊት እዚህ ቅርብ ካለው ሀኪም ቤት ገብታ ነበር አሉኝ፤ወዲያው አንድ ሀኪም እና አንድ ፓሊስ እቤት መጡ፤ብቻ ብዙ ማስፈራሪያና ዛቻ ደርሶኛል፤በዚህ ምክንያት ዘመናዊ ሀኪሞችን አብሮ መስራት ይቅርና ላያቸው እንኳን አልፈልግም ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት21/2012)፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ አገኘሁ እንዲህ ይላሉ፡- "ዘመናዊ ሀኪሞችንም ሆነ ህግን በጭራሽ አልፈራም፡፡ እኔ ጋ መጥቶ ያልዳነ የለም፤ብዙ አመት በዘመናዊ ትምህርት እድሜውን የፈጀው ዶክተር ያላዳናቸውን ብዙ ታማሚዎች አድኛለሁ፡፡ ማህበረሰቡም ከእነሱ ይልቅ በእኛ ላይ ነው እምነት ያለው፤በምሰጠው መድሀኒት አልጠራጠርም፤እምነትም እውነትም አለ" (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት24/2012)፡፡

ከአቶ አገኘሁ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች በሚሰጧቸው መድሀኒቶች ያላቸው ሙሉ እምነት እና በራስ መተማመን፤የዘመናዊ ሀኪሞችን እርዳታ እንዳይጠብቁ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ ያላቸው በራስ መተማመን እንዲጨምር እና ስራቸውን በልበ ሙሉነት እንዲሰሩ ማድረጉን ከቁልፍ መረጃ አቀባዩ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

በተጨማሪም ዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች የሀገረሰብ ህክምናውን እንደ ኋላቀር እምነት፣ አመለካከት እና ልማድ መቁጠራቸው፤ባለሙያዎቹንም እንደ ባላገር፣ ገጠሬ፤ያልተማረ አድርገው ማሰባቸው እና ለሙያውም ሆነ ለባለሙያዎቹ ክብር ማሳጣታቸው ዘመናዊ ሀኪሞችን እንዲጠሉ እንዳደረጋቸው አቶ ሸዋረገድ ከገለፁት ሀሳብ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ሀገር በቀል የሆነውን አውቀት በማጣጣል ዘመናዊ ህክምናውን እንዲቀበሉ ለማድረግ መሞከራቸው የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ ያላቸውን ዕውቀት በማጋራት በአብሮነት እንዳይሰሩ እንዲሁም ያላቸውን እምቅ እውቀት እንዲደብቁ፤ማድረጉን ከቀረቡት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች ለዘመናዊ ህክምናና ለባለሙያዎች ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ከቀረቡት ምንጮች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ዘመናዊ ሀኪሞች የባህል ህክምናውን ለመቀበል እምነት በማጣታቸው፤የሚያንፀባርቁት ስሜት በከፊል አሉታዊ መሆኑ፤ዘመናዊ የህክምና ተቋማት በሚከፍሉት ክፍያ፤ባህላዊ ሀኪሞቹ ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር በቂ አለመሆኑ እንዲሁም ባህላዊ ሀኪሞች በሚያዘጋጇቸው መድሀኒቶች ላይ ያላቸው ጠንካራ በራስ የመተማመን ስሜት እና በአጠቃላይ ባህላዊ መድሀኒቶች ምስጢራዊ ሆነው መቆየታቸው፤የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች፤ዘመናዊ ሀኪሞችን እንዲርቁ እና አሉታዊ አመለካከት እንዲፈጠርባቸው ማደረጉን የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

## 4.12. የባህል ሀኪሞች በታካሚዎች ዘንድ የሚመረጡባቸው ቅድመ ሁኔታዎች (ምክንያቶች)

ሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች፤በብሔር፣ በሀይማኖት፣ በፆታ እንዲሁም በአመለካከት የተለያዩ መሆናቸውን ቀደም ባለው (በማህበረ-ባህላዊ ዳራው ክፍል) ተገልጧል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎች የተለያየ ብሔረሰብ ተወላጆች፤ የተለያየ ሀይማኖት፣ እምነት እና አመለካከት ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው ወደ ባህል ህክምና ባለሙያዎች የሚመጡ የማህበረሰብ ክፍሎች፤የባህል ህክምና ባለሙያዎቹን የሚመርጡበት ቅድመ ሁኔታ ምን እንደሆነ፤የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ፡፡

የባህል ህክምና ባለሙያው አቶ ኑሩሁሴን ጋር ያገኘኋቸው ታካሚ አቶ አያልቅበት ሀብቴ ስለ ባህል ሀኪም ምርጫቸው እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡-

> እኔም ሆንኩ ልጆቼ አቶ ኑሩ ጋ ነው የምንመጣው፤እኔ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነኝ፤እሱ ሙስሊም ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ይህን አስቤ አላውቅም፡፡ የእሱ እጅ መድሀኒት ነው፤በአንድ ወቅት ታመምኩ፤ዘመዶቼ ኑሩሁሴንን ጠቆሙኝ፤ለመጀመሪያ ጊዜ ኑሩሁሴን ጋር መጣሁ፤ካየኝ በኋላ መድሀኒት ሰጠኝ፤ያለኝን ሁሉ አደረኩ፤ባለኝ ጊዜ ውስጥ ነው የዳንኩት፤ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሌላ መድሀኒተኛ ጋ ሄጄ አላውቅም፡፡ አሁን ከኑሩ ጋ ቤተሰብ ነን፤የሀይማኖት ልዩነታችን ትዝ ብሎኝ አያቅም፤አንቺ ስትጠይቂኝ ነው ያስታወስኩት (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት28/2012)፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ ሱሊህማን አብዲ ለህክምና ወደ እርሳቸው ስለሚመጡ ታካሚዎች ሲያስረዱ፡-

> እኔ ጋ የማይመጣ ሰው የለም፡፡ ብዙ ሰዎች ሲታመሙ ወደ እኔ ይመጣሉ፤እኔ በሀይማኖቴ ሙስሊም ነኝ፤እኔ ጋር የሚመጡት ግን ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞችና የሌላ ሀይማኖት ሰዎችም ናቸው፤አርጎቦች ይመጣሉ፣ አማሮችም፣ ኦሮሞዎችም፣ አፋሮችና ሌሎችም ይመጣሉ፡፡ አላህ በሰጠኝ እውቀት ለሁሉም መድሀኒት እሰጣለሁ፤ለኔ ሁሉም አንድ ናቸው፤ሙስሊም ስለሆነ ብዬ ከሌሎቹ የተለየ የማደርገው ነገር የለኝም፤ ለክርስቲያኑም ሆነ ለሙስሊሙ፤ለሌላውም ተመሳሳይ መድሀኒት ነው የማደርገው፤ታማሚው፤ከአላህ ጋር እንዲድን ነው የምፈልገው፡፡ እንዲያውም ታመው መጥተው፤ተዋውቀን ወዳጅ የሆንን ብዙ ክርስቲያኖች አሉ (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 22/2012)፡፡

በአቶ አገኘሁ ትርፌ ቤት ያገኘኋቸው የባህል መድሀኒት ተጠቃሚ ወ/ሮ ጦይባ መሀመድ ከባህል ሀኪሙ ጋር ያላቸውን ቀረቤታ ሲያስረዱ “ለእኔና ለልጆቼ ያሉን፤አገኘሁ ናቸው፤ አካባቢያችን ቆላማ ነው፤ልጆቼን ብዙ ጊዜ የቆላ ቁስል ነጥቆኝ ነበር፤እድሜ ለአገኘሁ፤ ተርፈውልኛል፤እሳቸው ከአላህ የተላኩ ናቸው፤እንደ አባቴ ነው የማያቸው፤ከዚህ ቤት አልጠፋም” (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት29/2012)፡፡

ሌላው አቶ ሙሳ ቤት ያገኘኋቸው ታካሚ አቶ ተመስገን ክንዴ ስለ ባህል ሀኪም ምርጫቸው ሲገልጹ “እኔ በሀይማኖቴ ፕሮቴስታንት ነኝ፤ሀይማኖቴን አስቤ አይደለም የምመጣው፣ ሙሳ ለእኔ ባለውለታዬ ነው፤ከሞት አትርፎኛል፤ዘመናዊ ሀኪም ቤት ገብቼ ታክሜ ያልዳንኩትን፤ ሙሳ በአንድ ጊዜ ነው ያዳነኝ፤ፈጣሪ እድሜ ይስጠው፤ሙሳ ቤት የማይመጣ ታካሚ የለም፤ እጹ መድሀኒት ነው” ይላሉ (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት4/2012)፡፡

ይህንኑ አስመልክቶ በሀኪም መንገሻ ሀይሌ ቤት ያገኘኋቸው ታካሚ አዘነች ታደለ ስለ ሀኪም ምርጫቸው እንዲህ ይገልጻሉ፡-

> እኔም ልጆቼም ከታመምን እንደ በሽታው አይነት ነው፤መድሀኒተኞቹን የምመርጠው፤ለቆላ ቁስል ፍቱን የሆነ መድሀኒተኛ አለ፤ለወፍ በሽታ ደግሞ ሌላ መድሀኒተኛ አለ፤ለሌሎችም እንደዚሁ ሌሎች መድሀኒተኞች አሉ፡፡ በዚህ መሰረት ነው መድሀኒተኞችኝ የምመርጠው፤አንደህመማችን የቆላ ቁስል ስንታመም፤ዙጢ ያሉት ኑሩሁሴን ጋር፤የወፍ በሽታ ምልክት ካየን፤አቶ አውራሪስ ጋር፤አይሬ ከታመምን ማደያ ቀበሌ ወደምትገኘው መድሀኒተኛ፤ወ/ሮ አረጋሽ ጋ እንሄዳለን፡፡ በመድሀኒት ሰጪዎች ቤት ከተለያዩ ብሔር ተወላጆች ጋ እንገናኛለን፤እንተዋወቃለን፤ ከአርጎቦች፤ ከአፋሮች፤ከኦሮሞች እና ከሌሎችም ጋር፤በሀይማኖትም፤ከሙስሊሞች፣ ከኦርቶዶክሶች፣ ከፕሮቴስታንቶች እና ከሌላ እምነት ተከታይ ጋር

> እንገናኛለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ ተገናኝተን ዘመድ፤ቤተሰብ ሆነን የምንጠያየቅ ብዙ ነን፤ቤተሰባዊ ግንኙነት ነው ያለን፡፡ ሀኪም አረጋሽ ጋ ተገናኝተን ሶስት አመት የሆነን ቤተሰቦች አለን (ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት24/2012)፡፡

ታካሚ ወ/ሮ አዘነች የሀገረሰብ ሀኪም ምርጫቸውን የሚያደርጉት የባህል መድሀኒት ቀማሚዎቹ እውቅ በሆኑባቸው መድሀኒቶች መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህም ለባህል ሀኪሞቹ ማህበረሰቡ ከሰጣቸው ሙያዊ ክብርና ዝና እንዲሁም አውቅና፤እውቀትን፣ ብቃትን እና ችሎታን ታሳቢ በማድረግ እንጂ ምንም አይነት የሀይማኖት፣የብሔረሰብ፣የፆታ እና የአመለካከት ልዩነቶችን ግምት ውስጥ እንደማያስገቡ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም በሀገረሰባዊ መድሀኒተኞቹ ቤት በሚደረገው ተደጋጋሚ ግንኙነት፣ ማህበራዊ ቅርርብን፣ ትውውቅ፣ ወዳጅነትን፣ አብሮ መኖርን፣ አንዱ የሌላውን ባህል፣ ወግ እና ማንነት አውቆ እና አክብሮ መኖር እንዲችል፤ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ባህላዊ መድሀኒት ቀማሚዎች ያላቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በባህላዊ የህክምና ስርዓት፤በሀይማኖት፣ በእምነት፣ በአመለካከት፣ በባህል እና ልማድ እንዲሁም ስርዓት ለየቅል የሆኑ፤ልዩ ልዩ አተያይ፣ አረዳድ፣ አመለካከት፣ ሰርዓት እና ወግ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በአንድ አላማ፤ለመዳን፣ ፈውስ ለማግኘት፤ግላዊ፣ ቤተሰባዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስቀጠል ወደ ሀገረሰብ ሀኪሞች ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ የህክምና ባለሙያዎች ታካሚዎቹ ያለባቸውን በሽታ በመለየት የበሽታውን ሁኔታ በመረዳት የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ሂደት የታካሚውን ዳራ መጠየቅ፤ከየት አካባቢ እንደመጣ፣ በምን እንደሚተዳደር፣ ሀይማኖቱን እና አጠቃላይ የአኗኗር ሁኔታው መጠየቅ በህክምና ሂደቱ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡ ይህም ታካሚውን ከበሽታው እንዲያገግም ከመርዳቱም በላይ፤ ምን ማድረግ እንዳለበት እና እንደሌለበት፣ ከምን መቆጠብ እንዳለበት፣ መስራት እና መስራት የሌለበትን ለማስረዳት፣ መመገብ ያለበትን እና በሽታውን የሚያባብሱ ምግቦችን ለመከልከል፤ የታካሚውን የአኗኗር፣ ስርዓት፣ ወግ፣ ባህልና ማንነት መረዳት በሽታው እንዳይባባስበት ለማድረግ፤ማህበራዊ እና የአኗኗር ሁኔታውን በመረዳት ህይወቱን ለመታደግ አንዲሁም የባህል፣ የልማድ እና ወግና ስርዓት ትውውቅን በመፍጠር ማህበራዊ መስተጋብሩን ለማጥበቅ ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በብሔር፣ በሀይማኖት፣ በአመለካከት፣ በፆታና በሌሎችም በባህል፣ በልማድ፣ በወግና ስርዓት የተለያዩ ይሁኑ እንጂ በማህበረሰብ ውስጥ አንድ የታመመ ሰው መድሀኒተኛ ጋር ለመሄድ፤አንድም ከዚህ ቀደም የነበረውን ተሞክሮ በማሰብ (ከዚህ ቀደም ታሞ ድኖ ከሆነ ወይም የቅርብ ቤተሰቡ፣ ዘመዱ እና ወዳጁ ታመው ድነው ከነበረ) ፤አልያም በመተዋወቅ፣ ካልሆነ በጥቆማ እንጂ የሀይማኖት እና የብሔር እንዲሁም የአመለካከት ልዩነቶችን ታሳቢ እንደማያደርጉ ከመስክ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

ሀገረሰባዊ ሀኪሞች ለታማሚዎች ፈውስ ከመስጠታቸው በተጨማሪ ማህበራዊ አንድነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳላቸው ተገልጧል፡፡ ይህም ሁሉም ብሔረሰብ፣ የሁሉም ሀይማኖት ተከታይ፤የፆታ፣ የዘር እና የአመለካከት ልዩነቱን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት፤ በአንድ አላማ፤ በተመሳሳይ ፍላጎት ወደ ባህል ህክምና ባለሙያዎቹ የሚሄዱ በመሆኑ ልዩነቶችን በማክበር፤ማህበረሰባዊ ተግባቦት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ባህላዊ ህክምና ስርዓቱ፤አንድነት፤ወዳጅነት፤እርስ በርስ መቻቻልንና አብሮ መኖርን በማስተማር ማህበራዊ ግንባታው ላይ ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ አንጻር ሀገረሰባዊ ሀኪሞች የማህበረሰቡን ጤንነት ከማስጠበቅ ባሻገር ለማህበረሰቡ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጡ አንድነትን፣ መግባባትን፣ ፍቅርን እና ተቻችሎና ተጣጥሞ መኖርን መስበኪያ ተቋማት መሆናቸውን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ" በሚል የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓብይ አላማ በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ሀገር በቀል የህክምና እውቀትን በመመርመር ማህበራዊ ልማዱን ገልፆ ማሳየት ነው፡፡ አላማውን ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ አስፋላጊ የሆኑ የመስክ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ ተሰብስበዋል፡፡ ፈቃደኛ ከሆኑ መረጃ አቀባዮች በፎቶና በድምጽ መረጃዎች ተሰንደዋል፡፡ በዚህ መልክ መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በይዘት በማደራጀት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በትንታኔው መሰረት የሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የባህል ሀኪሞች በሀይማኖት፣ ብሔር፣ በአመለካከት እና እምነት የተለያዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ በአካባቢው ያሉ የባህል ሀኪሞች በሽታን ለመለየት በረጅም ጊዜ ያካበቱትን ግላዊ እና ማህበረሰባዊ እውቀት በመጠቀም፣ ልማድ እና ስርዓታቸውን በማስተባበር የበሽታ አይነቶችን በማየት፣ በእጃቸው በመነካካትና የታካሚዎችን ስሜት በመጠየቅ የበሽታ አይነቶችን፣ ደረጃ እና ባህሪ እንደሚለዩ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

የባህል ሀኪሞች የታካሚን የአዕምሮ ጤንነት፣ የሕመም ዓይነት፣ የግለሰቡን ሁኔታ፣ መኖሪያ አካባቢ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ማኅበራዊ ኃላፊነት፣ የቤተሰብ እገዛና እንክብካቤን ማጤን፤የታካሚን ቀደምት የሕይወት ታሪክ መረዳት፤የሕመሙን ባሕሪይና ሁኔታ መለየት፤ታካሚን ማበረታታትና መደገፍ ቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን ከመስክ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ እነዚህ የሀገረሰብ ሀኪሞች አብዛኛውን ጊዜ ከዕፅዋት በሚገኙ ግብዓቶች መድሀኒት እንደሚቀምሙ ተረጋግጧል፡፡ እነዚህን ዕፆች ከጊቢያቸው፣ ከአካባቢያቸው፣ ከተራራ ላይ፣ ከወንዝ ዳር፣ ከፀበል ስፍራዎች እና ከመንገድ ዳር እንደሚያገኙ መረጃዎቹ አመላክተዋል፡፡

በመሆኑም የሀገረሰባዊ ህክምና ባለሙያዎቹ ዕፆቹን ለመሰብሰብ፤በአንዳንድ የክርስትና እምነት ተከታዮች ረቡዕ እና አርብ ይመረጣሉ፡፡ እነዚህ ቀናት መንግሰተ ሰማያት የሚከፈቱባቸው ቀናት ናቸው በሚል እምነት የሚመረጡ ሲሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ የባህል ሀኪሞች ደግሞ በማንኛውም ቀን መድሀኒት የሚሰበስቡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ለመድሀኒት ግብዓት የሚሆኑ ዕፆችን ለመሰብሰብ ከመሄዳቸው በፊት እንደ እምነት፣ ልማድ እና አመለካከታቸው፤ሰውነት (ገላን) መታጠብ፣ ከሰዎች ጋር ሰላም መፍጠር፣

መስገድ፣ መፀለይ፣ ብዙ አለማውራት፣ እራስን ማፅዳትና ከሰው ጋር አለመገናኘት፤እንደ በሽታው፣ እንደ መድሀኒቶቹ አይነትና ባህሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ለመድሀኒቱ ፈዋሽነት እና ለባህል ሀኪሙ በረከትን የሚያስጡ ተግባራት መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

ከእነዚህ ክንውኖች በኋላ ለመድሀኒት ግብዓት የሚሆኑ ዕፆችን ለመሰብሰብ የሚያስችሏቸውን ቁሶች (ቢላዋ፣ቀረጢትና ሌሎች ብረት ነክ ቁሶችን) በመያዝ ዕፅዋቱ ወደ ሚገኙበት ቦታ በመሄድ፤እንደ በሽታው አይነትና ባህሪ ከዕፅዋቱ፤ቅጠል፣ ፍሬ፣ አበባ፣ ስር፣ ግንድ፣ ቅርፊት እና ቀንበጥ በመሰብሰብ ያላቸውን የዘመናት እውቀት፣ ጥበብ፣ ችሎታ አስተባብረው በመውቀጥ፣ በመፍጨት፣ በመቀቀል፤በሚጠጣ፣ በሚቀባ፣ በሚታሰር፣ በሚታኘክ መልክ አዘጋጅተው ለታካሚዎች እንደሚሰጡ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ፤ማህበረሰቡን በብዛት የሚያጠቁ በሽታዎችም የቆላ ቁስል፣ አልማዝ ባለጭራ፣ የወፍ በሽታ፣ ምች፣ ላሽ፣ ኪንታሮት፣ ችፌ፣በእባብ መነደፍ፣ አይሬ፣ ተቅማጥ (ሆድ ቁርጠት) እና እከክ (ቁስል) መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ጥናቱ በጤና ስነ ምህዳር ንድፈ ሃሳብ መሰረት መቃኘቱ፤በአካባቢው የበሽታዎቹ መከሰት ዋና መንስኤ የአየር ንብረቱ ሞቃታማ (ቆላማ) መሆን የተለያዩ (ተናዳፊ/ተናካሽ) ነፍሳት እንዲራቡና በሚፈልጉት መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ማህበረሰቡ ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ እንዲሆን ማድረጋቸውንና እነዚህ በሽታዎች ሥነ ምህዳሩ በሚሰጠው ግብዓት የሚፈወሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲቻል አድርጓል፡፡

በባህል ህክምና ሂደቱ ለታካሚው መድሀኒት ከመስጠቱ በፊት የታማሚውን ዳራ ከታካሚው አልያም ከቅርብ ቤተሰቡ መጠየቅ፤ህመሙ ያለበትን ደረጃ እና በታካሚው ላይ የቆየበት ጊዜ፣ ምልክቶቹን እና የታካሚውን ሁኔታ መጠየቅ በሽታው ያለበት ደረጃ ታውቆ ታማሚው ተገቢውን ህክምና እንዲያገኝ (እንድታገኝ) ማድረግ፤የታካሚውን ህይወት ለመታደግ፣ የሀገረሰብ ህክምና ባለሙያዎቹ ከተጠያቂነት ለመዳን እንዲሁም ክብርና ዝና ለማስጠበቅ ተገቢ መሆኑን እና ይህም ተግባራዊ እንደሚደረግ ከመስክ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ መድሀኒቶቹም በተለያየ መጠን፤አይነትና ይዘት፤በሲኒ ተቀድተው፣ በጣት፤ተቆንጥረው፣ በቆርኪ ተለክተው እንደሚሰጡ በትንታኔው ክፍል ታይቷል፡፡

በጥናቱም አንዳንድ ዘመናዊ ሀኪሞች ወደ ባህል የህክምና አገልግሎት መስጫ ተቋም በመሄድ ህክምናውን እንደሚያገኙ ከአካባቢው ዘመናዊ ሀኪሞች የተገኙ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡

ይኸውም በዘመናዊ ህክምና መዳን የማይችሉ በሽታዎች በባህላዊ ሀክምና መዳን መቻላቸው ባህላዊው የህክምና አገልግሎት በዘመናዊ ሀኪሞችም እውቅና እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የባህል ሀኪሞች የህክምና እውቀቱን በአብዛኛው ከቤተሰብ፣ ከቅርብ ጓደኛ፣ ከአሳዳጊ ቤተሰብ እና ከታላላቅ ሰዎች ያገኟቸው መሆኑም መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ሀኪሞችም እውቀቱን እንዳገኙበት መንገድ፤እንደ ሀይማኖታቸው እና እምነታቸው፤አደራውን ለሚወጣ ልጅ፣ ገንዘብ ለማያታልለው፣ ሰዎችን መርዳት ለሚችል፤ አዛኝ ለሆነ (ለወንድም ሆነ ለሴት) ልጃቸው ማስተላለፍ የሚፈልጉ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የሀገረሰብ ሀኪሞች እውቀት ምስጢራዊ መሆኑን የተገኙት መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ይኸውም መድሀኒቱ ለሰው ከተነገረ ይረክሳል፤ምስጢሩን የተናገረ ሰው ቁጣ ይደርስበታል፣ ዕፆቹ በሰዎች ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ፣ አደራ ለመጠበቅ በሚል እና ከመድሀኒቱ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ላለማጣት ሲሉ ምስጢራዊ እንዳደረጓቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሸዋሮቢት እና አካባቢዋ የሚገኙ ዘመናዊ ሀኪሞችም፤ሀገረሰባዊ ሕክምና ከመድሀኒት መጠን፣ ከንፅህና ጉድለት እና በአሰጣጥ ሂደት ወቅት የሚፈጠሩ ስህተቶች፤የጤና ችግሮችን እንደሚያባብሱ ጠቁመዋል፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል ባህላዊ ሀኪሞች ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር ተቀራርበው መስራት ያለባቸው ቢሆንም ባህላዊ ሀኪሞቹ ከዘመናዊ ሀኪሞች ጋር የመቀራረብ ፍላጎት ስለሌላቸው ቸግሮቹን መቅረፍ እንዳልተቻለ መረጃዎቹ አመላክተዋል፡፡

በዚህ ጥናት የተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ፤ማህበረሰቡ ጤናውን ለመጠበቅ፤እራሱን ከበሽታ ለመከላከል ሀገር በቀል የሆነው እውቀት ያለውን ፋይዳ ያሳየ ሲሆን ይህን ሀገር በቀል እውቀትና ጥበብ፤የባህል መድሀኒት ቀማሚዎች፣ የባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች እና የታካሚው የቅርብ ቤተሰቦች በጋራ በመሆን ለመድሀኒቱ ፈዋሽነት እና ለታካሚው ጤና ሲባል የሚያደርጉት፣ የሚከውኑትን እና አጠቃላይ ያለውን ድባብ ለማሳየት የክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ አገልግሏል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች (የባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎችና የሀገረሰባዊ ሀኪሞች) በብሔር፣ በሀይማኖትና በአመለካከት የተለያዩ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የአካባቢው ማህበረሰብ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ወደ ሀገረሰብ

ሀኪሞች በመሄድ አገለግሎቱን ያገኛሉ፡፡ ይህም ማህበራዊ ተግባቦትን፣ እርስ በርስ መቻቻልና ተከባብሮ መኖርን እንዲሁም አንድነትን በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ባህላዊ ሀኪሞች የማህበረሰቡን ጤና ከመጠበቅ ባሻገር ማህበራዊ መስተጋብሩ እንዲጠነክር በማድረግ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ተቋማት መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2. ይሁንታ

በጥናቱ ሂደት ከተገኙ መረጃዎች እና በትንታኔ ከተደረሰበት ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

1. የአካባቢው ማህበረሰብ ለበሽታ መጠቃት ዋና መንስኤ የአየር ንብረቱ ቆላማ (ሞቃታማ) መሆኑ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት የአየር ንብረት ሁኔታው ላይ ቢሰሩ የተሻለ ይሆናል፡፡
2. የባህል ህክምና ተቋማት ማህበራዊ ተግባቦትን መፍጠሪያ በመሆናቸው የወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት ከባህል ሀኪሞቹ ጋር ግንኙነት በመፍጠር፤እውቅና ቢሰጣቸውና ማህበረሰባዊ አንድነቱ ላይ ጠንክረው ቢሰሩ መልካም ይሆናል፡፡
3. በማህበረሰቡ ውስጥ፤በክርስትና እና በእስልምና እምነት ወስጥ ያሉ ክብረ በዓሎች፣ ስርዓተ ከበራዎች እንዲሁም ሀገረሰባዊ እምነቶች ላይ ተጨማሪ ጥናት ቢደረግባቸው እና ማህበረሰባዊ ልማዱን ለሌላው ገልፆ ማሳየት ቢቻል መልካም ነው፡፡

## የማጣቀሻ ጹሑፎች


መስፍን ፈቃዱ፡፡ (2002)፡፡ “የሀገረሰባዊ መድሀኒቶች ቅመማና ባህላዊ አጠቃቀም በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ””፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጹሑፍ ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡

ምህረት ዳኜው፡፡ (2000ዓ.ም)፡፡ “በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሀኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጹሑፍ ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡

ሰለሞን ተሾመ፡፡ (2007ዓ.ም)፡፡ *ፎክሎር፤ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

ሻሂዳ ሁሴን፡፡ (2017)፡፡ *ሀገረሰባዊ የህክምና ጥበብ* ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተመስገን በየነ፡፡ (2003ዓ.ም)፡፡ “በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴዎች፤የመድሀኒት ቅመማና አሰጣጥ በግሼ ወረዳ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጹሑፍና ፎክሎር ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡

ታሪኩ አበራ፡፡ (2017)፡፡ “ሀይማኖት እና እምነት”፡፡ *Emmanuel International Gospel Ministry based on EOTC::*

ትዕግስት ምህረት፡፡ (2008 ዓ.ም)፡፡ “ሀገረሰባዊ የእንሰሳት በሽታ መለያ ዘዴዎች የመድሀኒት አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በይልማ ዴንሳ ወረዳ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጹሑፍ እና ፎክሎር ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡ :

አሰፋ ባልቻ፡፡(2008 ዓ.ም)፡፡ *የኢትዮጵያ ባህላዊ መድኃኒትና ሕክምና የምዕተ ዓመት ጉዞ፡፡* አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፡፡

ዓለማየሁ ዘሪሁን፡፡ (2000ዓ.ም)፡፡ “የኑዌር ማህበረሰብ ባህላዊ ህክምና እውቀት፣ አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጹሑፍ ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። አዲስ አበባ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፣፳፻ ዓ.ም።

…………*ቅዱስ ቁርዓን*። (1997ዓ.ም)። አዲስ አበባ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት።

ያለው እንዳወቀ። (2009ዓ.ም)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆች እና አተገባበር*። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ (ህትመት)።

ይሁኔ አየለ። (2010ዓ.ም)። *ሙሉ ጤናን ፍለጋ*። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደነቀ አበረ። (2003ዓ.ም)። "የሀገረሰባዊ መድሀኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ በወላይታ ሶዶ ከተማና አካባቢዋ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ት/ክፍል ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ፈቃደ አዘዘ። (1992ዓ.ም)።*የስነቃል መምሪያ*። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣።

ፍቅርተ ማቴዎስ። (2009ዓ.ም)። "ከዕፅዋት የሚገኙ ሀገረሰባዊ መድሀኒቶች እውቀት፣ አዘገጃጀት እና አሰጣጥ በከምባታ ብሔረሰብ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ት/ክፍል ለኤም. ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሪፓርት፤2011።

የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር የህዝብ ግንኙነት ሚዲያ ልማት ቢሮ ሪፓርት፤2011።

Abraham,D,Andargie,A,Berhanu,E. (2013). "Community Knowledge, attitude and Practice about malaria in a low endemic setting of Shewa Robit Town, northeastern Ethiopia".Addis Abeba: BMC/Public Health.

Abraraw,T.(1998)."Traditional Medicine in an Urban Center:Belief and Practices (the case of Desse Town, North Ethiopia)". MA Thesis, Department of Social Anthropology: Addis Ababa University.

Alemayehu,M.(1984).Traditional Ethiopian Medicines". Institute of Ethiopian Studies; *Eight International Conferences of Ethiopian Studies:* Addis Ababa University.

Assefa,B.(1992).“Traditional Medicine in Wollo Nature and History.” M.A Thesis, Department of History: Addis Ababa University.

Bascom,W.(1954). "Folklore and Anthropology." The Journal of American Folklore *66* (262); PP. 283-290.

Bauman, R.(1977).Verbal Art as Performance. Prospect Heights. IL: Waveland Press.

Bauman,R.(1986).Story, Performance, and Event; Contextual Studies of Oral Narratives. New York: Cambridge University Press.

Bauman,R.(1992).Folklore,Cultural Performance, and Popular Entertainments: A Communication-Centered Handbook. (Ed) New York: Oxford University Press.

Ben-Amos,D.(1975). “Folklore in African Society”. Research in African Literature. Vol 6.2: PP.165-198.

Bruce,A and Willcox,J.(2012).”Ecology and Enviromental Health”. https;//www,research gate,net/publication/266211170,Prineton U.Press.

Chokevivat,V and Chuthaputt,A.(2005). "The Role of Thai Traditional Medicine in Health Promotion"Thailand; Department for the Development of Thai Traditional and Alternative Medicine, Ministry of Public Health.

David, J. The Health of Ecology and the Ecology of Health. Pages 205-213 | Published online: 03 Jun 2010. https://doi.org/10.1080/20028091056836.

Desta,B. (2004). “Review of Traditional Medicine Research in Ethiopia” *Proceedings of a National Workshop*: Addis Ababa, 30 June-2July.

Dorothea, E. (1976). “Traditional Medicine and Magic among the Amhara of Ethiopian.” Paper Prepared for the conference on Ethiopian Feudalism Addis Ababa.

Dundes, A. (1980).*Interpreting Folklore India*. Indiana:University Press.

Fikadu,F. (2001).”The Role of Indigenous Medical Plants In Ethiopia Health Care Retrieved”. November 02,2017 from http:/www.hollerafica.

Finnegan,R. (1977). *Oral Poetry, its Nature,Significance and Social Context.* New York:Cambridge University Press.

Franklin,W. (2011). “How Do Religion and Belief Systems Influence Traditional Medicine and Health Care in Madagascar?” Independent Study Project (ISP) Collection. https://digitalcollections.sit.edu/isp_collection/1096.

Gennadiy,S,Rozenberga,V, Lazareva,V, Simonova,G, Lifirenkob,H, Lilija,A, and Sarapultseva, A.(2016). “Integration of the Problem of Medical Ecology on the Level of the Highly Urbanized Region”.INTERNATIONAL JOURNAL OF ENVIRONMENTAL & SCIENCE EDUCATION .VOL. 11, NO. 15, 7668-7683

Getachew,A,Dawit A,Timotewos,G and Kelbe,U. (2002).“Perceptions and Practices of Modern and Traditional Health Practiioners about Traditional Medicine in Shirka District, Arsi Zone, Ethiopia”. Journal of Health Development: Ethiopian Health and Nutrition Research.

Goldstein,K.(1964).A Guide for Field Workrs in Folklore. American Folklore Society by Folklore Associates, INC.

Helman, C. (1984). Culture, Health and Illness.An Introduction for Health Professionals. Bristol-London-Boston; wrighit PSG.

Jones, Michael. (1994). Putting Folklore to Use.(Ed). The University Press of Kentucky.

Kelley,T.(2008).”The Ecology of Environmental Health”.Jul21.doi.101177/ 11786302080020001, PP25-26.

Malinowski,B. (1922).*Two versions of Functionalism* .New York: Dutton.

Mekonen, M.(2010). “Indigenous Medicine, Beliefs and Practices Among The Kunama In Sheraro, Tigray” M.A. Thesis; Department of Ethiopian Study: Addis Ababa University.

Mekonen,W. (2019).Tradtional Medicinal Plants In Ethiopia,Oromia Agricultural Research institute, https://www.researchgate.net/publlcation.

Mirgissa,k.(1993).”Indigenous Medical Beliefs and Practices Among the Illubabor oromo”, MA Thesis Department of social Anthropology:Addis Ababa University

Radcliffe, B.(1922). *Social life and Customs*.Cambridge University Press:India.

Pankhurst,R.(1996).”The Characteristics of Traditional Ethiopian Medicine and its Traditional Pharmacopoeia”.International Conferences of Ethiopian studies; Addis Ababa university.

Rob,S .(2019). “What is the key difference between religion and belief?”Marinated in thoughts of belief; Former Catholic Seminarian.

Schoemaker, G. (1990). The Emergence of Folklore in Everyday Life: A Field Guide and Source Book. (Ed). Trickster Press.

Sims,M, and Stephens,M. (2005). Living Folklore; An Introduction to the Study of People and their Traditions.The Ohio State University.

Sofowora,A. (1982). Medicinal plants and traditional medicine in Africa . John Wiley and sons LTD.

Steiner, R. P. (1986). Folk medicine: the art and the science.NP.

WHO (2002). WHO Traditional Medicine Strategy 2002-2005. Geneva; World Health Organization.

WHO (2007). WHO International Standard Terminologies on Traditional Medic - ine in the Western Pacific Region. Geneva; World Health Organization.

Winkelman,M. (2009). Culture and Health Applying Medical Anthropology.San Francisco; John Wiley and Sons Imprint.

Yared,P. (2011).“Beliefs and Practices of Traditional Medicine Among Women In Reproductive Health care: A study in Damot woyde woreda. Wolaytta zone.” MA Thesis Department of sociology, Addis Ababa University.

Young,A. (1970). Medical Beliefs and Practices of Begemder Amhara. Published PhD Dissertation in Philadelphia: University of Pensylvania.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፡- የቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ሥም | ፆታ | እድሜ | ሀይማኖት | መኖሪያ ቀበሌ | መተዳደሪያ/ስራ | ቃለ መጠይቁ የተከናወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አውራሪስ ፍቃዴ | ወ | 61 | ኦርቶዶክስ | ዙጢ ቀበሌ (05) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 15፣19 እና መጋቢት 1/2012 |
| 2 | አቶ ሱሊህማን አብዲ | ወ | 59 | ሙስሊም | ማደያ ቀበሌ (04) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና እና ነጋዴ | የካቲት 22፤ መጋቢት4፣9/2012 |
| 3 | ወ/ሮ አረጋሽ ሽታዬ | ሴ | 48 | ኦርቶዶክስ | ፓፓዬ ሰፈር (02) | የባህል መድሀኒት ቀማሚ | የካቲት19፣26፤ መጋቢት 6/2012 |
| 4 | አቶ ሙሳ ሀሰን | ወ | 40 | ሙስሊም | ዙጢ ቀበሌ (05) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 13፣17፣23፣ 27 እና መጋቢት 5/2012 |
| 5 | አቶ ወሰኔለህ ጫኔ | ወ | 65 | ኦርቶዶክስ | ማደያ ቀበሌ (04) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 19፣ 26/2012 |
| 6 | አቶ ደረጀ ወሰኔ | ወ | 60 | ኦርቶዶክስ | ጫሬ ቀበሌ (03) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 19፣20፣ 28/2012 |
| 7 | አቶ አገኘሁ ትርፌ | ወ | 67 | ኦርቶዶክስ | ፓፓዬ ሰፈር (02) | የባህል መድሀኒት ቀማሚ | የካቲት 15፣24፣29 እና መጋቢት 4/2012 |
| 8 | አቶ አህመድ ጀማል | ወ | 63 | ሙስሊም | ማደያ (04) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ነጋዴ | የካቲት 12፣25 እና መጋቢት1/2012 |
| 9 | አቶ ኑሩሁሴን አህመድ | ወ | 66 | ሙስሊም | ዋንዛ ቀበሌ (08) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 13፣18፣28 እና መጋቢት7/2012 |
| 10 | አቶ ሽዋረገድ አጥናፉ | ወ | 54 | ኦርቶዶክስ | ዋንዛ ቀበሌ (08) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 21፣29 እና መጋቢት 10/2012 |
| 11 | አቶ ጀማል መሀመድ | ወ | 57 | ሙስሊም | ዙጢ ቀበሌ (05) | የባህል መድሀኒት ቀማሚ | የካቲት 17/2012 |
| 12 | አቶ መንገሻ ሀይሌ | ወ | 69 | ኦርቶዶክስ | የጫሬ ቀበሌ (03) | የባህል መድሀኒት ቀማሚና ገበሬ | የካቲት 19/2012 |

አባሪ ሁለት፡- በባህላዊ ሀኪሞች መኖሪያ ቤት የተገኙ የባህል መድሀኒት ተጠቃሚዎች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ሥም | ፆታ | እድሜ | ሀይማኖት | የመኖሪያ (ቦታ) ቀበሌ | መተዳደሪያ | ቃለ መጠይቁ የተከናወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አያልቅበት ሀብቴ | ወ | 46 | ኦርቶዶክስ | ዋንዛ ቀበሌ (08) | ግብርና | የካቲት 28/2012 |
| 2 | አቶ ሳኒ አሊ | ወ | 47 | ሙስሊም | ሽማኔ ማህበር (01) | ነጋዴ | መጋቢት1/2012 |
| 3 | ወ/ሮ ጦይባ መሀመድ | ሴ | 39 | ሙስሊም | ዙጢ ቀበሌ (05) | የቤት እመቤት | የካቲት29/2012 |
| 4 | አቶ ተመስገን ክንዴ | ወ | 49 | ፕሮቴስታንት | ውስቴምቧይ (07) | የመንግስት ስራ (ግብርና) | መጋቢት 4/2012 |
| 5 | ወ/ሮ አዘነች ታደለ | ሴ | 51 | ኦርቶዶክስ | 03 (ብቅ እንቅ) | ንግድ | የካቲት24/2012 |

## አባሪ ሶስት፡- ለአካባቢው ማህበረሰብ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ዘመናዊ ሀኪሞች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ሥም | ፆታ | እድሜ | ሀይማኖት | የሚገኙበት ቀበሌ | መተዳደሪያ | ቃለ መጠይቁ የተከናወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ደምሴ ዘውዴ | ወ | 54 | ኦርቶዶክስ | ዙጢ ቀበሌ (05) | (የግል) የህክምና ባለሙያ | መጋቢት2/2012 |
| 2 | ነርስ ስራነሽ ተስፋ | ሴ | 29 | ፕሮቴስታንት | ማደያ ቀበሌ (04) | የይፋት ሆስፒታል የጤና ባለሙያ | መጋቢት5/2012 |
| 3 | ደ/ር ደሳለኝ ተስፋ | ወ | 37 | ኦርቶዶክስ | ዙጢ ቀበሌ (05) | የይፋት ሆስፒታል የጤና ባለሙያ | መጋቢት7/2012 |

አባሪ አራት፡- ስለ ጥናቱ አካባቢ አጠቃላይ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ የሀይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች እና እናቶች መረጃ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ሥም | ፆታ | እድሜ | መተዳደሪያ (ስራ) | የሚገኙበት ቦታ (ቀበሌ) | ቃለ መጠይቁ የተከናወነበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሽጋው ንጋቱ | ወ | 42 | የህዝብ ግንኙነት ሚዲያ ልማት ባለሙያ | ሽማኔ ማህበር (01) | የካቲት 6፣7/2012 |
| 2 | አቶ አፈራ ንጉሴ | ወ | 85 | ግብርና | ውስቴምቧይ (07) | የካቲት28/2012 |
| 3 | አቶ ጌታነህ ፈቄ | ወ | 82 | ግብርና | ዋንዛ ቀበሌ (08) | የካቲት21/2012 |
| 4 | አቶ ደምሴ ጫኔ | ወ | 54 | ነጋዴ | ማደያ ቀበሌ (04) | የካቲት8/2012 |
| 5 | አቶ አወል ጀማል | ወ | 91 | ግብርና | ጎዜ አካባቢ | የካቲት21/2012 |
| 6 | አቶ ሰይድ አወል | ወ | 61 | ነጋዴ | ሽማኔ ማህበር (01) | የካቲት24/2012 |
| 7 | ቄስ ሙላቱ አይተነው | ወ | 52 | በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እና ግብርና | ጫሬ ቀበሌ (03) | የካቲት28/2012 |
| 8 | ቄስ አዱኛ አንዳርጌ | ወ | 48 | በቤተክርስቲያን አገልግሎት እና ግብርና | ማደያ ቀበሌ (04) | የካቲት14/2012 |
| 9 | መሪጌታ እንግዳሰው ሀይሌ | ወ | 46 | የቤተክርስቲያን አገልጋይ እና ነጋዴ | ጫሬ ቀበሌ (03) | መጋቢት 2፣ 3/2012 |
| 10 | አቶ አጥቃው በላይ | ወ | 49 | ነጋዴ | ፓፓዬ ሰፈር (02) | የካቲት27/2012 |
| 11 | ወ/ሮ አስካለ ደምሴ | ሴ | 43 | የጉሊት ነጋዴ | ብርቱካን ሰፈር (03) | መጋቢት4/2012 |

**አባሪ አምስት፡- የመስክ ምልከታ መከታተያ ቅጽ**

በምርምሩ ሂደት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ታሳቢ በማድረግ እና የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃደኝነት ከግምት ወስጥ በማስገባት የመስክ መረጃዎች ምልከታ ተካሂዷል፡፡

1. የባህል ሀኪሞቹ መድሀኒቶቹን ለመቁረጥ ከመሄዳቸው በፊት (ከእምነት፣ ከሀይማኖት እና ከልማድ) አንጻር ምን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ?
2. ለመድሀኒት ግብዓት የሚሆኑ ዕፆች መሰብሰቢያ፣ መቀመሚያና መስጫ፤የትኞቹ ቀናት እና ሰዓታት ይመረጣሉ?
3. ምን ምን ዕፆች ለመድሀኒትነት ያገለግላሉ? የትኛው የዕፅዋት ክፍል ለመድሀኒት ግብዓት ይሆናል?
4. በመድሀኒት ቅመማ ወቅት ግልጋሎት ላይ የሚውሉ ቁሳቁሶች ምንድን ናቸው?
5. የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ መድሀኒቶችን፤እንዴት ያዘጋጃሉ፤ይቀምማሉ?
6. መድሀኒቱ ለታካሚው እንዴት፣ በምን አይነት ሁኔታ ይሰጣል?
7. የባህል ህክምና ባለሙያዎቹ የሚከለክሏቸውና የሚፈቅዷቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
8. መድሀኒቱን ለታካሚዎች በሚሰጡበት ጊዜ የሚከውኗቸው ክዋኔዎች አሉ?
9. አጠቃላይ የመድሀኒት አሰጣጥ ሂደቱ ምን ይመስላል? (የባለሙያዎቹን እና የታካሚዎቹን ፈቃደኝነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት)፡፡
10. የታካሚዎችን ግብረ መልስ በንቃት መከታተል፤ምን ያደርጋሉ/ይከውናሉ?

**አባሪ ስድስት፡- ለባህል ህክምና ባለሙያዎች የቀረቡ ጥያቄዎች**

**ግላዊ መረጃ**

ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ!

- ✓ ስምዎን ማን ልበል? -----------------------
- ✓ ዕድሜ? --------------
- ✓ ሀይማኖት? ------------
- ✓ መኖሪያ ቦታ (ቀበሌ)? -----------
- ✓ መተዳደሪያ? -------------

**ስለሚያክሟቸው በሽታዎች እና መድሀኒቶቹን በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች**

1. ሙያውን እንዴትና ከማን ተማሩት?
2. በሙያው መስራት ከጀመሩ ምን ያህል አመት ሆኖዎታል?
3. በባህላዊ ህክምና የምትፈውሷቸው በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
4. ለበሽታዎቹ መከሰት መንኤው ምንድን ነው?
5. በብዛት ወደ እርሶ ቤት የሚመጡ ታካሚዎች በምን በሽታ የተያዙ ናቸው?
6. መቼ መቼ ያክማሉ?
7. የበሽታ መለያ ዘዴያችሁ ምንድነው? እንዴት ትለያላችሁ?
8. ለምትፈውሷቸው በሽታዎች መድሀኒት የሚሆኑ ግብዓቶችን ከምን ከምን ያገኛሉ?

   ሀ. ከዕፅዋት? -----------------------------

   ለ. ከእንስሳት? ----------------------------

   ሐ. ከማዕድናት? ----------------------------

   ከሶስቱም ይጠቀማሉ? ወይስ ከሁለቱ? ሀሳብዎን ይግለጹ?

   -------------------------------------------------------------------------------------
9. ለመድሀኒትነት የምትጠቀሟቸውን ዕፆች ከየት ያገኛሉ?
10. እነዚህን ግብዓቶች ለመሰብሰብ ከመሄዳችሁ (ከመጀመራችሁ) በፊት ምን ታደርጋላችሁ?
11. እንደ እምነት (ሀይማኖት) ስርዓታችሁ፣ ምን ቅድመ ሁኔታዎች አሉ? (የምታደርጓቸው ወይም የማታደርጓቸው) ተግባራት ምንድን ናቸው? ካሉ ቢያብራሩ

    -------------------------------------------------------------------------------

12.መድሀኒቱን ለመሰብሰብ የምትመርጢቸው ቀናት፣ሰዓታት አሉ?

ሀ. ካሉ ምን ምን ቀናት ናቸው? -----------------------------

ለ. ለምን ተመረጡ? ምክንያቱን ቢያስረዱ ----------------------------------------------

ሐ. የትኛው ሰዓት ይመረጣል? -------------------------------------------

መ. ለምን ተመረጠ? ምክንያቱን ቢገልጹ? ------------------------------

13.በመድሀኒት ስብሰባ፣ ቅመማ እና አሰጣጥ ወቅት የሚመረጡ ቀናት እና ሰዓታት ከሌሉ ለምን እንደማይመረጡ ሀሳብዎትን ይግለጹ?

-----------------------------------------------------------------------------------------------14. ለመድሀኒትነት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለመሰብሰብ የምትገለገሉባቸው ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው?

-------------------------------------------------------------------------------------

እነዚህ ቁሶች ለምን ተመረጡ? ------------------------------------

14.እንደ በሽታው አይነት እና እንደ መድሀኒቱ አይነት የተሰበሰቡት ተዋፅዖዎች እንዴት፣ በምን፣ መቼ ይዘጋጃሉ?

15.ሲዘጋጁስ ምን ምን ተጨማሪ ግብዓቶች ይካተታሉ?

16.ለታካሚው እንዴት ይሰጣሉ?

17.ለታካሚዎች የሚሰጡ መድሀኒቶች መጠን በምን ትለያላችሁ? (ለህጻናት፣ ለወጣቶች እና ለአዛውንቶች) ምን ያህል ነው? -----------------------------------------------------------------

18.እንደ በሽታው አይነት እና ደረጃ ታካሚው/ዋ ምን ይከለከላል/ች?

19.ታካሚው፤መድሀኒቱን ለምን ያህል ቀናት፣ ሳምንታት እንዲወስድ ይታዘዛል?

20.ታካሚው ከተፈወሰ በኃላ ምን እንዲያደርግ/እንድታደርግ ታዛላችሁ?

21.እናተስ የባህል ሀኪሞቹ የምታደርጉት፤የምትከውኑት ክንውን ይኖር ይሆን?

22.ታካሚዎች እንዴት ወደ እናንተ ይመጣሉ?

ሀ. በጥቆማ? -----------------------

ለ. በእውቅና? -----------------------

ወይስ? -----------------------------------------------------------------------

23.ታማሚዎችን ከህመማቸው ስትፈውሱ ምን ይሰማችኋል?

24.የባህል መድሀኒት እውቀት ምስጢራዊነት እንዴት ታዩታላችሁ?

25.ይህን እውቀት ለማን ብታስተላልፉ (ብታወርሱ) ትፈቅዳላችሁ?

ሀ. ምርጫችሁ ማን ነው? ----------------------------------

ለ. ለምን ተመረጠ/ች? --------------------------------

26.መንግስት እና ዘመናዊ ሀኪሞች ለእናንተ (ለባህል ሀኪሞች) ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

27.ማህበረሰቡ ስለ እናንተ፤ስለ ባህል ህክምና ምን እንዲያውቅ ትፈልጋላችሁ?

28.አጠቃላይ ስለምትሰጡትአገልግሎት መናገር የምትፈልጉት ምንድን ነው?

## አባሪ ሰባት፡- ለባህል ህክምና ተጠቃሚዎች የቀረቡ ጥያቄዎች
## ግላዊ መረጃ

ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ፡፡

1. ስምዎን ማን ልበል? -------------------------
2. እድሜ? ----------------------------
3. ሀይማኖት? -------------------
4. መኖሪያ ቦታ (ቀበሌ)? --------------------
5. መተዳደሪያ? --------------------------

## በሽታዎቹን እና ባህላዊ ህክምናውን አስመልክቶ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ማህበረሰቡን በብዛት የሚያጠቁ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
2. በአካባቢው ከሚከሰቱ በሽታዎች ውስጥ ከዘመናዊ ህክምናው ይልቅ በባህል ሀኪሞች ቢታዩ የተሻሉ የሚሆኑት በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
3. ወደ ባህል ሀኪሞች ለመሄድ ባህላዊ ሀኪሞቹን የምትመርጡበት ቅድመ ሁኔታ አላችሁ? ምንድነው? (ሀይማኖት፣ ጾታ ወይስ አውቅና) ሀሳብዎትን ይግለጹ?

   ------------------------------------------------------------------------------

4. እርሶና ቤተሰብዎ ስትታመሙ ለህክምና የምትሄዱት የት ነው?

   ሀ. ወደ ዘመናዊ ሀኪሞች?

   ለ. ወደ ባህላዊ ሀኪሞች?

   ሐ. ሁለቱንም ይጠቀማሉ?

   ለምን መረጧቸው? ምክንያቱን ያስረዱ?

   ---------------------------------------------------------------------------------

5. በየትኛው ህክምና ይተማመናሉ?

   ሀ. በዘመናዊው ህክምና?

   ለ. በባህላዊው ህክምና?

   ለምን? ምክንያቱን ቢገልጹ?

-----------------------------------------------------------------------------------------

6. ህክምናውን ለማግኘት ወደ ባህላዊ ሀኪሞች ስትሄዱ መድሀኒቱ ብቻ ያድነኛል ብላችሁ ታምናላችሁ? ወይስ ከእምነትና ከሀይማኖታችሁ ጋር ታያይዛላችሁ?
7. መድሀኒቱን በምትወስዱበት ጊዜ መድሀኒቱን ብቻ መውሰድ ነው? ወይስ ሌሎች ክንዋኔዎች አሉ?

   ካሉ ምን ምን ታደርጋላችሁ? -------------------------------------------

8. መድሀኒቱን የምትወስዱበት የተለየ ቁስ አለ? ምን? -------------------------------------
9. የሀገረሰብ መድሀኒት ቀማሚዎች ጋር ብዙ ጊዜ ይሄዳሉ?
10. ከባህል መድሀኒት ቀማሚዎች ጋር ያላችሁ ቀረቤታ ምን ይመስላል?
11. የባህል ሀኪሞቹ የማዳን ብቃት እስከምን ድረስ ነው?
12. ባህላዊ ሀኪሞቹ ለታካሚዎች ያላቸው አመለካከት እና አቀባበል ምን ይመስላል?
13. ስለ ባህል ህክምና መናገር የምትፈልጉት ነገር ካለ? ይግለጹ?

**አባሪ ስምንት፡- ለዘመናዊ ሀኪሞች የቀረቡ ጥያቄዎች**
**ግላዊ መረጃ**

ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ!

1. ስምዎን ማን ልበል?
2. እድሜ?
3. ሀይማኖት?
4. የሚኖሩበት ቦታ (ቀበሌ)?
5. መተዳደሪያ?

**ባህላዊ ህክምናውን አስመልክቶ የቀረቡ ጥያቄዎች**

1. ለባህላዊ ህክምና ያልዎት አመለካከት፤አወንታዊ ወይስ አሉታዊ? ለምን?

ምክንያቱን ቢያስረዱ? -----------------------------------------------------

2. በአካባቢው ማህበረሰቡን በብዛት የሚያጠቁ በሽታዎችን ይዘርዝሩ?

   -------------------------------------------------------------------------
3. ሀገረሰባዊ ህክምና ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ነው ብለው ያምናሉ? አዎ ካሉ፤እንዴት? አይ ካሉ፤ ለምን?
4. ሀገረሰባዊ ህክምና ለዘመናዊ ህክምና ያግዛል ብለው ያስባሉ? አለው ካሉ፤እንዴት? የለውም ካሉም ምክንያትዎን ይግለፁ?

   --------------------------------------------------------------------
5. እርሶ ወደ ባህላዊ ሀኪሞች ሄደው ያውቃሉ?
6. በእናንተ የህክምና ተቋም ለመታከም መጥተው ወደ ባህላዊ ህክምና የላካችኋቸው ታካሚዎች አሉ?
7. በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው ማህበረሰቡ የሚጠቀማቸው የትኞቹን ነው?

   ሀ. ዘመናዊ ህክምና? ለምን? ----------------------------------------------

   ለ. ባህላዊ ህክምና? ለምን? ------------------------------------------------
8. ባህላዊ ህክምናው ማሻሻል አለበት የምትሉት ማስተካከያ አለ?
9. ከባህል ሀኪሞች ጋር በጋራ መስራት ይፈልጋሉ?

10.ከባህላዊ ሀኪሞች ጋር ተቀራርበው ለመስራት ያደረጉት ጥረት አለ? አለ ካሉ፤የባህል ሀኪሞቹ ምን ምላሽ ሰጡዎት?

11.ከባህል ሀኪሞች ጋር ግላዊ ቀረቤታ አለዎት?

12.በአጠቃላይ ስለ ባህል ህክምና ማለት የምትፈልጉት ነገር ካለ ይግለጹ?

## አባሪ ዘጠኝ፡- በአካባቢው ለሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች፣የሀይማኖት አባቶች እና ተወላጆች የቀረቡ ጥያቄዎች

**ግላዊ መረጃ**

ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ!

1. ስምዎን ማን ልበል? ----------------------
2. እድሜ? --------------------------
3. ሀይማኖት? -------------------------
4. የመኖሪያ ቦታ (ቀበሌ)? --------------------
5. መተዳደሪያ? ------------------------------------

## ስለ ሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ ማህበረ ባህላዊ ዳራ በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ስለ ሸዋሮቢት ከተማ ስያሜ፣ አመሰራረት እንዲሁም የህዝብ አሰፋፈር የሚያውቁት ነገር አለ? ሀሳብዎትን ይግለጹ?
2. በሸዋሮቢት ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች የብሔር፣ የቋንቋና የሀይማኖት ስብጥር ምን ይመስላል?
3. በሸዋሮቢት ከተማ እና አካባቢዋ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የባህል ገጽታን በተመለከተ ያለዎትን ሀሳብ ይግለጹ?
4. በከተማዋና ዙሪያዋን የሚገኙ የቱሪስት ቦታዎች አሉ? (የፀበል ስፍራዎች፣ መስጅድ/ሌላ)

   መልስዎ አሉ ከሆነ፤ የት፤ የት አካባቢ ይገኛሉ?

   ------------------------------------------------------------------------

5. በጊዜ ሂደት ያሳዩት ለውጥ እና አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

**አባሪ አስር፡- ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት መገኛ ስፍራዎች እና የመረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ በከፊል**



ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት
የሚገኝበት የሮቢት ወንዝ አካባቢ



ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሀኒት
የሚገኝበት ኮረብታ



አቶ ሙሳ ሀሰን በጊቢያቸው ውስጥ የሚገኙ ዕፆችን ለአጥኝዋ ሲያሳዩ (የካቲት/2012)



አቶ ሙሳ ሀሰን በጊቢያቸው ውስጥ ከሚገኙ ዕፆች መድሀኒት ሲቆርጡ (የካቲት/2012)





አቶ ሙሳ ሀሰን የቆላ ቁስል ታካሚዋን ሲያክሙ (መጋቢት/2012)

አቶ ኑሩ ሁሴን አህመድ ስለህክምናቸው ለአጥኚዋ መረጃ ሲሰጡ (የካቲት/2012)



አቶ ኑሩ ሁሴን አህመድ ስለሀገረሰባዊ ህክምናቸው ለአጥኚዋ መግለጫ ሲሰጡ (የካቲት/2012)